# የአማራ ክልል
# የመረጃ መጽሐፍ

የ2015 ዓ.ም ህትመት



በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ
በሚዲያ ልማት፣
የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት
ዳይሬክቶሬት በመንግስት ፖሊሲ አፈፃፀም
ትንተና ቡድን የተዘጋጀ

ሰኔ 2016 ዓ.ም

## የአብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## የ2015 ዓ.ም ህትመት

## በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በሚዲያ ልማት፣ የፖሊስ ጥናትና አብዝሃነት ዳይሬክቶሬት በመንግስት ፖሊሲ አፈፃፀምትንተና ቡድን የተዘጋጀ

መጋቢት 2015 ዓ.ም

## የ ኢትዮጵ ራዕይ

በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሠባትና ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነው!

## የ ክልሉ ራዕይ

አስተማማኝ ሠላም፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሠፈነበት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰበት፣ ከድህነት የተላቀቀና መካከለኛ ገቢ ያለው ክልል እውን ሆኖ ማየት!

## የ ቢሮው ራዕይ

በመረጃ የበለገፀ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ እውን ሆኖ ማየት!”

የመጀመሪያው ህትመት "ብሔረ አማራ" በሚል መጠሪያ በ1995 ዓ.ም ተዘጋጀ፡፡ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ "የአማራ ክልል የመረጃ መጽሐፍ" በሚል ስያሜ መዘጋጀት ጀመረ፡፡



ዶ/ር ይልቃል ከፋለ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

## የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ካቢኔ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| <br>ዶ/ር ይልቃል ከፋለ<br>ርዕሰ መስተዳደር | <br>ዶ/ር ጌታቸው ጀምበር ም/ርዕሰ መስተዳድር | <br>አቶ አረጋ ከበደ<br>የስራና ስልጠና ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ ግዛቸው ሙሉነህ<br>የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሀላፊ | <br>አቶ ቢያዝን እንኳሆነ<br>ከተሞችና መሰረተ ልማት ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ሃይለማርያም ከፍያለው<br>የግብርና ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ አብየ ካሳሁን<br>የጠቅላይ ፍርድቤት ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ማማሩ አያሌው<br>ውሃና ኢነርጅ ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ኢንጅነር ዳኝነት ፈንታ<br>የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ሀላፊ |

| | | |
|---|---|---|
| <br>አቶ አንሙት በለጠ<br>የፕላንና ልማት ቢሮ ሀላፊ | <br>ወ/ሮ ብርቱካን ሲሳይ<br>የሴቶች፤ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሀላፊ | <br>አቶ እርዚቅ ኢሳ<br>የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሀላፊ |
| <br>አቶ ሲሳይ ዳምጤ<br>የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ኃላፊ | <br>አቶ ተስፋሁን አለምነህ<br>የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን | <br>ዶ/ር ማተቤ ታፈረ<br>የትምህርት ቢሮ ኃላፊ |
| <br>ዶ/ር ጥላሁን ማህሪ<br>የገንዘብ ቢሮ ሀላፊ | <br>አቶ ሙሀመድ ያሲን<br>የመንገድ ቢሮ ሀላፊ | <br>ዶ/ር ፀጋ ጥበቡ<br>የገቢዎች ቢሮ ሀላፊ |
| <br>ዶ/ር መልካሙ አብቴ<br>የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ | <br>አቶ ጣሂር ሙሀመድ<br>የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ | <br>አቶ ገረመው ገብረፃድቅ<br>የፍትህ ቢሮ ሀላፊ |

| | | |
|---|---|---|
| <br>አቶ እንድሪስ አብዱ<br>የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ | <br>ወ/ሮ ባንችአምላክ ገ/ማርያም<br>የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሐብት ልማት ኮምሽነር | <br>አቶ ሀይሌ አበበ<br>ማዕድን ሀብት ቢሮ ሀላፊ |
| <br>ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ<br>የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ሀላፊ | አቶ ደሳለኝ ጣሰው<br>የሰላምና ደህንነት ቢሮ ሀላፊ | . |

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## ብሔራዊ ዓርማ

<u>የዓርማው ትርጉም</u>

የስንዴ ዘለላ - የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ

ጊሩ - የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ

እርግቧ - ሠላምን

ሚዛኑ - ፍትህና ዲሞክራሲን

የላሊበላና የፋሲል ግንብ - የክልሉን ታሪክ የቅርስ ሃብት

የጭስ ዓባይ ፏፏቴ - የክልሉን የተፈጥሮ ሃብት ያመላክታል፡፡

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የሕዝብ መዝሙር



የታታሪ ሕዝቦች - - - የታሪክ ማህደር፣

የአኩሪ ባህል አምባ - - - የድንግል ሀብት አፈር፡፡

የሕዝቦችሽ ተስፋ - - - - ለሚ ክልላችን፣

በሠላም በፍትህ - - - በልማት ጉዟችን፣

ተባብረን በሥራ - - - እንገነባሻለን፡፡

የአማራነትን ክብር - - - ደማቅ አርማ ይዘን፣

ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - - - እኩል ተከባብረን፣

በፍቅር በአንድነት - - - አብርን እንዘልቃለን፡፡

## ማውጫ


ርዕስ ጉዳይ ገጽ

- የቢሮ ሀላፊ መልዕክት

I. የአማራ ክልል በጥቂቱ-------------------------------------------------------------------

II. ኢኮኖሚ ዘርፍ

- ግብርና ልማት---------------------------------------------------------------------------
- ከተሞችና መሰረተ ልማት --------------------------------------------------------
- ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ.................................................
- አካባቢና ደን ጥበቃ...........................................................
- መንገድ ልማት.............................................................
- መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት................................................
- ህዳሴ ግድብ................................................................
- እንስሳት ሀብት ልማት........................................................
- ንግድና ገበያ ልማት.........................................................
- ማዕድን ሀብት ልማት.........................................................
- ገቢ.......................................................................
- ስራና ስልጠና...............................................................
- ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት....................................................
- ፕላንና ልማት...............................................................
- ገንዘብና ልማት..............................................................
- ውሀና ኢነርጅ ልማት.........................................................
- መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም....................................................
- አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና..................................................
- ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት.....................................................

III. ማህበራዊ ዘርፍ

- ትምህርትና ስልጠና-----------------------------------------------------
- ሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ..................................................

- ባህልና ቱሪዝም…………………………………………………………………….
- ጤና ጥበቃ…………………………………………………………………….
- ወጣቶችና ስፖርት…………………………………………………………………….
- ሲቪልሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር…………………………………………….
- የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ…………………………………………………….
- የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ……………………………………..

IV. መልካም አስተዳደር ዘርፍ

- የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን……………………………………….
- ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና…………………………………………..
- ርዕሰ መስተዳድር…………………………………………………..
- አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን…………………………………………..
- ክልል ምክር ቤት…………………………………………………..
- ጠቅላይ ፍርድ ቤት……………………………………………….
- ፍትህ………………………………………………………………….
- ዋና ኦዲተር……………………………………………………..

V. አጠቃላይ መረጃ

- በክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ መስሪያቤቶች አድራሻ-------------------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ የትምህርት፣ የጤና፣ የትምህርት መገናኛ ፤የግብርና ኮሌጆችና ማሰልጠኛ ተቋማት አድራሻ-------------------------------------------------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዞኖች…………………………………………………..
  - በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች፣ሐይቆችና ተራሮች --------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና የቱሪስት መስብህ ሀብቶች----------------------------
  - ባለኮከብ ሆቴሎች-----------------------------
  - በክልሉ የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች -----------------------------------------------------

# የቢሮ ሀላፊው መልዕክት



የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት ለመፍጠር እንዲሁም የክልሉን ሁለንተናዊ ገፅታ ለመገንባት የተቋቋመና በዋነኝነት ይህንኑ ሃላፊነት ለመወጣት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡እንዲሁም ተቋማችን ቀልጣፋ፣ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ተመራጭ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ሆኖ ለመገኘት እና የክልሉን መንግስት ስትራቴጅክ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ግንባታ መሪ እቅድ በማሳካት ረገድ የሚኖረውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ የዘርፉን የኮሚዩኒኬሽንና ሚዲያ ቴክኖሎጂ አቅርቦት በማሳደግ ትክክለኛ መረጃ የመስጠትና የማስራጨት አቅሙን ለማጎልበት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የጀመርናቸው የልማትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ሪፎርም ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በክልላችን አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ተከታታይና ትክክለኛ መረጃዎችን በወቅቱ መስጠት ግንባር ቀደም ተልዕኮአችን ይሆናል፡፡

በተለይ መንግስት በክልላችን የተፈጠረውን ጦርነትና ግጭት በሰላማዊ መንገድና በድርድር ለመቋጨት እያደረገ ያለውን ጥረት እና የነበሩትን የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ስርዓት ክፍተቶች በመገምገምና በማስተካከል አስተማማኝ ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ ያከናወናቸውን ስራዎች ተከታትሎ በማሳወቅ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማጎልበት ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም የለውጥና የዘላቂ ሰላም ግንባታን ለማረጋገጥ የተጀመሩ የልማትም ሆነ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስራዎቻችንን ለማሳካት ባሳለፍናቸው አመታት ውስጥ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በጽንፈኛ ቡድኖችና ተላላኪዎች በተከፈተብን ጦርነት ምክንያት የለውጥ ጉዟችን ላይ አሉታዊ ተጽኖ ፈጥሯል ፡፡

ይሁን እንጅ ችግሩን መመከት የሚያስችሉ አማራጭ የመፍትሔ ፕሮግራሞችን በመዘርጋት በክልላችን የተረጋጋ የኢኮኖሚ ስርዓት እንዲረጋገጥና የኑሮ ውድነቱን በመቋቋም የተጀመሩ የመሰረተ ልማቶችን በማስቀጠል ላይ እንገኛለን፡፡ የሰብል ምርታማነትን ለማሳደግም ግባቶችን በወቅቱ በማቅረብ ለማስራጨት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል ፡፡

ነገር ግን ሰላምንና የህግ የበላይነትን በማስፈን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የምናደርገውን ጉዞ ለማደናቀፍና እኩይ የፖለቲካ ፍላጐታቸውን በህዝባችን ላይ ለመጫን የሚያሴሩና ስርዓት አልበኝነትን የሚከተሉ ቡድኖች ማህበረሰቡን ለእንግልት ከመዳረጋቸውም በላይ ውስጣዊ አንድነታችንን በመከፋፈል ክልሉን የግጭት ፣ የብጥብጥና የጦርነት ቀጠና በማድረግ ሰባዊና ቁሳዊ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

በመሆኑም ህገ-ወጦችንና ጽንፈኞችን በመታገልና በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚፈቱ ችግሮችን በመለየት የሚዲያና እና የኮሙዩኒኬሽን ዘርፉ ቀውሱን ለመቀልበስ በሚደረገው ርብርብ የራሱን ሚና በመወጣት በህብረተሰቡ ውስጥ የሚሰራጩ የተሳሳቱ ዝንባሌዎችን በትክክለኛ መረጃ ለማስተካከል ይሰራል፡፡

ከምንም በላይ ለሠላም ልእልና ሀብቱን፣ ጉልበቱንና ህይዎቱን ለመገበር የማይሰስተው ማህበረሰባችንን ደጀን በማድረግ እና ከሌሎች ክልሎች ወንድምና እህት ህዝቦች ጋር በመሆን በጋራ በአጥንትና በደም በገነቧት ሀገራቸው ዜጎች በማንነታቸው ሣይገፉና በህገ-ወጦች ሳይንገላቱ በየትኛውም የአስተዳደር አካባቢ መብታቸው ተከብሮ በፍትህ በእኩልነትና በሰላም መኖር እንዲችሉ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ በተጨማሪም ላለፉት ዘመናት አንዳንድ የፖለቲካ ቡድኖች እኩይ ዓላማቸውን ለማስፈፀም የአማራን ህዝብ በጥላቻ ትርዕክት ጨቋኝ እና ተስፋፊ ተደርጎ እንዲታይ በማድረግ ከየቦታው እንዲፈናቀል ተደርጓል፡፡ አፈናና ግዲያም ተፈጽሞበታል፡፡ ይህንንም እኩይ ሥራ በመቃወም ከፍተኛ መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡ ችግሩ በዘላቂነት እንዲፈታም መንግስት በህዝብ ድጋፍና የለውጥ እንቅስቃሴ የጀመረውን የለውጥ ጉዞ ዳር ለማድረስ በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጅ የአማራን ህዝብ በተሣሣተ ትርዕክት በጥርጣሬና በጥላቻ እንዲታይ ያደረጉ ቡድኖች በህዝብ የለውጥ ትግል ተገደው ወደ ዳር የተገፉ ቢሆንም ዛሬም በሕዝብ ውስጥ ተደብቀው እርስ በርስ ለማባላት የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም። በተለይ ወጣቶችን በማህበራዊ ሚዲያ አማካይነት ስሜታቸውን በመኮርኮር የብሔር፣ የሐይማኖት ወዘተ ግጭት ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ ሴራዎችን ይሸርባሉ ። ሐሰተኛ መረጃዎችንም በመፈብረክ በህዝብ ውስጥ አለመተማመን ለመፍጠር ይራወጣሉ፡፡

በመሆኑም ልማትን ለማፋጥንና ከድህነት ለመውጣት ህዝባችንን በማደራጀት እና በምንሰራቸው የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ስራዎች በማንቃት ዘላቂ ሰለምን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ በዋናነት የተሳሳቱና አፍራሽ ዘገባዎችን በመመከት የክልላችንና የሀገራችንን ገጽታ ለመገንባት የዲጅታል

ሚዲያውን በማዘመን ትክክለኛ መረጃዎችን በፍጥነት ለማሰራጨት የጀመርነውን አበረታች ተግባር በቀጣይነት በልዩ ትኩረት የምንፈጽመው ይሆናል፡፡

በተጨማሪም ሌሎች የሚዲያ አማራጮችንም በመጠቀም ትክክለኛ መረጃዎችን ለህዝብ እናደርሳለን፡፡ በተለይ መንግስት በመልካም አስተዳደርና በልማት በየዓመቱ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት የህትመት ውጤቶችን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎችንና የዕቅድ አፈጻጸም ውጤቶችን በማሳወቅ ህብረተሰቡ የበኩሉን እንዲወጣ ያነሳሳል፡፡ ባአጠቃላይ ከምናዘጋጃቸው የህትመት ውጤቶች ውስጥ ዓመታዊ የመረጃ መጻሐፍ አንዱ እና ትልቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ያካተታቸውን መረጃዎች በመመልከት ለቀጣይ ስራችን መሻሻል አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ ማድረግ ይገባል እላለሁ፡፡

ሰላም!



# I. የአማራ ክልል በጥቂቱ

የክልሉ ግብርና ቢሮ መረጃ እንደሚያሳየው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ9-14 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስና ከ36-40 ዲግሪ ምስራቅ ኬንትሮስ ሃሳባዊ መስመሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን 161 ሺ.ህ 828.4 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው፡፡ ክልሉ ከጠቅላላው የአገሪቱ የቆዳ ስፋት 15 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናል፡፡ ክልሉ በሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡

በአገራችን በከፍታው የሚታወቀውና 4,620 ሜትር ከፍታ ያለው የራስ ደጀን ተራራ የሚገኘው በዚሁ ክልል ሲሆን ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ የሚችሉ የበርካታ ወንዞች (አባይ፣ ተከዜ፣ አንገረብ፣ መገጭ) እና ሐይቆችም (የጣና፣ የዘንገና፣ የሎጎና፣ የአርዲቦ ...) ባለቤት ነው፡፡

የክልሉ የአየር ንብረት 2.35 በመቶ ውርጭ፣ 24.15 በመቶ ደጋ፣ 46.61 በመቶ ወይና ደጋና 26.71 በመቶ ቆላ ነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ598.3-1,692 ሚ.ሊ ሜትር ሲሆን በዓመት በአማካይ ከ12.4-27.8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሙቀት መጠን አለው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የስነ-ህዝብ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የክልሉ የህዝብ ብዛት ከ1999 የህዝብ ቆጠራ በመነሳትና በየዓመቱ በአማካይ የሚጨምረውን የ1.7 በመቶ የህዝብ ዕድገት ምጣኔ መነሻ በማድረግ በ2014 ዓ.ም. የተተነበ የህዝብ ብዛት 23,215,998 ነው፡፡ ይህም በፆታ ሲተነተን 11,564,711 ወንድና 11,651,287 ሴት እንደሆነ ያመላክታል፡፡የህዝብ ቁጥሩ በአዲስ ተቆጥሮ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከትግራይ ክልል ወደ አማራ ክልል የተመለሱ ወልቃይት ጠገዴ ሴቲት ሁመራ እንዲሁም ራያ አላማጣን የህዝብ ቁጥር አይጨምርም፡፡

ክልሉ ከአማራ ብሄር በተጨማሪ የአዊ፣ የኦሮሞ፣ የዋግ ኽምራ፣ የአርጎባና የቅማንት ብሄረሰቦች ይኖሩበታል፡፡ በ13 ዞን አስተዳደሮች (ሶስቱ የብሄረሰብ አስተዳደሮች እንዲሁ ከትግራይ ወደ አማራ ክልል የተመለሱ ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞኖች ናቸው) እንዲሁም በ8 ሪጆኦ ፖሊታን ከተሞች፣ በ69 የከተማ አስተዳደሮች፣ በ138 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች በ96 ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች በ 372 ታዳጊ ከተሞች በአጠቃላይ በ683 ከተሞች

የተዋቀረ ነው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አመሰራረት ፓርላሜንታዊ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ክልል ምክር ቤቱ 294 መቀመጫ ወንበሮች ያሉት ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች በተወሰኑ የምርጫ ክልሎች የምክርቤት አባላት ያልተመረጡ በመሆኑ የምክርቤት አባላት ብዛት 256 ሲሆን ከፆታ አንፃር 163 ወንድና 93 ሴት የምክር ቤት አባላት አሉት፡፡ የምክር ቤቱ አባላት የብልፅግና እና የአብን ተወካዮች ናቸው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉን አኩሪ ባህል ጠብቆ በማቆየት፣ የዱር እንስሳት ሀብት እንዲጠበቁና ለትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ሚናውን እየተጫወተ ይገኛል፡፡

እንዲሁም ለባለሀብቶችና የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሰላማዊ ስርዓት በማስፈን ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በዋናነት እንዲያግዝ የማድረግ አላማ ይዞ እየሠራ ይገኛል፡፡
ለክልላችን ኢኮኖሚ ማደግ አስተዋጽኦ የሚያደርጉና የቱሪስትን ቀልብ ከሚያማልሉ የመስህብ ሀብቶች መካከል በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካላቸው ኪነ-ህንፃዎች፣ ብርቅየ የዱር አራዊ ቶች፣ ታሪካዊ ቦታዎች፣ ልዩ ልዩ ድንቃ ድንቅ ቅርሶች፣ የአባይ ምንጭ ፏፏቴ፣ አስገራሚ ዋሻዎችና ፓርኮች እንዲሁም የጣና ደሴቶችና ገዳማት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሀገራችን በዩኔስኮ ከተመዘገቡት የዓለም ቅርሶች መካከል አራቱ በአማራ ክልል ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ርዕሰ መዲና ባሕርዳር ናት፡፡

የባሕርዳር ከተማ ከተቆረቆረች ረጅም የሚባል ዘመን ብታስቆጥርም በፈጣን የዕድገት ጐዳና ላይ ትገኛለች፡፡ የከተማዋ ነዋሪ ከመንግስት የከተሞች ልማት ፖሊሲ ጋር በመተዋወቅና ልማ ታዊ አስተሳሰብን እያዳበረ በመምጣቱ በባሕር ዳር ከተማ አስገራሚ ፈጣንና ሁለንተናዊ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

በከፊል በጣና ሃይቅ የተከበበችው እና የአባይ ወንዝ አካሎ የሚያልፋት ባሕርዳር በተፈጥሮ ሃብት የታደለችና የቱሪስቶች መናኸሪያ ከተማ ከመሆኗም በላይ ለንግድ አገልግሎት፣ ለባለ ኮከብ ሆቴሎች መገኛ እና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች እየተስፋፉ የሚገኙባት ከተማ ሆናለች፡፡

በአማራ ክልል ባሉ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ ከ100 በላይ ቱሪስት መኖን ሆቴሎች ሲኖሩ በዋና ከተማዋ በባሕርዳር ከ23 በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ወደ ከተማዋ ለሚገቡ እንግዶች አስፈላጊውን መስተንግዶ በመስጠት ይታወቃሉ፡፡

የአማራ ክልል በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ባለሃብቶችን እንደ ልማት ፍላጐታቸው ማስተናገድ የሚያስችሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን አቅፎ የያዘና ባለሃብቶች በመረጡት ዘርፍ ቢሠማሩ ትርፋማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ መረጃዎችን ለይቶ አደራጅቷል፡፡በዚህ መሠረት ባለሀብቶች ሊሠማሩበት በሚፈልጉት የኢንቨስትመንት መስክ አንፃር መረጃዎችን አገናዝበው መጠቀም እንዲችሉ የተመቸ ዕድል ፈጥሯል፡፡

ክልሉ ለአዝርዕት ተስማሚ የሆነ መሬት፣ የአየር ንብረትና እምቅ የውሃ ሀብት አለው፡፡ ይህም በዝናብም ሆነ በመስኖ የብዕር፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎችን፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎችን በስፋት ለማልማት ምቹ አድርጐታል፡፡ በክልሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሃብት እንዳለ ቢታወቅም የዘርፉ ልማት የሚካሄደው በተለመደው ኋላቀር አያያዝና የአረባብ ዘዴ በመሆኑ ሊገኝ የሚገባውን የምርት መጠንና ጥቅም ማግኘት ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የግል ባለሃብቶች በመስኩ በመሰማራት በዘመናዊ መልክ በመጠቀም በእንስሳት እርባታ እና በማድለብ፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ተዋፅኦ ገበያ ልማትና የእንስሳት ጤና ጥበቃ አገልግሎት ሊሳተፉ የሚችሉባቸው ዕድሎች ናቸው፡፡

በክልሉ ሰፊ የዓሣ ሀብት ይገኛል፡፡ከጣና ሐይቅ ብቻ በዓመት 15 ሺህ ቶን ዓሳ ማምረት ይቻላል፡፡ በተለይም ከሐይቆች ጣና፣ ሎጐና አርዲቦ፣ ከወንዞች አባይ፣ ተከዜና አንገረብ አስተማማኝ የዓሳ ሃብት ምንጮች መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ባለሃብቶች በዚህ ዘርፍ ቢሰማሩ የዓሳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ በማቋቋም ምርቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብ፣ እንዲሁም ተረፈ ምርቱን ለእንስሳት መኖ በማቀነባበር ያለውን የሃብት ክምችት ጥቅም ላይ ለማዋል ከማስቻሉም በላይ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

ከክልሉ የተፈጥሮ ደን ውስጥ ሙጫና የዕጣን ዛፍ ይገኙበታል፡፡ ይህን ሃብት ለማልማት 604,382 ሄክታር የሚሸፍን መሬት እንደሚኖር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን ይህ ዘርፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያልዋለ የኢንቨስትመንት መስክ ነው፡፡ በክልሉ የዕጣን ሀብት በስፋት የሚገኙባቸው ቆላማ ቦታዎች አዲአርቃይ፣ ታች አርማጭሆ፣ መተማ፣ ደራ፣

ደብረ ኤልያስ፣ ባሶሊበን፣ ዳንግላና ጓንጓ ሲሆኑ በአጠቃላይ በ9 ዞኖች በሚገኙ 39 ወረዳዎች በዓመት 200 ሺህ ቶን ዕጣንና የዱር ሙጫ ማምረት ይቻላል፡፡ ይህም በርካታ ባለሃብቶችን ሊያሳትፍ የሚችል አቅም ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡

በክልሉ ያለው የጤናና የትምህርት ሽፋን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ክልሉ ካለው የህዝብ ቁጥር አንፃር ሲታይ ገና ብዙ መሠራት እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ባለሃብቶች የሚታየውን የጤናና የትምህርት ሽፋን ለማሳደግ ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ ከአፀደ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት፣ በጤና አገልግሎት ደግሞ ከክሊኒክ እስከ ሆስፒታል እንዲሁም የጤናና የቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የመድሃኒት ማምረቻና የጅምላ ማከፋፈያዎችን በመክፈት ሰፊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማካሄድና ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

በአገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዕድገት እያሳዩ ከመጡት የኢንቨስትመንት ዘርፎች አንዱ የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ለዚህ ዘርፍ መስፋፋት ምክንያቶች ደግሞ የኢንዱስትሪው ኢንቨስትመንት መጨመርና ለንግድ ሥራ የሚውሉ ግንባታዎች ማስፈለጋቸው ነው፡፡ የህዝብ ብዛት ፈጣን ዕድገት እያሳየ መምጣትና የመኖሪያ ቤት እጥረት ሰፊ በመሆኑ እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮች በከተሞች ብቻ ሳይወሰኑ ገጠሩንም ማካለላቸው ለዘርፉ አስፈላጊነት ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ ስለዚህ ባለሃብቶች በዚህ መስክ የመኖሪያ ቤቶችን ለቢሮና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ህንፃዎችን ሰርተው ቢያከራዩና በተለያዩ የህንፃ ግንባታና የመንገድ ሥራዎች ላይ ቢሰማሩ ክልሉን ማልማት የሚችሉ ከመሆኑም በላይ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት ነው፡፡

ክልሉ ሰፊ የማዕድን ሐብት ባለቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ያለው የማዕድን

ልማት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በአብዛኛው ለግንባታ አገልግሎት የሚውል ድንጋይ በማምረትና በመጠቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክልሉ ያለውን ያልተነካ የማዕድን ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ብሎም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የማዕድን ፍለጋና ማምረት የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ የሚጋብዝ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ባለሀብቶች የተለያዩ የሐይል ግብአቶችን በመጠቀም ለልማቱ አጋዥ መሆን ይችላሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር የነፋስና የፀሐይ ሐይል በተለይ በገጠሩ አካባቢ ከፍተኛ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የሐይል ምንጮች መሆናቸውን በመገንዘብ በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

የክልሉ መንግስት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በሰጠው ልዩ ትኩረት መነሻነት የተለያዩ ርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል፡፡በፌዴራል መንግስት የተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ዎችን በመተግበር ለባለሃብቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተንቀሳቅሷል፤ ባለሃብቶችን ወደ ክልሉ ለመሳብና ለማበረታታት ለተመረጡ የከተማ ፕሮጀክቶች መሬት በአነስተኛ ክፍያ በማቅረብ ከመስራቱም በላይ ለአርሶ አደር የይዞታ መሬት ካሳ ከፍሎ ከሶስተኛ ወገን ነፃ በማድረግ ለአበባና አትክልት ልማት ኢንቨስትመንት መሬት በነፃ በማቅረብ እያበረታታ ይገኛል፡፡ በጣና ሀይቅ ዙሪያ ሊኖር የሚችለውን የልማት አማራጭ ለማወቅና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የጣና ሃይቅ አካባቢን በከፍተኛ ባለሙያዎች አስጠንቶ ያለውን ጥቅም የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ክልሉ ከጐረቤት ሀገሮች ከሱዳንና ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኙ ሀገር አቋራጭ መንገዶች፣ ዓለም-አቀፋዊና የሀገር ውስጥ በረራዎችን የሚያስተናግዱ የአውሮፕላን ማረፊ ያዎች እና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች በስፋት የተዘረጉበት ክልል ነው፡፡

በመሆኑም  ኢጋር አካላትና ባሃብቶች በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ዘርፎች ገብተው እንዲሳተፉ ክልሉ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አሟልቶ እየጠበቀ ነው፡፡ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

# II.ኢኮኖሚ ዘርፍ

## ግብርና ልማት

### የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀትን ማጠናከር

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የአርሶ አደሩን አደረጃጀት ማጠናከር የግብርና ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ እንዲሆን ያግዛል፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 119,406 የአባወራ እና እማወራ የልማት ቡድን ለማጠናከር ታቅዶ 119,406 (100%) ማደራጀት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 597,030 የ1ለ5 አደረጃጀት ለማጠናከር ታቅዶ 594,751 (99.6%) ለማጠናከር ተችሏል፡፡

### ሠርቶ ማሳያ ማጠናከርና ማካሄድ

በአርሶ አደር ማሳ የሚከናወን የግብርና ሰርቶ ማሳያ ምርትና ምርታማነትን ከመጨመሩ በተጨማሪ ለአርሶ አደሩ የእውቀት ሽግግር ያደርጋል በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በግብርና ስራ የተሰማሩ አርሶ አደሮችን እውቀት እና ክህሎት በማሳደግ የቴክኖሎጅና የአዳዲስ አሰራሮች ተጠቃሚ ለማድረግ የተለያዩ የግብርና ልማት ሠርቶ ማሳያዎችን በማከናወን በሰብል ልማት፤ በስርዓተ ምግብ፤ በመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ልማት በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል እና በሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ 67,118 ሠርቶ ማሳያ ለመስራት ታቅዶ 119,911 /179%/ ማድረስ ተችሏል፡፡

በመስኖ ልማት አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ሰርቶ ማሳያዎችን ለመስራት በአርሶ አደር ማሳ እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም በድምሩ 4,690 ሰርቶ ማሳያዎችን ለመስራት ታቅዶ በአርሶ አደር ማሳ እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም 4,773 (101.8%) ሰርቶ ማሳያዎችን በ951 ሄክታር መሬት ላይ መስራት ተችሏል፡፡

አርሶ አደሩ አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን እንዲጠቀምና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 6,574,946 አርሶ አደር የኤክስቴንሽን የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6,326,483 (96%) አርሶ አደር ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን በማጠናከርና በማዘመን የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ እንዲወጡ በማድረግ የአርሶ አደሩን የእውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በተሰራው ስራ 300 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማጠናከር ታቅዶ 261 (87%) ለማከናወን ተችሏል፡፡

## ሰብል ልማትና ጥበቃ

መንግስት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ እንደ አገሪቱ አንቀሳቃሽ ሞተር በመውሰድ በሰብል ልማትና ጥበቃ በ2014/2015 የምርት ዘመን 4,857,410 ሄክታር መሬት በማልማትና ምርታማነቱን በ29.4 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ 143,033,372 ኩንታል ምርት ለማምረት አቅዶ 4,807,709 ሄክታር (99%) በዘር በመሸፈን በቢሮ ቅድመ ምርት ትንበያ መሰረት 140,192,914 ኩንታል (98%) ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ከተሰበሰበው ምርት መካከል በኮምባይነርና ትሬሸር የተሰበሰበው 253,764 ሄክታር ሲሆን በምርት ደግሞ 4,992,328 ኩንታል መሰብሰብ ተችሏል፡፡እንዲሁም በተመረጡ 12 የኮሞዲቲ ሰብሎች 1,706,173 ሄክታር መሬት በማልማት 66,282,805 ኩንታል ለማምረት ታቅዶ 1,561,917.00 ሄክታር (91.5%) በዘር በመሸፈን ምርት የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡



የሩዝ ሰብል-ደቡብ ጎንደር (ፎገራ ወረዳ)



## የወጀልና ሽበልበረንታ ጤፍ-ምስራቅ ጎጃም

### የበልግ ሰብል አሰባሰብ

የምርት ብክነትን ለመከላከል የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው።ስለዚህ በበጀት አመቱ በበልግ እርሻ 218,286 ሄክታር ማሳ በማልማት 4,007,990 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ በተለያዩ ሰብሎች 230,312 ሄክታር (105%) ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል።

### የመኸር የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ

በበልግ ወቅት የሚጥለውን ዝናብ በመጠቀም የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ማከናወን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ሁነኛ መፍትሄ ነው፡፡በመሆኑም በ2015/16 መኸር ወቅት 5,033,643 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 1ኛ እርሻ 4,434,242 ሄክታር መሬት የታረሰ ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅዱ 88% ደርሷል፡፡ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት 1ኛ እርሻ ከታረሰው 4,032,548 ሄክታር ጋር ሲነጻጸር የእርሻ ሥራ አፈጻጸም 399,694 ሄክታር ጭማሪ አሳይቷል፡፡

## የዘር ስራ አፈጻጸም

በ2015/16 ምርት ዘመን በዘር ለመሸፈን ከታቀደው 5,033,643 ሄክታር ማሳ መካከል በዘር የተሸፈነው 1,725,471 ሄክታር (34%) ሲሆን በመስመር ለመዝራት ከታቀደው 2,413,679 ሄክታር መሬት መካከል 870,669 ሄክታር በመስመር መዝራት ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በተመረጡ 10 የኮሞዲቲ ሰብሎች 1,978,540 ሄክታር ማሳ ለማልማት ታቅዶ 1,708,053 ሄክታር (88%) ማሳ በመለየትና 34,356 (86%) ክላስተር በማደራጀት 594,751 ሄክታር (30%) ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡ከዚህም መካከል 804,902 ሄክታር በትራክተር ለማረስ ታቅዶ 391,062 ሄክታር (48.5%) ማሳ በ1,524 ትራክተር ማረስ ተችሏል፡፡

በ2015/16 ምርት ዘመን ለመኸር ልማት የሚውል በአዲስ 9,206,859 ኩንታልና የከረመ 288,153 ኩንታል በድምሩ 9,495,012 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ በአዲስ 5,296,670 ኩንታል (57%) የተገዛ ሲሆን እስከ በበጀት አመቱ መጨረሻ ከወደብ የቀረበ 3,056,843 ኩንታል (57.7%) ሲሆን የከረመውን 299,804 ኩንታል ጨምሮ 3,356,638 ኩንታል ለስርጭት ቀርቦ 2,937,354 ኩንታል (60%) ለአርሶአደር ተሰራጭቷል፡፡

በምርት ዘመኑ 357,000 ኩንታል የተለያዩ ምርጥ ዘሮችን ለማቅረብ ታቅዶ በጥራት ከተረጋገጠው መካከል 213,000 ኩንታል በመሰብሰብ በክሮፕ ካላንደሩ መሰረት ቅድሚያ የሚዘራው 130,205 ኩንታል ምርጥ ዘር ቀርቦ 117,918 ኩንታል (31%) ማሰራጨት ተችሏል፡፡

በምርት ዘመኑ ያጋጠመውን የሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ እጥረት በተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማካካስ የኮምፖስት ዝግጅትን 80,167,495 ሜትር ኩብ የታቀደ ሲሆን 78,040,063 ሜትር ኩብ (97%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ከዚህም 78,019,595 ሜትር ኩብ ኮምፖስት በ2,235,605 ሄክታር ማሳ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡



## የማዳበሪያ ስርጭት

## የቨርሚ ኮምፖስት ዝግጅት

በአካባቢያችን ተጥለው አካባቢን እየበከሉ የሚገኙ ቆሻሻዎችን በመጠቀም ወደ አፈር ማዳበሪያነት በመቀየር የቨርሚን ኮምፖስት ለማዘጋጀት በተሰራው ስራ በ2015 ዓ.ም ከታቀደው 390,317 ኩንታል የቨርሚ ኮምፖስት ውስጥ 198,172 ኩንታል (50.8%) ቨርሚ ኮምፖስት ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከተዘጋጀው 60,632 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት ጋር ሲነጻጸር 137,540 ኩንታል ጭማሪ አለው፡፡



ቨርሚን ኮምፖስት-አዴት ወረዳ

## የባዮሳለሪ ኮምፖስት ዝግጅት

የባዮ ጋዝ ተረፈ ምርትን በመጠቀም የባዮሰለሪ ኮምፖስት ለማዘጋጀት በተሰራው ስራ በበጀት አመቱ ከታቀደው 246,836 ሜትር ኩብ የባዮሳለሪ ኮምፖስት ውስጥ 137,861 ሜትር ኩብ (56%) ባዮሳለሪ ኮምፖስት ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከተዘጋጀው 62,815 ሜትር ኩብ ባዮሳለሪ ኮምፖስት የ75,046 ሜትር ኩብ ጭማሪ አለው፡፡አጠቃቀሙን በተመለከተ 12,838 ሄክታር ማሳ ላይ 136,936 ሜትር ኩብ ባዮሳለሪ መጠቀም ተችሏል፡፡

## የኮትቻ አፈር ልማት

በበጀት አመቱ በግብርና ባለሙያዎች ድጋፍ የጥቁር አፈር መሬትን በማንጣፈፍ አርሶ አደሩ ወደ ልማት እንዲገባ በመደረጉ 430,553 ሄክታር ማሳ በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ ለማጠንፈፍ ዕቅድ ተይዞ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በማከናወን እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ

የተለየ ማሳ 266,856 ሄክታር (62%) የታረሰ መሬት 192,077 ሄክታር (44%) እና በክላስተር ማደረጀት የተቻለው ደግሞ 5,637 ሄክታር ነው፡፡

## የህየወ ማዳበሪያ ልማት

በበጀት አመቱ 409,635 ሳቸት በማቅረብ 102,409 ሄክታር የጥራጥሬ ሰብል በህየወ ማዳበሪያ ለማልማት ታቅዶ 138,882 ሳቸት (34%) ቀርቦ 99.4% ማሰራጨት ተችሏል፡፡



መደበኛ ኮምፖስት ዝግጅት ሲጎበኝ -ሰከላ ወረዳ

## አሲዳማ አፈር ልማት

አሲዳማ አፈርን በኖራ በማከም የተሻለ ምርት ለማግኘት አንዱ አማራጭ ነው፡፡በመሆኑም በ2015 ዓ.ም የአሲዳማ አፈር ልማትን ለማከም 12,516 ሄክታር መሬት በዕቅድ ተይዞ 62,580 የአሲዳማ አፈር ናሙና ለማሰባሰብ ታቅዶ 61,095(97.6%) የአሲዳማ አፈር ናሙና ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው 58,101 የአፈር ናሙና

የ2,994 ጭማሪ አለው፡፡ ከዚህም ወደ አፈር ምርመራ ላቦራቶሪ 58,029 የአፈር ናሙና የተላከ ሲሆን ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ1,839 ጭማሪ አለው፡፡

## የኖራ አቅርቦት፣ ስርጭት እና አጠቃቀም

በበጀት አመቱ 250,320 ኩንታል ኖራ በማቅረብ 12,516 ሄክታር መሬት በኖራ ለማከም ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ 30,106 ኩንታል ኖራ ቀርቦ 21,494 ኩንታል (ከቀረበው 71.4 %) የተሰራጨ ሲሆን በ972 ሄክታር (7.8%) ማሳ ላይ 16,146 ኩንታል ኖራ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## የዘር ብዜት የፊዚካል ስራ

በ2015/16 ምርት ዘመን በመኸር ወቅት 22,258 ሄክታር መሬት ላይ 572,170 ኩንታል ዘር በተለያዩ ዘር አባዥ ድርጅቶች እና በተለያዩ የሰብል ዝርያዎች ቅድመ መስራችና መስራች የተመሰከረለት ዘር ለማባዛት ታቅዶ በአመቱ መጨረሻ 4,609.7 ሄክታር (20.7%) ማሳ በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

## የአትክልትና ፍራፍሬ መስኖ ውሃ አጠቃቀም

የመስኖ ልማት ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ በመሆኑ በበጀት አመቱ የአትክልት ፍራፍሬና መስኖ ልማት ስራ እንቅስቃሴ በነባር 246,194 ሄክታር እና በአዲስ 11,561 ሄክታር በድምሩ 257,755 ሄክታር መሬት በማልማት 47,475,059 ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ በነባር 247,243 ሄክታር (100%)፤ በአዲስ 32,824 ሄክታር (ከ100% በላይ) በድምሩ 280,067 ሄክታር መሬት (109%) በዘር በመሸፈን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ዙር **33,234,881 ኩንታል ምርት** (70%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት

የግብርና ስራ ያለ ውሀ ሊታሰብ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡የግብርና ስራ እጅግ ውጤታማ የሚሆነው የግብርናው ምርት የሚፈልገውን ውሀ መጠን በሚፈልገው መጠንና ጊዜ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡በመሆኑም በ2015 ዓ.ም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 252,000 ሄክታር መሬት በማልማት 10,000,000 ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት ታቅዶ 213,232 ሄክታር (84.6%)

መሬት በስንዴ ዘር የተሸፈነ ሲሆን 167,768 ሄክታር ላይ 6,239,710 ኩንታል (63%) ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡



የስንዴ ሰብል-ምስራቅ ጎጃም(ባሶ ሊበን ወረዳ)

## የቡናና ፍራፍሬ ችግኝ ዝግጅት

በበጀት አመቱ ቡና ለማልማት በተሰራው ስራ 11,000,000 ችግኝ በማፍላት በ3,520 ሄክታር ላይ ለመትከል ታቅዶ 9,062,983 (82.4%) ችግኝ ተዘጋጅቶ ለቀጣይ ተከላ ስራ እንክብካቤ እየተደረገለት ነው፡፡የቆላ ፍራፍሬ 7.5 ሚሊዬን ችግኝ በማዘጋጀት 13,472 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ 6,621,597 (88%) ችግኝ ተዘጋጅቶ የእንክቤካቤ ስራ እየተደረገለት ነው፡፡ የደጋ ፍራፍሬ 600,000 ችግኝ በማዘጋጀት 325 ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል ታቅዶ 663,864 (111%) ችግኝ ተዘጋጅቶ የእንክቤካቤ ስራ እየተደረገለት ይገኛል፡፡ከዚህ መካከል 872,513 የአቮካዶ እና 375,219 የማንጎ ችግኝ ለመከተብ ታቅዶ 574,795 የአቮካዶ እና 561,101 የማንጎ ችግኝ ተከትቦ ለተከላ ተዘጋጅቷል፡፡በተመሳሳይ በ2015/16 መኸር የቡናና

ፍራፍሬ ተከላ ጉድጓድ ዝግጅት ለቡና 4,254,805 (58%)፤ ለቆላ ፍራፍሬ 3,126,511 (53%) እና ለደጋ ፍራፍሬ 239,169 (45%) በድምሩ 7,620,485 (55%) የተከላ ጉድጓድ ተዘጋጅቷል፡፡

## የተፈጥሮ ሃብት ልማት ስራ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፤የደኖች መጨፍጨፍ እና የአፈር መከላት ለድርቅ መንስኤ ናቸው፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ የተፈጥሮ ሀብትን ወደ ነበረበት ለመመለስ በተሰራው ስራ 8,312 በነባር 236 በአዲስ በድምሩ 8,548 ተፋሰሶችን ለይቶ ወደ ተግባር ለማስገባት ታቅዶ 8,548 (100%) ተፋሰሶችን በመለየት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡በ2015 በጀት አመት የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ የሚሰራ 4,320,736 የሰው ሃይል ለመለየት ታቅዶ 4,247,708 (98%) መለየት ተችሏል፡፡የልማት መሳሪያ ቆጠራና ዝግጅትን ሲታይ 3,702,182 ለመለየት ታቅዶ 3,622,491 (97.8%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ 273,024 የቅየሳ መሳሪያ ለማዘጋጀት ታቅዶ 243,878 (89.3%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

እንደ ክልል በአማካይ 23 የስራ ቀናትን ሁሉም ተፋሰሶች የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት በህዝብ ንቅናቄ በድግግሞሽ 83,009,410 ሰው/ቀን ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 85,872,872 ሰው/ቀን (103%) ማሳተፍ ተችሏል፡፡ የ2015 ዓም የተፈጥሮ ሃብት 310,292 ሄክታር በተለያዩ መሬት ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት ታቅዶ 357,183 (115%) ሄክታር መሬት ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

በ2015 ዓ.ም ችግኝ ከመፈላቱ በፊት 201,289 ሄክታር የተከላ ቦታ ለመለየት ታቅዶ 199,101 ሄክታር መሬት (99%) መለየት ተችሏል፡፡ ለዚህም ለቀጣይ አረንጓዴ ልማት ስራችን 1.697 ቢሊየን ችግኝ በማቀድ ከዚህ ውስጥ 1.636 ቢሊየን (96.4.5%) ችግኝ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለአረንጎዴ አሻራ ስራ የሚሆን በቁጥር 1.53 ቢሊየን የችግኝ መትከያ ጉድጉድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በቁጥር 1.35 ቢሊየን (88%) ጉድጓድ ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡



ተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ- ደቡብ ወሎ ( አርጎባ ወረዳ)

# ከተሞችና መሰረተ ልማት

የአብክመ ከተሞችና መሰረተ-ልማት ቢሮ በከተሞች ጉዳይ ላይ ቁልፍ ሚና ያለውና ከተሞች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ ሞተርና ማዕከል፣ ውብና ጽዱ፣ ለኑሮ ተስማሚ እንዲሆኑ በማስቻል ለክልላችን ብሎም ለአገራችን ብልፅግና ወሳኝ የሆኑ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡ በመሆኑም ቢሮው የክልሉ ከተሞች ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የተከተሉ፣ በፕላን የሚመሩ፣ መሰረተ ልማት የተስፋፋባቸው፣ፅዱ፣ ውብ፣ የልማትና የአገልግሎት ማዕከል እንዲሆኑ በማስቻልና የዳበረ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን እንደ ተልዕኮ ይዞ የከተሞችን ልማት በማስፋፋት የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ባከናወናቸው ተግባራት በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

ይሁን እንጅ በአሁኑ ሰዓት በክልላችን በየአካባቢው አዳዲስ ከተሞች በመፈጠራቸው ምክንያት የከተማ ቁጥር መጨመር፣ ነባር ከተሞችም ወደ ጎን መስፋት፣ በዚህም የከተሞች ህዝብ ብዛት

በፍጥነት የጨመረበት እና የክትመት ምጣኔውም በፍጥነት እያደገ የመጣበት ሁኔታ አለ፣ ይህንኑ ተከትሎም በከተሞች የሥራ አጥነት መበራከት፣ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት በእጅጉ መጨመር፣ የመሰረተ ልማት ፋላጎትና ጥያቄ ማደግ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ተደራሽ እና አርኪ አለመሆን፣ የፕላን ጥሰትና ህገ-ወጥ የመሬት ወረራ የተበራከተበት ሁኔታ ላይ ይገኛል። በተለይም የከተማ ነዋሪውን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በከተሞች የሚታየውን ሌብነት በመታገል እና ተቋማዊ አፈፃፀምን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር በመፍጠር በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል።በመሆኑም እነዚህንና ሌሎች በከተሞች የሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ከተቋሙ የ10 ዓመት መሪ የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ የተቀዳ የ2015 በጀት ዓመት የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ ታቅዶ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል።

## ከተሞች እና መልካም አስተዳደር

በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በመጀመሪያ ሁሉም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ደረጃ ወጥቶላቸው ግልፅነት፣ተጠያቂነትና የተገልጋዩን እርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው። ከዚህም አኳያ በ2015 ዓ.ም በከተሞች የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል 7 የተለያዩ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው የወረዱ ሲሆን በክልሉ በሚገኙ 77 ከተማ አስተዳደሮች እና በ 7 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶች እንዲተገበሩ ለማድረግ ታቅዶ በ84 (100%) ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች እና 7 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል።

## የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግ

የህብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ለማሳካት በመንግስት ውስን በጀት ብቻ መሸፈን አይቻልም በመሆኑም በ2015 ዓ.ም በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የመብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ) ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 50% አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 651,692,591 ብር፣ በጉልበት 658,106,100 ብር፣ በቁሳቁስ 415,859,830 ብር

በድምሩ 1,725,658,521 ብር የሚገመት ገንዘብ ለልማት ስራዎች አስተዋጾ ተደርጓል። ለነዚህ የልማት ስራዎች በመንግስት በኩል 2,070,132,808 ብር ወጪ ተደርጓል።



በከተማ የውስጥ ገቢና በህብረተሰቡ ተሳትፎ የተሰራ መንገድ፡- ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም

በበጀት አመቱ የክልላዊ ልማት ፕላን እና የከተሞች ትስስር ፕላን ዝግጅት 100% እንዲጠናቀቅ በሚመለከተው አካል ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን ስራውን የሚሰራው UN Habitate ባዘጋጀው ወርክ ሾፕ ላይ ሁለት ጊዜ መሳተፍ ተችሏል። በአማካሪ ድርጅቱ የተዘጋጀውን የኢንስፔክሽን ሪፖርት በመገምገም ግብዓት ተሰጥቷል።

የፕላን ዝግጅት ሂደቱ አሁን ያለበትን ሁኔታ በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሪፖርት 100% ተጠናቋል። የነባራዊ ሁኔታ ጥናት 90% ተጠናቋል። ይህም ከአጠቃላይ ስራው 48% ድርሻ ይኖረዋል። በውሉ መሰረት የፕሮጀክቱ እድሜ 18 ወር ሲሆን ለ6 ወር የተራዘመ በመሆኑ አጠቃላይ ስራው በቀጣዩ በጀት ዓመት እስከ ታህሳስ 30/2016 ዓ/ም የሚጠናቀቅ ይሆናል።

## የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች

የከተማ መሬት ሃብትን ከንጥቂያና ከወረራ በመከላከል በቁጠባ ለላቀ ልማት ማዋል እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ዘመን ላይ ስለምንገኝ የጠራ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ማስተዳደር ይገባል። ከዚህም አኳያ ከተሞች በግልጽ የሚታወቅ የፕላን ወሰን እንዲኖራቸው በማድረግ የመሬት ሃብታቸውን በሚገባ ቆጥረውና መዝግበው ማስተዳደር እንዲችሉ የ203 ከተሞችን (77 ከተማ አስተዳደሮችና 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች) የፕላን ወሰን

እንደገና እንዲካለል በማድረግ የተሟላ መረጃ ተደራጅቶ ለመያዝ ታቅዶ 378 (ከ100% በላይ) ከተሞች መረጃቸውን አደራጅተው መያዝ ችለዋል፡፡

በበጀት አመቱ በ302 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) የተተከሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ታቅዶ 354 (ከ100% በላይ) ከተሞች በመሬት ላይ የሚገኙ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመለየት መረጃቸው ተደራጅቶ እንዲያዝና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ያደረጉ ናቸው፡፡ እንዲሁም በ302 ከተሞች (77 ከተማ አስተዳደሮች፣ 126 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች እና 99 ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች) የጠፉትንና የተነቀሉትን 600 የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በአዲስ እንዲተኩ ለማድረግ ታቅዶ ቀደም ሲል የጠፉ 2,117 (ከ100% በላይ) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መተካት ተችሏል፡፡ በበጀት አመቱ በ32 የUIIDP ፕሮግራም ተጠቃሚ ከተሞች የመሬት ሀብት ቆጠራና ምዝገባ ሥርዓት በመዘርጋት በከተሞች የፕላን ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ 250,000 ሄክታር ቦታዎችን በአገልግሎት አይነት በመቁጠርና በመመዝገብ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ208 ከተሞች 115,755.59 ሄክታር (46.3%) ቁራሽ መሬት መቁጠርና መመዝገብ ተችሏል፡፡

## የቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች

በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክያቶች ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረግ ፍልሰትን ተከትሎ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የቤት ልማት ስትራቴጂዎች ማለትም በሪል ስቴት 3,610 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 166 (4.6%) ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማኀበራት 38,261 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 29,555 (77.25%) ቤቶች፣በግለሰቦች 25,500 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 27,725 (108.73%) ቤቶች፣ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው 6,060 የኪራይ ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 1,668 (27.52%) የኪራይ ቤቶች በጠቅላላው 81,067 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ 59,114 (72.92%) ቤቶችን መገንባት ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ 97,542 ወንዶች እና 50,113 ሴቶች በድምሩ 147,655 የመኖርያ ቤት ፈላጊዎችን በ7,056 በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህራት እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

## የከተማ መሰረተ- ልማት ስራዎች

ከተሞች የልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል የክልሉ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቦ ዘርፈ-ብዙ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን የማስፋፋት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ሌላው UIIDP ፕሮግራም ከአለም ባንክ፣ ከከተሞች፣ ከክልሉ መንግስት እና ከህብረተሰቡ ተሳትፎ በሚገኝ ገንዘብ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህም በ2015 በጀት ዓመት በ32 UIIDP ፕሮግራም ተጠቃሚ ከተሞች ከአለም ባንክ ድጋፍ፣ ከክልሉ መንግስት ድጎማ፣ ከከተሞችና ከህዝቡ በተገኘ 4.8 ቢሊየን ብር ካፒታል በጀት 1,034 ፕሮጀክቶችን እንዲሁም የአለም ባንክ ድጋፍ በሌለባቸው 380 ከተሞች በህዝብ እና በከተሞች የውሰጥ ገቢ 848 አዲስ ፕሮጀክቶችን በድምሩ በ412 ከተሞች 1,882 የመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች በማከናወን የህዝባችን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

## በከተሞች የፕሮጀክቶች ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሁኔታ | በየከተሞች የፕሮጀክቶች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ከ2013 እና ከ2014 በጀት ዓመት የዞሩ | በ2015 በጀት ዓመት በአዲስ የታቀዱ | የጥገና ፕሮጀክቶች | የፕሮጀክቶች ድምር |
| የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶቸ ብዛት | 69 | 508 | 305 | 882 |
| ከ50% - 80% አፈፃፀም ያላቸው | 27 | 32 | 29 | 88 |
| ከ50% በታች አፈፃፀም ያላቸው | 6 | 38 | 20 | 64 |
| ድምር | 102 | 578 | 354 | 1034 |

## የመንገድ ግንባታ

የመንገድ ግንባታን በተመለከተ 200 ኪሎ ሜትር የጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ መንገድ ለመገንባት ዕቅድ ተይዞ 88.82 ኪሎ ሜትር (44.41%) ተገንብቷል፡፡ ጠጠር መንገድ 790 ኪሎ ሜትር ለመገንባት ታቅዶ 700.36 (88.65%) ኪሎ ሜትር ተገንብቷል፡፡ እንዲሁም 962 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመክፈት ታቅዶ 1,124.83 (ከ100% በላይ) ኪሎ ሜትር መንገድ መክፈት የተቻለ ሲሆን አስፓልት መንገድም በተመለከተ 45 ኪሎ ሜትር ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ 33.31 (74.02%) ኪሎ ሜትር ተገንብቷል ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ ለመገንባት ታቅዶ 161.94 (46.94%) ኪሎ ሜትር ተገንብቷል፡፡

## መንገድ ጥገና

በበጀት አመቱ 20 ኪሎ ሜትር ጌጠኛ መንገድ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 12.98 (64.9%) ኪሎ ሜትር ተጠግኗል፡፡ ጠጠር መንገድ ጥገናን በተመለከተ ደግሞ 610 ኪሎ ሜትር ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 565.25 (92.35%) ኪሎ ሜትር ተጠግኗል፡፡በተመሳሳይ 40 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 4.99 (11.19%) ኪሎ ሜትር የተጠገነ ሲሆን የውስጥ ለውስጥ መንገድ በጌጠኛ ድንጋይ ለማንጠፍና በጠጠር ለመስራት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

## የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎች

ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አንዱ በከተማ ፅዳትና ውበት ስራዎች ዙሪያ የተለያዩ የንቅናቄ ሰነዶችን በማዘጋጀትና የከተማውን ህዝብ በማወያየት በአብዛኛው ከተሞች የጽዳት ቀን ተወስኖ ነዋሪው ሰፈሩንና አካባቢውን እንዲያጸዳ በማድረግ በፅዳት ስራ እንዲሳተፍ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በ660 ከተሞች ለወንድ 413,000 እና ለሴት 413,000 በድምሩ 826,000 ነዋሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ለማሳተፍ ታቅዶ በ341 ከተሞች ለወንድ 512,061 እና ለሴት 495,602 በድምሩ 1,007,663 (ከ100% በላይ) ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን ወንድ 461,671 እና ሴት 460,351 በድምሩ 922,022 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍል በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ወርሃዊና ሳምንታዊ የፅዳት ቀን ወስኖ ተሳትፏል፡፡ በ210 ከተሞች የሚገኙ 5,150 ተቋማትና ግለሰቦች ከ20 - 50 ሜትር ርቀት ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን (የውሃ ማፋሰሻ በዮችን) እንዲያፀዱ ለማድረግ ታቅዶ በ265 (ከ100% በላይ) ከተሞችና ክፍለከተሞች የሚገኙ 8,640 (ከ100% በላይ) ተቋማትና ግለሰቦች ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን ማጽዳት ችለዋል፡፡በክልሉ በሚገኙ 77 ከተማ አስተዳደሮች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም አረንጓዴ ልማት ስርዓትን ለማሻሻል የተዘጋጁ ስታንዳርዶችና የአሰራር ማኑዋሎች በአግባቡ እንዲተገበሩ ለማድረግ በተሰራው ስራ በ89 (100%በላይ) ከተሞች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡



አረንጓዴ ልማት-ደብረ ማርቆስ

## የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች

በከተሞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙና ለምግብ እጥረት ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዲቻል የኢፌዲሪ መንግስት የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት በክልላችን ባሉ 17 ከተሞች (16 አዲስና በነባሩ በደሴ ከተማ) በኑሮ ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች የሆኑና የመስራት አቅም ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በህብረተሰብ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ማህበራዊ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች፣ በከተማ ግብርና እና በሌሎችም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች በማሳተፍና የስራ እድል በመፍጠር ገቢ እንዲያገኙና ከሚያገኙት ገቢም ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ ለማስቻል እየተሰራ ይገኛል፡፡

በምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ምንነት፣ የተጠቃሚዎች ምልመላ፣ ቅሬታ አቀራረብ፣ የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ፣ ወዘተ ላይ ለ336,000 ተጠቃሚዎች፣ ሕብረተሰብ፣ ባለድርሻ አካላት፣ አመራር እና ባለሙያ ወዘተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለመስራት ታቅዶ ለ350,035 ለከተማና ለቀበሌ አመራር፣ ለባለድርሻ አካላትና ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡





## የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም የመስክ ምልከታ-ላሊበላ

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ ስራዎች

የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናማ በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማበርከት የሚጠበቀበትን ሚና መጫወት እንዲቻል የሚገነቡ ግንባታዎች የህዝቡን ደህንነትና ጤንነት ያገናዘቡ እንዲሆኑና ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች አካታች መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጥራት ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ ለማስቻል የሬጉላቶሪ እና በዘርፉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ከቢሮው ከኮንስትራክሽን አንጻር የሚጠበቁ ቁልፍ ሥራዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ለ6,100 አነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ምዝገባ በማድረግ ለመመዘን ታቅዶ 5,435 (89.09%) ባለሙያዎችን በመመዝገብ ከተመዘገቡት ውስጥ 3,160 (58.14%) ባለሙያዎች ተመዝነው 1,815 (57.43%) ምዘናውን ያለፉ ሲሆን ከነዚህም ምዘናውን ያላለፉ 1,345 አነስተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ከአሰሪዎቻቸው ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የክህሎት ማሚያ የኩባንያ እና ትብብር ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 439 (32.63%) ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

# ኅብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ

## የቁጠባ አገልግሎትን ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም ብር 1,360,775,494 በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት መደበኛ ቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ 1,659,190,373 (100%) በላይ መደበኛ ቁጠባ ማሰባሰበ ተችሏል፡፡

## የብድር ስርጭት አግልግሎትን ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም ብር 6,620,306,519 የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበራት ለአባሎቻቸው ብድር ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 8,527,709,256 (100%) በላይ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባ ህብረት ስራ ማህበር ብድር በማሰራጨት ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም 127,274 (ሴት 43,147) የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## የኦዲት አገልግሎት

በ2015 ዓ.ም ለ72 ዩኒዮኖች የሂሳብ ምርመራ ለማድረግ እቅድ ተይዞ 67 (93%) ማከናዎን ተችሏል፡፡የኦዲት አገልግሎት ካገኙት ኅብረት ስራ ማህበር መካከል 5,356 መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር መካከል 4437 ያህሉ ብር 590,933,888.00 እና 56 ዩኒየኖች ብር 434,637,527.00 የተጣራ ትርፍ ማግኘት የቻሉ ሲሆን 533 መሠረታዊ ኅብረት ስራ ማህበር ብር 35,195,799.00 እና 75 ዩኒየኖች ብር 17,650,811.00 ኪሳራ ታይቶባቸዋል፡፡

## የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠት

በበጀት ዓመቱ ለ72 ኅብረት ስራ ማህበር ዩኒየኖችን የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 59 (82%) የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

## የሕግ አገልግሎት

የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ወክሎ በአደራጅ መስሪያቤቱ የህግ ባለሞያ እና በአቃቢ ህግ መስሪያቤት አቃብያነ ህግ ክስ የመመስረት ስራ የሚከናወን ሲሆን ለ558 ኅብረት ሥራ

ማኀበራት በ 759 ጉዳዮች ብር 47,538,519 ክስ የተመሰረተ ሲሆን በ414 ጉዳዮች ብር 21,435,977 ለኅብረት ሥራ ማኀበራት የተወሰነ ሲሆን ቀሪው ብር ለግለሰቦች ተወስኗል፡፡በተመሳሳይ በድርድር የተመለሰ ብር 48,820,041 እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ብር 23,298,143 በድምሩ 72,118,184/ ብር ማስመለስ ተችሏል፡፡

## መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኀበራትን ማቋቋም

በ2015 ዓ.ም 350 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኀበራትን ለማቋቋም ዕቅድ ተይዞ 2,520 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኀበራት የተቋቋሙ ሲሆን ፤ አፈፃፀሙም ከ100%በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ ለአፈፃፀሙ ከፍተኛ መሆን ምክንያቱ በፕሮጀክቶች እና በህብረተሰብ ፍላጎት በእንስሳት አርቢዎች የጋራ ፍላጎት ቡድኖች ወደ ኅብረት ስራ ማህበር በማደጋቸው እና የመስኖ ሃብት ልማት ኅብረት ስራ ማህበር በመቋቋማቸው ነው፡፡



ህብረት ስራ ማህበራትን ማቋቋም-,ደቡብ ጎንደር (ወረታ)

## ዩኔን ማቋቋም

የኅብረት ሥራ ማኀበራትን ዩኒየን ከማደራጀት አኳያ በምስራቅ ጎጃም ዞን እና በደቡብ ወሎ ዞን ሁለት የዘር ብዜትና ግብይት ዩኒየኖችን ማደራጀት የተቻለ ሲሆን 26 መስራች አባላትን እና 3,140,000 መነሻ ካፒታል ይዞ የተቋቋመ ሲሆን ከመመዝገቢያ 260,000 እና ከወረት ዕጣ 2,880,000 ብር በመያዝ ማደራጀት ተችሏል፡፡ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የተቋቋሙ ዩኔኖች የተለያዩ ጉባኤዎችን በማካሄድ የተለያዩ ውሳኔወችን አሳልፈዋል፡፡



ፀሀይ ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር -ማዕከላዊ ጎንደር

## አካባቢና ደን ጥበቃ

የአማራ ክልል የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት፣ ብክነትንና መጤ ወራሪ ዝርያዎችን በመቆጣጠር የህብረተሰቡን ደህንነት የማረጋገጥ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት እንዲቻል መስሪያቤቶችና ፈጻሚዎችን የማስተባበር፣ የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ተግባራትን በማከናወንና የአጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን ተሣትፎና ተጠቃሚነት የማሳደግ ተልዕኮ ይዞ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

### አየር ንብረት ለውጥ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት

በበጀት አመቱ የልማት ሥራዎች ከአካባቢ ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ ለማድረግ በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ በቅድሚያ በመገንዘብ የማጣጣሚያ እና የማስተሰሪያ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡ ስለሆነም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልትን ለህብረተሰቡ በማስገንዘብ፣ የልቀት ቅነሳ ተግባሪ መስሪቤቶችን በማስተባበር እና በመከታተል ረገድ ተግባራትን በዕቅድ አካተው እንዲተገብሩ ተደርጓል፡፡የተሻሻሉ ሃይል ቆጣቢ ምድጃዎችና ሶላር ቴክኖሎጅዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የማስተዋወቅ፣ ተደራሽ የማድረግና የመከታተል ስራ የተከናወነ ሲሆን በድምሩ 188,550 ቴክኖሎጂዎች ተደራሽ ሆነዋል፡፡ ነገር ግን አመራሩ ለአየር ንብረት ለውጥ ሥራዎች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ፣ በታችኛው አደረጃጀት ተግባሩን የሚያስተባብርና የሚከታተል ራሱን የቻለ ባለሙያ አለመኖሩ እና የቅንጅታዊ አሰራር መጓደል በክፍተት የታዩ ናቸው፡፡

ስድስት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎችን ለመታደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጆዎች ተግባራዊ የሚደረጉባቸው ስልቶችን እንዲያካትቱ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ እንዲያገኙና እንዲተገብሩ ማድረግ

በ2015 ዓ.ም 4,000 ለሚሆኑ አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች የሚያቀርቡትን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ በመገምገም መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ ይሁንታ ፈቃድ እና ለ1,500 ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ5,986 (ከ100% በላይ) አዲስ ፕሮጀክቶች ሰርተፊኬት እንዲሁም ለ2,968 (ከ100% በላይ) ነባር ፕሮጀክቶች ማደስ የተቻለ ሲሆን ከይሁንታ ፈቃድ፣ ዕድሳትና ቅጣት 650,000 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 2,297,100 (ከ100% በላይ) ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## የአካባቢ ተፅዕኖ ማማከር ፈቃድ

በበጀት አመቱ ለ50 የአካባቢ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ለ29 አማካሪዎች የእድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 49 (98%) የአካባቢ አማካሪዎች ፈቃድ እና ለ22 (69%) እድሳት መስጠት ተችሏል፡፡ የይሁንታ ፈቃድ አግኝተው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች በገቡት ውለታ መሠረት እየሰሩ መሆናቸውን በአካባቢ ክትትል፣ ምርመራና ቁጥጥር በማረጋገጥና ግብረ መልስ በመስጠት ህግ እንዲከበር ለማድረግ የሚስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የይሁንታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ስራ የገቡ 3,000 ፕሮጀክቶች በገቡት ውለታ መሰረት መተግበራቸውን በክትትል ለማረጋገጥ ታቅዶ 4,616 በሚሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን በተደረገው ክትትልም 1,991 ፕሮጀክቶች ላይ የቁጥጥር ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም ከፍተኛ ብክለትና ብክነት ባደረሱ እና የህግ ጥሰት በፈጸሙ 147 ፕሮጀክቶች ላይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የገንዘብና እስራት  እርምጃ ተወስዷል፡፡

## የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋድ

በአስራ አንድ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ ክትትልና ቁጥጥር ለማከናወን ታቅዶ በ27 ከተሞች ተከናውኗል፡፡ ክትትልና ቁጥጥር በተደረገባቸው ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አስወጋጅ ማህበራት የግብአት አለመሟላት፣ የቋሚና ጊዜያዊ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አለመኖር፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ተቀናጅቶ አለመስራት፣ የአመራሩ ትኩረት ማነስና የመሳሰሉት ችግሮች እያጋጠሙ ሲሆን እነዚህን ችግሮች ቀርፎ የከተሞችን ጽዳትና ውበት የማስጠበቅ ስራ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

## ግንዛቤ ፈጠራ

በስትራቴጅዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የአሰራር ሥርዓቶች ዙሪያ ለ5 ሚሊዮን (ሴት 2 ሚሊዮን) ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ በኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያዎች አማካኝነት ለ5,073,748 (ሴት- 2,986,877) ሰዎች ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን አፈጻጸሙ 101%

ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 3,166,925 (ሴት- 1,027,558) ወጣቶች ናቸው፡፡ የተፈጠረው ግንዛቤ ፈጠራ ጥሩ ቢሆንም በተፈጠረው ግንዛቤ ፈጠራ የመጣው ለውጥ የሪፖርቱ አካል ሆኖ መቅረብ ቢችል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና መልሶ መጠቀም፣በአረንጓዴ ልማትና ተዛማጅ ጉዳዮች በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር የተሞክሮ ሰነድ መቀመር የተቻለ ቢሆንም በተቀመረው ተሞክሮ መሠረት የተሰራ ስራ የለም፡፡

### በአካባቢና ብዝሃ ሕይወት ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ

መጤ፣ ተስፋፊና ወራሪ የአረም ዝርያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በዓይነትና በመጠን እየጨመሩ የሚገኙ ሲሆን በሥነ ምህዳር ላይ መዛባትን እያስከተሉ ከመሆናቸውም በላይ በምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ ይገኛል፡፡ በህብረተሰብ ተሳትፎ 1,438.27 ሄክታር እና በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ በትራክተር ማሽን በመታገዝ 140 ሄክታር በድምሩ 1,578.27 ሄክታር የእምቦጭ አረም ተወግዷል፡፡ አፈጻጸሙ 64.9% ሲሆን በዘመቻ የተሳተፈው የሰው ሀይል ብዛት 116,446 (ሴ 26,806) ነው፡፡ በተመሳሳይ ቅንጨ፣ አቀንጭራ፣ የወፍ ቆሎ እና የመሳሰሉ 60,000 ሄክታር መጤ ወራሪ ዝርያዎችን 562,475 (ሴት 200,000) ሰዎች በዘመቻ በማሳተፍ ለማስወገድ ታቅዶ 182,031 ሄክታር መጤና ወራሪ አረም ዝርያዎችን በ793,191 (ሴት- 420,055) ሰዎች ተሳትፎ ለማስወገድ ተችሏል፡፡ ክንውኑ ከ100% በላይ ሲሆን በዘመቻ ከተሳተፉት መካከል 524,178 (ሴት 184,398) ወጣቶች ናቸው፡፡

### የደን ልማትና ሽፋን

የደን ሀብት ልማት ትልቅ የኢኮኖሚ አቅም እንዲሆን እና ከደን ጭፍጨፋና ውድመት ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ መጠን በከባቢ አየር ላይ መጨመርን ለመቀነስ የደን ሃብትን በስፋት ማልማትና ያሉትን መጠበቅ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በመንግስት ደኖች ውስጥ 5,250 ሄክታር የተከላ ቦታ ለመለየትና 20,800 የማበልጸጊያ ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ 4262 (81%) ሄክታር መሬት መለየትና 100,679 (ከ100% በላይ) ችግኝ መትከል ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በደን ልማት ላይ በተሰማሩ ፕሮጀክቶች አማካኝነት 250 ሄክታር የተከላ ቦታ ለማዘጋጀትና 625,000 የችግኝ ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ 19,075 ሄክታር የተከላ ቦታ ማዘጋጀትና 25,793,268 ችግኞችን ተከላ ማካሄድ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ በላይ ነው፡፡

በበጀት አመቱ 800,000 ሄክታር ለሚሆኑ የተፈጥሮ ደኖች የተጠናከረ ጥበቃ በማካሄድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ለማበርከት ታቅዶ ለ992,856 ሄክታር የተፈጥሮ ደኖች ጥበቃ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ

124% ነው፡፡ በኃይማኖት ተቋማት እና አምልኮ ስፍራዎች የሚገኙ ደኖች እንዲጠበቁ እና አያያዛቸው እንዲሻሻል እየተሰራ ሲሆን በእነዚህ ሥፍራዎች ለሚገኙ 3,474 ሄክታር ደኖች እንዲጠበቁ ለማድረግ ታቅዶ 4,206 ሄክታር ደኖች ጥበቃ ተደርጓል፡፡ 52,000 ሄክታር የተራቆተ ተራራማ መሬት ከንክኪ ነጻ ሆኖ እንዲያገግም የመከለልና የማልማት ስራ ለመስራት ታቅዶ 91,687 ሄክታር የተራቆተ መሬት ከንክኪ ነጻ ሆኖ እንዲለማ ማድረግ ተችሏል፡፡ አሳታፊ የደን ልማት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ደን በዘላቂነት እንጠብቅ፣ እንክብካቤ እንዲደረግለትና ጥቅም ላይ እንዲውል እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት 173,434 (102%) ሄክታር መሬት በአሳታፊ የደን አያያዝና አስተዳደር ስርዓት እንዲጠበቅ ተደርጓል፡፡



የቃብትያ ሁመራ ብሔራዊ ፓርክ የማኅበረሰብ ጥብቅ ደን-ወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን

## ህጋዊ የደን ዝውውር እንዲኖር ማድረግ

በበጀት አመቱ የደን ምርት ውጤቶች የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ለሚጠይቁ 500 ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ 165 የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል፡፡ ለሰባት ነጋዴዎች የደን ምርት ውጤቶች የማምረት ፈቃድ በአዲስ ለመስጠት ታቅዶ ለ78 ሰዎች የማምረት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለ37 ነጋዴዎች የደን ምርት ውጤቶች የማምረት ፈቃድ እድሳት ለመስጠት ታቅዶ የ112 ሰዎችን ፈቃድ ማደስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ 249% ነው፡፡ 28 ባለሀብቶችና 29 የተደራጁ ወጣቶች በድምሩ 57 ድርጅቶችና የተደራጁ ወጣቶች ዕጣንና ሙጫ የማምረት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም 3,145 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 2,862 እና ጥቁር 283) ተመርቶ ወደ ገበያ እንዲቀርብ ለማድረግ ታቅዶ 5,677 ኩንታል ዕጣን (ነጭ 4,012 ኩንታል እና ጥቁር 1,665 ኩንታል) ተመርቶ ለገበያ ቀርቧል፡፡ 450 ኩንታል ሙጫ ለማምረት በዕቅድ ተይዞ 1,912 ኩንታል ሙጫ ተመርቶ በህጋዊ መንገድ ተንቀሳቅሷል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ተመርተው የተገኙ ምርቶችን ዕጣን 61 ኩንታል (ነጭ 56 እና ጥቁር 5)፣ ሙጫ 56 ኩንታል፣ አጠና (ወራጅና ቋሚ) 4,601 ሜትር ኩብ፣ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ) 212 ሜትር ኩብ፣ ግንዲላ 149 ሜትር ኩብ፣ ፍልጥ 155 ሜትር ኩብ፣ ማገዶ 435 ሜትር ኩብ፣ ከሰል 6,222 ሜትር ኩብ ውርስ ተደርጓል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ተከማችተው ከተገኙ የደን ምርቶች ውስጥ 3 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 4.5 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ ብር 250 ሚሊዮን ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 214 ሚሊዮን ብር ገቢ እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙ 86% ነው፡፡

## የስራ ዕድል ፈጠራ

በዘርፉ ቋሚ የስራ ዕድል ለ20,000 (ሴት- 7,500) እንዲሁም ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለ180,000 (ሴት- 30,000) በድምሩ ለ200,000 (ሴት- 37,500) ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በቋሚ ለ24,330 (ሴት 4,652) እና በጊዜያዊ ለ200,630 (ሴት 54,628) በድምሩ ለ224,960 (ሴት- 59,280) (112%) ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ በቋሚ 13,089 እና በጊዜያዊ 155,250 በድምር 168,339 (ሴት- 73,389) ወጣቶች ናቸው፡፡የስራ ዕድል የተፈጠረባቸው የስራ መስኮችም በደን ልማት፣ በከሰል ማምረት፣ በዕጣንና ሙጫ ማምረትና መሸጥ፣ በጫኝና አውራጅ እና ከቦታ ቦታ ማጓጓዝ ናቸው፡፡

## የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎችን ማልማት

በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች የሚገኘው 5,689 ሄክታር የተጎዳ መሬት እንዲያገግም ለማድረግ ታቅዶ በቦረና፣ ጎደቤ፣ ማህበረ ስላሴ፣ መንዝ፣ ባህርዳር ሚሊኒየም፣ አቡነ ዮሴፍ እና ጮቄ ጥብቅ ስፍራዎች 6,487 (114%) ሄክታር መሬት ተከልሎ እንዲያገግም ተደርጓል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ቁጥር 50,000 (ሴ- 25,000) ለማድረስ ታቅዶ በመንዝ፣ ጎደቤና ባህርዳር ሚሊኒየም ፓርክ በድምሩ 42,345 (ሴ- 7,475) የአገር ውስጥና የውጭ ጎብኝዎች ተሳትፈዋል፡፡ ትሮፒካል ዋይልድ ላይፍ የተሰኘ የዱር እንስሳት ላኪ ድርጅት ወደ ውጭ አገር ለሽያጭ ካቀረባቸዉ 5 ጉሬዛዎች የታክስ ክፍያ 85 በመቶ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ 161,000 ብር ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በጥብቅ ስፍራዎች ከኢኮ ቱሪዝም፣ ከፊልምና ሌሎች አገልግሎቶች 1.1 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 0.852 (77.45%) ሚሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

# መንገድ ልማት

## የመንገድና ድልድይ ጥናትና ዲዛይን ስራወች

በበጀት አመቱ ጠቅላላ ርዝመታቸው 806.21 ኪሎ ሜትር የሆኑ 17 ፕሮጀክቶች የመንገድ ጥናትና ዲዛይን ስራ 95.94% ለመስራት ታቅዶ በአማካኝ 90.63% (የዕቅዱን 94.5%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 100% የተጠናቀቁ 14 መንገዶች ሲሆኑ እነሱም (ሮቢት አዋስ ቆላይት፤ደሴዙሪያ ዳባ መግለቢያ ሞቴ አያታ ጥድገበያ ተንታ መቅ/አምባ ወተት ዳውንት፤ክርክሪት አለንጌ ከርቢያ፤ግንድ መጣያ ዝራርጌ፤ዳጊ አዲስአለም ገርጨጭ፤ግንደ ወይን ጠጅ ባህር፤አሮጌ ምንጃር ሰቃዋጮ አክሪሚት ግንደበል፤አዘና ቆንዘና ቻ/ጊዮርጊስ፤ጎመር - ዳኪ-ጃምቢ፤ማጀቴ ወዠድ፤ጋማውበር ጃዊ፤እብናት መቀጠዋ፤አዲስ አለም ዛጋንሳ ዛናት ሞትኮላ ሌባመጣያ ጃራገዶ፤ሽበል በረንታ ወግዲ)፤2ቱ (ገርቢ መታሆራ፤ደብረወይላመገንጠያዲውና ሰራምሪ መሪ) ከ15% እስከ 35% አፈጻጸም የደረሱ ሲሆን ዋዘቦ ደርባ በምቢያወንዝ ማይጋሳ በወቅቱ በነበረው የጸጥታ ስጋት ምክንያት ስራው መሰራት የማይችል መሆኑን ወረዳው ባሳወቀን መሰረት ወደ ቀጣዩ በጀት አመት ተሸጋግሯል፡፡

ከድልድይ ጥናትና ዲዛይን አኳያ 17 ተንጠልጣይ የዕግረኛ ድልድዮችን 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረዳ ገጠር መንገድ ዘርፍ በአምስት ዞን 107.45 ኪሎ ሜትር መንገድ እና ከ6 ሜትር እስከ 24 ሜትር ስፋት ያላቸው 47 የኮንክሪት ድልድዮች የጥናትና ዲዛይን ስራ ተሰርቷል፡፡






**የዲዛይን ርክክብ ስራ**

***መንገድ ግንባታ***

**በገጠር *መንገድ* ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በ**43 **ፕሮጀክቶች** 210 **ኪሎ ሜትር፤በመንግስት የልማት ድርጅቶች በ** 2 **ፕሮጀክቶች** 12.35 **ኪሎ ሜትር እና በወረዳ ምክር ቤት በጀት እና በህብረተሰቡ ተሳትፎ በ**48 **ወረዳዎች** 66 **ፕሮጀክቶች** 360 **ኪሎ ሜትር በጠቅላላው በ**111 **ፕሮጀክቶች** 582.35 **ኪሎ ሜትር *መንገድ ለመገንባት ታቅዶ* በዌትድ አቬሬጅ** 566.24 **ኪሎ ሜትር** (97.2%) ***መንገድ* መገንባት ተችሏል፡፡**




መንገድ ግንባታ -ደቡብ ጎንደር (ጉና በጌምድር)

መንገድ ጥገና

በወረዳ ምክር ቤትና በህብረተሰቡ ተሳትፎ መንገድ ጥገና በ121 ፕሮጀክቶች 7000 ኪሎ ሜትር፤በክልሉ በጀት ድንገተኛ ጥገና በ48 ፕሮጀክቶች 189 ኪሎ ሜትር፤በፌደራል መንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ በ 200 ፕሮጀክቶች 4,309 ኪሎ ሜትር በጠቅላላው በ369 ፕሮጀክቶች 11,498 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 12,817.87 ኪሎ ሜትር ከዕቅድ በላይ 111.5% ማሳካት ተችሏል፡፡






መንገድ ጥገና -ደዋ ጨፋ ወረዳ

## ድልድይ ግንባታ

በበጀት አመቱ 23 የኮንክሪት ድልድዮችን በበጀት ዓመቱ በአማካኝ 55.7% ለማድረስ ታቅዶ 56.5% (ከዕቅድ በላይ) መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 100% ተጠናቀው ለትራፊክ አገልግሎት ክፍት የተደረጉ 19 ድልድዮች ሲሆኑ እነሱም (ቢኮሎ አባይ፤ አንዳሳ፤ ማይሰፍሮ፤ ማላ፤ ሰንበቴ ቁጥር አንድ፤ሰንበቴ ቁጥር ሁለት፤ሙገጭት፤ባምብላ፤ዘቢት፤ዋሸራ፤ሲዳ ቁጥር ሁለት፤መልካድሞ፤ጂያ፤ኩራር፤ተፌ፤አሻር፤ቸክሲ፤ለምለም ተራራ እና አይራራ)፤ከ85-93% የደረሱ 2 (ደባሪ እና ሰወሰዋ)፤ዥጣ 20.87%፤መሎ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያለው መሆኑን ከተላከው ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡




ድልድይ ግንባታ-ሰሜን ወሎ (በራያቆቦ)

### ከተንጠልጣይ የዕግረኛ ድልድይ ግንባታ

ከተንጠልጣይ የዕግረኛ ድልድዮች አኳያ 21 ድልድዮችን በአማካይ 96.67% ለማድረስ ታቅዶ 96.2% (የዕቅዱን 99.5%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 100% ተጠናቀው ለትራፊክ አገልግሎት ክፍት የተደረጉ 19 ድልድዮች ሲሆኑ እነሱም (ክንድአውጥ፣ዘንዘን፣ማር ውሃ፣ሚስኩ፣ኪትራ፣ፌንደንን፣ጦጢት፣እንስያ፣በለገዝ፣አጣዬ፣ሸህእርዳ፣ሙገጭት፣ጣና በለስ፣ቶራ፣ባሪያ የሞተበት፣ጀማ፣ዱራ፣ተሚ እና ማላ)፣95% የደረሱ 2 (ጋዞ እና ፈሰስ) ናቸው፡፡

### የመንገድ ርክክብ ስራ

ከዚህ በፊት ተገንብተዉ ርክክብ ያልተደረገባቸዉ በሰባት ዞኖች ዉስጥ ከሚገኙት 453.24 ኪሎ ሜትር ውስጥ በበጀት ዓመቱ 241 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመረከብ ታቅዶ 448.17 ኪሎ ሜትር ከዕቅድ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

## የህብረተሰብ ተሳትፎና ሃብት ማሰባሰብ

የክልሉ መንግስት በሁሉን አቀፍ የወረዳ ገጠር መንገድ ዘርፍ ለመንገድ ግንባታና ጥገና ሃብት በወረዳና ህብረተሰብ ተሳትፎ በሚገኝ ገንዘብ እንዲሰራ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ቢሮው በ2015 በጀት ዓመት ብር 549,100,000 ለማሰባሰብ አቅዶ 1,107,815,342 በመሰብሰብ ከዕቅድ በላይ የተሰበሰበ ሲሆን ከዚህም ውሰጥ 764,070,473 (68.97%) የህብረተሰቡ ድርሻ ሲሆን በዚህም ሃብት 410.41 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ፣2243.12 ኪሎ ሜትር በማሽን ጥገና፣62 የተለያየ መጠንና አይነት ያላቸው ስትራክቸሮች ግንባታና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ 7 ድልድዮች እየተገነቡ ይገኛል በዚህም የክልሉን የመንገድ ተደራሽነትና ሽፋን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ በየጊዜው ከሚላከው ሪፖርትና ከሚደረገው የመስክ ድጋፍና ክትትል ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ከስራ እድል ፈጠራና ከወጣቶች ተጠቃሚነት አንጻር

የስራዕድል ፈጠራና የወጣቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ 5,280 ታቅዶ 34,803 ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል ከዕቅድ በላይ የተፈጸመ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ቋሚ 1157 (ወንድ 924 ሴት 233 ) የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

## የፌደራል አስፋልት መንገዶች የክትትልና ድጋፍ

በክልላችን የሚገነቡ የአስፋልት የመንገድ ፕሮጀክቶች ብዛት 59 ሲሆን ዓመታዊ የግንባታ ዕቅዱ 532 ኪሎ ሜትር ታቅዶ 273 ኪሎ ሜትር (የዕቅዱን 51.3%) በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ ጠጠር 1051.5 ኪሎ ሜትር አስፋልት 2790.53 ኪሎ ሜትር በድምሩ 3842.03 ኪሎ ሜትር መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 3,664.5 ኪሎ ሜትር (95.1%) መፈጸም የተቻለ ሲሆን በተደረገ የክትትልና ድጋፍ ስራ የወሰን ማስከበር ችግር ከነበረበቸው 50 ፕሮጀክቶች ውስጥ 47 እንዲፈታ የተደረገ ቢሆንም ከፍተኛ ትኩረትና ክትትል የሚሻው ጉዳይ መሆኑን ያመላክታል፡፡ከዚህ በተጨማሪም በጸጥታ ችግር ምክንያት ቁመው ከነበሩ 30 ፕሮጀክቶች ውስጥ 23 ወደ ስራ ሲገቡ ቀሪው 7 ባሉበት የቆሙ መሆኑን በየጊዜው ከሚላከው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመንገድ ፈንድ የበጀት ድጋፍ የመንገድ ጥገና ዕቅድ አፈጻጸም በመንገድ ጥገና በአራቱም ክላስተሮች ማለትም በጎጃም፣ጎንደር፣ወሎ፣ደብረ ብርሃን ጥገና ጽ/ቤቶች በመደበኛና ወቅታዊ ጥገና በአመቱ 3,915.62 ኪሎ ሜትር ታቅዶ 4305.47 ኪሎ ሜትር (ከዕቅድ በላይ 109.96%) በሌላ በኩል በክልል መንግስት በጀት ድንገተኛ ጥገና በበጀት ዓመቱ 189 ኪሎ ሜትር መንገድ

ለመጠገን ታቅዶ 188 ኪሎ ሜትር (99.5%) እንዲሁም 56 የተለያየ አይነትና መጠን ያላቸውን ስትራክቸሮች መጠገን ተችሏል።

### የክላስተሮች የጥገና አፈፃፀም

| ተ.ቁ | የክላስተር ስም | የዓመቱ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ በኪሎ ሜትር | ክንውን በኪሎ ሜትር | አፈጻጸም በፐርሰንት |
| 1 | ጎጃም ጥገና ጽ/ቤት | 1,099.82 | 1,181.72 | 107.45% |
| 2 | ጎንደር ጥገና ጽ/ቤት | 933.86 | 1017.96 | 109.01% |
| 3 | ወሎ ጥገና ጽ/ቤት | 1,336.70 | 1,487.55 | 111.29% |
| 4 | ሰ/ሸዋ ጥገና ጽ/ቤት | 545.24 | 618.24 | 113.39% |
| | ድምር | 3915.62 (በብር 377,579,977.26) | 4305.47 | 109.96 % |

## መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት

### የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች

በበጀት አመቱ 22,237 ሄክታር ማልማት የሚችሉና በ2014 በጀት አመት የጥናትና ዲዛይን ሥራቸው በአማካሪዎች ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ የ57 መካከለኛ ነባር መስኖ ፕሮጀክቶችን 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 36 (63%) ፕሮጀክቶች በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ከታቀደው ዕቅድ አኳያ 89.3% መፈጸም ተችሏል።

በወረዳና በዞን ደረጃ በጥናትና ዲዛይን ዘርፍ አዲስ 7,409 ሄክታር የሚያለሙ እና 20,656 የሚሆነውን የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 167 አዲስ የአነስተኛ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን በማጠናቀቅ እና በማጽደቅ በበጀት አመቱ ወደ ግንባታ እንዲገቡ የታቀደ ሲሆን 9,705.32 ሄክታር መሬት በማልማት 29,450 ማህበረብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ 185 (110.8%) ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ የተሰራ ሲሆን የፕሮጀክቶች ቁጥር ከዕቅድ በላይ የሆነው ወረዳዎች ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በዕቅድ ይዘው ስለተገበሩ ነው።

በበጀት 26,949 ሄክታር የሆነና 304,369 ህዝብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 76 አዲስ ፕሮጀክቶችን በአማካሪ ድርጅቶች በኩል እንዲከናወን በማድረግ የሙሉ ጥናታቸውን 50% ለማድረስ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን ፕሮጀክቶን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

ገምግሞ በማጣራት 38 ፕሮጀክቶችን ለልህቀት ዲዛይን፣ 15 ፕሮጀክቶችን ለላሊበላ ዲዛይን እና 23 ፕሮጀክቶችን ደግሞ ለግል አማካሪዎች ለመስጠት በቢሮው ማኔጅመንት ተወስኖ ሁለቱ አማካሪ ድርጅቶች የቦታ መረጣና የማረጋገጥ ስራ በመስራት ወደ ስራ እንደገቡ ቢደረግም የተመዘገበ ውጤት አለመኖሩ በቀጣይ በጀት ዓመት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

## የግንባታና ክትትል

በዘላቂ ልማት ግብ ፕሮጀክት በጀት፡ 7,412.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 23 የነባር መካከለኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከደረሱበት 61.63 በመቶ አማካኝ አፈፃፀም በመነሳት 92.14 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 69.92% ማድረስ የተቻ ሲሆን አፈጻጸሙ 47.5% ብቻ ነው፡፡ ጉማራ እና አበያ ማስፋፊያ፣ ሚሌ ኮትቻ መስኖ ልማት፣ ግልገል አባይ መስኖ ልማት፣ ጉማራ መስኖ ልማት፣ አበያ ማስፋፊያ መስኖ ልማት፣ የሰርፀ ወልድ ፕሮጀክት የዲዛይን ማሻሻያ፣ የበሬሳ መስኖ ልማት እና የአዋሽ ተፋሰስ 19 የጉድጓድ ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ያልገቡ ሲሆን ለአፈፃፀሙ ማነስ አበይት ምክንያቶች መካከል የግንባታ ግብዓት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መናር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለገዙት ሲሚንቶ ደረሰኝ ማግኘት አለመቻል፤ የተቋራጭ አፈፃፀም ደካማ መሆን እና ተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ የማህበራዊ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ 4,592.87 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 86 ነባር አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከ50.52% አፈፃፀም በመነሳት 98.3% ለማድረስ ታቅዶ 35.89% በመፈጸም 71.71% ማድረስ ተችሏል፡፡ 1,500 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 30 አዲስ ፕሮጀክቶች ግንባታ በዚህ ዓመት በመጀመር አማካኝ አፈፃፀማቸውን 25.71 በመቶ ማድረስ የበጀት ዓመቱ እቅድ ሲሆን በአራተኛው ሩብ ዓመት 50.1 በመቶ በመፈፀም አጠቃላይ አፈፃፀሙን 50.1 ማድረስ ተችሏል፡፡ 1,700 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 50 አዲስ አነስተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በዚህ ዓመት በመጀመር አማካኝ አፈፃፀሙን 24.13 በመቶ ማድረስ ታቅዶ 44.49 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ 9,595.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 36 አዲስ መለስተኛ መስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች በዚህ ዓመት በመጀመር አማካኝ አፈፃፀማቸውን 20.13% ለማድረስ ታቅዶ 3,720.85 ሄክታር የሚያለሙ የ18 ፕሮጀክቶች የግንባታ ውል ድርድር ስምምነት ሂደት ጊዜ በመፍጀቱ እና 5874.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 18 ፕሮጀክቶች በበጀት እጥረት ምክንያት ወደ ግንባታ መግባት ባለመቻላቸው አፈፃፀማቸው 10% ብቻ ነው፡፡



የመስኖ ፕሮጀክት የመስክ ክትትልና ድጋፍ -ምስራቅ ጎጃም

## በግብርና አድገት ፕሮግራም በጀት ድጋፍ የተገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች

በተለያየ በጀት ዓመት የተጀመሩ 2,790.5 ሄክታር የሚያለሙ 16 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከ67.72% አማካኝ አፈጻጸም በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 19.94 በመቶ በመፈጸም አጠቃላይ አፈፃፀሙን 87.65% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 1,630 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 8 መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን (ዝልሂ፣ ሽገዝ፣ ገራይ3፣ ውምብሪት፣ ላህ2፣ አምባገነን፣ በርበራ 2ና3 እና ፈጣም ታጀት) ማጠናቀቅ ተችሏል። በዚህ ዓመት የተጠናቀቁ እና በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች በድምሩ 880 ሄክታር መሬት በመልማት ላይ ይገኛሉ። ሌሎች ቀሪ ዝንግኒ መልሃ-2፣ የሃሙስ ወንዝ፣ አባይ-3፣ ብልቅ፣ አይነቁራ እና የዳንዲኒ እና በርበራ-1 የመስኖ ልማ ፕሮጀክች በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈለገው መንገድ እየሄዱ ስላልሆነ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት የሚጠበቅ ይሆናል።



የመስኖ ፕሮጀክት የምርቃ ስነስርዓት( በግብርናእድገትፕሮግራም)-ዳንግላ ወረዳ

## በተሳትፎአዊ አነስተኛ (ኢፋድ) በጀት የተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በተሳትፎአዊ አነስተኛ (ኢፋድ) መስኖ ልማት በጀት ድጋፍ በተለያየ በጀት ዓመት የተጀመሩ 1,703 ሄክታር የሚያለሙ 7 ነባር የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከ72% አማካይ አፈጻጸም በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 81.33% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 1,336 ሄክታር መሬት ማልማት የሚችሉ 4 ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ በሆጣ 242.5 ሄክታር፣ ቦርከና ተረፎ 200 ሄክታር፣ ጤና 400 ሄክታር፣ ጨረቲ-2 172 ሄክታር፣ ወርቄ 215 ሄክታር በድምር 1,229.5 ሄክታር መሬት እየለማ ይገኛል፡፡

## በሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮግራም የበጀት ድጋፍ የተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በበጀት አመቱ 20 ሄክታር ማልማት የሚችል የደባሪ ውሃ ማቆሪያ የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ በ2014 ከደረሰበት 87.2 በመቶ በመነሳት ለማጠናቀቅ ታቅዶ 11.77 በመቶ ብቻ በመፈፀም አጠቃላይ አፈፃፀሙን 98.97 በመቶ ላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ ከፌደራል መንግስት በሰቆጣ ቃል ከዳን ፕሮግራም አማካኝነት በተለይ በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎችን ትኩረት በማድረግ እንዲሰራ በተገኘ 10 ሚሊየን ብር በድምሩ 5 ፕሮጀክቶችን በበጀት በመደገፍ አማካኝ አፈፃፀማቸውን 71.8% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 159 ሄክታር የሚያለሙ 5 ፕሮጀክት ተጠናቀዋል፡፡

## ባለ አነስተኛ ይዞታ (ሺዲፕ) በጀት የተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በተለያዩ ዞን እና ወረዳዎች 1,620.21 ሄክታር የሚያለሙ 33 መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የሚገኙ ሲሆን አማካኝ አፈፃፀማቸው 75.55% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 624 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 13 ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## በተለያዩ የፕሮግራም በጀት ምንጮች የተገቡ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በተለያዩ የበጀት ምንጭ የሚገነቡ የማልማት አቅማቸው 2,033.5 ሄክታር የሆኑ 54 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ታቅዶ 86.21 በመቶ ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1318.5 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 37 ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቋል፡፡

## በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት መስኖ ልማት

በጦርንት የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት በተገኘ 51 ሚሊየን ብር ገደማ በጦርነቱ ከፍተኛ ውድመት በደረሰበት በሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ እና ቆቦ ከተማ የሚገኙ የከርሰ ምድር መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ለማስገባት በተያዘው እቅድ መሰረት የማልማት አቅማቸው 440.8 ሄክታር የሆኑ 10 የግፊት እና ከፊት ግፊት መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ከቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር እና በመለየት እንዲሰሩ በእቅድ የተያዙ ቢሆንም የተመደበው በጀት ሁሉንም ማሰራት የማይችል በመሆኑ ወደ ስራ አልተገባም፡፡

## በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የተገነቡ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች

በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ በሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም በታቀፉ ወረዳዎች በዚህ ዓመት በግንባታ እቅድ ከተያዙ 30 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች መካከል 2 ፕሮጀክቶች ባለፈው በጀት ዓመት ወደ ግንባታ የገቡ እና 7 ፕሮጀክቶች በዚህ በጀት ዓመት ወደ ግንባታ እንዲገቡ የተደረጉ ሲሆኑ ቀሪ ፕሮጀክቶች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ስራ መግባት አልቻሉም፡፡

## ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታና ክትትል

በክልላችን በፌደራል መንግስት በጀት ግንባታቸው የሚከናወኑ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች (በመገጭ ግድብ ሊለማ የሚችለውን 10,980 ሄክታር) ሳይጨምር በአጠቃላይ 22,310 ሄክታር መሬት ሊያለሙ የሚችሉ 4 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ለአሰራር እንዲመች በ7 ውል ተከፍለዋል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ በአጠቃላይ 16.9 ቢሊዮን ብር በጀት እንደሚያስፈልግ ይገመታል፡፡ አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ረዥም ጊዜ በመውሰዳቸው የክልሉ መንግስት እና ህዝብ ከፕሮጀክቶች ማግኘት ያለበትን ጥቅም ብቻ

ማሳጣት ሳይሆን ህዝብ በመንገስት ላይ እምነት እንዳይኖረው በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ከመሆናቸውም በላይ የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ጭምር ያሳጡ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የመስኖ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሁኔታ መገምገም፣ ችግሮችን መለየት እና የመፍትሄ አቅጣጫወችን ለማስቀመጥ ከሚኒስተር መስሪያቤቱ የበላይ ሀላፊዎች፣ ከክልሉ መንግስት የበላይ ሃላፊዎች፣ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተደጋጋሚ የመስክ ምልከታ (መገጭ እና ርብ ግድቦች፣ መገጭ ሰራባ መስኖ፣ ላይኛው እና ታችኛው ርብ፣ አጅማ ጫጫ፣ ቆጋ እና ጣና በለስ ፕሮጀክቶች) እና የባለድርሻ አካላት ውይይቶችን በማድረግ አፈፃፀማቸውን በመገምገም ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ የእነዚህ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በተመለከተ **መገጭ ግድብ** የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በመነሳት 5.583% በማሳደግ ወደ 69.283% ማሳደግ የታቀደ ሲሆን 1.386% ብቻ በመጨመር 65.086% የደረሰ ሲሆን አፈፃፀሙ 24.8% ብቻ ነው፡፡ **ላይኛው ርብ መስኖ ፕሮጀክት** ፕሮጀክቱ ከነበረበት 34.39% በመነሳት 68.17% ለማድረስ ታቅዶ 8.72% ብቻ በመፈጸም 43.11% ማድረስ ተችሏል፡፡ **ታችኛው ርብ መስኖ ፕሮጀክት** 68.24% አፈፃፀም ደረጃ ላይ ደርሶ ውሉ ተቋርጦ በ2013 ዓ.ም ለአባይ ኮንስትራክሽን ተሰጥቶ እየተሰራ ነው፡፡ **አጅማ ጫጫ መስኖ ፕሮጀክት** በሰሜን ሸዋ ዞን በአንጎልላ ጠራ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ 7,000 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል ፕሮጀክት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በ3 ሎቶች የተከፋፈለ ሲሆን ሶስቱንም ሎቶች የአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ውል የወሰደ ሲሆን አፈፃፀሙ ከሌሎች ፕሮጀክቶች አንፃር ሲታይ የተሻለ ቢሆንም ፕሮጀክቱ ለግንባታ ካለው ምቹ ሁኔታ አንፃር እና ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ የተጓተተ ፕሮጀክት ነው፡፡ **ጣና በለስ መስኖ ልማት ፕሮጀክት** 4,790 ሄክታር ማልማት የሚያስችለውን ስራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከ4,790 ሄክታር ውስጥ በዚህ በጀት ዓመት 1,200 ሄክታር ማልማት የሚችል መሬት ስራዎች ማጠናቀቅ በመቻሉ ለልማት ዝግጁ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በቀጣይ በጀት ዓመት ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡና በምርትና ምርታማነት ጭማሪ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## የስራ ዕድል ፈጠራ

በዚህ ዘርፍ 8,538 (ሴ-1193) ለሚሆኑ ስራ አጥ ወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር 6,356.07 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል 1,014 ሞተር ፓምፖችን መስጠት ተችሏል፡፡

# ህዳሴ ግድብ

### የሶሻል ሚዲያ/ፌስ ቡክን/ ከመጠቀም አኳያ

ሕዝባዊ ተሳትፎውን በተመለከተ የግድቡን የስራ ደረጃና ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ መረጃዎችን ከተለያዩ የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች በሕትመትና በኤሌልክትሮኒክስ የተላለፉትን ዘገባዎች በጽ/ቤቱ የፌስ ቡክ አድራሻ በመልቀቅ ለሕዝብ መረጃ የማቅረብና የፌስ ቡክ ተከታዮችን ቁጥር የማሳደግ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዚህ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት ዓመታዊ በተለያዩ ሚዲያዎች በተለይም ከፋና፣ ከዋልታ እና ከኢቲቪ ብሮድካስት ኮርፐሬሽን እና ከሌሎች ሚዲያዎች የተገኙ እንዲሁም በጽ/ቤቱ የተዘጋጁ 59 የጽሑፍና የምስል፣ 57 የተንቀሳቃሽ ምስል(ቪዲዮ)፣ 23 የጽሑፍ ብቻ፣ 79 በምስል መረጃዎች እንዲሁም 51 አጫጭር መልዕክቶች ተዘጋጅተው በጽ/ቤቱ ፌስ ቡክ ተለቅቋል፡፡ ከፌደራል ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፌስ ቡክ ገጽ ላይ የተገኙ ዜናዎችም በእኛ ፌስ ቡክ አማካይነት መረጃዎች እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

### መደበኛ ሚዲያዎችን ከመጠቀም አኳያ

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በወቅታዊ የህዳሴ ግድብ ዙሪያ ስለአለው እንቅስቃሴ በክልላችን የሚገኙ ነዋሪዎችን በማነጋገር የተለያዩ ዘገባዎችን በሁሉም ሚዲየሞች ዘግቦ ከማስተላለፉ በላይ ለቀጣይ በምን መልኩ ድጋፍ ማድረግ እንዳሰቡ አስተያየቶቻቸውን በመሰብሰብ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ አደርጓል፡፡ በዚህ ዙሪያ ከጽ/ቤቱ ጋር በመተባበር እና ትኩረት በመስጠት በተለያዩ ጊዜያት በሁሉም ሚዲየሞች እና በተለያዩ ቋንቋዎች(በክልሉ በሚገኙ በተለያዩ ኤፍ ኤሞች፣ በቴሌቪዥን ጣቢያ፣ በጋዜጣ) ዜና እንዲሁም ዜና ትንታኔ በማዘጋጀት እና ሰፊ የአየር ሽፋን በመስጠት ለሕዝቡ መረጃ በወቅቱ እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጽዖ አብርክቷል፡፡

### የሚዲያና የሕዝብ ንቅናቂ(የሞብላይዜሽን)ተሳትፎን በተመለከተ

በወቅታዊ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሥራ እንቅስቃሴና የክልላችን ሕዝብ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ እያደረገ ስላለው ሁለንተናዊ አስተዋጾኦ ማለትም በጉልበት፣ በገንዘብና በዕውቀት እያበረከተ ስላለው ጉዳይ በተለያዩ መልኮች መረጃ በመስጠት የሕዝብ ንቅናቂ(የሞብላይዜሽን) እና ተሳትፎ ሥራ ተሥርቷል፡፡ በዚህም መሠረት በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን፣ በኢትቪ፣ በፋና ብሮድ ካስት፣ በዋልታ፣በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት፣ በፌስ ቡክ ለተለያዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በማድረግ የሕዝብ ንቅናቂ(የሞብላይዜሽን) እና ተሳትፎ ሥራ ተሠርቷል፡፡

በተለይም በክልላችን በተካሄደው የአርንጓዴ አሻር ዘመቻ ለይ በችግኝ ተከላ ወቅት፣ ይህንን ተግባር ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር በማያያዝ ግንዛቤ በመስጠት የሕዝብ ንቅናቂ የመፍጠር ተግባር ተከናውኗል፡፡

የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ የጽ/ቤት ፌስቡክ ላይክ በማድረግ ከ1,367 እና ተከታዮቻችን ደግሞ ከ1,355 በድምሩ 2,722 በላይ ተከታዮች እና የፌስቡክ ገጹን (ፔጁን) ላይክ ላደረጉ አካላት

መረጃዎችን ማድረስ በመቻሉ የሕዝብ ንቅናቄ(የሞብላይዜሽን)ሥራው የተሳለጠ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ስለ ህዳሴ ግድብ በክልላችን ስላለው እንቅስቃሴ ስለ ግንባታው አፈጻጸም፣ስለ ወቅታዊ ጉዳዮች የተለያዩ የሚዲያ ተቋማትን በመጠቀም በተቻለ አቅም ኅብረተሰቡን ለማንቀሳቀስ(ለማነቃቃት) ተሞክሯል፡፡ በዚህ ረገድም በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በአጋርነት የተሻለ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ስለሆነም በቴሌቪዥን፣ በመደበኛ ሬዲዮ፣ በFM አማካኝነት በየጊዜው በዜናዎች፣ በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አማካኝነት ስለግድቡ ሥራ የተዘገቡትን የዘገባ ሥራዎች የተመለከታቸውን/ያዳመጠውን/ ሰዎች ወይም የኅብረተሰብ ክፍል በቁጥር መግለፅ ግምታዊ ቢሆንም መረጃው የደረሰው ሕዝብ ቁጥር ከሚዲያው ተከታታይ የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በሕዝቡን ዘንድ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችል መረጃ መስጠቱ ተጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡

## የተፋሰስ ልማት ሥራዎች

በ2015 ዓ.ም በክልላችን በክረምት ወራት የተፈጥሮ ሀብት የተፋሰስ ልማት ሥራ መከናወኑ የሚታወቅ ሲሆን የተሳተፉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር እና የጉልበት አስተዋጾኦ በገንዘብ ሲተመን ከክልል ግብርና ቢሮ የደረሰን በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ላይ ተካትቶ ቀርቧል፡፡

## የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ 12ኛ ዓመት በዓል አከባበር

የታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 12ኛ ዓመት በዓል አከባበር በተመለከተ በመነሻነት ካለፉት ዓመታት በተገኘው ልምድ መሠረት ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ለአብነት የፓናል የውይይት መነሻ ጽሑፍ፣ የበራሪ ወረቀት ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡በተመሳሳይ የታላቁ ህዳሴ ግድብ አራተኛ የውሀ ሙሌትን በተመለከተ የተለያዩ ሚዲያዎች የገፅታ ግንባታ ስራ እንዲሰሩ የህዝብ ግንኙነት ስራ ተሰርቷል፡፡



የታላቁ ህዳሴ ግድብ አራተኛው የውሀ ሙሌት-ጉባ

## መረጃዎችን ወደ ሕዝብ ማድረስ

በልዩ ልዩ የሚዲያ ተቋማት ወቅታዊ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማለትም የ12ኛውን ዓመት በዓል በምናከብርበት ጊዜ ግንባታው ወደ ወሳኝ ምዕራፍ በተሸጋገረበትና 3ኛው ዙር የውኃ ሙሌት እና 2ኛው የኃይል ማመንጨት ተግባር ተከናውኖ 90 በመቶ የሚሆነው የግድቡ ሥራ ተጠናቅቆ የኤሌክትሪክት ኃይል በማመንጨት በጀመረበት ወቅት ላይ ሆነን በዓሉን የምናከብር በመሆናችን ተሳትፎውን የበለጠ አጉልቶታል፡፡

ለአገር ውስጥ ለተለያዩ ሚዲያዎች ክልሉ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ያበረከተውን አስተዋፆኦ በተመለከተ መረጃ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በክልላችን የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚገኙ ሙሁራን በአሚኮ እስቲዲዮ ውይይት ላይ ተገኝተው ሀሳባቸውን አካፍለዋል፡፡ በዚህም መሰረት በሁሉም ሚዲያዎች መረጃ ለህበረተሰቡ ለማድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

## የቦንድ ሽያጭ ሳምንትን በተመለከተ

የግድቡ ግንባታ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ እና ቀጣይ የጀመርነውን ለማጠናቀቅ ያስችለን ዘንድ ከአሁን በፊት የነበረውን የሕዝብ ጥንካሬ በማስቀጠልና የቁጠባ ልምዳችንን በማጎልበት የተገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግ ያለማንም አስገዳጅነት ሁሉም በየደረጃው በአለው አቅም ሁሉ ቦንድ እንዲገዛ ከኢትዮጵያ ልማትና ንግድ ባንኮች ጋር በስልክና በአካል በመወያየት ሥራውን በማስቀጠል ላይ ነን፡፡

## የክትትልና ድጋፍ ሥራን በተመለከተ

የክልላችን ሕዝብ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ መሳካት በልዩ ልዩ አግባቦች የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በላይ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በአብክመ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተሰማራ ቡድን በ2ኛው ሩብ ዓመት የሪፖርት አፈጻጸምና በ12ኛው ዓመት በዓል አከባበር ላይ በተለያዩ ዞኖችና ከተማ አስተዳድሮች በመገኘት ከኢትዮጵያ ልማትና ንግድ ባንኮች ጋር ሰፊ የሆነ ውይይት ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ከኢትዮጵያ ታሪክ ባህልና ቅርስ አድን በጎ አደራጎት ድርጅት ጋር የህዳሴ ጉዞ ቱር 2 በክልላችን በሚገኙ በደብረማርቆስ፣ በጎንደር፣ በደብረታቦር፣ በላሊበላ፣ በደሴ እና በኮምበልቻ ከተሞች በመገኘት ቦንድና ፒኖችን በመሸጥ፣ 8100 ኤ ብሎ መልዕክት በመላክ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ አስተዋጽዖ እንዲበረከት ተደርጓል፡፡

በክልላችን የሴቶችና ወጣቶች ሊግ በዚህ የስራ ዘመን ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስራ የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ ዕቅድ አውጥተው በመንቀሳቀስ ላይ በመሆናቸው፣ በ3ኛው ሩብ ዓመት አፈጻጸም ላይ እና የቦንድ ግዥውን ለማስተባበርና ለማፋጠን ይረዳ ዘንድ በአብክመ በታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ የሚመራ ቡድን በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ፣በወልቃይት ሰቲት ሁመራ ዞን እና በምዕራብ ጎንደር ዞን በመገኘት ከንግድና ልማት ባንኮች ፣ከዞኑና ከተማ አስተዳደሩ ኮሙኒኬሽን መምሪያ ጋር ከዞኑ ወጣቶችና ሴቶች ሊግ ጋር እና በዞን ደረጃ ከሚመለከታቸው ኃላፊና ባለሙያዎች ጋር በአካል አግኝተን በመወያየት ቦንድ የሌላቸው ከሆኑ በወቅቱ እንዲቀርብላቸው በማመቻቸትና የሪፖርት አላላክን በተመለከተም በማስረዳት ቡድኑ በሁሉም ቦታዎች ላይ በመገኘት ፕሮግራሙ እንዲሳካ እና ውጤታማ እንዲሆን የበኩሉን እንቅስቃሴ በማድረግ ተምልሷል፡፡ እንዲሁም ከፌደራል የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የመጣ ቡድን በሰኔ ወር በህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና በንግድ፣በልማት ባንክና በሴቶችና ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤቶች በመገኘት በጋራ ውይይት በማድረግ የክትትልና ድጋፍ ስራውን አጠናቆ ተመልሷል፡፡

## በሕዝብ ንቅናቄ የተሳተፉ አካላት ብዛት

በሶሻል ሚዲያ መረጃ ያገኙ በድምሩ 2,722 ሰዎች ሲሆኑ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ የተሳተፉ አርሶ አደሮች ብዛት በድግግሞሽ 10,440,221 ሰዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በድምሩ 10,442,943 ሰዎች ተሳትፈው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ለመሥራት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ስለ ህዳሴ ግድብ፣ ስለ ግንባታው አፈጻጸም፣ ስለ ወቅታዊ ጉዳዮች የተለያዩ የሚዲያ ተቋማትን በመጠቀም በኅብረተሰቡ ዘንድ ንቅናቄ ለመፍጠር ተችሏል፡፡ በተለይ በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በአጋርነት የተሻለ ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ስለሆነም በቴሌቪዥን፣ በFM እና በየጊዜው በየዜናዎች በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች አማካኝነት ስለግድቡ ሥራ የተሠራ ሲሆን በቁጥር መግለጽ ግምታዊ ቢሆንም ንቅናቄ የተፈጠረላቸው እና መረጃው የደረሰው ሕዝብ ቁጥር ከሚዲያው ተከታታይ የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል፡፡በመሆኑም ሕዝቡን ለማንቀሳቀስ የሚተገበሩ ተግባራትና መረጃ የመስጠቱ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው ይሆናል፡፡

## የጉብኝት ፕሮግራም ማመቻቸት

ግድቡን ከቦታው በአካል ሄዶ ማየት የሚፈጥረው መነሣሣትና ለቀጣይ ድጋፍና ተሳትፎ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በ2015 ዓ.ም ይህን ተግባር አጠናክሮ ለመቀጠል በዕቅድ ተይዞ በየደረጃው ኅብረተሰቡ ግድቡ የደረሰበትን ደረጃ በአካል እንዲያይ የተጠናከረ የቅስቀሳ ሥራ ለመሥራት ጥረት ተደርጓል፡፡ የጎብኝ ፍላጎት ጥያቄ እየቀረበ ቢሆንም በክረምቱና በቤንሻጉል ጉምዝ ክልል ያለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ማስተናገድ አልተቻለም፡፡

በያዝነው በጀት ዓመት በጽ/ቤት ደረጃ ጽ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የጉብኝት ፕሮግራም እንደክልል በጉብኝት የሚሳተፉ 350 የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ዕቅድ ይዘናል፡፡ ነገር ግን እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ የተካሄደ ጉብኝት ባይኖርም ህዳሴ ግድቡን መጎብኘት ከተጀመረበት ወቅት አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ በጉብኝት የተሳተፉት ጎብኝዎች ቁጥር ወንድ 51,651፣ ሴት 2,799፣ ድምር 54,450ሰዎች ታላቁን የህዳሴ ግድብ በአካል ሄደው ጉብኝት ያካሄዱ ሲሆን፣ ከጉብኝት በኂላ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አሳድሯል፡፡

## የእንቦጭ አረምን በተመለከተ

ከዓመታት በፊት ጀምሮ በጣና ሐይቅ ላይ የእንቦጭ አረም ተከስቶ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህን መጤ የእንቦጭ አረም ከጣና ሐይቅ ላይ ለማስወግድ በሚደረገው ዘመቻ ሁሉ ጣናን መታደግ እና ታላቁን የኢትጵያን ህዳሴ ግድብ መታደግ እንደሆነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንዛቤ እንዲያዝበት ከመደረጉም በተጨማሪ በአማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት መግለጫ በመስጠት ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል እንዲሁም በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡ይህ በመሆኑም ከሁሉም አካባቢ በተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች በጉልበት ሥራ እና በተለያየ ዘዴ እንቦጭን የማስወገድ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## የሀብት አሰባሰቡ ሂደት

ታላቁ የህዳሴ ግድብ በሕዝብና በመንግሥት የፋይናንስ አቅም ግንባታው ከተጀመረ 12ኛ ዓመቱን ይዟል፡፡ ግድቡ ከመሠረት ግንባታው ጀምሮ አሁን እስካለበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ሀብትን በማሰባሰብ በኩል ጥሩ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የመንግሥት ሠራተኛው እና መንግሥታዊ ያልሆኑ መስሪያቤቶች ሠራተኞች፣ የንግዱ ኅብረተሰብ፣ አርሶ አደሩ፣ ባለሀብቱ፣ ተቋማትና ድርጅቶች፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የእምነት ተቋማት ወዘተ… የመሳሰሉት የበኩላቸዉን ድጋፍ በማድረግ ተሳትፈዋል፡፡ እስከዚህ በጀት ዓመት ድረስ የድጋፍ መዋጮውን ያላቋረጡ የመንግሥት ሠራተኞች እንዳሉም ከተለያዩ አካላት የሚደርሱን ሪፖርቶች ያመላክታሉ፡፡ በዚህም መሠረት የቦንድ ግዥና ልገሳ በበጀት ዓመቱ በሁሉም የድጋፍ አይነቶች ብር 20,000,000.00 ለማሰባሰብ ዕቅድ ተይዞ በእቅዱ መሰረት የተከናወኑት፡-

- ከመንግሥት ሠራተኞች . .. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ብር 2,810,759.81
- ከባለሀብቱና ከንግዱ ኅብረተሰብ ……………………………………….ብር 5,855,384.81
- ከአርሶ አደሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ብር 785,559.81
- ከተቋማት፣ ከድርጅቶች ከመያድ እና ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች . . ብር 6,852,812.48
- በልገሳ ከተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች የተሰጠ-………………………… ብር 1,043,217.12 በድምሩ ብር17,347,734.03 ተገኝቷል፡፡

## የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ

በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ የህዳሴ ግድቡን ዓላማ መሠረት ባደረገ መልኩ በተለያዩ ቦታዎች ላይ 248,738 ሔክታር መሬት ላይ 1.429 ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል፡፡የህዝቡ ተሳትፎ የጉልበት አስተዋጽኦ በገንዘብ ሲተመን ብር 1,366,179,272.00 የሚገመት ሥራ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የ2015 ዓ.ም የሀብት አሰባሰብ

የ2015 ዓ.ም የሀብት አሰባሰብ በተመለከተ የቦንድ ግዥና ልገሳ ብር 17,347,734.03፤የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ ብር 1,366,179,272.00 ጠቅላላ ድምር ብር 1,383,527,006.03 ደርሷል፡፡ በቦንድ ግዥ እና በልገሳ የገንዘብ አስተዋፅኦው በየኅብረተሰብ ክፍሉ ሲተነተን ከመንግሥት ሠራተኞች ብር 510,429,476.05፤ከባለሀብቱና ከንግዱ ህብረተሰብ ብር 101,023,951.19፤ከአርሶ አደሩ ብር 236,020,455.08፤ከድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብር 332,088,733.15 ፤በልገሳ ከተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች የተሰበሰበ ብር 9,2 89,665.69 በድምሩ ብር 1,188,852,281.16 ተሰብስቧል፡፡በሌላ በኩል ከልዩልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ብር 31,388,850.00 ሲሆን ጠቅላላ ድምር ብር 1,220,241,131.16 መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## በአጠቃላይ የተፋሰስ ልማት ስራዎች

የህዳሴ ግድቡን መሠረት ባደረገ መልኩ በተሠሩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ሥራዎችና በሥነ-ሕይወታዊ ዘዴ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በዚህ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት የጉልበት አስተዋጽዖ በገንዘብ ሲተመን በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ ብር 1,366,179,272.00 አስተዋጽዖ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ በተፋሰስ ልማት ሥራዎቻችን በተከታታይ ለ12 ዓመታት በአጠቃላይ የጉልበት አስተዋፅኦው በገንዘብ ሲተመን በድምሩ ብር 33,801,866,094.00 አስተዋጽዖ ተደርጓል፡፡ታላቁ ህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ በአማራ ክልል በተለያዩ የአባይ ተፋሰስ አካባቢዎች የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራ መስራት ተችሏል፡፡



ታላቁ ህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ የተከናወነ የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራ

የቦንድ እርክክብን በተመለከተ

በበጀት ዓመቱ የቦንድ ርክክብ ለመፈፀም በዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም መሰረት እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ አልተከናወነም፡፡ በአጠቃላይ ከመጀመሪያ እስካሁን ድረስ የቦንድ ግዥ

ከፈፀሙት 336,482 ሠራተኞች ውስጥ 336,482 ያህሉ ቦንድ ተረክበዋል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ደርሷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በነበረን ድጋፍና ክትትል ወቅት አንዳንድ ተቋማት የሰበሰቡትን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ቦንድ እንዲቀየር አለማድረጋቸውን ታውቋል፡፡

### የችግኝ ተከላን በተመለከተ

የህዳሴ ግድቡን ዓላማ መሠረት በማድረግ በክልላችን በተለያየ ቦታ 248,738 ሄክታር መሬት ላይ 1.43 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ዕቅድ ተይዞ በችግኝ ተከላ የተሸፈነ መሬት ደግሞ 176,067.2 ሄክታር መሬት ሲሆን የተተከለ ችግኝ ደግሞ 1.429 ቢሊዮን ሲሆን በዚህም መሠረት በሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም ችግኝ ለመትከል ኅብረተሰቡ በተደጋጋሚ በተለያየ ጊዜና ቦታ በነቂስ ወጥቶ ለአረንጓዴው ልማት እርብርብ ማድረግ በመቻሉ በየደረጃው ከፍተኛ የሆነ ውጤት መገኘቱ ተዘግቧል፡፡ ይህም በመሆኑ የታላቁ የኢትዮጵያን ህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

በአጠቃላይ የህዳሴ ግድቡ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ ከቦንድ ግዥ፣ ከልገሳ፣ ከልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች፣ ከተፋሰስ ልማት ሥራዎች እስከ በጀት ዓመቱ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም ድረስ በድምሩ ብር 35,022,107,225.16 አስተዋጽዖ ተደርጓል፡፡

# እንስሳት ሃብት ልማት

### የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም የሥጋ ምርትን 370,625 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 466,163 ቶን የዕቅዱን ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡በተመሳሳይ የወተት ምርት 1,515,388 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 1,679,245 ቶን የዕቅዱን 100% በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡የእንቁላል ምርት 670 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ 772 ሚሊዮን በማከናወን የዕቅዱን ከ100% በላይ ተፈጽሟል፡፡የዓሳ ሥጋ ምርት 34,119 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 29,477 በማድረስ የዕቅዱን 82% ተከናውኗል፡፡ የማር ምርት 22,054 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 29,355 ቶን የዕቅዱን ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡ቆዳና ሌጦ 8,593,324 ለገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ 8,990,141 በማከናወን የዕቅዱን 95% ተፈጽሟል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሩ ከእንስሳት ሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በባለሙያ የተደገፈ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት በወተት እና በስጋ ምርት ተጠቃሚ እንዲሆን እገዛ ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው፡፡



የአርሶ አደር የእንስሳት ሀብት-ምዕራብ ጎንደር መተማ ወረዳ

ልቅ ግጦሽ ማስቀረት

በበጀት አመቱ ልቅ ግጦሽ ለማስቀረት በተሰራው ስራ በ39,861 ልቅ ግጦሽ በማስቀረት እና 1,392,794 ሄክታር መሬት በማጠናከር የልቅ ግጦሽ ስርዓትን ለማስቀረትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ ታቅዶ በ38,520 (96%) ጎጦች በ1,105,214 ሄክታር (79%) መሬት ላይ የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡

## የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል እና ጥበቃ

በበጀት አመቱ በዝርያ ማሻሻያ ስራ 388,200 የዳልጋ ከብቶችን ለማዳቀል ታቅዶ 341,996 በማዳቀል (88%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን በዚህም የጥጃ ውልደቱን 115,712 ለማስወለድ ታቅዶ 135,547 (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በንጹህ ፎገራ ከብት አቅርቦት ከተዳቀሉት 15,789 ጥጆችን ለማስወለድ ታቅዶ 150,490 (100%) በላይ ጥጆች ተወልደዋል፡፡እንዲሁም በበጀት አመቱ አርሶ አደሩ የተለያዩ እንስሳትን በማርባት ላይ ይገኛል፡፡



የወተት ላሞች-ደንግላ ወረዳ

## የእንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት

በበጀት ዓመቱ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችና መደበኛ የበሽታ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለ57,984,079 እንስሳት የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ67,493,763 ከ100% በላይ እንስሳት የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡እንዲሁም 25,637,594 እንስሳት የቅድመ መከላከል የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ ለ33,061,680 ከ100% በላይ እንስሳት የሕክምና አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል፡፡በተጨማሪም ለ12,508,650 እንስሳት የፈውስሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ታቅዶ 12,913,875100% በላይ እንስሳት የፈውስሕክምና ተሰጥቷቸዋል፡፡እንዲሁም 100 ክሊኒኮችን ለመገንባት ታቀዶ 51 (51%) ኪሊኒኮችን መገንባት ችሏል፡፡እንዲሁም በበጀት አመቱ እንስሳትን በሰው ሰራሽ ዘዴ ዝርያ ማሻሻል ተችሏል፡፡



እንስሳትን በሰው ሰራሽ ዘዴ ዝርያ ማሻሻል-ዳንግላ ከተማ አስተዳደር

## ንግድና ገበያ ልማት

በ2015 ዓ.ም የንግዱን ማህበረሰብ በአደረጃጀት መምራት እንደሚገባና የንግድ ሪፎርሙን ለመተግበር ደጋፊ ሚናውን እንዲወጣ ለማድረግ የክልሉን ነጋዴዎች በተለያዩ አደረጃጀት ውስጥ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡በመሆኑም አዲስ የህዝብ ክንፍ ከማቋቋም አንፃር 50 አዲስ የዘርፍ ማህበር ለማቋቋም ታቅዶ 18 (36%) የዘርፍ ማኅበራትን በማቋቋም ወንድ 4,524 ሴት 1250 ድምር 6,074 አዲስ የዘርፍ ማህበር አባል ማፍራት የተቻለ ሲሆን ከአባላቱ መዋጮ 552,850 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡አዲስ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት አባላት ወንድ 30,262 ሴት 11,491 ድምር 41,753 በማፍራት ከአባላቱም 3,194,868 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

## *የዋጋ ንረትን ማረጋጋት*

በበጀት አመቱ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብና ተዘዋዋሪ በጀት በመመደብ ገበያ የማረጋጋት ስራ እንዲመቻች ባደረጉ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ማለትም ምስራቅ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደሴ ከተማ፣ ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ከተማ፣ ጎንደር ከተማ፣ አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ ምዕራብ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሃን፣ ደብረ ማረቆስ እና ማዕከላዊ ጎንደር በድምሩ ብር 439,249,589 በማስመደብ 326,228.3 ኩንታል የግብርና ምርት እንዲሁም 3,171,346 ሊትር የምግብ ዘይት፣ *የዳቦ ዱቄት 61,152 ኩንታል፣ ፓስታ በካርቶን 23,349.5፣ መኮሮኒ 11,865 ኩንታል፣ ጨው 29,108 ኩንታል፣ ደረቅ ሳሙና በቁጥር 1,391,495፣ ፈሳሽ ሳሙና 54,076 ሊትርና ሻይ ቅጠል በካርቶን 700 በማቅርብ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ጥረት የተደረገ ቢሆንም የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት ባለመቻሉ ለወደፊት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡*



*የኑሮ ውድነትን ወይም የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የተካሄደ ውይይት-ባህርዳር*

## የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ

በንግድና ግብይት ዘርፍ 1,798,703 ለሚሆኑ ለንግዱና ለሸማቹ ማህበረሰብ፣በንግድ ማህበረሰብ በምዝገባና ፈቃድ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ዙሪያ፣ በሸማቾች አዋጅ፣ በዘመናዊ ሰብል ግብይት አሰራር መመሪያው እና በእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ1,914,991 የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት ተችሏል፡፡

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ መስጠት

በ2015 ዓ.ም ለ94,461 ነጋዴዎች የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 95,207 (ከ100% በላይ) የምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት *ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከንግድ ምዝገባ አገልግሎት ጋር ተያይዞ 800 የንግድ ስም ለማጣራትና ለመመዝገብ ታቅዶ 1,057 (ከ100% በላይ)፣16,151 የድርጅት ስም ለማጣራት እና ለመመዝገብ ታቅዶ 20,213 (100% በላይ)፣ 13,046 የንግድ ምዝገባ ማሻሻያ ለማድረግ ታቅዶ 36,754 (ከ100% በላይ)፣ 2,289 ምትክ የንግድ ምዝገባ ለመስጠት ታቅዶ 1,981 (86%) ማከናወን ተችሏል፡፡*

## አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ አገልግሎት

በ2015 ዓ.ም 114,140 የንግድ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት እቅድ ተይዞ 122,187 (ከ100% በላይ) *ማከነወን የተቻለ ሲሆን ከፈቃድ አገልግሎት ጋር ተያይዞ 11,014 ንግድ ስራ ፈቃድ ለማሻሻል ታቅዶ 13,564 (ከ100 በላይ) የንግድ ፈቃድ ማሻሻል ተችሏል፡፡*

## የንግድ ስራ ፈቃድ አድሳት

በበጀት አመቱ 414,169 የንግድ ፈቃድ እድሳት ለመስጠት ታቅዶ 331,999 (80%) የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳት የተሰጠ ሲሆን ሁሉንም አገልሎቶች በኦንላይን ለመስጠት ታቅዶ 606,827 ነጋዴዎች አገልግቱን ማግኘት ችለዋል፡፡ይሁንእንጅ 25,558 ነጋዴዎች በተለያዩ ምክንያቶች ፈቃዳቸውን ሰርዘዋል፡፡ ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ እድሳት አገልግሎት 46,632,750 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 76,735,694 (164.6%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና እድሳት አፈፀፀም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻፀር አፈጻጸሙ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡

## የውጭ ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን

በ2015 ዓ.ም የውጭ ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን ስራውን በማጠናከር ጠንካራ የንግድ ስርዓት ለመፍጠር በተሰራው ስራ የበር ከበር ጉብኝት (የውጭ ኢንስፔክሽን) በዓመቱ በድግግሞሽ 1,313,944 ድርጅቶችን ለመጎብኘት ታቅዶ 1,325,019 (ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ በውጭ ኢንስፔክሽን 131,983 ጉድለቶች ተገኝተው በ131,983 ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ተወስዷል፡፡ *የተወሰደው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በዝርዝር ሲታይ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ* 80,663፣ *እሽጋ* 38,598፣ *እገዳ* 12,237፣ *ስረዛ* 24፣ *በእስራት የተቀጡ* 14፣ *በገንዘብ የተቀጡ* 43፣ *በገንዘብና በእስራት የተቀጡ* 42፣ *በነፃ የተለቀቁ 67፣ በሂደት ላይ ያሉ ደግሞ* 295 *ሲሆኑ በተወሰደው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መሰረት 60,466 አዲስ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ 5,131 የንግድ አድራሻቸውን እንዲያስተካከሉ፣ 2,130 ባወጡት የንግድ ስራ ፈቃድ እንዲሰሩ፣ 65 ባዕድ ነገር ከመቀላቀል እንዲታቀቡ፣ 675 የመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃን በተመኑ እንዲሸጡ፣ 4,379 ደረጃውን በጠበቀ የመለኪያ መሳሪያ እንዲሸጡ፣ 71 የሙያ ብቃት ማርጋገጫ እንዲያሟሉ፣2,939 ካፒታላቸውን እንዲያስተካካሉ፣3,223 ቀላቅሎ ከመነገድ እንዲታቀቡ፣ 2,596 ቅርንጫፍ እንዲከፍቱ ፣ 36,487 የዋጋ ዝርዝር እንዲለጥፉ፣ 3,439 እራሳቸውን ከንግድ መረቡ እንዲያገሉ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በተወሰደው እርምጃ 3,035,701 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡*ከዚህ በተጨማሪ ህገ ወጥ ንግድን ለመቆጣጠር በተሰራው

ስራ ከመሠረታዊ ምርቶች 182,202 ሊትር የምግብ ዘይት፣ 667,459 ሊትር ነዳጅ ፣ 3,867 ኩንታል ስኳር፣ 2,154 ኩንታል የስንዴ ዱቄት፤ከግብርና ምርት አኳያ 2,384 ኩንታል በርበሬ፣ 5,360 ኩንታል ቡና፣ 13,485 ኩንታል ጤፍ፣ 1,016 ኩንታል ምስር፣942 ኩንታል ሩዝ፣5,236 ኩንታል ስንዴ፣ 1,248.16 ኩንታል አተር፣ 1,294 ኩንታል ቦሎቄና 11,810 ኩንታል ሌሎች በደምሩ 42,775.16 ኩንታል የሰብል ምርት እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ምርቶች አኳያ 2,446 ኩንታል ደረቅ ምግብ ነክ ሸቀጦች ጤፍ ዱቄት፤ በርበሬ ዱቄት፣ 542,840 ሊትር ፈሳሽ ምግብ ነክ ሸቀጦች፣ 62,734 አልባሳት፣ 23,602 ሊትር ኬሚካል፣3,331 ሊትር ፀረ-ተባይ መድሃኒት፣16,534 ኤሌክትሮኒክስ፣ 25,199 ኩንታል ሲሚንቶ፣ 4,342 ነጠላ ጫማ፣ 4,496 ቆርቆሮ፣ 731,991 ሌሎች በህገ ወጥ መንገድ መያዝ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች በፈሳሽ 117,997 ሊትር፣ በጠጣር 41,181.25 ኪሎ ግራም በገንዘብ ሲገመት 8,687,967 ብር የሚያወጣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበባቸው ምርቶች በአሰራር ስርዓቱ መሰረት የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ ህገወጥነትን በመከታተል ከተወሰዱ ርምጃዎች የተገኘ ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድና ግብይት ስርዓቱ ውስጥ ያለውን ተፅእኖ በመቀነስ ረገድ ሲታይ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የህገወጥነት አዝማሚያው ሲታይ በየጊዜው እያደገ ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ ተለይቷል፡፡ በህገ-ወጥ የቁም እንስሳት ግብይት የተያዙ የቁም እንስሳት 1,418 ዳልጋ ከብት፣ 1,882 በግ፣ 815 ፍየል፣ 595 ጋማ ከብት፣17 ግመል በድምሩ 4,727 የቁም እንስሳት፣57 ቆዳና ሌጦ በክትትል ሊያዙ ችለዋል፡፡ በህግ-ወጥ ከተያዙት እንስሳት ተሸጠው 3,389,580 ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡



በህገወጥ የንግድ ቁጥጥር ዙሪያ የተካሄደ ውይይት-ባህርዳር

## የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ

የሸማቹን መብት ለማስከበር የተጠናከሩ ሸማች ማህበራትና ዩኒየንኖች በማቋቋምና በማጠናከር የሸማቹን ጥቅም ከማስከበር አኳያ የሸማች ህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር የገበያ ማረጋጋት ስራ ለመስራት 428 ታቅዶ ሁሉንም ተደራሽ የተደረ ሲሆን የሸማቾች ጥበቃ ማህበራትን በማቋቋምና በማጠናከር ወደ ስራ ለማስገባት 20 ታቅዶ 15 የሸማች ጥበቃ ሲቪክ ማህበራት ማከናወን ተችሏል።



በመርከብ ዩኒየን የተካሄደ የዋጋ ማረጋጋት ስራ-ባህርዳር

## መሠረታዊ ምርቶች አቅርቦትና ስርጭት

በ2015 ዓ.ም ለክልሉ መቅረብ የነበረበት 220,300 ኩንታል ስኳር ቢሆንም የቀረበ 94,163.5 ኩንታል (43%) ሲሆን ከቀረበው ውስጥ 89,396.5 ኩንታል ለህብረተሰቡ የተሰራጨ ሲሆን ቀሪ 4,767 ኩንታል ስኳር በመጋዝን ውስጥ ይገኛል፡፡የምግብ ዘይት አቅርቦትና ስርጭት በአምሰባል የንግድ ስራዎች ድርጅት፣ በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኔኖች፣በበላይነህ ክንዴ አስመጭና ላኪ ድርጅት፣ በጊልቤና፣በአርክቴክት ኢንጅነሪነግ እና በዋን እስታር እና አሰፋ አማካኝነት በማቅረብ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ለክልሉ የተመደበ 19,673,564 ሊትር የምግብ ዘይት፣ ከተመደበው ውስጥ የቀረበ 17,194,555 ሊትር ሲሆን የተመደበው የምግብ ዘይት ሙሉ በሙሉ ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የመሰረታዊ ምርት የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ሲሆን በክልሉ 248 ስራ ላይ ያሉ የነዳጅ ማደያዎች ሲኖሩ ከዚህ ውስጥ በተለያዩ ምክንያት የማይሰሩ 46 ማደያዎች ሲሆኑ ሁሉም የሚሰሩ ማደያዎች በዲጅታል የግብይት ስርዓት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በበጀት ዓመቱ የቀረበ የነዳጅ መጠን

333,507,073 ሊትር ናፍጣ፣ 89,080,153 ሊትር ቤንዚን እና 5,427,326 ሊትር ነጭ ጋዝ ቀርቦ ለተጠሚው ተሰራጭቷል፡፡ *የመሰረታዊ ምርት ስርጭት ብክነትን ለመቆጣጠርና ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ቸርቻሪዎችን ኦዲት ማድረግ አንዱ ተግባር ሲሆን 165,180 ኦዲት ለማረግ ታቅዶ 58,405 (35%) የክዋኔ ኦዲት ማድረግ ተችሏል፡፡* በኦዲቱም 117.09 ኩንታል ስኳር፣ 3,238 ሊትር የምግብ ዘይት ጉድለት የተገኘ ሲሆን በተገኘው ጉድለትም ለ339 ነጋዴዎች የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ 185 ነጋዴዎች ከትስስር የተሰናበቱ እንዲሁም 3 ነጋዴዎች ለህግ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

በመሰረታዊ ምርት አቅርቦት በሁሉም ምርቶች እጥረት ያለ ቢሆንም ስኳርና ቤንዚን ላይ የሚስተዋለው እጥረት ግን ጎላ ያለ ነው፡፡ በቀጣይም ከነዳጅ ሽያጭ አኳያ ማደያ ላይ የሚፈጽሙ ባለሙያዎችና በአሽከርካሪዎች በኩል በካሽ ለመገበያየት የመፈለግ ዝንባሌ እና የታለመለት ድጎማ ለህዝብ አገልግሎት ባልሰጡ ይልቁንም በጋራዥ ለቆሙ መኪናዎች አገልግሎት እንደሰጡ አድርጎ ነዳጅ መስጠት ስለተስተዋለ አሰራሩን ማጥበቅ እንደሚገባ ተለይቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## የገበያ መሰረተ ልማት

በ2015 ዓ.ም የ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ገበያ መሰረተ ልማትን በመገንባትና ነባሮችን በማጠናከር የግብይት ስርዓቱን ምቹ ለማድረግ ግብ ተይዞ ተከናውኗል፡፡በመሆኑም 1,433 ነባር የተሻሻሉ የገበያ መሰረተ ልማትን በማጠናከር ወደ ስራ ለማስገባት እቅድ ተይዞ 1,327 (92%) ማሻሻል የተቻለ ሲሆን 274 አዲስ የገበያ መሰረተ ልማት ለማቋቋም ታቅዶ 181 (66%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመረጃ ዳታ ቤዝና ዌብ ሳይት አገልግሎት በመዘርጋት የገበያ መረጃ ዋጋ በማቅረብ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግብይት እንዲጠናከር ሳምንታዊ የግብርና እንዲሁም 52 ጊዜ የኢንዱስትሪ ምርቶች የገበያ ዋጋ መረጃ ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት ታቅዶ 49 (94%) ጊዜ መላክ ተችሏል፡፡ የተመረጡ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ዋጋ አዝማሚያ በተለይም ከወርሃዊ የክልል አማካኝ ንፅፅር፣ ካለፈው ወር ንፅፅር እና ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር ንፅፅር በመስራ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በዓመቱ 12 ጊዜ ለማቅረብ ታቅዶ ሁሉንም ማከናወን ተችሏል፡፡

## *የስሚንቶ ግዥ፣ቁጥጥርንና ስርጭት*

*በተመረጡ አከፋፋዮች መግባት የነበረበት የሲሚንቶ ምርት መጠን 2,440,000 ሲሆን ወደ ክልሉ የገባ 1,026,343 ኩንታል ብቻ ነው። ግዢ የተፈጸመበት የስሚንቶ መጠን 1,388,414.9 ኩንታል፣ በመጓጓዝ ላይ ያለ የስሚንቶ መጠን 10,850 ኩንታል፣ ለተጠቃሚው የተሸጠ/የተሰራጨ/ 988,782 ኩንታል፣ በመጋዘን ያለ 71,671.5 ኩታል ነው። በመሆኑም በሲሚንቶ አቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም ላይ ውስንነቶች ስላሉ በልዩ ትኩረት መስራት ያስፈልጋል።*



**በሲሚንቶ አቅርቦት ዙሪያ የተካሄደ ውይይት -ባህርዳር**

## የአገር ውስጥ ግብይትን በማሳለጥ የዋጋ ግሽበትን መከላከል

የሰብልና የኢንዱስትሪ ምርት ትስስር በማጠናከር የዋጋ ማረጋጋት ስራውን ውጤታማ ለማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል።ከዚህ ውስጥ አንዱ የግብርና ምርት ትስስር የተፈጠረ ሲሆን በዓመቱ 4,013,341 ኩንታል ለማስተሳሰር ታቅዶ 4,932,015 ኩንታል (ከ100% በላይ) ማስተሳሰር ተችሏል። የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ከተቀመጡ አቅጣጫዎች ውስጥ የእሁድ ገበያን በሁሉም ዞኖች፣ ሪጂኦ-ፖሊታን እና ከተማ አስተዳደሮች በማቋቋም አምራቹንና ሸማቹን

በቀጥታ በማገናኘት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸምት ማድረግ ተችሏል፡፡ከዚህ አኳያ በ120 ከተሞች የገበያ ቦታ ለማቋቋም ታቅዶ 83 (69%) የእሁድ ገበያዎች ተቋቁመው ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በሸማቾችና ህብረት ስራ ማህበራት አማካኝነት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ማነቆ የሆነውን የፋይናንስ ችግር በመፍታት በዞኖችና ከተሞች 383,752,415 ብር በጀት በመመደብ 852,991 ኩንታል የግብርና ምርት እንዲሁም 120,691 ኩንታል ጠጣር እና 3,102,893 ሊትር ፈሳሽ የኢንዱስትሪ ምርቶች ለመንግስት ሰራተኛውና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪ ማቅረብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም ድረስ የዋጋ ግሽበቱ በየወሩ እየጨመረ ይገኛል፡፡ እንደ ሀገር ያለው የዋጋ ግሽበት እንደተጠበቀ ሆኖ በክልላችን እየተስተዋለ ያለው የዋጋ ግሽበት 38 በመቶ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ምግብ ነክ ምርቶች 39.99 በመቶ ሆኖ ታይቷል፡፡ ምግብ ነክ ያልሆኑ ደግሞ 32 በመቶ ግሽበት እንዳለ መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል የተዘጋጀውን የአምስት ወር እቅድ በትኩረት በመፈፀም ችግሩን ማቃለል የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት እየተተገበረ ይገኛል፡፡

በበጀት አመቱ ከእንስሳት ገብይት አኳያ በመሸኛ ትስስር የተፈጠረላቸውን 1,561,511 የቁም እንስሳት ለማስተሳሰር ታቅዶ 1,432,180 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 91% ነው፡፡ ከቆዳ ግብይት አኳያ በትስስር ለፋብሪካ የቀረበ ቆዳና ሌጦ 3,949,999 ለማስተሳሰር ታቅዶ 3,565,097 (90%) ማስተሳሰር ተችሏል፡፡ ከስጋ ምርት አኳያ በተለይ የበአላት ወቅቶችን መሰረት ተደርጎ በተሰራው ሰፋፊ ንቅናቄ በከተሞች በተመጣጣኝ ዋጋና በበቂ መጠን ማቅረብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ስጋ በቶን ዕቅድ 532 ክንውን 653 (ከ100 በላይ%)፣ ዓሳ በቶን ዕቅድ 2,822 ክንውን 2,678 ቶን (94%)፣ ወተት በቶን ዕቅድ 177,940 ክንውን 171,598.2 ቶን (96%)፣ ዶሮ በቁጥር ዕቅድ 2,862,903 ክንውን 3,703,888 (ከ100% በላይ)፣ እንቁላል ዕቅድ 28,295,471 ክንውን 31,027,094 (ከ100% በላይ) በማስተሳሰር ዘርፉ የኑሮ ውድነቱን በማቃለል ድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ ጅምር ጥረቶች ታይተዋል፡፡

## የወጪ ምርቶች ግብይት

በበጀት አመቱ በክልሉ ተመርተው ወደ ውጭ የሚወጡ አስገዳጅ ዋና ዋና የሰብል ምርት ዓይነቶች (ሰሊጥ፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ቀይ ቦሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ ማሾ፣ ጥቁር ቦሎቄ፣ ቡላ ቦሎቄ፣ ዥንጉርጉር ቦሎቄ) ሲሆኑ በአመቱ 4,107,836 ኩንታል በመሸኛ ለመላክ ታቅዶ 4,590,366 ኩንታል (ከ100 % በላይ) ማከናወን ተችሏል፡፡ ከእንስሳት ሀብት አኳያ በግና ፍየል በቁጥር 22,528 ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 15,261 (67.7%)፣ ዓሳ በቶን ዕቅድ 25 ክንውን

28.42 (113.6%)፣ እንዲሁም የአለቀለት ቆዳ ዕቅድ 3,300,000 ፊትስኩየር ክንውን 363,934 (11%) ፊት ስኩየር ማከናወን ተችሏል፡፡

*በ2015 ዓ.ም የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ከሰብል ምርት የዓመቱ ዕቅድ 426,000,000 ዶላር ክንውን 632,000,000 (148.5%) ዶላር፣ ከእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ዕቅድ 7,980,172 ዶላር ክንውን 2,831,711.28 (35.48%)፣ የኢንዱስትሪ ምርት (ከጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችና ከአግሮ ፕሮሰሲንግ) ዕቅድ 37,000,000 ክንውን 34,900,000 (94.3%)፣ ከማዕድን ግብይት ዕቅድ 46,720,000 ክንውን 29,778,460 (64%) ደላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን በሌላ መኩል ደግሞ ከአበባ ምርት ኤክስፖርት ዕቅድ 280,000 ክንውን 16,500,000 (ከ100% በላይ) ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የታቀደ የውጭ ምንዛሬ ገቢ* 517,980,172 ዶላር ሲሆን ክንውን 716,010,171.279 ዶላር (138%) የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፡፡

## የማዕድን ሃብት ልማት

### የማዕድን ፍለጋና መሠረታዊ ጅኦ-ሳይንስ ካርታ ስራ

የክልላችን የማዕድን ሃብት ለማልማት በቁርጠኝነት በመነሳት የስነ ምድር ጥናት ሽፋኑን ወደ 33.33% ማድረስ ተችሏል፡፡ክልላችን የበርካታ ማዕድናት መገኛ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ከ45 በላይ የማዕድን አይነቶችም በከፍተኛ ክምችትና መጠን በጥናቱ ተገኝተዋል፡፡ 20,000 ካሬ ኪሎ ሜትር በገፀ-ምድር አና መልክዓ-ምድራዊ ቅኝት የማዕድን ልማት ቀጠናዎችን የመለየት ሥራን ለማከናዎን ታቅዶ 20,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡ በዚህም የማዕድን የልማት ቀጠና አካባቢዎች የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን፣ ብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት የያዘ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡

### የሥነ - ምድር ጥናት

የክልሉን የሥነ - ምድር ጥናት በ1:50,000 መስፈርት ሽፋኑን ለማሳደግ በተሰራው ስራ 1:50,000 መስፈርት ቀደም ብለው የተጀመሩ ነባር ኘሮጀክቶች ማለትም በአዊ ብሄረሰብ በአየሁ ጓጉሣ ወረዳ ኢናባራ ወንበርማ ወረዳ በ1357 ካሬ ኪሎ ሜትር የሥነ - ምድር ጥናት ለማጥናት ዕቅድ ተይዞ ዋና የመስክ ሥራ ተግባራት በመፈፀም የቤተ-ሙከራ ተግባር ብቻ የቀረው ከአጠቃላይ ተግባሩ ውስጥ 95% የተከናወነ ሲሆን ወርቅ፣ ኦፓል፣ ግራናይት፣ እምነበረድ፣ ጃስፐር ፣አጌት፣ባዛልት እና የመሳሰሉትን ማእድናት በጥናቱ ተገኝተዋል፡፡ በደቡብ ጎንደር ዞን (ስማዳ እና ጋይንት ወረዳዎች) በ2257.42 ካሬ ኪሎ ሜትር የስነምድር ጥናትና

ካርታ ስራን ለማጠናቀቅ ታስቦ 100% መፈፀም ተችሏል። በጥናቱ ከተገኙ ማዕድናት መካከል ኦፓል፣እጌት፣ ኳርቲዝ፣ ባዛልት እና የመሳሰሉት ማግኘት ተችሏል።

በ2015 ዓ.ም የክልሉን የማእድን የሥነ - ምድር ጥናት ለማከናዎን 1:50,000 መስፈርት 12,846 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት የሚሸፍን አዲስ ፕሮጀክቶችን ለመፈጸም እቅድ ተይዞ 11,561.4 ካሬ ኪሎ ሜትር ጥናቱ የተጠናቀቀ ሲሆን በጥናቱ ከ 13 በላይ የማዕድን ዓይነቶች ማለትም እንደ ኦፓል፣ ሲናባር (የሜርኩሪ ኦር)፣ ኮፐር፣ ኒኬል፣ ሳልፈር፣ የድንጋይ ከሰል፣ ካኦሊን፣ ራዮላይት (በተሻለ ጥራት)፣ አግኒም ብራይት፣ ጃስፐር፣ ዶሎማይት፣ ካልሳይት፣ የማዕድን ውሃ እና ሌሎችም ማእድናት ማግኘት ተችሏል።




የስነ-ምድር ጥናት-ምስራቅ ጎጃም (ጠዋር ዞቫር)

የከበሩና እና የጌጣጌጥ ማዕድናት ክምችት ግመታ

በ2015 ዓ.ም 24 ካሬ ኪሎ ሜትር በአራት የክልሉ አካባቢዎች የጌጣጌጥ ማዕድናት (ወረቅ፤ ኦፓል፤ አጌት፤ ጃስፐር) ፍለጋና ክምችት ግመታ በ5 ካሬ ኪሎ ሜትር በሰሜን ሸዋ ዞን በሚዳ ወረሞ ወረዳ ከርከሬ ቀበሌ በተመረጠ ቦታ፣ በ5 ካሬ ኪሎ ሜትር ሰሜን ወሎ ዞን አንጎት ወረዳ በተመረጠ ቦታ የከበሩ ማዕድናት ጥራት፣ ስርጭትና ክምችት ግመታ ጥናት ለማከናወን ታቅዶ ዋናው የመስክ ስራው የተከናወነ ሲሆን የማዕድን ናሙናውም ለላብራቶሪ ተልኮ በምርመራ ላይ ሲገኝ አፈጻፀሙም 70% እንዲሁም በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር በዚገም ወረዳ በ4 ካሬ ኪሎ ሜትር፣ በወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን በ10 ካሬ ኪሎ ሜትር በተመረጡ ቦታ የወርቅ ማእድን ጥራት፣ ስርጭትና ክምችት ግመታ ጥናት ለማካሄድ ዕቅድ ተይዞ ዋናው የመስክ ስራው የተከናወነ ሲሆን የማዕድን ናሙናውም ለላብራቶሪ ተረጋግጦ የተሻለ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል አፈጻፀሙም ከዓመቱ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ የብረት እና ብረት ነክ (ሊቲኒየም፣ ኒኬል፣ ኮፐር ወዘተ) ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት ቦታዎች መረጃ ሽፋን 58 ካሬ ኪሎ ሜትር ለማድረስ ታቅዶ 100 ፐርሰንት መፈጸም ተችሏል፡፡

ስትራቴጂካሊ ጠቀሜታ ያላቸው እሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስተሪዎችን (የወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የብረት፣ የሲሚኒቶ ፋብሪካ፣ የጂብሰም፣ የማርብል) 70 የምርመራና የምርት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዶ ለ64 አምራች ኢንዱስትሪዎች የምርመራና ምርት ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከ91.4% ሆኗል፡፡ በተለይ የሲምንቶ ፋብሪካ ለመገንባት አምስት የምርት ፍቃድ ከወሠዱት መካከል፤ የሁለቱ የፋብሪካ ግንባታ ሂደት (በረንታ ሲሚንቶ እና ለሚ-እንሣሮ ናሽናል ሲሚንት ፋብሪካዎች) በመልካም ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡የለሚ አንሣሮ ናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ የሲቪል ስራው (የግንባታ መሠረቱን ጨምሮ አጠቃላይ ሲቪል ስራው ሲሆን)፤የኤሌክትሮ መካኒክስ ስራውም ተጀምሯል፡፡ ይህ ፋብሪካ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ በ2016 ዓ.ም ታህሣስ ወር ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ በቀን 130 ሺህ ኩንታል የሲሚንቶ ምርት በማምረት የሲሚንቶ ችግርን እንደሚያቃልል ታምኖበታል፡፡

የኢንዱስትሪ ማዕድናት የምርመራ ስራ ፈቃድ እና አነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት ፍቃድ ለ72 ጠያቂዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ108 (ከ100% በላይ) አነስተኛ ደረጃ እንዲሁም የከፍተኛ ኮንስትራክሽን የማዕድን ማምረት ፍቃድ ለ50 ፈቃድ ጠያቂዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ85 (44 የግራናይት፣ 7 የእብነ በረድ፣ 34 የጥቁር ድንጋይ) (ከ100% በላይ) ፍቃድ ጠያቂዎች መስጠት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የወርቅ ማዕድን አቅራቢነት፣ የከበሩ ማዕድናት ዕደ ጥበብ ብቃት እና ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ማደያ 148 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ149

(100%) ጠያቂዎች መስጠት ተችሏል፡፡ ለ5,973 ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃዶች እና ለ260 አነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2,724 (45.6%) ማከናወን ተችሏል፡፡

## የማዕድንን ገቢ ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ 28,531 ኪሎ ግራም ጥሬ ኦፖል እና 2,306 ኪሎ ግራም የተዋበ ኦፖል ለውጭ ገቢያ ለማቅረብ ታቅዶ 39,114.97 ኪሎ ግራም ያልተዋበ እና 526.78 ኪሎ ግራም የተዋበ ኦፖል ወደ ውጭ በመላክ 4.88 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 2,185,813.78 የአሜሪካ ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 44.78% ላይ ነው::
በተጨማሪም 70 ኪሎ ግራም ወርቅ ከክልሉ ለብሔራዊ ባንክ በማቅረብ 5,000,000 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ 121.180 ኪሎ ግራም ወርቅ በማቅረብ 6,604,310 የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡
የማዕድን ሐብታችን በማልማት የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት በቁርጠንነት ከመስራት ባሻገር ከዘርፉ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢ በእጅጉ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን በበጀት ዓመቱም ከሮያሊቲ፣ ከመሬት ኪራይ፣ ከፈቃድ አገልግሎት እና ሌሎች ተዛማጅ የ አገልግሎት ክፍያዎች ብር 100,400,000 ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዞ ብር 81,105,882.1 (ከሮያሊቲ- ብር 29,383,495.1 ከቁርጥ ዋጋ ብር 32,119,525.3፣ ከከመሬት ኪራይ፣ ከፈቃድና ሌሎች አገልግሎቶች ብር 19,612,861.7) በመሰብሰብ 80.78% መፈፀም ተችሏል፡፡

## ማዕድን ምርት መጠንን ማሳደግ

በክልላችን የሚመረተው የኮንስትራክሽንና ግንባታ የማዕድናትን ምርት መጠን በማሳደግ ለሀገር ውስጥ ኢንዲስትሪዎች በማቅረብ በክልላችን በማስመረት 6,246,887.31 ሜትር ኩብ ለማቅረብ ታቅዶ 5,414,425.23 ሜትር ኩብ (አፈፃፀሙም 74%) አምርቶ ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ፍጆታ የሚውል የማዕድን አይነቶች በተመለከተ (ለሲሚንቶ፣ ለግራናይት፣ ለብርጭቆ፣ ለሴራሚክስና ለብረት) ማዕድናትን 1,037,002 ቶን በአገር ውስጥ ለመተካት ዕቅድ ተይዞ 677,429 ቶን በማምረት ማቅረብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 65.33% ሆኗል፡፡ የግንባታ ማዕድናትን በነፃ የመጠቀም መብት ላላቸው አካላት 1,724,400 ሜትር ኩብ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በነፃ ለማቅረብ ዕቅድ ተይዞ 2,404,202 ሜትር ኩብ ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ ሆኖም የግንባታ ማእድናትን በነጻ በመጠቀም በነፃ የመጠቀም መብት ያላቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች

95,540,300 የሚሆን ብር ከወጭ እንዲድኑ ታቅዶ ብር 68,788,985 የሚሆን ገንዘብ ከማውጣት እንዲድኑ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙም 71.99% ነው፡፡ በበጀት አመቱ 707,775.2 ቶን ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ውጤቶች (ስሚንቶ፣ ግራናይት፣ ብርጭቆ፣ሴራሚክና ብረት) በአገር ውስጥ በሚመረቱ የማዕድን ውጤቶች ለመተካት ዕቅድ ተይዞ 677,429 ቶን እንዲያመርቱና እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙ 95.7% ነው፡፡ እነዚህ የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች ከውጭ የሚመጡ የማዕድናት ምርቶች የተተኩ ሲሆን በዚህም 4,823,738,250 የኢትዮጵያ ብር የውጭ ምንዛሬን ማዳን ተችሏል፡፡




# የጌጣጌጥ ማዕድናት

### በማዕድን ዘርፍ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት

በ2015 ዓ.ም 30,907 ኪሎ ግራም የከበረ ማዕድንን ወደ ውጭ በመላክ እንዲሁም ብሔራዊ ባንክን ለማስገባት ዕቅድ ተይዞ 39,762.93 ኪሎ ግራም ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡የአካባቢ እንክብካቤ እና የማህበረሰብ ልማት ፈንድ 6,500,000 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ10 ባለፈቃዶች ብር 3,174,464 (47%) የተሰበሰበ ሲሆን የተሰበሰበውን

የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት ፈንድ ኮሚቴ በማዋቀር ፕሮጀክት እንዲሰሩ እና በሚፈልጉት ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ ተችሏል፡፡

### በማዕድን ዘርፍ የስራ እድል ፈጠራ

በማዕድን ዘርፉ ከሚሰማሩ ባለሃብቶች፣ ኩባንያዎች እና ኢንተርፕራይዞች ለ52,858 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዞ ለ50,977 (ወንድ- 37,432 ሴት- 13,545) ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የዕቅዱን 96.44% መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከተፈጠረው የስራ ዕድል መካከል 35,684 (ወንድ- 24,979 ሴት- 10,705) የሚሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡




የግራናይት ማዕድን ፋብሪካ-ባህርዳር

## ገቢ

### የገቢ አሰባሰብ ሁኔታ

በ2015 ዓ.ም በክልሉ የሚደረገውን የፀረ ድህነት ትግል አጠናክሮ ለማስቀጠል የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ አሟጦ ለመሰብሰብና የክልሉን የልማት ፋይናንስ ፍላጎት ለማሳካት ዘመናዊ የግብር አስተዳደር ስርዓት ግንባታ ተዘርግቶ በየደረጃው ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ስለሆነም ለልማት የሚውል ፋይናንስ ማቅረብ፣በክልላችን የተጀመረውን የልማት ጉዞ መደገፍ፣የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት መገንባት እና የህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ መሰረታዊ የእቅዱ አካሎች ሲሆኑ የገቢ አሰባሰቡንም በታክስ ሰራዊት ግንባታና በተደራጀ መዋቅር በመፈጸም ውጤቶችን ለማምጣት ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በቁርጠኝነት በመፍታት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት መጠቀም የተቻለ ሲሆን በዚህም መሰረት በ2015 በጀት ዓመት ከመደበኛና ከከተማ አገልግሎት ገቢ በድምሩ ብር 42.85 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ 37.97 የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙም ከአመቱ 88.62% ሆኗል፡፡ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው ገቢ ብር 27 ቢሊዮን ጋር ሲነጻጸር በብር 10.97 ቢሊዮን (40.63%) ዕድገት አሳይቷል፡፡



የንግዱ ማህበረሰብ ግብር ሲከፍል

የግብር ከፋዮች ቅሬታ አፈታት

በበጀት አመቱ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ይዘው የሚቀርቡ ግብር ከፋዮችን ምላሽ ለመስጠት በተሰራው ስራ በአስራ ሁለት ወራት በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የቀረቡ ቅሬታዎች 2,515 ሲሆን ምላሽ የተሰጣቸው ደግሞ 2,510 (99.80%) ናቸው፡፡በሌላ በኩል የቀረቡ የታክስ በዛብኝ ቅሬታዎችን ምላሽ በመስጠት የማጽናት ምጣኔን ወደ 92% ለማሳደግ በተሰራው ስራ ከግብር ጋር በተገናኘ ለቅሬታ ሰሚ ቡድን 26241 አቤቱታዎች ቀርበው በማፅናት 23656(90.15%) ግብር ከፋዮች ምላሽ መሰጠቱን ያሳያል፡፡በዚህ መሰረት የማጽናት ምጣኔን ወደ 92% ለማድረስ ታቅዶ 90.42% የማጽናት ምጣኔ የተደረሰ ሲሆን አፈጻጸሙም 98.2% መሆኑን ያሳያል፡፡የቀረቡ የግብር ይግባኞችን ምላሽ በመስጠት ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን ወደ 90% ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን አፈጻጸሙን 79.50% ሆኗል፡፡



የግብር ከፋዮች ቅሬታ አፈታት

## የታክስ ህግ ተገዥነት አፈጻጸምን በማሻሻል ገቢን ማሳደግ

በበጀት አመቱ የግብር ከፋዮችን በባህሪና በስጋት በመፈረጅ አፈጻጸምን ለማሻሻል በተሰራው ስራ በአጠቃላይ 26,902 ግብር ከፋዮች የተፈረጁ ሲሆን የስጋት ፍረጃው አፈጻጸም በድምሩ 16962(99.98%) ግብር ከፋዮችን በስጋት ፍርጀው በማካተት ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

## የግብር ከፋዮችን ቁጥር በማሳደግ የገቢ መሰረትን ማስፋፋት

በ2015 ዓ.ም የግብር ከፋዮችን ቁጥር በማሳደግ የገቢ መሰረትን ለማስፋት በተሰራው ስራ የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 358,380 ለማሳደግ ታቅዶ የንግድ ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 345,326 በማሳደግ አፈጻጸሙን 96.36% ማድረስ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በበጀት አመቱ የምስጉን የግብር ከፋዮችን ቁጥር ለማሳደግና ለማበረታታት ምስጉን ግብር ከፋዮችን መሸለም ተችሏል፡፡



የምስጉን ግብር ከፋዮች የሽልማት ስነ-ስርዓት

## ግብር ከፋዮችን በደረጃ መክፈል

በ2015 ዓ.ም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 24,100 ለማድረስ ታቅዶ ወደ 19,724 (81.84%)፣ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 15,150 ለማሳደግ ታቅዶ ወደ

13,951(92.09%) እንዲሁም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ቁጥር ወደ 319,130 ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 311,651 (97.66 %) ማድረስ ተችሏል፡፡

## ሥራና ስልጠና

መንግስት ትኩረት ከሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሥራና ሥልጠና ዘርፍ ነው፡፡ ዋነኛ ተልዕኮውም በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ሃይል ማቅረብ፣ የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት የኢንተርፕራይዞችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣ አዋጭ ቴክኖሎጂ መኮረጅና ማሸጋገር፣ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ናቸው:: በዚህም መሰረት ቢሮው በ2015 በጀት ዓመት በኢንተርፕራይዝ ምሥረታና ስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች፣ በስራ ስምሪትና የስራ ገበያ መረጃ ስራዎች፣ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች፣ በውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ስራዎች፣ በተቋማት አቅም ግንባታ አግባብነት እና ብቃት ማረጋገጫ ስራዎች፣ በገበያ ልማትና ግብይት ስራዎች፣ በግንባታና ግብዓት አቅርቦት ስራዎች እንዲሁም በሌሎች የስራ ክፍሎች በርካታ ተግባራትን ማከናወን ችሏል፡፡

### የኢንተፕራይዝ ምሥረታና የሥራ ዕድል ፈጠራ

በበጀት ዓመቱ በከተማ ግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች 40,936 ኢንተርፕራይዞች በመመስረት፣ 585,084 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ 42,057 ኢንተርፕራይዞች የተመሰረቱ ሲሆን በዚህም ቋሚ 386,691፣ ጊዜያዊ 207,774 በአጠቃላይ ወንድ 342,406 ሴት 252,059 በድምሩ ለ594,465 ስራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም 102.74%፣ ስራ ዕድል በመፍጠር 101.6% ነው፡፡እንዲሁም በገጠር በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች 40,936 ኢንተርፕራይዞች በመመስረት፣ 585,084 የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 17,256 ኢንተርፕራይዞች የተመሰረቱ ሲሆን በዚህም ቋሚ 489,928፣ ጊዜያዊ 179,738 በአጠቃላይ ወንድ 477,344 ሴት 192,322 በድምሩ ለ669,666 ስራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም 74.6%፣ ስራ ዕድል በመፍጠር 108.34% ሆኗል፡፡

## የኢንዲስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች

በዕድገት ተኮር ዘርፎች ለተሰማሩ 27,278 (ነባር 19,744, አዲስ 7,534) ኢንተርፕራይዞች (81,476 አንቀሳቃሾች) ክፍተትንና የእድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ27,058 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 69,267 ሴት 34,670 በድምሩ 103,937 አንቀሳቃሾች) ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙም በኢንተርፕራይዝ 99.19%፣ በአንቀሳቃሽ ከ127.56%ነው፡፡

የእድገት ደረጃንና ክፍተትን መሠረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በመስጠት በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ በሁሉም ደረጃዎች 11,037 ኢንተርፕራይዞችን ከደረጃ ደረጃ ለማሸጋገር ታቅዶ በከተማ 11,326 በገጠር 704 በድምሩ 12,030 ኢንተርፕራይዞችን ማሸጋገር ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ 108.99% ነው፡፡

## የግንባታና ግብዓት አቅርቦት ሥራዎች

በበጀት ዓመቱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በከተማና በገጠር 5,418 ሄክታር ቦታ ለ34,650 ኢንተርፕራይዞች (69,300 አንቀሳቃሾች) የመስሪያና መሸጫ ቦታ በማዘጋጀትና ጥቅም ላይ በማዋል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የተዘጋጀ መሬት ለሼድ ግንባታ፣ ለግብርና፣ ሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ወዘተ…) በድምሩ 28,557.86 ሄክታር ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙ በቦታ ከ100% በላይ ነው፡፡ እንዲሁም 22,916 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 113,012 ሴት 53,528 በድምሩ 166,540 አንቀሳቃሾች) በተዘጋጀው መሬት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በኢንተርፕራይዝ 66.43%፣በአንቀሳቃሽ ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡

## የውጭ አገር የሥራ ስምሪት

በ2015 ዓ.ም 26,000 ሥራ ፈላጊ ዜጎች በተደረገላቸው ድጋፍ አማካኝነት መብትና ደህንነታቸው ተጠብቆ በኤጀንሲዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 107 ሴት 5,077 ድምር 5184 ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የስደት ተመላሽ ዜጎችን መልሶ ማቋቋም

በበጀት አመቱ 12,800 ከስደት ከተመለሱ ዜጎች መካከል ከስደት ለሚመለሱ ዜጎች የተለያዩ ድጋፎችንና ማቋቋሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በማጠናከር እና በማመቻቸት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በዘላቂነት እንዲቋቋሙ ለማድረግ

100% ተመላሾችን ለማቋቋም በተያዘው እቅድ መሠረት ወንድ 3,972 ሴት 3,009 ድምር 6,981 የማቋቋሚያ ድጋፍ የተመቻቸላቸው ሲሆን አፈፃፀም 54.53% ነው፡፡

## የአገር ውስጥ የገበያ ትስስር

በ2015 ዓ.ም በከተማና በገጠር በሀገር ውስጥ ገበያ በዕድገት ተኮር ዘርፎች ለ43,024 ኢንተርፕራይዞች (ለ129,072 አንቀሳቃሾች) ብር 3,226,800,000 ለማስተሳሰር ታቅዶ በከተማ 32,414፣ በገጠር 7,347 ድምር 39,716 ኢንተርፕራይዞችን፣ (በከተማ 103,809 በገጠር 46,713 በድምሩ ለ150,522 አንቀሳቃሾችን)፣ በብር 6,764,415,546 የገበያ ትስስር መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ በኢንተርፕራይዝ 92.41%፣በአንቀሳቃሽ እና በብር ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

## የውጭ ሀገር ገበያ

በበጀት አመቱ በኤክስፖርት ስታንዳርድ የማምረትና ወደ ውጭ ሀገር ኤክስፖርት ለማድረግ አቅምና ፍላጐት ያላቸውን 73 ነባር እና 47 አዲስ በድምሩ 120 ኢንተርፕራይዞችን (360 አንቀሳቃሾችን) 1,059,000 ዶላር የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ነባር 89፣ አዲስ 24 በድምሩ 113 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 984 ሴት 258 በድምሩ 1,242 አንቀሳቃሾች) ከምርት ሽያጭ 1,193,821 ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈፃጸሙ በኢንተርፕራይዝ 94.16%፣ በአንቀሳቃሽ፣ በብር ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡

## የሥራ ሥምሪት ቁጥጥር አገልግሎትን መስጠት

በ2015 በጀት ዓመት ለ45 ጥያቄ ላቀረቡና መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ  የአገር ውስጥ ኤጀንሲዎች አዲስ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፤ ለ35 ኤጀንሲዎች ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙም 77.7% ማድረስ ተችሏል፡፡በስራ ላይ ላሉ 125  የአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ኤጀንሲዎች እድሳት ለመስጠት ታቅዶ፣ ለ111 ኤጀንሲዎች ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙ 81% ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ155 ኤጀንሲዎች ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ143(92.2%) ኤጀንሲዎች ቁጥጥር ተደርጓል፡፡

## ቁጠባ

በበጀት አመቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ችግር ለመፍታት እንዲያመችና የቁጠባ ባህል እንዲጐለብት ለማድረግ በተሰራው ስራ ብር 2,813,719,845 ቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ ከ239,792 ቆጣቢዎች ብር 4,060,610,074 ቁጠባ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ በብር ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## ብድር ስርጭት

በበጀት አመቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር ለመፍታት በመደበኛ ብድር ብር 1,959,648,629፣በተዘዋዋሪ ብድር ብር 1,557,501,177 በድምሩ ብር 3,517,149,806፣በመደበኛ ለ26,129፣በተዘዋዋሪ ለ10,383 በድምሩ ለ36,512 ኢንተርፕራይዞች (መደበኛ 78,387፣ ተዘዋዋሪ 20,767 በድምሩ ለ99,154 አንቀሳቃሾች) ብድር ለመስጠት ታቅዶ፣መደበኛ ብድር ለ36,755 ኢንተርፕራይዞች (82,559 (ወንድ 49,030 ሴት 33,529) አንቀሳቃሾች) ብር 2,800,140,961 ተሰራጭቷል፡፡አፈፃፀም በኢንተርፕራይዝ 140.66%፣ በአንቀሳቃሽ 105.32%፣በብር 142.88% ይሸፍናል፡፡ተዘዋዋሪ ብድር ለ7,087 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 6,505 ሴት 3,792 ድምር 10,297) አንቀሳቃሾች ብር 1,241,486,180 ተሰራጭቷል፡፡አፈፃፀም በኢንተርፕራይዝ 68.25%፣ በአንቀሳቃሽ 49.58%፣ በብር 79.71% ሆኗል፡፡በአጠቃላይ ለ43,842 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 55,535 ሴት 37,321 ድምር 92,856 አንቀሳቃሾች) ብር 4,041,627,141 የተሰጠ ሲሆን፣ አፈፃፀም በኢንተርፕራይዝ 104.48%፣ በአንቀሳቃሽ 93.64%፣ በብር 114.9% ማከናወን ተችሏል፡፡

## የቦታ አቅርቦት በተመለከተ

በበጀት ዓመቱ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በከተማና በገጠር 5,418 ሄክታር ቦታ ለ34,650 ኢንተርፕራይዞች (69,300 አንቀሳቃሾች) የመስሪያና መሸጫ ቦታ በማዘጋጀትና ጥቅም ላይ በማዋል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ፣ የተዘጋጀ መሬት ለሼድ ግንባታ 592.15 ሄክታር፣ ለግብርና 25,044.88 ሄክታር፣ ሌሎች (አሸዋ፣ ድንጋይ፣ የወንዝ ጠጠር፣ ወዘተ…) 2,920.83 ሄክታር በድምሩ 28,557.86 ሄክታር ቦታ የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙ በቦታ ከ100% በላይ ነው፡፡ እንዲሁም 22,916 ኢንተርፕራይዞች (ወንድ 113,012 ሴት 53,528 በድምሩ 166,540 አንቀሳቃሾች) በተዘጋጀው መሬት ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በኢንተርፕራይዝ 66.43%፣ በአንቀሳቃሽ ከ100% በላይ ተከናውኗል፡፡

## የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ሥራዎች

በበጀት አመቱ የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና በመንግስትና በግል ኮሌጆች 91,566 (ወንድ 34,529 ሴት 57,037) ሰልጣኞችን መቀበል የተቻለ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ስልጠናቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ አፈፃፀሙም 69.51% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ 926,309 (በከተማ 445,285፣ በገጠር 481,024) ሰልጣኞች የኢንተርፕሪነርሺፕ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአጠቃላይ በከተማና በገጠር ወንድ 554,496 ሴት 398,945 በድምሩ ለ953,441 ሥራ ፈላጊ ዜጐች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙ 102.92% ነው፡፡በተመሳሳይ የቴክኒካል ክህሎት ስልጠና በተመለከተ 455,318 (በከተማ 202,324 በገጠር 252,994) ለመስጠት ታቅዶ በአጠቃላይ በከተማና በገጠር ወንድ 311,026 ሴት 224,785 በድምሩ 535,811 ዜጎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙ 117.67% ነው፡፡ የቴክኒካል አጫጭር ስልጠና ከወሰዱት 25% (133,953) በምዘና ማሳለፍ በሚል ታቅዶ የተመዘኑት በከተማና በገጠር 95,451 (ወንድ 32,473 ሴት 62,978) ሲሆኑ አፈፃፀሙ 71.25% ነው፡፡ ስልጠና ከወሰዱት ውስጥም በከተማና በገጠር 653,057(ወንድ 410,148 ሴት 242,909) ከስራ ጋር ተሳስረዋል፡፡

# ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

የአማራ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የክልሉን ግብርና ልማት ምርታማነት ለማሳደግና ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ አስተዋጽኦ ለማድረግና ችግር ፈቺ እና ፍላጎት ተኮር የግብርና ቴክኖሎጂዎችን እና ምክረ-ሃሳቦች ማፍለቅ/ማላመድ/ የመነሻ ዘር/ቴክኖሎጂ ብዜት/፣ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ፣የክልሉን የግብርና ምርምር ስራዎችን ማስተባበር እና የግብርና ልማትን ለማሳደግና ለማፋጠን የሚያግዙ የፖሊሲ እና ስትራቴጂ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ የመሳሰሉ ዋና ዋና ተልዕኮዎችን ያከናውናል፡፡ በዚህም መሰረት ኢንስቲትዩቱ በ2015 በጀት ዓመት በሁሉም ዘርፎች 88.44 በመቶ አፈፃፀም አስመዝግቧል፡፡

## ሰብል ምርምር

በበጀት ዓመቱ ከታቀዱት 311 (270 በመኸር፣ 41 በመስኖ) የምርምር ስራዎች 307 (266 በመኸር፣ 41 በመስኖ) ሙከራዎች በታሰበላቸው ደረጃ ተከናውነዋል፡፡አፈፃፀሙ 98.7% ነው። እንደየሰብሉና የምርምር ስራው አይነት አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ክትትልና ግምገማ ተከናውኗል፡፡ በበጀት አመቱ በአጠቃላይ 43 ቴክኖሎጂዎችን ለማውጣት ታቅዶ 39 (90.70%) ማውጣት ተችሏል።

## እንስሳት ምርምር

ምርምሩ ዋና ዋና የእንስሳት እርባታ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያግዙ የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ስራዎቹም በዋናነት በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ ልማት፣ በእንስሳት ጤና፣ ስነ-አመጋገብን ማሻሻል እና የእንስሳት አያያዝ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እነዚህም የምርምር ስራዎች በዳልጋ ከብት፣ በበግና ፍየል፣ በዶሮ፣ በንብና በዓሳ ላይ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ የእንስሳት ምርምር ዘርፉ ለልማቱ አጋዥና ለዘርፉ እድገት ቁልፍ ችግሮች ላይ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ጥራት ያላቸውን ቴክኖሎጂዎችንና ምክረ ሃሳቦችን በብቃት ማቅረብ እንዳለበት በመታመኑ በበጀት ዓመቱ 85.71 ፐርሰንት ቴክኖሎጂዎች ወይም ምክረ ሃሳቦችን ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

## አፈርና ውኃ ምርምር

ምርምሩ በተለያዩ ስነ-ምሕዳሮች 64 የምርምር ሥራዎችን በማካሄድ ሁሉንም ያከናወነ ሲሆን በአፈር ለምነት ምርምር 12፣በግብርና ውሃ አያያዝ ምርምር 6 እና በአፈርና ውሃ ጥበቃ ምርምር 2 በድምሩ 20 ቴክኖሎጂዎችን/ምክረ ሃሳቦችን / ለማውጣት ታቅዶ በአፈር ለምነት 10 በግብርና ውሃ አያያዝ 4 እና በአፈርና ውሃ ጥበቃ 4 ቴክኖሎጂዎች በድምሩ 18 (90%) ቴክኖሎጂዎችን/ምክረ ሃሳቦችን / አውጥቷል፡፡

## ደን ምርምር

ምርምሩ በሰው ሰራሽ ደን ምርታማነትና አጠቃቀም ማሻሻል፣ በተፈጥሮ ደን አያያዝና አጠቃቀም፣ በአግሮፎሬስትሪ ልማትና አጠቃቀም፣ የተራቆቱ አካባቢዎችን ማገገምና መልሶ ማልማት፣ በቀርከሃ ልማት፣ እንጨት-ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች (ዕጣን፣ ሙጫ፣ ቁርቁራና ፍርጣጣ) ልማት፣ የአየር ንብረት ለውጥ ከመላመድና ከመቋቋም አንጻር እና በብዝሃ ሕይወት ጥበቃና ልማት ዙሪያ ያተኮሩ የምርምር ሥራዎችን አካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ 44 ሙከራዎችን ለማከናወን አቅዶ 42 የተከናወኑ ሲሆን አፈጻጸሙም 95.4% ነው፡፡

## በማህበራዊ ምጣኔ ሃብትና ግብርና ኤክስቴንሽን ምርምር

በበጀት አመቱ የማህበራዊ ምጣኔ ሃብት ጥናት የታቀዱት 16 (4 በሰብል፣ 7 በእንስሳት፣ 3 በአፈርና ውሃ 2 በሌሎች) ጥናቶች ሲሆኑ ሁሉም የተከናወኑ ጥናቶቹ ናቸው፡፡ ስራዎቹም 6 ነባር እና 10 ደግሞ አዲስ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል 7 ጥናቶች ተጠናቅቀዋል፡፡

## ዘር ምርምር

በዘር ጥራት ምርምር ከታቀዱት በጠቅላላው 7 የምርምር ሙከራዎች ውስጥ 4 ነባር እና 3 አዲስ ሙከራዎች ሁሉም ተከናውነዋል፡፡ የዘር ምርታማነትንና ጥራትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የአሰራር ስልቶችን በማጥናት የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ፣ ዘርን ሳይበላሽ ማቆየት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን መገምገም፣ የአርሶአደሮችን የሰሊጥ የዘር ምንጭ መፈተሽ እንዲሁም የላም ድንች ዘርን በክልሉ ደጋማ ቦታዎች ለማምረት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፈተሽ የመሰሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ የምርምር ስራዎች ውስጥ 2 የምርምር ስራዎች ታቅደው 3 የምርምር ስራዎች ተጠናቀዋል፡፡

## በ2015 ዓ.ም አዳዲስ ዝርያዎች ያስለቀቁ ተመራማሪዎች

| | የሰብል ዓይነት | የዝርያው ስም | ያስለቀቀው ማዕከል | ዝርያውን ያስለቀቁ ተመራማሪዎች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጤፍ | አጣዬ | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ አትንኩት ፈንታሁን |  |
| | ስንዴ | ሰከላ (AUS-90667) | አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ መሌ ጥላሁን |  |
| | ስንዴ | ሻሎም (ETBW9006) | ስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ አገኘሁ መኮንን | |
| | የምግብ ገብስ | ፈጠነች (GNT1808) | ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ ማስረሻ ጋሻው |  |
| | የምግብ ገብስ | ግሸን (Acc204669-1) | ስሪንቃ ግብርና ምርምር ማዕከል | አቶ አካሉ ገብሩ |  |

<table>
<tr><td></td><td>ዳጉሳ</td><td>አዴት-06</td><td>አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል</td><td>አቶ አቡኑ ማረፊያ በሬ</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>ሰሊጥ</td><td>ማርዘነብ<br>(Accession159)</td><td rowspan="2">ጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል</td><td rowspan="2">አቶ እንዳልካቸው አክሊሉ</td><td rowspan="2"></td></tr>
<tr><td></td><td>ጥጥ</td><td>ጃንተከል</td></tr>
<tr><td></td><td>ድንች</td><td>ወርቂ</td><td>አዴት ግብርና ምርምር ማዕከል</td><td>አቶ ማንአምኖ ወርቃየሁ</td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="3"></td><td rowspan="3">ድንች</td><td rowspan="3">ብርሃን</td><td rowspan="4">ደብረ ብርሃን ግብርና ምርምር ማዕከል</td><td>አቶ ዘሪሁን ከበደ</td><td></td></tr>
<tr><td>አቶ ጌታነህ ጌጡ</td><td></td></tr>
<tr><td rowspan="2">አቶ ናትናኤል ግርማ</td><td rowspan="2"></td></tr>
<tr><td></td><td>ድንች</td><td>ዳኘው</td></tr>
</table>

# ፕላንና ልማት

## የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማነት ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም የበጀት ማስተዳደሪያ የትኩረት ነጥብ ማዘጋጀትና ለቢሮዎችና ለወረዳዎች ማሰራጨት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተፈፅሟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጸደቀ በጀትን ለሚመለከታቸው ቢሮዎችና ወረዳዎች ለማሳወቅ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ የቢሮዎችን የመደበኛና የካፒታል በጀት ማሳወቂያ አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 61 ተቋማት መደበኛ በጀትና ለ33 ተቋማት ካፒታል በጀት ማሳወቂያ በማዘጋጀት ሙሉ በሙሉ የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

የ2015 ዓ.ም የወረዳዎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችና ብሔረሰብ አስተዳደሮችን በጀት ለማጠቃለል ታቅዶ የ223 አስተዳደር እርከኖች በጀት ሙሉ በሙሉ በማጠቃለል የእቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የክልሉ የበጀት ድልድል ድርሻ ሲታይ ክልል ቢሮዎች ደመወዝ 38.91 በመቶ፤ ስራ ማስኬጃ 23.5 በመቶ፤ካፒታል በጀት 37.59 በመቶ ድርሻ ሲይዙ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ደመወዝ 75.94 በመቶ፤ ስራ ማስኬጃ 13.33 በመቶ፤ካፒታል 10.74 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡የድህነት ተኮር ሴክተሮች ድርሻ ከ60% በላይ ለማድረስ ታቅዶ 59.31% ብቻ ድረሻ ይዟል፡፡ይህም አስተዳደር ዘርፍ ላይ የሚወጡ አስገዳጅ ወጪዎች እያደጉ መምጣታቸው እንደ ክልል ተቋማት የሚታዩ በጥቅል የሚያዝ በጀት እያደገ መምጣት ለመቀነሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## በህትመት የበጀት መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ

የ2015 ዓ.ም የክልሉን የተጠቃለለ በጀት የሚያሳይ መጽሐፍ በማዘጋጀት በሃርድና በሶፍት ኮፒ ለሚመለከተው ማድረስ ተችሏል፡፡የ2015 ዓ.ም የክልሉን ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ለማዘጋጀት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ መፈፀም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የጸደቀ በጀት በልዩ ልዩ መንገዶች ለህዝብ ይፋ ለማድረግ ታቅዶ 96 ፐርሰንት ወረዳዎች በማስተዋቂያ፣ በባነር፣ በበራሪ ወረቀት፣ በማህበራዊ ሚዲያ እና በአካባቢ ሬዲዮ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የ2016 ዓ.ም በጀት ዝግጅት

የ2016 ዓ.ም በጀት ለማዘጋጀት የበጀት የጊዜ ሰሌዳውን ተከትሎ ለክልል ቢሮዎች፣ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የበጀት ጥሪ የማስተላለፍ፣የ2016 ዓ.ም በጀት ጥያቄ ከክልል ቢሮዎች የመቀበል እንዲሁም የበጀት ሰሚ ማካሄድ ስራዎች ታቅደው ሶስቱም ተግባራት በዕቅዱ መሰረት መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዚህም በጀት የማዘጋጀት እና ከክልል ባለ በጀት መስሪያ ቤቶች ጋር በቀረበው ጥያቄ ላይ እየተማመኑ በመሄድ መደበኛና ካፒታል በጀት ስራዎችን ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡

## የጸደቀ በጀት

ለበጀት አመቱ ለክልሉ የጸደቀው በጀት በተያዘለት የጊዜ ገደብና ለተያዘለት ዓለማ በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል የመከታተል፣ከተደለደለ በኋላ በስራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን የመፍታት፣የተጨማሪ የበጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የውሳኔ አስተያየት የማቅረብ፣በበጀት ዓመቱ መካከል ላይ የሚገኙ ተጨማሪ ገቢዎች ካሉ በተጫማሪ በጀትነት የማሳዎጅ ፣ በብድር የተሰጡ በጀቶችን ማስመለስ፣ የ2014 በጀት ዓመት በጀት መዝጋትን መቶ በመቶ ማጠቃለል፣ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ በጀት ነክ ጥያቄዎችን ምላሽ መስጠት ተግባራትን ለማከናወን ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡በዚህ መሰረት ከተለያዩ አካላት የቀረበውን የብር 12.37 ቢሊየን ተጨማሪ በጀት ጥያቄ ቀርቦ የውሳኔ አስተያየት በማቅረብ እንዲገመገም የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በልማት ድርጅቶች ለሚካሄዱና በተለያየ ችግር ሳይከፈሉ ለቆዩ ፕሮጄክቶች ብር 451,926,985.54 ጨምሮ በድምሩ ብር 5.29 ቢሊየን የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው መልሶ የተመደበ 1 ቢሊየን ብር ለሚመለከታቸው ተቋማት የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል ፡፡

ውሳኔ ያረፈባቸውን ተጨማሪ በጀቶች የበጀት ዝውውር ቅጽ አዘጋጅቶ ማሰራጨትና በአይቤክስ ስርዓቱ ለመመዝገብ ታቅዶ እቅዱን 1558 የበጀት ዝውውር በማዘዋወር 100% ማሳካት ተችሏል፡፡በቢሮውና በጣምራ የተፈጸሙ የበጀት ዝውውሮችን በወቅቱ በመመዝገብ በጀቱን ማስተካከል፣የተፈጸሙ ዝውውሮች ሙሉ በሙሉ ወደ አይቤክሱ እንዲመዘገቡ በማድረግ የተስተካከለ በጀትን ወቅታዊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ብድር የወሰዱ ወረዳዎችን ተከታትሎ የወሰዱትን ብድር ማስመለስ ስራ በዕቅድ ተይዞ ከ2015 በጀት ዓመት ታሳቢ ብድር የወሰዱ 62 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ብር 256,965,429 የበጀት ዝውውር በማዘጋጀት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ብድር ለሚጠይቁ 20 ወረዳዎች ብድር ለመስጠት ታቅዶ ከ97 ወረዳዎች የብድር ጥያቄ ቀርቦ ከፍተኛ ችግር ያለባቸውንና ሌሎች በተለያየ ምክንያት

የተቀነሰባቸው ገንዘብ እንዲመለስ በማድረግ ለ56 ወረዳዎች ብር 327,314,122 ብድር መስጠት ተችሏል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የተስተካከለ በጀት እስከ ህዳር 30/2015 ለመዝጋት ታቀዶ እስከ ህዳር 30/2015 በጀቱን ሙሉ በሙሉ ማጠቃለል ተችሏል፡፡በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ የጸደቀ በጀት ብር 80,104,669,397፤በተጨማሪነት የታወጀ በጀት ብር 907,186,813.00 እንዲሁም የተስተካከለ በጀት ብር 81,011,856,209.00 ሲሆን እስከተስተካከለ በጀት ያለውን በጣሪያ በመግጠም የማጠቃለል ስራ ተሰርቷል፡፡በበጀት አዘጋግ ወቅት የታዩ ችግሮች ወጪዎች በወቅቱ አለመመዝገብ፣ ዓመቱን ሙሉ ወጪ ያልተመዘገበላቸው ተቋማት መኖር፣ ከበጀት በላይ ወጪ ተፈጽሞ መገኘት፣ ስራ ላይ ያልዋለ ሰፊ በጀት መገኘት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

## የበጀት አጠቃቀም ማሻሻል

የበጀት አጠቃቀም ለማሻሻል ለአስፈጻሚ መስሪያቤቶች ግብረ መልስ በመስጠት፣ተራፊ በጀቶችን በማንሳት ስራ ላይ እንዲውል እንደገና በመደልደል፣ አፈጻጸሙ በየደረጃው እየተገመገመ የመስተካከያ ርምጃ እንዲወሰድ በመስራት 2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም ከ2013 ዓ.ም ለማሻሻል ቢታቀድም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የ2014 ዓ.ም ጥቅል የበጀት አፈጻጸም 91.56% ሆኗል፡፡ ይህም በ2013 ዓ.ም ከነበረው 94.6 በመቶ በ3.02 በመቶ ቀንሷል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በጦርነቱ ምክንያት የታቀደው የገቢ ዕቅድ መሰብሰብ ባለመቻል ነው፡፡

## የ2015 ዓ.ም በጀት አጠቃቀም

የ2015 ዓ.ም የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ ወደ አይቤክስ በገባው የወጪ ሪፖርት መሰረት ለደመወዝ 91.58 በመቶ፣ለስራ ማስኬጃ 67.34 በመቶ፣ለካፒታል 20.99 በመቶ በጠቅላላ 57.69 በመቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡ይህም አፈጻጸም በተለይም የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም አሁን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ችግሮች ተለይተው አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል፡፡በአጠቃላይ የበጀት አጠቃቀሙ ሲታይ የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በጥሩ ደረጃ ቢገኝም የካፒታል በጀት አጠቃቀም ዝቅተኛ ነው፡፡ እንደ ክልል በ2014 ዓ.ም ከነበረው አጠቃቀም 91.56 በመቶ በ2015 ዓ.ም ወደ 80 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በቀጣይ ወጪዎች ተጠቃለው ሲገቡ አፈጻጸሙ ሊለወጥ እንደሚችል ቢታሰብም የበጀት እጥረት ባለበት ክልል ያለውን ውስን ሃብት በበጀትም ወቅት ስራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ ችግር ስለሆነ በተለይ

አስፈጻሚ መስሪያቤቶች በተገቢው በጀታቸውን ስራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡ስራ ላይ የማይውል በጀት ሲኖር ደግሞ ተራፊ በጀቱን ለይተው እንዲመልሱ አስገዳጅ አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

## ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል

የ2015 በጀት ዓመት የከተሞች ልዩ ድጐማ  በጀትን በቀመር መደልደል እንዲሁም አፀድቆ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ 203 ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ለ2015 በጀት ዓመት ለከተሞች ልማት ፈንድ ልዩ ድጐማ ብር 1,200,000,000 የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በማከፋፈያ ቀመሩ መሰረት ብር 912,000,000 ለነባር 47 ከተማ አስተዳደሮች፤ብር 126,000,000 ለ126 መሪ ማዘጋጃቤት ከተሞች ለእያንዳንዳቸው ብር 1,000,000፤ብር 30,000,000 ወደ ሪጂዮፖሊታን ለተሸጋገሩ ሁለት ከተማ አስተዳደሮች (ደብረታቦር እና ወልድያ) መቋቋሚያ ለእያንዳንዳቸው ብር 15,000,000፣ ብር 120,000,000 በ2014 በጀት አመት ሥራ ለጀመሩ 30 ከተማ አስተዳደሮች ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000,000 እና ብር 12,000,000 ለደብረብርሃን፣ደብረማርቆስ እና ኮምቦልቻ ከተሞች በክፍለ ከተሞች ለሚያካሂዱት የቢሮ ግንባታ እና ቋሚ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ግዥ ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000,000 የተመደበ ሲሆን የበጀት ድልድሉ ለሚመለከታቸው 77 ከተማ አስተዳደሮች እና 126 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከ77 ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ለ76 (ከሃይቅ ከተማ አስተዳደር በስተቀር) በጀቱን ስራ ላይ ስለማዋል የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላታቸው የወጪ መርጃ መላክ ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ለ2016 ዓ.ም ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ለመስራት የሚያግዙ መረጃዎችን በናሙና ከተመረጡ ነባር 96 ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ብሔረሰብ አስተዳደሮች የ2014 እና 2015 በጀት ዓመት የሴክተሮችን አደረጃጀት ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ76 ወረዳዎች በመሰብሰብ የእቅዱን 79.16% ተፈፀሟል፡፡ እንዲሁም ከ2014 ዓ.ም በኋላ አዲስ የተቋቋሙ ከተማ አስተዳደሮች፣ ከዙሪያ ወረዳ ወደ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ሽግሽግ ያደረጉ 42 የገጠር ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች በ2015 ዓ.ም ያሉበትን አደረጃጀት ታሳቢ ያደረገ በክልሉ ከሚገኙት 220 ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች መረጃ ለማሰባሰብ ታቅዶ የ220 ወረዳዎችንና ከተማ አስተዳደሮችን መረጃ በማሰባሰብ የእቅዱን 100% ማሳካት ተችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ2014 ዓ.ም ብር 106,758,635 ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ሲሆን ከእቅድ በላይ ከተሰበሰበው መደበኛ ገቢ ውስጥ ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳሮች 50 ፐርሰንት ወይም ብር 53,379,318 መጠቀም እንዲችሉ ተደርጓል፡፡እንዲሁም የ2016 በጀት ማዘጋጀትን በተመለከተ የበጀት የጊዜ ሰሌዳውን ተከትሎ የበጀት ጥሪ ለማካሄድ ታቅዶ ለክልል ቢሮዎች፣ ወረዳዎችና

ከተማ አስተዳደሮች የበጀት ጥሪ የማስተላለፍ ስራ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡የ2016 በጀት ጥያቄንም ከክልል ቢሮዎች ለመቀበል ታቅዶ ከ61 ቢሮዎች 55 ቢሮዎች የበጀት ጥያቄ የመቀበል ስራ ተሰርቷል፡፡በዚህ ዘርፍ እስካሁን ጥያቄ ያላቀረቡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጤና ቢሮ፣ ማዕድን ቢሮ፣ፖሊስ ኮሚሽን፣ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፣ባህልና ቱሪዝም ቢሮና ወልድያ ሆስፒታሎች ናቸው፡፡

## ጠንካራ የሀብት አስተዳደርና የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት

ለክልል ልማት ማስፈፀሚያ የሚሆን ከፌደራል ከተመደበ ብር 44.38 ቢሊየን በጀት ድርሻ ሲሆን ከዚህ ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ብር 44.38 ቢሊየን ወይም 100% ተልዕኮ በIBEX የምዝገባ ስራው ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ከፌደራል የተላከውንና ከክልሉ የተሰበሰበውን ገቢ ጨምሮ ለክልል ቢሮዎች መደበኛ በጀት ብር 7.34 ቢሊየን ካፒታል በጀት ብር 6.02ቢሊየን በድምሩ ብር 13.36 ቢሊየን ሙሉ በሙሉ በክፍያ ጣሪያና በዝውውር ተላልፏል፡፡ ለዞኖች ደግሞ ብር 6.03 ቢሊየን እንዲሁም ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተመደበላቸው በጀት ውስጥ ብር 40.21 ቢሊየን ጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በ12 ወራት ከመንግስት ግምጃ ቤት ይተላለፋል ተብሎ የተያዘውን ብር 59.60 ቢሊዮን ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ይህም የክልሉን ልማት በተቀመጠለት መርሃ ግብር መሰረት ለማከናወን የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ከዚህ በተጨማሪም በበጀት አመቱ ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ከፌደራል መንግስት ከተመደበው ብር 3.02 ቢሊየን ውስጥ በ12 ወራት ብር 3.02 ቢሊየን ወይም 100% ገንዘብ ገቢ የተደረገ ሲሆን ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽ የተላለፈው ብር 1.53 ቢሊየን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 1.296 ቢሊየን እና ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ የተላለፈው ብር 2.14 ቢሊዮን ቢሆንም ብር 410.86 ሚሊየን ከ2014 በጀት ዓመት የዞረ ስለሆነ ለ2015 ዓ.ም ከተመደበው ላይ ብር 1.728 በተጠየቀውና በታዘዘው መሰረት የመጣው ገንዘብ በሙሉ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

## የመንግስት ግምጃ ቤት የመደበኛ እና ካፒታል በጀት መመዝገብ

በ2015 ዓ.ም ከመንግስት ግምጃ ቤት ከተመደበው በጀት የወጪ አፈፃፀም ሲታይ በ2015 በጀት ዓመት እስከ የሰኔ 30 ድረስ የወጪ ሂሳብ የመደበኛ በጀት ድምር ብር 60.70 ቢሊዮን፣ የካፒታል በጀት ብር 11.23 ቢሊየን ጠቅላላ ድምር ብር 71.99 ቢሊዮን በIBEX የመመዝገብ ስራ ተሰርቷል፡፡አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ሁሉም ቢሮዎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ወቅታዊ የሂሳብ ምዝገባ በIBEX አጠቃለው ባለመመዝገባቸው እንዲሁም የመደበኛም ሆነ በካፒታል በጀት የሚሰሩ ስራዎች በውሉ መሰረት ቅድሚያ ክፍያ የሚፈጸም

ሲሆን ይህ የተከፈለ ገንዘብ ስራው፤አገልግሎቱ፤ ዕቃው/ንብረቱ/ ካልተጠናቀቀ ወይም ገቢ እስካልሆነ ድረስ በመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ የሚቆይ በመሆኑ በወጪ ባለመመዝገቡ ነው፡፡

በ2015 ዓ.ም የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በIBEX ምዝገባ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 25,718,088,986.84 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 17,219,689,531.75 ያሳያል፡፡የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብን መረጃ አጥርቶ በመያዝና የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በማጠናከር ሂሳቡን የማወራረድ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡በመሆኑም ከ3-10 ዓመት ድረስ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,449,456,754 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 1,092,994,563 ያለ ሲሆን 30% ለማወራረድ በተያዘው እቅድ መሰረት በቢሮ ደረጃ በ12 ወራት ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 734.84 ሚሊየን ላይ ብር 642 ሚሊየን /87%/ እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 327.9 ሚሊየን ላይ ብር 866 ሚሊየን /264%/ ማወራረድ ተችሏል፡፡ ለዚህም ውጤት መገኘት ሪፖርት በማያደርጉ ተቋማት ላይ የገንዘብ ዝውውር እንዳይተላለፍላቸው ከማድረግ በተጨማሪ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተወሰነ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡

## በሌሎች የበጀት ምንጮች(ቻናሎች) የሚመጣን ሀብት ማስተዳደር

በ2015 ዓ.ም በቻናል አንድ የመጣውን ብር 14 ቢሊየን ቀልጣፋ የክፍያ አገልግሎትና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር በማስፈን በፕሮግራሙ የሚገኝ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ለማድረግ በተሰራው ስራ በቻናል አንድ ውስጥ 10 ፕሮግራሞች ያሉ ሲሆን እስከ 12ኛው ወር ድረስ ብር 13.63 ቢሊየን (ከአለፈው ዓመትና በበጀት ዓመቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ከተለቀቀው የተገኘ ሲሆን) ብር 10.6 ቢሊየን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም የወጪ አፈፃፀም ከአመታዊ በጀት አንፃር 73% ሲሆን ወደ ክልሉ ከገባው ገንዘብ አንፃር ሲታይ 77% መሆኑን ያሳያል፡፡

## የመንግስታትና የበየነ መንግስታት በጀት አፈጻፀም

በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የመንግስታትና በየነ መንገስትታት ፕሮጀክቶች ሀብት ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም እንዲኖር በተሰራው ስራ ባለፉት 12 ወራት በUN ኤጀንሲዎች የገንዘብ ድጋፍ ለሚከናወኑ ተግባራት ከ2014 ዓ.ም የዞረ ብር 246,366,895.86 እንዲሁም በዚህ አመት የተመደበና ተጠይቆ ወደ ክልሉ የመጣ ብር 945,742,493.22 ሚሊየን በድምሩ ብር

1,192,109,389.08 ሲሆን ብር 161,786,022.08 ስራ ላይ በማዋል የእቅዱን 70% መፈፀም ተችሏል፡፡

## የበጎ-አድራጎት እና ማህበራት ድርጅቶች የበጀት አጠቃቀም

በ2015 ዓ.ም 250 አዳዲስ ፕሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 4.5 ቢሊየን ብር ለማግኘት ታቅዶ እስከ ሰኔ ወር 2015 ዓ.ም መጨረሻ 271 (ከ108.4 %) አዳዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈራረም ብር 8.9 ቢሊየን (198%) ማግኘት ተችሏል፡፡አዲስ በተፈረሙት ፕሮጀክቶች 10 ሚሊየን ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ 17.89 ሚሊየን ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የመንግስት ንብረት ግዥና አወጋገድ

የተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ግዥ ለማከናወን በተሰራው ስራ በክልሉ ለሚገኙ መስሪያቤቶች አገልግሎት የሚውሉ 77 ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ የ80 ተሽከርካሪዎች ግዥ ተፈፅሟል፡፡በተመሳሳይ በቁጥር 73 ማሽነሪዎች ለመግዛት ታቅዶ 35 ግዥ ተከናውኗል፡፡ከዚህ በተጨማሪም 74 የተለያዩ ሞተር ሳይክል ለመግዛት ታቅዶ 67 ሞተር ሳይክሎች ግዥ ተፈጽሞ ገቢ ሁነዋል፡፡እንዲሁም ለአንዳሳ ግብርና ምርምር 1 አውቶቡስና ለባህርዳር ከተማ አስተዳደር 2 አውቶቡሶችን ለመግዛት ታቅዶ የ3ቱም አውቶቡሶች ግዥ ተፈፅሞ ለህዝብ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

## የእቅድና ልማት

በበጀት አመቱ የተከለሰውን ክልላዊ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ በማስተቸት በክልሉ ካቢኔ ቀርቦ ጸድቋል፡፡ አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡ከ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ተናባቢና ዕቅዱን ወደ ተግባር ሊያስገባ የሚችል የክትትልና ግምገማ መሣሪያ ተደርጎ የሚታየውን የፖሊሲ ማትሪክስ ማዘጋጀትም አንዱ በዕቅድ የተያዘ ተግባር ሲሆን በታቀደው መሠረት ዶክመንቱ ተዘጋጅቷል፡፡በየደረጃው ላሉ 250 የሴክተር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ለዞን ፕላን ቡድን መሪዎች እንዲሁም ለቢሮው ሠራተኞች በተከለሰው የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ዙሪያ ኦሬንቴሽን ለመስጠት ታቅዶ ሴት 65 ወንድ 98 በድምሩ 163 አካላት በመስጠት የዕቅዱን 65.2% መፈጸም ተችሏል፡፡እንዲሁም የ2015 ዓ.ም አንድ ክልላዊ የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ክንውን 1 አፈፃፀም 100 % ሆኗል፡፡ክልላዊ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት መመሪያ ለማውጣት በዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን በዚህ መሠረት መመሪያው ተዘጋጅቶ በቢሮው የበላይ አካላት በተሰጠው አስተያየት መሠረት ተስተካክሎ ሙያዊ

አስተያየት እንዲሰጥበት ለፍትህ ቢሮ ተልኮ የመጨረሻ ቅርጽ ይዞና ተጠናቆ ለፐላንና ልማት ተልኳል፡፡አፈፃፀሙም 100% ሆኗል፡፡

በ2015 ዓ.ም ዞኖች፣ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸውን ዕቅድ እንዲያዘጋጁ መነሻ ዕቅዶችን የመላክ እንዲሁም በስልክም ሆነ በአካል መጥተው ለሚጠይቁት ቴክኒካዊ ድጋፍ ምላሽ የመስጠት ሥራ ተሠርቷል፡፡ለአብነት ያህልም ከሁመራ ከተማ፣ ደሴ ከተማ፣ ኮምቦልቻ ከተማ፣ሞጣ ከተማ፣ዓምደ ወርቅ ከተማ የመጡ የሴክተር ባለሙያዎች ቡድን በጀታቸውን ችለው መጥተው በአጠቃላይ ስለ ዕቅድና በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የአውስትራሊያ መንግስት በሄልቬታስ ኢትዮጵያ በኩል የገንዘብ ድጋፍ በማድረጉ ምክንያት ለ3 ዓመታት የሚቆይ የማህበረሰብ አሳታፊ ዕቅድ በአዳዲስ ተጨማሪ 3 ዞኖች እና 16 ወረዳዎች ስራው እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡በአንደኛው ዙር ከ2 ዞኖችና ከ10 ወረዳዎች ለመጡ 44 ሠልጣኞች የአሠልጣኞች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በ2ኛው ዙርም ተመሳሳይ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት በመደረግ ላይ ነው፡፡የተቀናጀ ማህበረሰብ አቀፍ አሳታፊ ዕቅድን በ16 ተጨማሪ ወረዳዎች ለማስፋት ዕቅድ ተይዞ 100 % መፈጸም ተችሏል፡፡

## የበጀት አጭር መግለጫ

በበጀት አመቱ ህጻናት ተኮር በሆኑ በሶስት ሴክተር መስሪያቤቶች የተጀመረውን የህጻናት አጭር የበጀት መግለጫ ሰነድ ወደ አስር ሴክተር መስሪያቤት በማሳደግ በየዓመቱ ማሻሻያ የሚደረግ ሲሆን የስድስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ማለትም የትምህርት፣ የጤና፣የውሃና ኢነርጅ፣ግብርና፣ሴቶች ህጻናት፣ወጣቶች እንዲሁም የአሰሪና ሰራተኛ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች የ2014 በጀት ዓመት መረጃዎችን በማካተት ከ2008 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ማድረግ ተችሏል፡፡ወደ አማርኛ የመተርጎም ሥራ በመስራት ላይ ነው፡፡ የህፃናትን የመከላከል ስራ የሚሰሩ ሴክተሮችን ማለትም የሰላምና ደህንነት፣የፍትህ፣የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የወሳኝ ኩነቶች አገልግሎት ከ2008 - 2014 በጀት አመት ያለው አጭር የበጀት መግለጫ ሰነድ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ ለዩኒሴፍ ተልኳል፡፡በተመሳሳይ በክልል ደረጃ የአንድ አመት አጭር የማክሮ ኢኮኖሚ ትንተና ዶክመንት በማዘጋጀት ለሚመለከተው ተልኳል፡፡በሌላ በኩል ተቋማት የሚልኳቸው ዕቅዶች የሴቶችንና የወጣቶችን፤የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ያካተተ መሆኑን እና መረጃው በፆታ የተከፋፈለ መሆኑን እያንዳንዱን ሰነድ በመፈተሽ የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ ተቋማት የሚልኳቸው ሪፖርቶችና

መረጃዎች የዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ዕቅድ 27 ክንውን 27 አፈጻጸም 100% እንዲሁም ሴቶች እና ወጣቶች በስልጠናና ስራ እድል ፈጠራ 30% ተጠቃሚ ማድረጋቸውን መከታተል ዕቅድ 27 ክንውን 27 አፈጻጸም 100% ነው፡፡

## ክትትልና ግምገማ

በ2015 ዓ.ም አራት ጊዜ ክልላዊ የእቅድ አፈጻጸም የክትትልና ድጋፍ መርሃ ግብር ለማከናወን ታቅዶ በሁለት ዙር በሁለት ቡድን የተዋቀረ የባለሙያዎች ቡድን በማዘጋጀት በአስራ አንድ ዞኖች 23 ወረዳዎችና 6 ከተማ አስተዳደሮች የመስክ ድጋፍና ግምገማ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 50% ሲሆን የመስክ ስራውን ለመስራት የተቋማቱን ዕቅድ አፈፃፀም በዋና ዋና መለኪያዎች ተመስርቶ ቸክሊስት ተዘጋጅቶ  የመስክና የዴስክ ክትትልና ግምገማ በሰባት ሴክተሮች የተካሄደ ሲሆን በየሴክተሮቹ የታዩ አበረታች አፈጻጸሞችን፣ ጉድለት የታየባቸውንና በሂደቱ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት በየደረጃው እውቅና ተፈጥሮባቸው መፍትሄ እንዲሰጣቸው ከወረዳና ዞን አመራሮች ጋር በአካል በመገናኘት ግኝቶችን በማሳወቅና በፅሁፍ የተዘጋጁ ግብረ መልሶችን በየደረጃው እንዲደርሱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡በሌላ በኩል በየደረጃው የሚመጡ ሪፖርቶችን በመገምገም ለክትትል፣ድጋፍና ግምገማ ተግባራት በግብዓትነት መጠቀም ዕቅድ 3 ክንውን 3 አፈጻጸም 100% ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ 27 ተቋማት የሚልኳቸው ሪፖርቶችና መረጃዎች የዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያካተቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ታስቦ 100% የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከ27ቱ ተቋማት ሴቶች እና ወጣቶች በስልጠናና ስራ እድል ፈጠራ 30% ተጠቃሚ ማድረጋቸውን ለመከታተል ዕቅድ ተይዞ አፈጻጸም 100% በማረጋገጥ ለየተቋማቱ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

## የልማት ፕሮጀክቶች እቅድ ዝግጅት

በበጀት አመቱ የልማት ፕሮጀክቶች እቅድን ለማዘጋጀት የሚያግዙ የተደራጁ መረጃዎችን ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ተሰርቷል፡፡በክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች በፕሮጀክቶች ዕቅድ ዝግጅት ላይ የሚታዩ  ችግሮችን መለየት ዕቅድ1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ነው፡፡የተለዩ ችግሮችን መነሻ በማድረግ ለተቋማት ድጋፍ ማድረግ ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚሁ ጋር በተገናኘ በመንግስት መስሪያቤቶች ወጥ የሆነ የልማት ፕሮጀክቶች ፕላን እንዲኖር ለማስቻል የተዘጋጀውን ፎርማት ማሻሻል ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡የልማት

ፕሮጀክቶች ፕላን መረጃዎችን ምቹ በሆነ መንገድ ማደራጀት ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ነው፡፡

## የህግ ማዕቀፍና ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋት

የተዘጋጀው ክልላዊ የልማት ፕሮጀክቶች አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ እንዲጸድቅ ክትትል ማድረግ ዕቅድ 1 ክንውን (በሂደት ላይ ያለ) ሲሆን ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ የልማት ፕሮጀክቶችን ለመለየት፣ቅደም ተከተል ለማስያዝና በበጀት እንዲደገፉ ለማድረግ የተዘጋጀውን መመዘኛ መስፈርት ማሻሻል ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡በልማት ፕሮጀክት ዝግጅት የተገኘ ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ለቀጣይ የፕሮጀክቶች ዝግጅት በግብዓትነት እንዲውል ማድረግ ዕቅድ1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡

## የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ

በ2015 ዓ.ም ክትትልና ግምገማ የሚደረግባቸውን 40 ፕሮጀክቶችን ለመለየት ታቅዶ ክንውኑ 40 ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡ የመስክና ዴስክ ክትትልና ግምገማ ማድረግ ዕቅድ 4 ክንውን 2 አፈጻጸም 50% ሲሆን የመስክ ስራዎችን በጥንካሬና በድክመት መለየትና ግብረ መልስ መስጠት ዕቅድ 4 ክንውን 2 አፈጻጸም 50% ተከናውኗል፡፡ በበጀት አመቱ በ4 ዞኖች እና በ13 የተመረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ክትትልና ግምገማ ተደርጓል፡፡በተደረገው የመስክ ክትትልና ግምገማ የተገኙ ግኝቶችን ግብረ -መልስ ተዘጋጅቷል፡፡በምስራቅ አማራ ለሚገኙ 3 ዞኖች የፕላን ቡድን በአካል በመገኘት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡

## ሶሽዩ ኢኮኖሚና መልካምደራዊ መረጃዎች

የክልሉን ሶሽዩ ኢኮኖሚና መልካምደራዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፤ በመተንተንና በማሳተም የመረጃን ተደራሽነትና ጥራት ለማሳደግ በተሰራው ስራ የክልሉን አጠቃላይ የልማት አመልካች ለመስራት በተዘጋጅው ፎርማት መሰረት መረጃ ማሰባሰብ ዕቅድ 11 ክንውን 11 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡ የክልሉን አመታዊ ስታትስቲካል አብስትራክት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ለህትመት ምቹ በሆነ ሁኔታ ማደራጅት ዕቅድ 24 ክንውን 24 አፈጻጸም 100% መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል የአዲሶቹ ሪጅኦ ፖሊታንት ከተሞች የሶሾ-ኢኮኖሚ ጥናት ለማካሄድ የሚስችል መረጃ ለማሰባሰብ ታቅዶ 70% ተከናውኗል፡፡ የከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎች ወሰኖቻቸውን ወቅታዊ ማድረግ ዕቅድ 244 ክንውን 52 አፈጻጸም 21.3% ብቻ

ነው፡፡የወረዳዎችን፤ የከተማ አስተዳደሮችን ፤ቀበሌዎች ብዛት የቆዳ ስፋት እንዲሁም ከዞንና ከወረዳ ዋና ከተማ ያላቸው ርቀት በኪሎ ሜትር መረጃ ማደራጅት ዕቅድ 222 ክንውን 222 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡

## ጥቅል ምርት ግመታ መረጃ መሰብሰብ

ጥቅል ምርት ግመታ የመጀመሪያው ረቂቅ የክልል ኢኮኖሚ ግመታ ሠነድ ፅሁፍ ማዘጋጀትና ለቢሮው የበላይ አመራር አቅርቦ ማስተቸት ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100%፤ለፅሁፉ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን በመስክም ሆነ በዴስክ ላይ መሰብሰብ ዕቅድ 16 ክንውን 16 አፈጻጸም 100%፤የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት የመጨረሻ ክልላዊ ጥቅል ምርት ግመታ ሠነድ ማዘጋጀት ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% ሆኗል፡፡ ለ2014 በጀት ዓመት ጥቅል ምርት ግመታ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ፎርማቶችን ማዘጋጀት እና መከለስ ዕቅድ 24 ክንውን 24 አፈጻጸም 100%፤ በባህርዳር ከተማ ከሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የመረጃ ምንጭ ተቋማት መረጃዎችን መሰብሰብ ዕቅድ 50 ክንውን 50 አፈጻጸም 100%፤በባህርዳር ከተማ ከሚገኙ ተቋማት የተሰበሰቡ መረጃዎችን እየገመገሙ ወደ ኮምፒዩተር ማስገባት ዕቅድ 10 ክንውን 10 አፈጻጸም 100%፤በዞንና በወረዳ ደረጃ መረጃ የሚሰበስቡ ባለሙያዎች የሚጠቀሙበትን ማንዋል ማሻሻል ወይም መከለስ ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100%፤ከወረዳና ከዞን ተሞልተው የተላኩ መረጃዎችን ምልዑነትና ትክክለኛነት እየገመገሙ ችግር ያለባቸው መረጃዎች እንዲሟሉ ማድረግ ዕቅድ 10 ክንውን 10 አፈጻጸም 100%፤በዞንና በወረዳ ደረጃ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመገምገም ወደ ኮምፒዩተር የማስገባትና የማደራጀት ሥራ መሥራት ዕቅድ 24 ክንውን 24 አፈጻጸም 100%፤በአዲስ አበባ እና በክልሉ ባለሙያዎች ለሚሰበሰቡ መረጃዎች ፎርማቶችን ማዘጋጀት ዕቅድ 17 ክንውን 17 አፈጻጸም 100%፤በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች በመዘዋወር መረጃዎችን መሰብሰብ ዕቅድ 12 ክንውን 12 አፈጻጸም 100%፤በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን መሰብሰብ ዕቅድ 110 ክንውን 110 አፈጻጸም 100%፤ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልሉ ውስጥ በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ወደ ኮምፒዩተር በማስገባት የማደራጀት ሥራ መሥራት ዕቅድ 6 ክንውን 6 አፈጻጸም 100% ነው፡፡ ወደ ኮምፒዩተር የገቡና የተደራጁ መረጃዎችን ጥራትና ታማኒነት መገምገም ዕቅድ 6 ክንውን 6 አፈጻጸም 100% ናቸው፡፡

## የክልል ኢኮኖሚ ግመታ

የንዑስ ሴክተሮችን እሴት ጭማሪ በመገመትና ውጤታቸውን በመገምገም ወደ ዋና ዋና ሴክተሮች እሴት ጭማሪ የማጠቃለልና ከበፊት ዓመታት ጋር የሚኖራቸውን አንድምታ መገምገም ዕቅድ 2 ክንውን 2 አፈጻጸም 100% የተሰራ ሲሆን ለ2014 በጀት ዓመት ጥቅል ምርት በወቅቱ የገበያ ዋጋ እና በቋሚ ዓመት የገበያ ዋጋ ምርቱ በመነጨበት የአገማመት ዘዴ በመገመት የእድገት አዝማሚያውን የመገምገም ሥራ መሥራት ዕቅድ 2 ክንዉን 2 አፈጻጸም 100% ተከናውኗል፡፡

### የ2014 ዓ.ም የክልሉን ዓመታዊ ጥቅል ምርት (GDP) ወይም የኢኮኖሚ አፈፃፀም የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| 1 | ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች የእድገት ምጣኔ | የ2014 ዓ.ም እድገት ምጣኔ |
|---|---|---|
| 1.1 | ግብርና ሴክተር | 2.9 |
| 1.2 | ኢንዱስትሪ ሴክተር | 6.5 |
| | አምራች ኢንዱስትሪ | 16.7 |
| 1.3 | አገልግሎት ሴክተር | 8.6 |
| | ክልላዊ ጥቅል ምርት (GDP) | 5.1 |
| 2 | ዋና ዋና የኢኮኖሚ ሴክተሮች ከጥቅል ምርቱ ያላቸው ዓመታዊ ድርሻ | በ2014 ዓ.ም ከጥቅል ምርቱ የነበራቸው ድርሻ |
| 2.1 | ግብርና ሴክተር | 53.5 |
| 2.2 | ኢንዱስትሪ ሴክተር | 15.6 |
| | አምራች ኢንዱስትሪ | 7.9 |
| 2.3 | አገልግሎት ሴክተር | 32.3 |

### ስነ-ህዝብ እና ልማት

በበጀት አመቱ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስነ-ህዝብ እና ልማት ትስስር ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ዕቅድ 200 ክንውን 142 አፈጻጸም 71% (30 በመቶ ሴቶች) ተከናውኗል።ዓመታዊ የስነ-ህዝብ እና ልማት መጽሄት ማዘጋጀት እና አሳትሞ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት/300 ኮፒ/ ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100% (የቀረ ኢዲቲንግ ና ህትመት) ሲሆን ወቅታዊ የስነ-ህዝብ እና ልማት ጉዳዮችን አስመልክቶ ሁለት ብሮሽሮችን ማዘጋጀት ዕቅድ 1 ክንውን 1አፈጻጸም 100% መሆኑን ያመለክታል።

ወቅታዊ እና ዘመናዊ የስነ-ህዝብ መረጃ አያያዝ፣ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በተሰራው ስራ በእድሜ ክፍፍል እና በነጠላ እድሜ የክልሉን የህዝብ ቁጥር በመተንበይ በተለያዩ ዘዴዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ዕቅድ 2 ክንውን 2 አፈጻጸም 100% ነው።የከተሞችን አስተዳደራዊ ወሰን ለውጥ መሰረት በማድረግ የህዝብ ብዛት መረጃን ወቅታዊ ማድረግ ዕቅድ 20 ክንውን 12 አፈጻጸም 60% ሆኗል።ከ12 ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በወረዳ ምክርቤት በኩል ያላቸውን አስተዳደራዊ ወሰን ለውጥ የሚያረጋግጥ ማስረጃ(ቃለ-ጉባኤ) ያሟሉ (ዱር ቤቴ፣ ሞጣ፣ ደጀን፣ ደባርቅ፣ መካነ ሰላም፣ ዳባት፣ ወረታ፣ ነፋስ መውጫ፣ አንዳቤት እና ጃራገዶ) የህዝብ ብዛት መረጃ የማስተካከልና ከአጎራባች ወረዳ ጋር የርክክብ ስራ ተሰርቷል።መረጃ አሟልተው ያላቀረቡ እና ያልተሰራላቸው መካነ-እየሱስ እና ላሊበላ ናቸው።

## ገንዘብና ልማት

### የወጪ አስተዳደር

በ2015 ዓ.ም የክልሉን በጀት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለክልሉ ልማት ለማዋል እና ከብክነት በፀዳና ተጠያቂነት በሰፈነበት አግባብ ለልማት ማስፈፀሚያነት እንዲውል ለማድረግ የበጀት ድልድል በማካሄድ እቅዱን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል። በበጀት አመቱ የክልሉ በጀት ዋነኛ የገቢ ምንጮችንና የሚገኘውን ሀብት ለክልሉ የልማት ሥራዎች ማስፈፀሚያ በጀት እንዲሆን በክልል ምክር ቤቱ በጀት አፀድቆ ወደ ስራ መግባት ተችሏል።

### የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማ ማድረግ

የ2015 የበጀት ማስተዳደሪያ የትኩረት ነጥብ ማዘጋጀትና ለቢሮዎችና ወረዳዎች ማሰራጨት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተፈፅሟል። ከዚህ በተጨማሪም የጸደቀ በጀትን ለሚመለከታቸው

ቢሮዎችና ወረዳዎች ለማሳወቅ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡በተመሳሳይ የቢሮዎችን የመደበኛ የካፒታል በጀት ማሳወቂያ አዘጋጅቶ ለማሰራጨት ታቅዶ 61 ተቋማት መደበኛ በጀትና ለ33 ተቋማት ካፒታል በጀት ማሳወቂያ በማዘጋጀት ሙሉ በሙሉ የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

የ2015 ዓ.ም የወረዳዎችን፣ከተማ አስተዳደሮችና ብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖችን በጀት ለማጠቃለል ታቅዶ የ223 አስተዳደር እርከኖች በጀት ሙሉ በሙሉ በማጠቃለል የእቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡በዚህ መሰረት የክልሉ የበጀት ድልድል ድርሻ ሲታይ ክልል ቢሮዎች ደመወዝ 38.91 በመቶ፤ ስራ ማስኬጃ 23.5 በመቶ፤ካፒታል 37.59 በመቶ ድርሻ ሲይዙ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ደመወዝ 75.94 በመቶ፤ ስራ ማስኬጃ 13.33 በመቶ፤ካፒታል 10.74 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡የድህነት ተኮር ሴክተሮች ድርሻ ሲታይ ከ60% በላይ ለማድረስ ቢታቀድም 59.31% ብቻ ድረሻ ይዟል፡፡ይህም አስተዳደር ዘርፍ ላይ የሚወጡ አስገዳጅ ወጪዎች እያደጉ መምጣታቸው እንደ ክልል ተቋማት የሚታዩ በጥቅል የሚያዝ በጀት እያደገ መምጣት ለመቀነሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

የ2015 ዓ.ም የክልሉን የተጠቃለለ በጀት መጽሐፍ ለማዘጋጀት ታቅዶ በሃርድና በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅቶ እንዲሰነድ ተደርጓል፡፡የ2015 ዓ.ም የክልሉን ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ለማዘጋጀት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተፈጽሟል፡፡ የጸደቀ በጀት በልዩ ልዩ መንገዶች ለህዝብ ይፋ ለማድረግ ታቅዶ 96 በመቶ ወረዳዎች በማስተዋቂያ፣በባነር፣ በበራሪ ወረቀት፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በአካባቢ ሬዲዮ ለህዝብ ይፋ ተድርጓል፡፡

## የ2016 ዓ.ም በጀት ማዘጋጀት

የ2016 ዓ.ም በጀት ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት የበጀት የጊዜ ሰሌዳውን ተከትሎ ለክልል ቢሮዎች፤ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የበጀት ጥሪ የማስተላለፍ ፤የ2016 ዓ.ም በጀት ጥያቄ ከክልል ቢሮዎች የመቀበል እንዲሁም የበጀት ስሚ ማካሄድ ስራዎች ታቅደው ሶስቱም ተግባራት በዕቅዱ መሰረት መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዚህም በጀት የማዘጋጀት እና ከክልል ባለ በጀት መስሪያ ቤቶች ጋር በቀረበው ጥያቄ ላይ እየተማመኑ በመሄድ መደበኛና ካፒታል በጀት ስራዎችን ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡በመሆኑም በክልሉ የጸደቀው በጀት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለተያዘለት ዓለማ በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል የመከታተል፤ከተደለደለ በኋላ በስራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን የመፍታት የተጨማሪ የበጀት ጥያቄዎችን መርምሮ የውሳኔ አስተያየት የማቅረብ በበጀት ዓመቱ መካከል ላይ የሚገኙ ተጨማሪ ገቢዎች ካሉ በተጫማሪ

በጀትነት የማሳዎጅ ፤በብድር የተሰጡ በጀቶችን ማስመለስ፣የ2014 በጀት ዓመት መዝጋትን መቶ በመቶ ማጠቃለል፣ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ በጀት ነክ ጥያቄዎችን ምላሽ መስጠት ተግባራትን ለማከናወን ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡በዚህ መሰረት ከተለያዩ አካላት የቀረበውን የብር 12.37 ቢሊየን ተጨማሪ በጀት ጥያቄ ቀርቦ የውሳኔ አስተያየት በማቅረብ እንዲገመገሙ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በልማት ድርጅቶች ለሚካሄዱና በተለያየ ችግር ሳይከፈሉ ለቆዩ ፕሮጀክቶች ብር 451,926,985.54 ጨምሮ በድምሩ ብር 5.29 ቢሊየን የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው መልሶ የተመደበ 1 ቢሊየን ብር ለሚመለከታቸው ተቋማት የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ ውሳኔ ያረፈባቸውን ተጨማሪ በጀቶች የበጀት ዝውውር ቅጽ አዘጋጅቶ ማሰራጨትና በአይቤክስ ስርዓቱ ለመመዝገብ ታቅዶ እቅዱን 1558 የበጀት ዝውውር በማዘዋወር 100% ማሳካት ተችሏል፡፡በቢሮውና በጣምራ የተፈጸሙ ዝውውሮችን በወቅቱ በመመዝገብ በጀቱን ማስተካከል፤ የተፈጸሙ ዝውውሮችን ሙሉ በሙሉ ወደ አይቤክሱ እንዲመዘገቡ በማድረግ የተስተካከለ በጀትን ወቅታዊ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት ብድር የወሰዱ ወረዳዎችን ተከታትሎ የወሰዱትን ብድር ማስመለስ ስራ በዕቅድ ተይዞ ከ2015 በጀት ዓመት ታሳቢ ብድር የወሰዱ 62 ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ብር 256,965,429 የበጀት ዝውውር በማዘጋጀት እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ብድር ለሚጠይቁ 20 ወረዳዎች ብድር ለመስጠት ታቅዶ ከ97 ወረዳዎች የብድር ጥያቄ ቀርቦ ከፍተኛ ችግር ያለባቸውንና ሌሎች በተለያየ ምክንያት የተቀነሰባቸው ገንዘብ እንዲመለስ በማድረግ ለ56 ወረዳዎች ብር 327,314,122 ብድር መስጠት ተችሏል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የተስተካከለ በጀት እስከ ህዳር 30/2015 ዓ.ም ለመዝጋት ታቅዶ እስከ ህዳር 30/2015 ዓ.ም በጀቱን ሙሉ በሙሉ ማጠቃለል ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ የጸደቀ በጀት ብር 80,104,669,397፤በተጨማሪነት የታወጀ በጀት ብር 907,186,813.00 እንዲሁም የተስተካከለ በጀት ብር81,011,856,209.00 በመሆን እስከተስተካከለ በጀት ያለውን በጣሪያ በመግጠም የማጠቃለል ስራ ተሰርቷል፡፡ በበጀት አዘጋግ ወቅት የታዩ ችግሮች ወጪዎች በወቅቱ አለመመዝገብ፣ ዓመቱን ሙሉ ወጪ ያልተመዘገበላቸው ተቋማት መኖር፣ ከበጀት በላይ ወጪ ተፈጽሞ መገኘት፣ ስራ ላይ ያልዋለ ሰፊ በጀት መገኘት ዋና ዋና ችግሮች ነበሩ፡፡

## የ2015 ዓ.ም የበጀት አጠቃቀም

የ2015 በጀት አመት የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ ወደ አይቤክስ በገባው የወጪ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ለደመወዝ 91.58 ፐርሰንት፣ለስራ ማስኬጃ 67.34 ፐርሰንት፣ለካፒታል 20.99 ፐርሰንት በጠቅላላው 57.69 ፐርሰንት ስራ ላይ ውሏል፡፡ ይህም አፈጻጸም በተለይም የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም አሁን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ በመሆኑ ችግሮች ተለይተው አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል፡፡በአጠቃላይ የበጀት አጠቃቀሙ ሲታይ የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በጥሩ ደረጃ ቢገኝም የካፒታል በጀት አጠቃቀም ዝቅተኛ ነው፡፡ እንደ ክልል በ2014 በጀት ዓመት ከነበረው አጠቃቀም 91.56 በመቶ በ2015 ዓ.ም ወደ 80 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በቀጣይ ወጪዎች ተጠቃለው ሲገቡ አፈጻጸሙ ሊለወጥ እንደሚችል ቢታሰብም በጀት እጥረት ባለበት ክልል ያለውን ውስን ሃብት በበጀትም ወቅት ስራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ ችግር ስለሆነ በተለይ አስፈጻሚ መስሪቤቶች በተገቢው መንገድ በጀታቸውን ስራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ ስራ ላይ የማይውል በጀት ሲኖር ደግሞ ተራፊ በጀቱን ለይተው እንዲመልሱ አስገዳጅ አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡




የበጀት አጠቃቀም ለበጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ቀርቦ ሲገመገም-ባህርዳር

## ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ማስፈን

የ2015 በጀት ዓመት የከተሞች ልዩ ድጉማ በጀትን በቀመር መደልደል እና አፀድቆ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ 203 ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ለ2015 በጀት ዓመት ለከተሞች ልማት ፈንድ ልዩ ድጉማ ብር 1,200,000,000 የተመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በማከፋፈያ ቀመሩ መሰረት ብር 912,000,000 ለነባር 47 ከተማአስተዳደሮች፣ብር 126,000,000 ለ126 መሪ ማዘጋጃቤት ከተሞች ለእያንዳንዳቸው ብር 1,000,000፣ብር 30,000,000 ወደ ሪጂዮፖሊታን ለተሸጋገሩ 2 ከተማ አስተዳደሮች (ደብረታቦር እና ወልድያ) መቋቋሚያ ለእያንዳንዳቸው ብር 15,000,000፣ ብር 120,000,000 በ2014 በጀት አመት ሥራ ለጀመሩ 30 ከተማ አስተዳደሮች ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000,000 እና ብር12,000,000 ለደብረብርሃን፣ደብረማርቆስ እና ኮምቦልቻ ከተሞች በክፍለ ከተሞች ለሚያካሂዱት የቢሮ ግንባታ እና ቋሚ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ግዥ ለእያንዳንዳቸው ብር 4,000,000 የተመደበ ሲሆን የበጀት ድልድሉ ለሚመለከታቸው 77 ከተማ አስተዳደሮች እና 126 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከ77 ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ ለ76 (ከሃይቅ ከተማ አስተዳደር በስተቀር) በጀቱን ስራ ላይ ስለማዋል የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላታቸው የወጪ መርጃ ተልኳል፡፡

በሌላ በኩል ለ2016 በጀት ዓመት ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ለመስራት የሚያግዙ መረጃዎችን በናሙና ከተመረጡ ነባር 96 ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ብሔረሰብ ዞኖች የ2014 ዓ.ም እና 2015 በጀት ዓመት የሴክተሮችን አደረጃጀት ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ76 ወረዳዎች በመሰብሰብ የእቅዱን 79.16% ተፈፀሟል፡፡ እንዲሁም ከ2014 በጀት አመት በኋላ አዲስ የተቋቋሙ ከተማ አስተዳደሮች፣ ከዙሪያ ወረዳ ወደ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ሽግሽግ ያደረጉ 42 የገጠር ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች በ2015 በጀት አመት ያሉበትን አደረጃጀት ታሳቢ ያደረገ በክልሉ ከሚገኙት 220 ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች መረጃ ለማሰባሰብ ታቅዶ የ220 ወረዳዎችንና ከተማ አስተዳደሮችን መረጃ በማሰባሰብ የእቅዱን 100%ማሳካት ተችላል፡፡ በሌላ በኩል በ2014 በጀት አመት ብር 106,758,635 ከእቅድ በላይ የተሰበሰበ ሲሆን ከእቅድ በላይ ከተሰበሰበው መደበኛ ገቢ ውስጥ ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳሮች 50 ፐርሰንት ወይም ብር 53,379,318 መጠቀም እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

## የ2016 ዓ.ም በጀት ማዘጋጀት

የ2016 ዓ.ም በጀት ማዘጋጀትን በተመለከተ የበጀት የጊዜ ሰሌዳውን ተከትሎ የበጀት ጥሪ ለማካሄድ ታቅዶ ለክልል ቢሮዎች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የበጀት ጥሪ የማስተላለፍ ስራ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ የ2016 በጀት ጥያቄንም ከክልል ቢሮዎች ለመቀበል ታቅዶ ከ55 ቢሮዎች የበጀት ጥያቄ የመቀበል ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህ ረገድ እስካሁን ጥያቄ ያላቀረቡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጤና ቢሮ፣ ማዕድን ቢሮ፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፣ ባህልና ቱሪዝም ቢሮና ወልድያ ሆስፒታሎች ናቸው፡፡

## የሀብት አስተዳደርና የገቢ አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት

ለክልል ልማት ማስፈፀሚያ የሚሆን ከፌደራል ከተመደበ ብር 44.38 ቢሊዮን በጀት ድርሻ ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም ድረስ ብር 44.38 ቢሊየን ወይም 100% ተልዕኮ በIBEX የምዝገባ ስራው ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

ከፌደራል የተላከውንና ከክልሉ የተሰበሰበውን ገቢ ጨምሮ ለክልል ቢሮዎች መደበኛ በጀት ብር 7.34 ቢሊዮን ካፒታል በጀት ብር 6.02 ቢሊዮን በድምሩ ብር 13.36 ቢሊዮን ሙሉ በሙሉ በክፍያ ጣሪያና በዝውውር ተላልፏል፡፡ እንዲሁም ለዞኖች ብር 6.03 ቢሊዮን፤ ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተመደበላቸው በጀት ውስጥ ብር 40.21 ቢሊዮን ጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ ተችላዋል፡፡ በአጠቃላይ በ12 ወሩ ከመንግስት ግምጃ ቤት ይተላለፋል ተብሎ የተያዘውን ብር 59.60 ቢሊዮን ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ይህም የክልሉን ልማት በተቀመጠለት መርሃ ግብር መሰረት ለማከናወን የበኩሉን አስተዎፅኦ አድርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በበጀት አመቱ ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ከፌደራል መንግስት ከተመደበው ብር 3.02 ቢሊየን ውስጥ በ12 ወሩ ብር 3.02 ቢሊየን ወይም 100% ገንዘብ ገቢ የተደረገ ሲሆን ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽ የተላለፈው ብር 1.53 ቢሊዮን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 1.296 ቢሊየን እና ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ የተላለፈው ብር 2.14 ቢሊዮን ቢሆንም ብር 410.86 ሚሊየን ከ2014 በጀት ዓመት የዞረ ስለሆነ ለ2015 በጀት ዓመት ከተመደበው ላይ ብር 1.728 በተጠየቀውና በታዘዘው መሰረት የመጣው ገንዘብ በሙሉ ተላልፏል፡፡

## የመደበኛ እና ካፒታል በጀት ወጭ አፈፃፀም

በበጀት አመቱ ከመንግስት ግምጃ ቤት የተመደበው በጀት የወጪ አፈፃፀም ሲታይ በ2015 ዓ.ም እስከ የሰኔ 30 ድረስ የወጪ ሂሳብ የመደበኛ በጀት ድምር ብር 60.70 ቢሊዮን፣ የካፒታል በጀት ብር 11.23 ቢሊዮን ጠቅላላ ድምር ብር 71.99 ቢሊዮን በIBEX የመመዝገብ ስራ ተሰርቷል፡፡

በ2015 ዓ.ም የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ በIBEX ምዝገባ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 25,718,088,986.84 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 17,219,689,531.75 ይታያል፡፡በሌላ በኩል የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብን መረጃ አጠርቶ በመያዝና የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በማጠናከር ሂሳቡን ማወራረድ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡በመሆኑም ከ3-10 ዓመት ድረስ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,449,456,754 እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 1,092,994,563 ያለ ሲሆን 30% ለማወራረድ በተያዘው እቅድ መሰረት በቢሮ ደረጃ በ12 ወሩ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 734.84 ሚሊዮን ላይ ብር 642 ሚለዮን ብር/87%/ እና ተከፋይ ሂሳብ ብር 327.9 ሚሊዮን ላይ ብር 866 ሚሊዮን /264%/ ማወራረድ ተችሏል፡፡ ለዚህም ውጤት መገኘት ሪፖርት በማያደርጉ ተቋማት ላይ የገንዘብ ዝውውር እንዳይተላለፍላቸው ከማድረግ በተጨማሪ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተወሰነ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡

## በሌሎች የበጀት ምንጮች(ቻናሎች) የሚመጣን ሀብት አስተዳደር በተመለከተ

በሌሎች የበጀት ምንጮች(ቻናሎች) የሚመጣን ሀብት ለማስተዳደር በተሰራው ስራ በቻናል አንድ የሚመጣውን ብር 14 ቢሊዮን ቀልጣፋ የክፍያ አገልግሎትና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር በማስፈን በፕሮግራሙ የሚገኝ ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግን በተመለከተ በቻናል አንድ ውስጥ 10 ፕሮግራሞች ያሉ ሲሆን እስከ 12ኛው ወር ድረስ ብር 13.63 ቢሊዮን (ከአለፈው ዓመትና በበጀት ዓመቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ከተለቀቀው የተገኘ ሲሆን) ብር 10.6 ቢሊዮን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም የወጪ አፈፃፀም ከአመታዊ በጀት አንፃር 73% ሲሆን ወደ ክልሉ ከገባው ገንዘብ አንፃር ሲታይ 77% ነው፡፡

## የመንግስታትና የበየነ መንግስታት በጀት አፈጻጸም

በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የመንግስታትና በየነ መንግስትታት ፕሮጀክቶች ሀብት ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ በተሰራው ስራ በበጀት ዓመቱ ባለፉት 12 ወራት በUN ኤጀንሲዎች የገንዘብ ድጋፍ ለሚከናወኑ ተግባራት ከ2014 ዓ.ም የዞረ ብር 246,366,895.86

እንዲሁም በዚህ አመት የተመደበና ተጠይቆ ወደ ክልሉ የመጣ ብር 945,742,493.22 ሚሊየን በድምሩ ብር 1,192,109,389.08 ሲሆን ብር 161,786,022.08 ስራ ላይ በማዋል የእቅዱን 70% መፈፀም ተችሏል፡፡

## ሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶች በኩል የሚመጣውን ሀብት አጠቃቀም

ሲቪል ማህብረሰብ ድርጅቶች በኩል የሚመጣውን ሀብት አጠቃቀም ውጤታማ ለማድረግ በተሰራው ስራ 250 አዳዲስ ፕሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም 4.5 ቢሊየን ብር ለማግኘት ታቅዶ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ 271 (ከ108.4 %) አዳዲስ ፕሮጀክቶች ጋር ስምምነት በመፈራረም ብር 8.9 ቢሊዮን (198%) ማግኘት ተችሏል፡፡አዲስ በተፈረሙት ፕሮጀክቶች 10 ሚሊየን ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን ታቅዶ 17.89 ሚሊየን ህዝብ ተጠቃሚ መሆናቸውን ያሳያል፡፡




የመንግስትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዓመታዊ የምክክር መድረክ-ባህርዳር

# ውሃና ኢነርጅ ልማት

## የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን

በ2015 ዓ.ም በገጠር የተለያየ አቅም ያላቸው 1358 አነስተኛ 10 ከፍተኛ  የውሃ ተቋማት ግንባታ በማከናወን 149,387 ወንድ፣ 160,418 ሴት በድምሩ 307,639 የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ በማድረግ የገጠር የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 72.21% ላይ በ1.7% በመጨመር ወደ 73.85% ማሳደግ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ በከተማ በተጠናቀቁ ትልልቅ 8 የከተማ የንጹህ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች 139,198 (62,975 ወንድ፣ 68,223 ሴት) ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ የከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 69.24% ላይ የ2.93% የሽፋን እድገት በማምጣት የከተማ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን 72.17% ማድረስ ተችሏል፡፡በበጀት አመቱ የከተማ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን በ3.5% ለማሳደግ በእቅድ ተይዞ የተሰራ ሲሆን በአጠቃላይ በ2015 በጀት ዓመት በአስራ ሁለት ወራት በገጠርና በከተማ በተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች 427,837 (ወንድ 205,362 እና ሴት 222,475) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 71.77% ላይ በ1.95% በመጨመር ወደ 73.64% ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የውኃ ተቋማትን ወጭ ቆጣቢ ማድረግ

በ2015 ዓ.ም 25 በዲዝል ጀኔሬተር የሚሰሩ የውኃ ተቋማትን ወደ ሶላር ለመቀየር በተያዘው እቅድ መሰረት 22 የውኃ ተቋማትን ወደ ሶላር የመቀየር ስራ ተከናውኗል አፈጻጸሙም 88% ነው፡፡ እንዲሁም በዲዝል ጀኔሬተር የሚሰሩ የውኃ ተቋማትን ወደ ትራንስፎርመር ለመቀየር በተሰራው ስራ 28 ታቅዶ የ26 የመጠጥ ውኃ ተቋማትን ወደ ትራንስፎርመር መቀየር ተችሏል አፈጻጸሙም 93% ሆኗል፡፡

## የውኃ ተቋማትን መጠገን

በአስቸኳይ ጊዜ እንዲከናወኑ በእቅድ ከተያዙ ተግባራት መካከል የመልሶ ማቋቋምና የውሀ ተቋማትን የመጠገን ስራ አንዱና ዋነኛው ነበር፡፡በዚህም መሰረት በአጠቃላይ 1,430 የውኃ ተቋማትን ለመጠገን ታቅዶ በጥቅሉ 1,260 የውሃ ተቋማትን  በመጠገን አፈጻጸሙ 88%

ሆኗል፡፡ከዚህም በተጨማሪ 223 በጦርነቱ የወደሙ የውሃ ፓምፖችን ገዝቶ ለመተካት ተችሏል፡፡

## ከውሀ ልማት ጋር የተያያዙ አስቸኳይ ተግባራትን ማከናወን

በ2015 ዓ.ም ከ225 ኪሎ ሜትር በላይ የውሃ ቧምቧ ግዥ በመፈጸም በተለያዩ ምክንያቶች ከአገልግሎት ውጭ የነበሩ 28 የውኃ ተቋማትን ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡ በጦርነቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ንጹህ የመጠጥ ውኃ ለማድረስ የውኃ መጫኛ ቦቲዎችና ለጀኔሬተር አገልግሎት የሚውል ነዳጅ (180,638 ሊትር) ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ውኃ ያቀረቡበት ክፍያን ጨምሮ ብር 40,305,748.55 ወጪ ሆኖ ለ623,569 ህዝብ ንጹህ የመጠጥ ውኃ ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው በጊዜያዊ መጠለያና ከፍተኛ የውሃ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ብር 172,098,535.76 ወጪ የተደረገበት የመጸዳጃ ቤት ግንባታ፣ ሻወር አገልግሎት መስጫ ግንባታ፣ የእጅ መታጠቢያ፣ የቧንቧ ዝርጋታና ፣ የስነ ንጽህና ግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ከአስቸኳይ ስራዎች አንጻር በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር 568 አዲስ፣ቀላልና ከፍተኛ የውሃ ተቋማት ጥገና ስራዎች፣ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ዕቃዎች ቧንቧዎችና መገጣጠሚያዎች የአቅርቦትና ገጠማ ስራ፤ በተለያዩ የገጠር ቀበሌዎችም የእጅ ፓምፖችን የአቅርቦትና ተከላ እንዲሁም የጥገና ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም በጠቅላላው ብር 446,932,551.19 ወጪ በማድረግ 3,295,470 ህዝብ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡በቢሮው በኩልም የባለሙያና ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪ ድጋፍ አድርጓል፡፡ብር 10,232,316.11 ወጪ የተደረገባቸው 139 የውሃ ማጠራቀሚያ ሮቶዎችም በተለያዩ ቦታዎች በማስራጨት ተከላ ተደርጓል፡፡

## የውሀ ብክነትን መቀነስ

በ2015 ዓ.ም በአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ የመጠጥ ውሃ ተቋማት ባለቤት እንዲኖራቸው ለማስቻልና የውኃ ተቋማት አስተዳደር ስራውን ምቹና ዘላቂ ለማድረግ 45 የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት እና 40 የገጠር መጠጥ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በማቋቋም ለ309 ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡የመጠጥ ውሃ ተቋማትን የብልሽት ምጣኔም በ2014 በጀት አመት መጨረሻ ከተደረሰበት 11.61% ወደ 10.56% ለመቀነስ ታቅዶ በአስራ ሁለት

ወራት ወደ 11.45% የቀነሰ ሲሆን ይህም የእቅድ አፈፃፀም ከ12 ወሩ 90.47%፡፡ በከተሞች ያለውን የውሃ የብክነት መጠንም ከ22.68% ወደ 20 % ለመቀነስ ታቀዶ ወደ 21.51 % የቀነሰ ሲሆን ይህም የእቅድ አፈፃፀሙ ከበጀት አመቱ 81.8% መሆኑን ያሳያል፡፡

## አማራጭ ኢነርጅን መጠቀም

በአማራጭ ኢነርጅ ዘርፍ በክልላችን አማራጭና ታዳሽ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች በስፋት የተሰራጩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች ሲሆኑ በበጀት አመቱ 182,410 ታቅዶ 188,468 ማሰራጨት ተችሏል፡፡አፈጻጸሙም 103.32% ሆኗል፡፡ስለሆነም የተሻሻሉ የኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች ስርጭት ሽፋን በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት 63.14% ላይ 3.8% በመጨመር ወደ 67.07% ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 188,468 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች በመሰራጨታቸው 212,968.14 ቶን ካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ አየር እንዳይለቀቅ፤103,307.70 ቶን የማገዶ እንጨት ከመንደድ ድኗል እንዲሁም 7,915.61 ሄክታር ደን ከመመንጠር መታደግ ተችሏል፡፡

## የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ መገንባት

የክልሉን ህብረተሰብ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ 1744 የባዮጋዝ ማብለያዎች ለመገንባት ታቅዶ 2094 መገንባት ተችሏል፡፡አፈጻጸሙም 120.07% ነው፡፡በመሆኑም በተገነቡ የባዮጋዝ ማብለያዎች 2094 የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በእነዚህ የባዮ ጋዝ ማብለያዎችም በአንድ አመት 9423 ቶን ካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ አየር እንዳይለቀቅ፤ 4585.86 ቶን የማገዶ እንጨት ከመንደድ በማዳን፤565,380 ኩንታል ኮምፖስት በማምረት እንዲሁም 188.46 ሄክታር ደን ከመመንጠር መታደግ ተችሏል፡፡

## የሶላር ማሾዎችን ማሰራጨት

በበጀት አመቱ 80,000 የሶላር ማሾዎችን ለህብረተስቡ ለማሰራጨት ታቅዶ 62354 ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 69.6% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ 35,000 የቤተሰብ ሶላር ሆምሲስተም ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 33,684 ሶላር ማሰራጨት ተችሏል፡፡

## የተለያዩ የሙያ ፈቃዶችን መስጠት

በበጀት አመቱ ለ530 (171 ሴ፤ 349 ወ) አዲስ ፍቃድ ለመስጠት / የግንባታ ባለሙያ ፍቃድ፣የግንባታ ብቃት ማረጋገጫ፣ የአማካሪ ባለሙያ ፍቃድ፣የአማካሪ ብቃት

ማረጋገጫ፣የጉድጓድ ቁፋሮ ባለሙያ ፍቃድ፣ወዘተ የባለሙያና ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ ለ529 ፍቃድ ተሰጥቷል፡፡የ12 ወር እቅድ አፈጻጸሙ 99.4% ሆኗል፡፡ በበጀት አመቱ ነባር ፈቃድ ለማደስ በተሰራው ስራ ለ806 ነባር ፈቃድ ማደስ፤ የግንባታ ባለሙያ ፍቃድ፣የግንባታ ብቃት ማረጋገጫ፣ የአማካሪ ባለሙያ ፍቃድ፣ የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ፣ የጉድጓድ ቁፋሮ ባለሙያ ፍቃድ፣ ወዘተ ለማደስ ታቅዶ በድምሩ 711 ነባር ፈቃድ የማደስ ስራ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከዓመቱ 88.21% ሆኗል ፡፡

## የጥናትና ዲዛይን ስራ መስራት

በክልሉ ባሉ ከተሞች ማለትም ደሴ፣ ጎንደርና ደብረ ብርሃን የአጭር ጊዜ ዝርዝር የጥናትና ዲዛይን ስራ 100% ለማከናወን ታቅዶ 100% ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡በ3ቱም ከተሞች (ደሴ፣ ጎንደርና ደብረ ብርሃን) የስዌሬጅ ዝርዝር የጥናትና ዲዛይን ስራ ለማጠናቀቅ 100% ለማከናወን ታቅዶ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ዕቅድ አፈጻጸሙ በበጀት አመቱ መጨረሻ 100% ሆኗል፡፡ በአራቱም ከተሞች (ባህር ዳር፣ ደሴ፣ ጎንደርና ደብረ ብርሃን) MIS ቢል አካውንቲንግ የጥናት ስራ ለማከናወን ታቅዶ ስራው በውሃና ኢነርጂ ሚኒስተር የተከናወነ ሲሆን በዚህም መሰረት 100% ደርሷል፡፡ በሌላ መልኩ አነስተኛ ገቢ ባላቸው አካባቢዎች የውሃ ማስፋፊያ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 100% የልይታ ስራና ጥናት ተከናውኗል፡፡ በባህር ዳር ከተማ ነባር 05 /አምስት/ የጋራና የህዝብ መፀዳጃ ቤት ጥገና ለማጠናቀቅ ታቅዶ የጥገና ስራቸው ተጀምሮ 100% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 10 የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የግንባታ ስራቸው ተጀምሮ 100% ማድረስ ተችሏል፡፡ በደሴ ነባር 05 የጋራና 05 የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የግንባታውን 50% ማድረስ የተቻለ ቢሆንም በተቋራጩ አቅም ውስንነት ምክንያት ውሉ ሊቋረጥ ችሏል፣ጎንደር ነባር 07 የጋራና 08 የህዝብ መፀዳጅ ቤት ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የግንባታውን 50% ማድረስ ተችሏል ፡፡

## የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት መስራት

በ2015 ዓ.ም የባህርዳር ከተማ የአባይማዶ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡የዚህ ፕሮጀከት በየጊዜው የገጠሙትን የተለያዩ ችግሮች በመፍታት እና አሁን ላይ ግንባታው ቢካሄድ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ወጭ እንደሚያስከትል በመረዳት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የተሰራ ፕሮጀክት ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ በማእከላዊ ጎንደር ዞን ለሚገኘው የዙይ-ሐሙሲት እና አካባቢው ህብረተሰብ የሚያገለግለውን የንጹህ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክት ከአለም ባንክና ከፌዴራል ውሃና ኢነርጂ እንዲሁም ከክልሉ መንግስት ከ1.1

ሚሊዮን ብር በማስመደብ እንዲጀምር የተደረገበት ሁኔታም ቢሮው የህብረተሰቡን ጥያቄና ችግር ለመመለስ በከፍተኛ ትጋት እየሰራ መሆኑን ማሳያ ነው።

# መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

## የመሬት አስተዳደርና ካዳስተር ስራዎች

በበጀት ዓመቱ ለ476,606 ባለይዞታዎች 1,906,425 የማሳ ካርታ በማዘጋጀት የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ464,251 (97.41%) ባለይዞታዎች 1,716,335 (90.03%) የማሳ ካርታ ተዘጋጅቶ የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ተችሏል።



*የ2ኛ ደረጃ ሰርተፊኬት ስርጭት ማሳያ*

## የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርን ለብድር ዋስትና ማስያዝ

በበጀት አመቱ 3,667 ባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸውን የብድር ዋስትና አስይዘው ብር 183,333,000 የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 6,381 (ወንድ 4,520፣ ሴት 1,861) ባለይዞታዎች ደብተራቸውን በማስያዝ ብር 507,105,096 እንዲበደሩ ተደርጓል። ከዚህ ውስጥም ከ64 ሚሊየን ብር በላይ የአይነት ብድር (ጄነሬተር፣

ትራክተር እና ሌሎችም) የተሰጡ ሲሆን 443,820,880 ብር ደግሞ በጥሬ ገንዘብ የተሰጠ ብድር ነው፡፡ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

## የመሬት መረጃን ወደ ዘመናዊ አሰራር በማስገባት

የመሬት መረጃን መመዝገብና ኮምፒውተራይዝድ ማድረግ በበጀት አመቱ 300,000 ባለይዞታዎችን 2,000,000 የማሳ መረጃ በዘመናዊ መልኩ ለመመዝገብ እቅድ ተይዞ 364,728 ባለይዞታዎችን 1,681,639 ማሳ መረጃ ወደ ኮምፒውተር የመመዝገብ ሥራ የተሰራ ሲሆን አፈፃፀሙም የባለይዞታዎችን መረጃ በዘመናዊ መልኩ የመመዝገብ ስራ 121% እና የማሳ መረጃን ደግሞ 84% መፈጸም ተችሏል፡፡

## ያለ አግባብ ይዞታቸውን አጥተው የነበሩ ባለይዞታዎች ይዞታ ማስመለስ

በ2015 ዓ.ም ያለ አግባብ ይዞታቸውን ያጡ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ በማጥራት ይዞታቸው እንዲመለስላቸው ለማድረግ 5,052 ታቅዶ የ4,386 (ወንድ 2,142፣ ሴት 2,244) ባለመብቶች ማለትም ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎችም) መሬት እንዲመለስላቸው ተደርጓል፤ አፈፃፀሙም ከ86.2% በላይ ነው፡፡



*ይዞታቸውን የመጠቀም መብታቸው የተመለሰላቸው ግለሰቦች*

## የመጠቀም መብት የሌላቸው ግለሰቦች የያዙትን መሬት ማስመለስ

በበጀት ዓመቱ የመሬት ይዞታ መብት ህጉ መሬት ከነፈጋቸው 4,326 ግለሰቦች 3,000 ሄክታር ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ከተውጣጡ 2,699 ግለሰቦች 1,424 ሄክታር መሬት ማስመለስ ተችሏል፤ አፈፃፀሙም ከባለይዞታ አንጻር ሲታይ ከ62 ፐርሰንት በላይ ነው፡፡

## የተገፉና የተወረሩ የወል መሬቶችን ማስመለስ

በበጀት ዓመቱ በ108,139 ህገ ወጦች ከተወረሩና ከተገፉ የወል መሬቶች ላይ 21,806 ሄክታር መሬት ለማስመለስ ታቅዶ ከተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የ105,012 ህገ-ወጦች 27,428 ሄክታር መሬት የማስመለስ ስራ ተከናዉኗል፡፡

## የገጠር ቀበሌ ማእከላት ግንባታ ስራዎች

የገጠር ቀበሌ ማእከላት የእድገት ማእከል ሆነው የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ በበጀት ዓመቱ የ180 ቀበሌ ማእከላትን አዲስ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ221 ቀበሌዎች አዲስ ፕላን ተዘጋጅቶላቸዋል፤ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

## የካሳ ምትክና ዘላቂ መልሶ ማቋቋም ስራዎች

በበጀት ዓመቱ ለ579 አርሶ አደሮች ትክ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ ታቅዶ ከካሳ ክፍያ በተጨማሪ 2,033 (1,184 አባወራና እማወራ፣ 435 አባወራ፣ 414 እማወራ) አርሶ አደሮች ትክ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ ተደርጓል፤ አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለሚለቁ 57,917 ባለይዞታዎች ብር 21,500,488,198 ለመገመት ታቅዶ የ61,001 ባለይዞታዎች ብር 22,589,919,570 ካሳ የተገመተ ሲሆን አፈጻፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ 57,917 ባለይዞታዎች 21.5 ቢሊዮን ብር ካሳ ተገምቶ እንዲከፈላቸው ለማድረግ በታቀደው መሰረት ለ37,951 ባለይዞታዎች ብር 13,358,061,881 የካሳ ክፍያው ተፈፅሟል፤አፈፃፀሙም ከባለይዞታ አንጻር 65% ሲሆን ከተከፈለ ካሳ መጠን አኳያ ደግሞ 62% ነው፡፡

## በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ ባለይዞታዎችን በዘላቂነት ማቋቋም

በበጀት ዓመቱ ለ5,792 (4,054 አባወራና እማወራ፣ 1,158 አባወራ፣ 579 እማወራ) አርሶ አደሮች የመኖሪያ ቦታ እንዲያገኙ ታቅዶ ለ6,406 (3,206 አባወራና እማወራ፣1,493 አባወራ፣ 1,460 እማወራ) አርሶ አደሮች የመኖሪያ ቦታ ተሰጥቷል፤ አፈፃፀሙም 90.6% ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪ ለ11,583 (8,108 ወንድ፣ 3,475 ሴት) እድሜአቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆናቸው የአርሶ አደር ልጆች የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለመስጠት ታቅዶ ለ9,338 (5,961 ወንድ፣3,377 ሴት) ልጆች ተሰጥቷል፤ አፈፃፀሙም 81% ነው፡፡

### የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ስራዎች

በበጀት ዓመቱ ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል እና ለባለሃብቶች የሚተላለፍ 23,518 ሄክታር መሬት ለመለየት ታቅዶ በክልልና በዞን ደረጃ ሊተላለፍ የሚችል 21,264.1 ሄክታር መሬት በመለየት ከ90% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚውል 100 ሄክታር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ 813.5 ሄክታር መሬት መለየትና የእቅዱን ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ለአገልግሎት ዘርፍ የሚውል 100 ሄክታር ነጻ መሬት ለመለየት ታቅዶ በዞንና ወረዳ ደረጃ የሚተላለፍ 67.1 ሄክታር መሬት በመለየት የእቅዱን 67.1% መፈፀም ተችሏል፡፡ በዚህም ነጻ መሬቶችን ለማስተላለፍ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ 250፣ በኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ 131፣ በአገልግሎት ዘርፍ 53 በድምሩ 434 ባለሀብቶችን በመመሪያው መሰረት መለየት ተችሏል፡፡

## አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና

የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራትን በማከናወን የዝግጁነት አቅምን ለማሳደግ መደበኛ የአደጋ ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በዞኖች የመኸርና የበልግ ቅድመ ምርት ግምገማ እንዲሁም ድህረ ምርት ግምገማ እንዲካሄድ ተደርጓል፤ የክረምቱን ዝናብ ተከትሎ የጎርፍ፣ የበረዶ፣ የመሬት መንሸራተት እና ሌሎች አደጋ በተከሰተባቸው የደቡብ ጎንደር፣ የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ወሎ እና የምዕራብ ጎጃም ዞኖች በተለያዩ ወረዳዎች የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ስጋት ጥናት ማድረግ ተችሏል በዚህም አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጀት ለተጎጅዎች አስፈላጊ ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ለማድረስ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በጦርነቱ ሳቢያ ጉዳት በደረሰባቸው ወረዳዎች ያለውን የስነ ምግብ ሁኔታ ለማወቅ ይቻል ዘንድ ፈጣን ዳሰሳዊ የስነ ምግብ ጥናት በሶስት ዞኖች በሚገኙ አራት ወረዳዎች (ሠቆጣ ዙሪያ፣ ዝቋላ፣ ራያ ቆቦና አዲአርቃይ) 4 ጊዜ ጥናቱ ተከናውኖ መረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

## የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስራዎችን በማከናወን የህብረተሰቡን አደጋ ተጋላጭነት መቀነስ

በክልሉ መንግስት 43 ሚሊዮን ብር እና በአውሮፓ ህብረት 25 ሚሊዮን ብር በተገኘ በጀት በ20 ወረዳዎች የጎርፍ መከላከል ስራ ለመስራት ታቅዶ በ16 ወረዳዎች (80%) ወቅታዊና የተሻለ የጎርፍ መከላከል ስራ በመስራት ሊደርስ የሚችልን አደጋ መቀነስ ተችሏል፡፡



የጎርፍ መከላከል ስራ (ሰሜን ወሎ - ሐብሩ ወረዳ)

## የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅምን ማጎልበት

በበጀት አመቱ የክልሉን የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ሀብት ለማሳደግ በተሰራው ስራ ከክልሉ መንግስት በ410 ሚሊዮን ብር 61,580.5 ኩንታል እህል እና 7,153 ጂኦሜምብሬን በግዥ በማቅረብ እንዲሁም በዞንና ከተማ አስተዳደሮች አስተባባሪነት ከህብረተሰቡ በተሰበሰበ 16,946,276 ብር እና 11,834 ኩንታል እህል የአጋሮችንና የፌደራል መንግስትን የድጋፍ ክፍተት ሊሞላ በሚችል መልኩ ለተፈናቀሉ ዜጎች ለድጋፍና ለመልሶ ማቋቋም ስራ እንዲውል ተደርጓል፤ ይህም ከሌሎች አቻ ክልሎች አኳያ ሲታይ አፈጻፀሙ ዝቅተኛ ቢሆንም ጅምር ጥረቱ ግን አበረታች ነው ማለት ይቻላል፡፡

## ለአደጋ ለተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የዕለት ምግብ ድጋፍ አቅርቦትና ስርጭት

በ2015 ዓ.ም የቅድመ ምርት ግምገማና ጥናት መሰረት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው 3,489,507 የህብረተሰብ ክፍሎች በጥናት ተለይተው ከተፈቀደላቸው ውስጥ በ1ኛ ዙር 541,714(15.5%) ድጋፍ ፈላጊዎች ድጋፍ ማግኘታቸውንና 2ኛው ዙር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ከክልሉ መጠባበቂያ ክምችት ለተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ለ189,601 ተጠቃሚዎች የሚውል 28,733 ኩንታል የምግብ እህል ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በክልሉ ልዩ ትኩረት የሚሹ ወረዳዎችን ለመለየት ይቻል ዘንድ በየ6 ወሩ በተካሄደው ስራ የመጀመሪያ ትኩረት ለሚሹ 20 ወረዳዎች 2,037 ሜትሪክ ቶን አልሚ ምግብ ለ492,156 ተጠቃሚዎች (ለ284,593 ህጻናት እና ለ207,563 እናቶች) ተጨማሪ አልሚ ምግብ ማቅረብና ማሰራጨት ተችሏል፡፡



## በድርቅ ለተጎዱ የተደረገ ድጋፍ -ጃናሞራ ወረዳ

በክልሉ በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙትን የማሰራጫ ፤መጋዘኖች በእርጅና እና በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ ለመጠገን በሁሉም ዞኖች ዳሰሳዊ ጥናት በማድረግ የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አካባቢዎች በመለየት ከክልሉ መንግስት በተመደበ 10 ሚሊየን ብር 17 የወረዳና 2 የክልል መጋዘኖችን ለመጠገን ዕቅድ ተይዞ 15 (79%) ሙሉ በሙሉ በመጠገን ወደ ስራ ማስገባት መቻሉ በጥንካሬ የሚገለፅ ነው፡፡

## የአደጋ ጊዜ ፈጣን ምላሽ ድጋፍ

በበጀት ዓመቱ በአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጭ ሴፍቲኔት አማካኝነት በአደጋ ለተጎዱና ተጋላጭ ለሆኑ 517,534 በልማታዊ ሴፍቲኔት በማህበረሰብ ስራ ተጠቃሚ ለሆኑ አካላት እንዲሁም 1,362,878 ከልማታዊ ሴፍቲኔት ውጭ ለሆኑ በድምሩ 1,880,412 የህብረተሰብ ክፍሎች ከ2 እስከ 5 ወር ለትራንስፌር አገልግሎት የሚውል ድጋፍ በአጠቃላይ ብር 1,304,985,548

ለወረዳዎች ተላልፎ ብር 1,300,086,503 (90%) ለተጠቃሚዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

### የእህል ድጋፍ

በ2015 በጀት ዓመት ኤፍ ኤች ኢትዮጵያ በተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት የሚደገፉ ወረዳዎች 31,308.54 ኩንታል እህል ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ 31,308.54 ኩንታል (100%) ወደ ወረዳዎች ገብቶ ለ88,460 ተጠቃሚዎች መሰራጨት ተችሏል፡፡

## ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት

በተለያዩ ስልቶች የማስተዋወቅ ስራ ከተሰራላቸው ባለሃብቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች መልምሎ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ በራሳቸው ተነሳሽነት የሚመጡትን ባለሃብቶች ጨምሮ በአመቱ 175 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ስራ ሲገቡ ለ212,503 ወንድ እና 187,782 ሴት በድምሩ ለ400,285 ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 3,000 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ 483.7 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ስራ ሲገቡ ለ621,995 ወንድ እና 406,164 ሴት በድምሩ ለ1,028,159 ዜጎች የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 4,724 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ተደርጓል፤ የኢንቨስትመንት ፈቃድም ሆነ ያስመዘገቡት ካፒታል አፈጻጸም ከ100% በላይ ነው፡፡

### ለልማት የሚውል የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦት

በበጀት አመቱ በሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለተለያዩ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላን የተመላከተ መሬት ማዘጋጀት በሄክታር እቅድ 3,809 ሲሆን ክንውኑ ደግሞ 5,340.6 ነው፤ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ለልማትየሚውል በሳይት ፕላን የተመላከተ መሬት ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ

በበጀት አመቱ በሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለተለያዩ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላን የተመላከተ 3,690.15 ሄክታር መሬት ከ3ኛ ወገን ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 1477.7 ሄክታር መሬት ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 40.04% ነው፡፡

በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ለቀረቡ ፕሮጀክቶች 15,570 ሄክታር በሳይት ፕላን ለማመላከት በእቅድ ተይዞ 17,018.9 ሄክታር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ 12,618 ሄክታር መሬት ከ3ኛ ወገን ነጻ ለማድረግ እቅድ ተይዞ 15,550.2 ሄክታር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% በላይ ነው፡፡

## የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሚለሙባቸው ሳይቶች መሰረተ ልማት ማሟላት

በበጀት ዓመቱ ለአዲስና ነባር ሁለገብ የኢንዱስትሪ መንደሮች /ፓርኮች/ መሰረተ ልማት ማሟላትን በተመለከተ ለጠጠር መንገድ 276.36 ኪሎ ሜትር እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን 135.8 ኪሎ ሜትር ማከናወን ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 49.1% ነው፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክትን ችግር በጥናት በመለየት የመሰረተ ልማት ችግርን መፍታት

የመንገድ ችግር ያለባቸውን 300 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ለመለየት ታቅዶ 542 ተከናውኗል፤ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ ከእነዚህ መካከል የ150 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የመንገድ ችግር ለመፍታት ታቅዶ 244 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

የመብራት ችግር ያለባቸውን 400 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለመለየት 708 ማከናወን ተችሏል፤ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል 200 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የመብራት ችግር ለመፍታት ታቅዶ 257 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

የውሃ ችግር ያለባቸውን የ150 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ለመለየት እቅድ ተይዞ 300 ማከናወን ተችሏል፤ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል 150 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን የውሃ ችግር ለመፍታት ታቅዶ 131 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 87.33% ነው፡፡

የስልክ ችግር ያለባቸውን 20 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ለመለየት እቅድ ተያዞ 22 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለ20 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የስልክ ችግር ለመፍታት እቅድ ተይዞ 14 ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 70% ነው፡፡

## ምርት ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተ ልማት ችግር መፍታት

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ችግር በሚፈልጉት መጠንና ጥራት ማሟላት የሚያስፈልግ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት ለ764 አነስተኛ፣ ለ154 መካከለኛ፣ለ88 ከፍተኛ በድምሩ ለ1006 አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት ላይ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን የመሰረተ ልማት ችግር ለመፍታት በእቅድ ተይዞ ለ409

አነስተኛ፣ለ179 መካከለኛ፣ለ81 ከፍተኛ በድምሩ ለ567 ለሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሰረተ ልማት ችግር መፍታት ተችሏል፡፡

## የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ከገቢ ግብር ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ

ከገቢ ግብር ነጻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥያቄ ያቀረቡ የግብርና፣ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ፕሮጀክቶች እቅድ 40 ተይዞ ክንውን 70 ሲሆን አፈፃፀሙም 175% ነው፡፡ ከግብር ነጻ ተጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክቶች 40 ታቆዶ 38 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 95% ነው፡፡

## የኢንቨስትመንት የግብዓት አቅርቦት ችግር መፍታት

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት በመጨመር የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን የግብአት ችግር በሚፈልጉት መጠንና ጥራት ማሟላት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ በጀት ዓመት ለ339 አነስተኛ፣ ለ162 መካከለኛ፣ ለ96 ከፍተኛ በድምሩ ለ597 አምራች ኢንዱስትሪዎች በ2,109,000,000 ሚሊዮን ብር 103,341 ቶን በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የግብአት ችግር ለመፍታት በእቅድ ተይዞ በ11,160,000,000 ቢሊዮን ብር 581,892 ቶን በማቅረብ ለ414 አነስተኛ፣ ለ213 መካከለኛ፣ለ132 ከፍተኛ በድምሩ ለ759 አምራች ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ችግርን ለመፍታት ተችሏል፡፡

## የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግ

በነባርና በአዲስ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ተጨማሪ አቅም በመፍጠር ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የኤክስፖርት ገቢን የማሳደግ ስራ ተሰርቷል፡፡

በነባር ለ2 አነስተኛ፣ለ6 መካከለኛ፣ ለ39 ከፍተኛ በድምሩ ለ47 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች 21,821.04ቶን በመላክ 91.6 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ ክንውኑ ሲታይ ለ1 አነስተኛ፣ለ6 መካከለኛ፣ለ30 ከፍተኛ በድምሩ ለ37 አምራች ኢንዱስትሪዎች 74,450.09 ቶን በመላክ 116.36 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 100 % ነው፡፡

በአዲስ 6 አምራች ኢንዱስትሪዎችን 686 ቶን በመላክ 21 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ታቅዶ ለ2 ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ከ4,126 ቶን 11.16 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ በድምሩ በአዲስና ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች በበጀት ዓመቱ ከ53 አምራች

ኢንዱስትሪዎች ከተገኘ ከ22,507.04 ቶን ምርት 112.6 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከ 39 አምራች ኢንዱስትሪዎች የተገኘ 78,576.09 ቶን ምርት በመላክ 127.52 ሚሊዩን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ የገቢ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

## የስራ እድልን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ 176 አነስተኛ፣ 87 መካከለኛ፣ 59 ከፍተኛ በድምሩ 322 አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት በማስገባት ለ9,032 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 140 አነስተኛ፣ 80 መካከለኛ፣ 35 ከፍተኛ በድምሩ 255 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በአዲስ ወደ ምርት በማስገባት ለ7,440 ግለሰቦች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 1290 አነስተኛ፣ 452 መካከለኛ፣ 192 ከፍተኛ በድምሩ 1,934 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከርና በመደገፍ ለ8,529 ግለሰቦች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 797 አነስተኛ፣ 540 መካከለኛ፣150 ከፍተኛ በድምሩ 1,487 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከርና በመደገፍ ለ11,190 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡



በአምራች ኢንዱስትሪዎች የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች-ኮምቦልቻ ፤ደብረ ብርሃን(በቀኝ በኩል

በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለዜጎች ቋሚ የስራ እድል እንዲፈጥሩ መደገፍ

በአጠቃላይ ዘርፎች የአፈፃፀም ለውጥ ባመጡ ፕሮጀክቶች ለ37,532 ግለሰቦች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 36,619 (23,970 ወንድ፣12,649 ሴት) የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 88% ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ  ሲሆን የወጣቶችን ድርሻ ስንመለከት 9,368 ታቅዶ የነበረ ቢሆንም

7,892 ማከናወን ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 84% ነው፡፡ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተም 61 ታቅዶ የነበረ ቢሆንም 13 ማከናወን ተችሏል፤ ከእነዚህ ውስጥ 8 ወንድና 5 ሴት ናቸው፡፡

# III.ማህበራዊ ዘርፍ

## ትምህርትና ስልጠና

### የትምህርት ቤት አመራሮች እና መምህራን ቅጥርና ስምሪት

በ2015 ዓ.ም መጀመሪያ የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ለማሟላት በተሰራው ስራ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 2,271 የጉድኝት ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን 2,218 (ወንድ 2,138፣ ሴት 73) ነባር እና አዲስ ሱፐርቫይዘሮችን በማሰማራት 97.7% የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በሁለተኛ ደረጃ 240 የጉድኝት ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን 226 (ወንድ 212፣ ሴት 14) ነባር እና አዲስ ሱፐርቫይዘሮችን በማሰማራት 94.2% የተሟላ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡

ርዕሰ መምህራንን ለሟሟላት በተሰራው ስራ ለ562 አፀደህፃናት 558 (ወንድ 205፣ ሴት 353) ርዕሰ መምህራን ወይም 99.3%፣ ለ3,577 የአንደኛ ደረጃ (1ኛ - 6ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች 3,512 (ወንድ 3,196፣ ሴት 316) ወይም 98.2%፣ ለ5,767 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች 5,667 (ወንድ 5,338፣ ሴት 329) ወይም 98.3% እና ለ659 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 646 (ወንድ 630፣ ሴት 16) ወይም 98.0% ርዕሰ መምህራንን ማሰማራት ተችሏል፡፡

መምህራንን ለማሟላት በተሰራው ስራ በነባር ስምሪት እና በቅጥር ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ በአጸደ ህፃናት 3,356 (ወንድ 127፣ ሴት 3,229) እና በ "ኦ ክፍል" 9,873 (ወንድ 959፣ ሴት 8,914)፣ ለአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 146,005 (ወንድ 77,130፣ ሴት 68,875) እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ 44,394 (ወንድ 32,502፣ ሴት 11,892) መምህራን በማስተማር ላይ ናቸው፡፡ ከኦ ክፍል ቅድመ አንደኛ ደረጃ በስተቀር በሌሎች ክልላዊ ጥቅል የመምህራን ብዛት በታቀደው መሰረት የተሟላ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል አዳዲስ መምህራንን ለመቅጠር በተደረገው እንቅስቃሴ በአጸደህፃናት ቅድመ-አንደኛ ደረጃ 334 (ወንድ 18፣ ሴት 316)፣ በኦ ክፍል ቅድመ-አንደኛ ደረጃ 880 (ወንድ 69፣ ሴት 811)፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 3,974 (ወንድ 2,529፣ ሴት 1,445) እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ 719 (ወንድ 509፣ ሴት

210) መምህራንን በአዲስ መቅጠር ተችሏል፡፡በድምሩ በሁሉም ደረጃ ቅጥር የተፈፀመላቸው አዲስ መምህራን 5,907 (ወንድ 3,125፣ ሴት 2,782) ሆኗል፡፡

## የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦትና ጥገና

በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁሳቁስ አቅርቦት ለማሟላት በተሰራው ስራ 14,618 አዲስ ጥቁር ሰሌዳዎችን ለማሟላት ታቅዶ 13,706 (93.8%)፣ ኮምባይንድ ዴስኮችን 71,037 ታቅዶ 55,774 (78.5%)፣ ማጣቀሻ መጽሃፍትን 122,931 ታቅዶ 110,630 (90.0%)፣ ሬዲዮኖችን 10,169 ታቅዶ 9,835 (96.7%) እና ሳይንስ ኪቶችን 2,304 ታቅዶ 1,020 (44.3%) ማቅረብ ተችሏል፡፡ ጥገናን በሚመለከት የጥቁር ሰሌዳ የ21,004 ታቅዶ የ19,534 (93.0%) እንዲሁም የኮምባይንድ ዴስክ 84,668 ታቅዶ 83,351 (98.4%) ጥገና ተካሂዷል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁሳቁስ አቅርቦትን ለማሟላት በተሰራው ስራ 3,106 አዲስ ጥቁር ሰሌዳዎችን ለማሟላት ታቅዶ 2,587 (83.3%)፣ ኮምባይንድ ዴስኮችን 19,447 ታቅዶ 11,446 (58.9%)፣ማጣቀሻ መጽሃፍትን 78,526 ታቅዶ 76,044 (96.8%) እንዲሁም ኮምፒተሮችን 4,537 ታቅዶ 2,653 (58.5%) ማሟላት የተቻለ ሲሆን በአዲስ ኬሚካል የቀረበላቸው ትምህርት ቤቶችን ብዛት 482 ታቅዶ 263 (54.6%) ማድረስ ተችሏል፡፡ጥገናን በሚመለከት የጥቁር ሰሌዳ የ5,014 ታቅዶ የ4,771 (95.2%)፣ የኮምባይንድ ዴስክ 29,782 ታቅዶ የ27,317 (91.7%) እና የኮምፒተር 3,172 ታቅዶ የ2,164 (68.2%) ጥገና ማካሄድ ተችሏል፡፡

## የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት

በበጀት አመቱ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የተጓደለባቸውን የተማሪ አርምቸርና ሌሎች የፍርኒቸር ውጤቶችን እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለመማር ማስተማር አስፈላጊ ግብአቶች እንዲሟሉ ተደረጓል፡፡

## የቅደመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (አፀደህፃናት) መሠረተልማት ማሻሻል

አዲስ በተከፈቱ አጸደህፃናት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 140 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ 161 (115.0%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡በሌላ በኩል በነባር ትምህርት ቤቶች መጨናነቅ ለመቀነስ እና ያረጁትን አፍርሶ በአዲስ ለመተካት መማሪያ ክፍል ግንባታ ይሰራል፡፡ በመሆኑም መጨናነቅ በመፈጠሩ ምክንያት በአፀደህፃናት ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ የተገነቡ ክፍሎች 307 ታቅዶ 255 (83.1%) እና በመልሶ መተካት 175 ታቅዶ 196 (113.1%) ማካሄድ ተችሏል፡፡

## የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሠረተልማት ማሻሻል

በበጀት አመቱ መጀመሪያ ከነበሩት 14 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የዳስ ትምህርት ቤቶች መካከል 5 ትምህርት ቤቶችንና 81 መማሪያ ክፍሎችን በሙሉ ወደ ቆርቆሮ መቀየር ተችሏል፡፡ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ በእርጅና እጅግ የተጎሳቆሉና የፈራረሱ ትምህርት ቤቶችን ብዛት 815 ሲሆን ከእነዚህ መካከል በበጀት አመቱ 285 (35.0%) ትምህርት ቤቶችን መልሶ የመገንባት ስራ ተሰርቷል፡፡

በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ አዲስ በተከፈቱ ትምህርት ቤቶች መካከል 354 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ 237 (66.9%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡በሌላ በኩል በነባር ትምህርት ቤቶች መጨናነቅ ለመቀነስ፣ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሳደግ እና ያረጁትን አፍርሶ በአዲስ ለመተካት የመማሪያ ክፍል ግንባታ ይሰራል፡፡ በመሆኑም የነባር ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ተጨማሪ ክፍሎች 1,449 ለመገንባት ታቅዶ 1,299 (89.6%)፣ መጨናነቅ በመፈጠሩ ምክንያት በተጨማሪ የተገነቡ ክፍሎች 3,386 ታቅዶ 3,185 (94.1%) እና በመልሶ መተካት 2,170 ታቅዶ 1,978 (91.2%) ክፍሎች ግንባታ ማካሄድ ተችሏል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሠረተልማት ማሻሻል

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእርጅና እጅግ የተጎሳቆሉና የፈራረሱ ትምህርት ቤቶች ብዛት 8 ሲሆን ከእነዚህ መካከል በበጀት አመቱ የ3 ትምህርት ቤቶች የእቅዱን 37.5% እንዲሁም የ111 መማሪያ ክፍሎችን መልሶ መገንባት ስራ ተሰርቷል፡፡በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ አዲስ በተከፈቱ ትምህርት ቤቶች መካከል 262 መማሪያ ክፍሎችን ለመገንባት ታቅዶ ክንውን 264 (100.8%) ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡ በሌላ በኩል በነባር ትምህርት ቤቶች መጨናነቅ ለመቀነስ፣ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሳደግ እና ያረጁትን አፍርሶ በአዲስ ለመተካት መማሪያ ክፍል ግንባታ እየተሰራ ሲሆን የነባር ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ተጨማሪ ክፍሎች 238

ለመገንባት ታቅዶ ክንውን167 (70.2%)፣ መጨናነቅ በመፈጠሩ ምክንያት በተጨማሪ የተገነቡ ክፍሎች 955 ታቅዶ ክንውን 732 (76.6%) እንዲሁም በመልሶ መተካት 127 ታቅዶ ክንውን 84 (66.1%) ክፍሎች ግንባታ ማካሄድ ተችሏል፡፡

የድጋፍ ሰጭ አገልግሎት ክፍሎች ግንባታ መጸዳጃ ቤት 212 ታቅዶ ክንውን 90 (42.5%)፣ አስተዳደር ክፍል 482 ታቅዶ ክንውን 398 (82.6%)፣ ቤተመጽሃፍት ክፍል 107 ታቅዶ ክንውን 45 (42.1%) እንዲሁም የቤተሙከራ ክፍል 164 ታቅዶ ክንውን 55 (33.5%) ተገንብቷል፡፡ የመጠጥ ውሃ በአዲስ ግንባታና ማስፋፋት በ113 ትምህርት ቤቶች ታቅዶ ክንውን በ57 (50.4%) እና አጥር ግንባታ በ170 ትምህርት ቤቶች ታቅዶ ክንውን በ126 (74.1%) ተካሄዷል፡፡



ዋግ ህምራ ዞን ጋዝ ጊቢላና ድሀና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

የተማሪዎች የነፍስ ወከፍ በጀት ማሟላት

የተማሪዎች የነፍስ ወከፍ በጀት ለማሟላት በተሰራው ስራ ለ2,113,703 ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 21,876,964 (ይህም በአማካይ ብር 10.35 ለአንድ ተማሪ ማለት ነው)፣ ለ1,481,538 የ5ኛ-8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 23,893,782 (በአማካይ ብር 16.13 በተማሪ)፣ ለ615,409 የ9ኛ-10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 13,192,092 (በአማካይ ብር 21.44 በተማሪ) እንዲሁም ለ375,041 የ11ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብር 15,694,548 (በአማካይ ብር 41.85 በተማሪ) በጠቅላላው ለ4,585,691 ተማሪዎች ብር 74,657,384.50 (በአማካይ ብር 16.23 በተማሪ) ተመድቧል፡፡ ይህም በአጠቃላይ በተማሪ ቁጥር መመደብ ከሚገባው ብር 74,420,330.00 ጋር ሲነጻጸር 100.3% ነው፡፡ በሌላ በኩል በአለፈው አመት መጨረሻ በጠቅላላው ለ4,266,470 ተማሪዎች ብር 62,458,278.00 51,049,451.75 (በአማካይ ብር 11.42 በተማሪ) ጋር ሲነጻጸርም ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡

## የትምህርት ቤት የድጎማ በጀት ማሟላት

በ2015 በጀት ዓመት ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም የመንግስት ት/ቤቶች (የአንደኛ፤ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ) ለሚገኙ ተማሪዎች እና የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት በድምሩ ብር 306,146,060.00 የድጎማ በጀት የተመደበ ሲሆን በየደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች እና ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ተሰልቶ ለትምህርት ቤቶች ገንዘቡ ተላልፏል፡፡

## የህብረተሰብ ተሣትፎ

በ2015 በጀት ዓመት እቅድን በመፈፀም ረገድ ከህብረተሰብ ተሣትፎ ብር 2,178,490,431.60 (በጥሬ ገንዘብ ብር 724,858,425.49፣ በቁሣቁስ ብር 608,687,753.54 እና በጉልበት ብር 844,944,252.58) ለማሰባሰብ ታቅዶ ክንውኑ ብር 2,892,173,248.32 (በጥሬ ገንዘብ ብር 1,055,726,888.45፣በቁሣቁስ ብር 738,962,679.06 እና በጉልበት ብር 1,097,483,680.81) ሲሆን በዚህ መሠረት የእቅድ አፈፃፀሙ 132.76% ሆኗል፡፡ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በህብረተሰብ ተሳትፎው የገንዘብ እና ቁሳቁስ ድጋፍ ከፍተኛ ደረጃ የያዘ ሲሆን ትምህርት ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ በተጨባጭ ለመስጠት የተሻለ አፈጻጸም ነው፡፡ ይህን ተሳትፎ ያደረጉ የክልላችን ነዋሪዎች ቁጥርም በድግግሞሽ 35,890,759 (ወንድ 32,489,537፣ ሴት 3,401,222) ለማድረስ ተችሏል፡፡በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች የውስጥ ገቢያቸውን በማመንጨት በየዓመቱ በሚያዘጋጁት ዕቅድ ውስጥ እየተካተተ ለሚያስፈልጋቸው ተግባር የመንግሥትን የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ጠብቀው በስራ ላይ የሚያውሉት ይሆናል፡፡ከዚህ

በመነሣት በትምህርት ዘመኑ በትምህርት ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብር 973,954,501 ለመሰብሰብ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ የነበረው ክንውን ብር 991,815,685 ወይም 101.8% ሆኗል፡፡በተጨማሪም ሰብአዊ ግብአትን ማሟላት ቀዳሚው ተግባር ሲሆን በዚህም ከሚያስፈልገው 225,956 የሰው ሀይል መካከል 220,567 (ወንድ 125,192፣ ሴት 95,375) ወይም 97.6% የዞን/ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎችና ሌሎችም በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡

## ያልተማከለ የትምህርት አመራርና አስተዳደር

በበጀት አመቱ የተደራጁና ውጤታማ የሆኑ የተማሪ ወላጆች ማህበር ብዛት 70% ለማድረስ ታቅዶ በበጀት አመቱ መጨረሻ በተደረገው የማጠናከር ስራ መደራጀት ከሚገባቸው 166 ማህበራት መካከል 110 የተደራጁ በመሆኑ ከእቅዱ 94.7% ተከናውኗል፡፡

## የመጸዳጃ እና ንጽህና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ብዛት 87.2% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 8,281 ወይም 90.2% ትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 103.5% ሆኗል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 40.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 2,946 ወይም 32.1% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 80.2% ሆኗል፡፡

በበጀት አመቱ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶት የመፀዳጃ ቤት ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 98.4% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 641 ወይም 97.3% ትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 98.9% ሆኗል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 70% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 510 ወይም 77.4% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 139.0% ሆኗል፡፡

ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 65.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4,430

ወይም 47.4% ትምህርት ቤቶች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 72.9% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 85.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 511 ወይም 77.5% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 91.2% ሆኗል፡፡



ሰሜን ወሎ ዞን ሮቢት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

አዲስ የተገነባ መፀዳጃ ቤት

### ኮምፒውተር ቤተሙከራና የሳይንስ ላብራቶሪ አገልግሎት ማሻሻል

በብሮድባንድ ኔትዎርክ መሰረተ ልማት ተሳስረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በበጀት አመቱ መጨረሻ 50% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 308 ወይም 46.7% ትምህርት

ቤቶች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ሲሆኑ ከታቀደው አፈፃፀሙም 93.5% ሆኗል፡፡ የተደራጀ የኮምፒዩተር ክፍል ያላቸውን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በበጀት አመቱ መጨረሻ 90.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 524 ወይም 88.3% ትምህርት ቤቶች የተደራጀ የኮምፒዩተር ክፍል ያላቸው ከታቀደው አፈፃፀሙም 88.3% ሆኗል፡፡

የሣይንስ ቤተ-ሙከራ ክፍል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 51.9% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4,847 ወይም 51.9% ትምህርት ቤቶች የሣይንስ ቤተ-ሙከራ ክፍል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 99.9% ሆኗል፡፡ በሶስቱም የትምህርት አይነቶች የሳይንስ ላብራቶሪ የተሟላላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 65.5% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 334 ወይም 50.7% ትምህርት ቤቶች በሶስት የሳይንስ ትምህርት አይነቶች ቤተ-ሙከራ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 77.4% ሆኗል፡፡



## የትምህርት ቤት ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ክፍሎችን ማሟላት

በበጀት አመቱ ቤተመጻህፍት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 63.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 5,454 ወይም 59.4% ትምህርት ቤቶች ቤተመጻህፍት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙም 94.3% ሆኗል፡፡ ቤተመጻህፍት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 96.7% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 635 ወይም 96.4% ትምህርት ቤቶች ቤተመጻህፍት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙም 99.7% ሆኗል፡፡

የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 73.9% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 6,507 ወይም 69.6% ትምህርት ቤቶች ማዕከል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 94.2% ሆኗል፡፡በሁለተኛ ደረጃ የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 77.6% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 523 ወይም 79.4% ትምህርት ቤቶች የስርዓተ-ትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 102.3% ሆኗል፡፡

የስፖርት ሜዳ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 84.2% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 6,980 ወይም 74.7% ትምህርት ቤቶች ሜዳ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 88.8% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የስፖርት ሜዳ ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት 90.1% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 579 ወይም 87.9% ትምህርት ቤቶች ሜዳ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 97.5% ሆኗል፡፡

## የተቋማት ግንባታ ማስፋፋት፣ እድሳት እና ጥገና

በመንግስት፣ በህብረተሱ እና በአጋር አካላት የተገነቡ አዲስ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት 166 ለማድረስ ታቅዶ 49 ትምህርት ቤቶች ወይም ከታቀደው 29.5% ተገንብተው ተጠናቀዋል፡፡ እድሳት ያካሄዱ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 2,815 ለማድረስ ታቅዶ የ2,498 ትምህርት ቤቶች እድሳት ተካሂዷል፡፡ በመሆኑም

ከታቀደው አንጻር አፈፃፀሙ 88.7% ሆኗል፡፡ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተቋማትን በማስፋፋት ረገድ ደረጃቸውን ያሳደጉ (ከ1ኛ - 6ኛ ወደ 1ኛ - 8ኛ) ትምህርት ቤቶች ብዛት 75 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በበጀት አመቱ 70 ትምህርት ቤቶች ወይም ከታቀደው 93.3% ደረጃቸውን ከአንደኛ ደረጃ ወደ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ወደ 1ኛ - 8ኛ) አሳድገዋል፡፡

በተመሳሳይ በመንግስት፣ በህብረተሱ እና በአጋር አካላት የተገነቡ አዲስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 27 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን እስከ አመቱ መጨረሻ 13 ትምህርት ቤቶች ወይም ከታቀደው 48.1% ተገንብተው ተጠናቀዋል፡፡ እድሳት ያካሄዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት አስከ አመቱ መጨረሻ 71 ለማድረስ ታቅዶ የ121 ትምህርት ቤቶች እድሳት ተካሂዷል፡፡ ይህም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከታቀደው አንጻር አፈፃፀሙ 170.4% ሆኗል፡፡

## በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራት

በበጀት አመቱ እንዲከናወኑ ከታቀዱ ተግባራት አንዱ በተማሪዎች ስነ ምግባርና ባህሪ የረኩ የተቋም ማህበረሰብ ክፍል እና ወላጆች ብዛት በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 60.15% ወደ 69% ማድረስ ታቅዶ በዚህም መሰረት የዚህ ዕቅድ አፈጻጸም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በዚህ ጥናት 10 ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች፣17 ወረዳዎች እና 23 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡በጥናቱ በጥቅሉ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የተቋማትና የወላጆች ዕርካታ 52.4% ነው፡፡ ይህ ውጤት ባለፈው ዓመት ከተመዘገበው በ7.75% ያነሰ ሲሆን ከዕቅዱ ደግሞ በ16.6% ያንሳል፡፡ይህም በተማሪዎች ስነምግባር የወላጆችና የተቋማት ርካታ ከአማካይ በላይ ቢሆንም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ውጤቱ ጉዳዩን በቀጣይ ወካይ የሆነ ቁጥር በመጠቀም አጥንቶ ችግሮችን በመለየት ስልት ተቀይሶ መሰራ ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

በትምህርት ቤት በአንድና ከዚያ በላይ ክበባት /በልዩ ልዩ ተጓዳኝ ትምህርት/ የሚሳተፉና አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎች ተሳትፎ 70% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ 4,554,039 (ወንድ 2,217,386፣ ሴት 2,336,653) ተማሪዎች መካከል 3,521,218 (ወንድ 1,724,938፣ ሴት 1,796,280) ተሳታፊዎችን ማለትም 77.3% (ወንድ 77.8%፣ ሴት 76.9%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከታቀደው 110.5% ነው፡፡

ለማህበረሰቡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎች ተሳትፎ ባለፈው አመት ከነበረበት 40% ወደ 48% ለማድረስ ታቅዶ ከ1,678,207 (ወንድ 756,598፣ ሴት 921,609) የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል 828,551 (ወንድ 422,888፣ ሴት 405,663) በበጎ ፈቃድ የተሳተፉ ተማሪዎችን ወይም 49.4% (ወንድ 55.9%፣ ሴት 44.0%) ማድረስ ተችሏል፡፡

## የመምህራንን እና ትምህርት አመራሩን የትምህርት ደረጃ ማሟላት

ለደረጃው የተቀመጠውን (ሰርትፊኬትና በላይ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 62.0% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ በደረጃው በማስተማር ላይ ከሚገኙት 13,229 (ወንድ 1,086፣ ሴት 12,143) መካከል በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሰርትፊኬትና በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን 11,563 (ወንድ 835፣ ሴት 10,728) ወይም 87.4% (ወንድ 76.9%፣ ሴት 88.3%) በማድረስ ከእቅዱ 106.6% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የዲፐሎማ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በአመቱ መጨረሻ 100% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በደረጃው በማስተማር ላይ ከሚገኙት 85,217 (ወንድ 40,345፣ ሴት 44,872) መካከል የዲፐሎማ የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን 84,460 (ወንድ 40,081፣ ሴት 44,379) ወይም 99.1% (ወንድ 99.3%፣ ሴት 98.9%) በማድረስ ከእቅዱ 99.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በአመቱ መጨረሻ 14.5% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በደረጃው በማስተማር ላይ ከሚገኙት 60,788 (ወንድ 36,785፣ ሴት 24,003) መካከል የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን 10,089 (ወንድ 6,074፣ ሴት 4,015) ወይም 16.6% (ወንድ 16.5%፣ ሴት 16.7%) በማድረስ ከእቅዱ 114.5% መፈጸም ተችሏል፡፡በተጨማሪም የመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በ2015ዓ.ም 100% ለማድረስ ታቅዶ በደረጃው በማስተማር ላይ ከሚገኙት 43,462 (ወንድ 31,974፣ ሴት 11,488) መካከል ዲግሪና በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን 43,305 (ወንድ 31,843፣ ሴት 11,462) ወይም 99.6% (ወንድ 99.6%፣ ሴት 99.8%) በማድረስ ከእቅዱ 99.6% መፈጸም ተችሏል፡፡እንዲሁም ለደረጃው የተቀመጠውን የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ብዛት በመቶኛ በ2015ዓ.ም 86.4% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ በስራ ላይ ከሚገኙት 9,189 (ወንድ 8,542፣

ሴት 647) አመራሮች መካከል ዲግሪና በላይ ያላቸው 8,143 (ወንድ 7,555፣ ሴት 588) ወይም 88.6% (ወንድ 88.4%፣ ሴት 90.9%) ሲሆን ከታቀደው 102.6% መፈጸም የተቻለ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰመምህራን ብዛት በመቶኛ እስከ አመቱ መጨረሻ 79.5% ለማድረግ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 646 (ወንድ 630፣ ሴት 16) የደረጃው ርዕሰመምህራን መካከል ሁለተኛ ድግሪ ያላቸውን 516 (ወንድ 500፣ ሴት 16) ወይም 79.9% (ወንድ 79.4%፣ ሴት 100.0%) በማድረስ ከታቀደው 100.5% መፈጸም ተችሏል፡፡ለደረጃው የተቀመጠውን (የመጀመሪያ ዲግሪ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ብዛት በ2015ዓ.ም 100% ለማድረግ ታቅዶ እስከ ዓመቱ መጨረሻ በክልሉ ከሚገኙ 2,218 (ወንድ 2,138፣ ሴት 80) የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች መካከል የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸውን 2,171 (ወንድ 2,093፣ ሴት 78) ወይም 97.9% (ወንድ 97.9%፣ ሴት 97.5%) በማድረስ ከታቀደውም 97.9% መፈጸም ተችሏል፡፡በመጨረሻም ለደረጃው የተቀመጠውን (ሁለተኛ ዲግሪ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች ብዛት በ2015 ዓ.ም 94.0% ለማድረግ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ 226 (ወንድ 212፣ ሴት 14) የሁለተኛ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች መካከል ሁለተኛ ድግሪ ያላቸውን 214 (ወንድ 200፣ ሴት 14) ወይም 94.7% (ወንድ 94.3%፣ ሴት 100.0%) በማድረስ ከታቀደው ጋር ሲነፃፀርም 100.7% መፈጸም ተችሏል፡፡

## የመምህራን እና ትምህርት አመራሩ ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ

በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ በበጀት አመቱ ወደ 100.0% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 146,005 (ወንድ 77,130፣ ሴት 68,875) መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 140,527 (ወንድ 74,028፣ ሴት 66,499) ወይም 96.2% (ወንድ 96.0%፣ ሴት 96.6%) በማድረስ ከእቅዱ 96.2% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ድርሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 43,462 (ወንድ 31,974፣ ሴት 11,488) መምህራን መካከል ተሳታፊዎችን 42,232 (ወንድ 31,192፣ ሴት 11,040) ወይም 97.2% (ወንድ 97.6%፣ ሴት 96.1%) በማድረስ የእቅዱን 97.2% መፈጸም ተችሏል፡፡በተጨማሪም በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ርዕሰመምህራን ድርሻ በበጀት አመቱ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ ርዕሰመምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን

8,906 (ወንድ 8,301፣ ሴት 605) ወይም 97.0% (ወንድ 97.3%፣ ሴት 93.8%) በማድረስ ከእቅዱም 97.0% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰመምህራንን ድርሻ በበጀት አመቱ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ ርዕሰመምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 623 (ወንድ 608፣ ሴት 15) ወይም 96.4% (ወንድ 96.5%፣ ሴት 93.8%) በማድረስ የእቅዱን 96.4% መፈጸም ተችሏል፡፡በተጨማሪም በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በበጀት አመቱ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከሚገኙ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 2,176 (ወንድ 2,100፣ ሴት 76) ወይም 98.1% (ወንድ 98.2%፣ ሴት 95.0%) በማድረስ ከእቅዱም 98.1% መፈጸም ተችሏል፡፡

## የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን ማሻሻል

በበጀት አመቱ የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት 1:50 እና በመካከለኛ ደረጃ 1:40 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን እስከ አመቱ መጨረሻ በጥቅሉ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃዎች 3,591,326 ተማሪዎች በ96,978 ሴክሽኖች በመማር ላይ ሲሆን ጥምርታው በጥቅሉ 1:37 ሆኗል፤ በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 135.0% ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ 962,713 ተማሪዎች በ17,880 ሴክሽኖች ለመማር በመምዝገባቸው ጥምርታው 1:54 ደርሷል፤ በመሆኑም የእቅድ አፈጻጸሙ 74.3% ነው፡፡

## ክበባትንና የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ማጠናከር

በበጀት አመቱ መጨረሻ በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በተሰበሰበ መረጃ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 3,014,828 (ወንድ 1,488,192፣ ሴት 1,526,636) ተማሪዎች እና በሁለተኛ ደረጃ 661,421 (ወንድ 303,019፣ ሴት 358,402) ተማሪዎች ተሳታፊ በልዩ ልዩ ክበባት ውስጥ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

በዚህም የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ክበብ ያላቸው አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 100% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 8,964 ወይም 95.9% ትምህርት ቤቶች ክበቡ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙም

95.9% ሆኗል፡፡ የመንገድ ደህንነት ክበብ ያላቸው አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 5,001 ወይም 53.5% ትምህርት ቤቶች ክበቡ ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 53.5% ሆኗል፡፡

በትምህርት ቤቶች የተደራጁ የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ብዛት 234 ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል 282 ትምህርት ቤቶች ድጋፍ መስጫ ማዕከል ያደራጁ ሲሆን ከታቀደው አንፃር አፈፃፀሙ 120.5% ሆኗል፡፡

## የትምህርት ተቋማት ለመማር ማስተማር ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ

የኢንስፔክሽን አገልግሎትን በሚመለከት የሚጠበቁ ውጤቶችን በማካተት እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በአመቱ መጨረሻ የማጠቃለያ መጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ አፀደሕፃናት ት/ቤቶች ብዛት በቁጥር 10 ለማድረስ ታቅዶ ለ 10 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ በመሰጠቱ የእቅድ አፈጻጸሙ 100% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የማጠቃለያ መጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ ኦ-ክፍል ት/ቤቶች ብዛት 48 ለማድረስ ታቅዶ በ48 ትምህርት ቤቶች ተከናውኗል፤ይህም ከእቅዱ 100% የተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡

የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 3,588 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ለ3,600 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ ተሰጥቶ የእቅድ አፈፃፀሙ 100.3% ደርሷል፡፡ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ያገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት እስከ አመቱ መጨረሻ 259 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ለ260 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ ተሰጥቶ የእቅድ አፈፃፀሙ 100.4% ደርሷል፡፡ በኢንስፔክሽን አፈፃፀም ከደረጃ በታች ለሆኑ አፀደህጻናት የቅድመ-አንደኛ ት/ቤቶች የተሰጠ ዳግም ኢንስፔክሽን አገልግሎት ብዛት በቁጥር እስከ አመቱ መጨረሻ 236 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ለ253 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ ተሰጥቶ የእቅድ አፈፃፀሙ 107.2% ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ ለ"ኦ" ክፍል የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተሰጠ ዳግም ኢንስፔክሽን አገልግሎት ብዛት በቁጥር እስከ አመቱ መጨረሻ 161 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ለ225 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱ ተሰጥቶ የእቅድ አፈፃፀሙ 139.8% ደርሷል፡፡

በስርዓተትምህርት ዝግጅት የታቀደ ኢላማ ዝግጅታቸው የተጠናቀቀ እና በሙከራ ትግበራ የዳበሩ የግዕዝ መማሪያና የማስተማሪያ መጽሃፍት ብዛት በአለፈው አመት ከነበረበት 2 በበጀት

አመቱ መጨረሻ ወደ 4 ክፍ ማድረግ (የአንድ ክፍል ደረጃ መጨመር) ሲሆን በ2015 ዓ.ም የግዕዝ ትምህርት ሙከራ ትግበራ ለማካሄድ በአራት ዞኖች 6 ትምህርትቤቶች ተመርጠው 6 መምህራን እንዲዘጋጁ የተደረገ ሲሆን በ3ኛ ክፍል ትምህርቱን ለማስጀመር የሚያስችል የአምስት ቀናት ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በ3 ቋንቋ ዝግጂታቸው ተጠናቆ ለ2016 ዓ.ም ሙሉ ትግበራ ዝግጁ የሆኑ የ2ኛ ደረጃ (9ኛ እና 10ኛ ክፍል) መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ብዛት 12 ሆኗል በሚለው የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍሎች የሶስት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አዊኛ እና ኦሮሞኛ) መጻሕፍት ዝግጅትን በተመለከተ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማሩ ምቹ ለማድረግ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ንፁህ መጠጥ ውሀ መገንባት ተችሏል፡፡



የንፁህ መጠጥ ውሀ ግንባታ -ጣና ሀይቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-ባህርዳር

## አዲስ ስርዓተትምህርት በሙሉ ትግበራ ደረጃ ማካሄድ

በ2015 ዓ.ም ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ብዛት 340 ለማድስ ታቅዶ ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸውን መጻሕፍት ብዛት 324 (162 መማሪያ፣ 162 ማስተማሪያ) ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.3% ነው፡፡ የተሟላ አፈጻጸም ማስመዝገብ ያልተቻለው የትርጉም ስራው ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ወደ ሙሉ ትግበራ ያልተገባበት በኦሮሞኛ ቋንቋ የሥነ ጥበብ ትምህርት 16 (8 መማሪያ፣ 8 ማስተማሪያ) መጽሐፍት በመኖራቸው ነው፡፡ ነገርግን በ2015 ዓ.ም ዝግጅቱ ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል፡፡

## የሙሉ ትግበራ መጽሃፍት ትውውቅ

የመጽሃፍት ትውውቅን በሚመለከት አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ ትግበራ የሚፈጽሙ በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ 152,840 መምህራን እና ቅድመ አንደኛ ክፍል ደረጃ 1 ለሚያስተምሩ 9,193 አመቻቾች የሥርዓተ ትምህርት የትውውቅ ስልጠና አግኝተው ወደ ስራ ገብተዋል የሚል አመልካች ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በመጀመሪያ በክልሉ 9,511 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 2,323 የጉድኝት ማዕከላት እና ከ 152,840 በላይ የመጀመሪያና የመካከለኛ ደረጃ መምህራን ያሉ ሲሆን ሙሉ ትግበራ የተገባበትን አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ለሁሉም መምህራን በማስተዋወቅ የመማር መስተማሩን ሂስለሆነም ሥርዓተ ትምህርቱን ለመምህራን ለማስተዋወቅ አስተባባሪ በነበሩ አካላት የማሰልጠኛ ሞጁል ተዘጋጅቶ የአሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡ ዋና አሰልጠኞችን መጽሐፍት ካዘጋጁ መምህራን መካከል 73 (ወንድ-70 ሴት-3) ተመልምለው ስልጠና በመስጠት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህም በመቀጠል 657 (ወንድ 482፣ ሴት 175 ) በክልል ደረጃ ለጉድኝት አሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡ መምህራን እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ሂደቱ የተቃና እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር የቢሮው ቀዳሚ ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡በዚህም ሂደት በክልል ደረጃ መሰልጠን ያለባቸው 20,317 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ሲሆኑ በጉድኝት ማዕከል ደረጃ ደግሞ 132,523 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ይሰለጥናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ የሚሰጠው ሥልጠና ለሁሉም 21 ዞኖች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ሂደት የአሰልጣኖች ስልጠና የወሰዱ መምህራን በድምር 21,538 ( ወንድ 14,544፣ ሴት 6,994) ሲሆኑ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ 106% ይሆናል፡፡ በተለያየ ዙር እና የሥልጠና ማዕከላት በአሰልጣኝነት የተሳተፉ መምህራን 1,680( ወንድ 1,294፣ ሴት 386) ሲሆኑ የዞንና የወረዳ

ባለሙያዎች 534(ወንድ 449፣ ሴት 85) በአስተባባሪነት በሂደቱ ተሳትፈዋል፡፡ መረጃ ከላኩት 19 ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች ሥልጠናውን ይወስዳሉ ተብለው የተለዩት 110,953 (ወንድ 59,170፣ ሴት 51,783) መምህራን ሲሆን ስልጠና የወሰዱት 98,192 (ወንድ 53,172፣ ሴት 45,020) መምህራን ናቸው፤ አፈጻጸሙም 89% መሆኑን የተላከው መረጃ ያሳያል፡፡ በተለያየ ምክንያት 12,761( 5,998 ሴት 6,763) መምህራን ወይም 11% የመጽሐፍ ትዉዉቅ ስልጠናውን አልወሰዱም፡፡ ይህም ዞንና ወረዳ የ2016 ዓ.ም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሥልጠና ያልወሰዱ መምህራንን በትምህርት አይነት በመለየ የሥርዓተ ትምህርት ትውውቅ ማድረግ የሚገባ መሆኑን መረጃው ያስገነዝባል፡፡

## የመጽሃፍት አቅርቦት

የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የተማሪ መፀሀፍት ጥምርታ 1:3 እንዲሆን በተያዘው እቅድ መሰረት የተሰሩ ዝርዝር ስራዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ በሙሉ ትግበራ ሊገቡ በሚችሉ 460 የየትምህርት አይነቱ መጽሃፍት ለተማሪዎች 1 ለ 1 ለማዳረስ በቁጥር የሚያስፈልገው የመጽሃፍት ብዛት 31,668,812 ይሆናል፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው በጀት ከፍተኛ በመሆኑ በበጀት አመቱ 1 ለ 3 ለማዳረስ 8,888,172 መጽሃፍትን ለማሳተም ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡ እየታተመ ያለውን መጽሐፍት የናሙና ማረጋገጥ ስራ እስከ ነሀሴ 10 የተሰራ ቢሆንም እስከ 3ኛዉ ሩብ ዓመት የገባዉ 1,438,324( አማርኛ፣ ሂሳብና አካባቢ ሳይንስ-7ኛ ክፍል፤ እንግሊዝኛ 5 እና 6ኛ ክፍል፤ አካባቢ ሳይንስ 6ኛ ክፍል እና አዊኛ ቋንቋ 3፣6ና 7ኛ ክፍል) ዘጠኝ የትምህርት ዓይነት ብቻ ነበር፡፡ እስከ አራተኛዉ ሩብ ዓመት ለህትመት ከተሠጡት 44 ዓይነት ማስተማሪያ መጽሐፍት መካከል ተጨማሪ 12 ዓይነት መጥተው የመጽሐፍቱን ትክክለኛ ነት ከካሜራ ሬዲው ጋር ተረጋግጦ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል፡፡ በመሆኑም ከ44 ዓይነት መጽሐፍት 21 ዓይነት አገር ውሥጥ ገብተዋል፡፡ ሌሎች 23 ዓይነት መጽሐፍት በጉዞላይ እንደሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በተጨማሪም ቢያንስ ለመምህራን የሚሆን በትምህርት ቤት ደረጃ ሁለት ሁለት በየትምህርት አይነቱ እንዲደርስ ታስቦ 52 የትምህርት አይነት የተማሪዎች መጽሐፍት ብዛት 944,882 ታትሞ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡በሦስቱ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ትርጉም የተሰራላቸው መጽሐፍት፣ አፋን ኦሮሞ አፍመፍቻ እና ኸምጣና አፍመፍቻ ቋንቋ በአጠቃላይ 82 አይነት 835,732 የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች 1:1 በሚደርስ ሁኔታ የዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በመስጠት ህትመቱ እየተካሄደ ሲሆን የህትመት ናሙና

የማረጋገጥ ስራም ተሰርቷል፡፡ በሦስቱ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ትርጉም የተሰራላቸው መጽሐፍት፣ አፋን ኦሮሞ አፍመፍቻ እና ኽምጣና አፍመፍቻ ቋንቋን ጨምሮ በአጠቃላይ 82 አይነት 835,732 (የአፋን ኦሮሞ 326427፣ የኽምጠኛ 220821፣ አዊኛ 288484) የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች 1:1 በሚደርስ ሁኔታ የዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በመስጠት ህትመቱ ተጠናቆ ለተማሪዎች በመሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡

IRC የሚባል ረጂድርጅት ከሌጎ ፋውንዴሽን ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ካሜራሬዲውን ከቢሮው በመውሰድ 24 ሚሊዮን ብር በሚሆን ወጭ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች 87,590 መማሪያ መጽሐፍት ታትመው መጥተው የቢሮውና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት በ29/07/2015 ዓ.ም ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ መጽሐፉም በጦርነቱ ተጎድተው ለነበሩ 6 ዞኖች፣ 27 ወረዳዎች ስር ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ድርጅቱ እያሰራጨ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ እስከ ሩብ አመቱ መጨረሻ በድምሩ 3,306,528 መጽሃፍት ታትመው የተሰራጨ ሲሆን ቀሪዎቹን መጽሃፍት ለማስገባት የሚጠበቀው የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ተገኝቶ ሁሉም መጽሃፍ ወደ አገር ውስጥ የገባ በመሆኑ በቀሪ ወራት ገብተው ወደ ትምህርት ቤት የማሰራጨት ስራ ይሰራል፡፡

## የስርዓተ-ትምህርት ግምገማ

ስርአተትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተደረጉ ጥናትና ምርምር (ተግባራዊ እና መሠረታዊ) ብዛት 2,631 ለማድረስ ታቅዶ በአመቱ መጨረሻ የተሰሩ ምርምሮች ብዛት 13,575 (ተግባራዊ12,471 እና መሰረታዊ 1,104) በመሆናቸው ከእቅዱ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡2015 ዓ.ም የተሻለ ጥናትና ምርምር (ተግባራዊ እና መሰረታዊ) በመስራት በክልል ደረጃ እዉቅና የተሰጣቸው የመምህራንና ትምህርት ባለሙያዎች 6 ሆኗል፡፡

በ2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና ከወሰዱት 336,261(ወንድ 153,459፣ ሴት 182,802) ተማሪዎች መካከል ከ50% በላይ ያስመዘገቡት 228,430 (ወንድ 106,163፣ሴት 122,267) አፈጻጸሙም 67.93% (ወ 68.98%፣ ሴ 66.88%) ይሆናል፡፡ በ2013 የትምህርት ዘመን ለፈተና ከተቀመጡት መካከል 50% እና በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች 67.08% (ወንድ 68.3%፣ ሴት 65%) ሲሆኑ በበጀት አመቱ የተመዘገበው የተማሪዎች ውጤት ከአምናው ጋር ሲነፃፀር የ2014 በጀት ዓመት መጠኑ

የጨመረ ቢሆንም ከተቀመጠው ግብ አኳያ ሲታይ ያልተደረሰ ስለሆነ በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራርና ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ለ8ኛ ክፍል በተወሰነው የመቁረጫ ነጥብ መሰረት በ2015 በጀት ዓመት ወደ 9 ክፍል የተዛወሩ ተማሪዎች 315,185 (ወንድ 142,930፣ ሴት 172,255) ሲሆኑ አፈጻጸሙ 93.73% (ወንድ 93.14%፣ ሴት 94.23%) ሆኗል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች 50% እና በላይ፣ 35% የሚሆኑ ተማሪዎች 75%ና በላይ እንዲሁም 15% የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ 85%ና በላይ ማምጣት የሚል ግብ ተጥሎ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን አፈጻጸሙ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት ዓይነት 50% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት 100% ለማድረስ ታቅዶ በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ለፈተና ከተቀመጡ 4,191,005 (ወንድ 2,023,045፣ ሴት 2,167,960) ተማሪዎች መካከል 50% እና በላይ ያመጡ 3,710,650 (ወንድ 1,790,599፣ ሴት 1,920,051) ወይም 88.5% (ወንድ 88.5%፣ ሴት 88.6%) ናቸው፤ በመሆኑም ከእቅዱ  አፈጻጸሙ 88.5% ነው፡፡

በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 75% እና በላይ ተማሪዎች ብዛት 35% ለማድረስ ታቅዶ በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ለፈተና ከተቀመጡት ተማሪዎች መካከል 75% እና በላይ ያመጡ 1,070,503 (ወንድ 543,344፣ ሴት 527,159) ወይም 25.5% (ወንድ 26.9%፣ ሴት 24.3%) ናቸው፡፡ በመሆኑም ከእቅዱ አፈጻጸሙ 73.0% ነው፡፡ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁሉም የትምህርት ዓይነት  85% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት 15% ለማድረስ ታቅዶ በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ለፈተና ከተቀመጡት ተማሪዎች መካከል 85% እና በላይ ያመጡ 515,539 (ወንድ 266,292፣ ሴት 249,247) ወይም 12.3% (ወንድ 13.2%፣ ሴት 11.5%) ናቸው፤ በመሆኑም ከእቅዱ  አፈጻጸሙ 82.0% ደርሷል፡፡

## የሒሳብና ሳይንስ ትምህርትን ጥራት ማሻሻል

የተሟላ ቤተሙከራ ካላቸው 334 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ለSTEAM ፕሮግራም የተሟላ ላብራቶሪ ያደራጁ ብዛት በመቶኛ 25.% ለማድረስ ታቅዶ ያደራጁትን ትምህርት ቤቶች 97 ወይም 29% ማድረስ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እቅድ አፈፃፀሙ 116.2%

ነው፡፡የሳይንስ ቤተሙከራ አደረጃጀትን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለው ጥረት ይደረጋል፡፡ በSTEAM የስራ ላይ ስልጠና የሰለጠኑ መምህራን ብዛት 37% ለማድረስ ታቅዶ በክልል ደረጃ ለ489 (ወንድ 437፣ ሴት 52) የሳይንስ መምህራኖች ተግባራዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ሂደት ወንድ 22 ሴት 2 ድምር 24 አሰልጣኞች ተሳትፈዋል፡፡ ከትምህርት ሚኒስተር ጋር በመቀናጀት ለ 55 (ወንድ 54፣ ሴት 1) የትምህርት አመራሮች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በክልል ደረጃ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች ብዛት በቁጥር በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 10 በ2015 በጀት ዓመት ወደ 20 ከፍ ብሏል በሚለው ውጤት በየትምህርት ቤቱ ከሚገኙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የክበብ አባላት በየደረጃው ማለትም በትምህርት ቤት፣ በወረዳ እና በዞን ተመልምለው በመጡ የፈጠራ ስራ ባለቤቶች ተሳታፊነት ከግንቦት 25 -28/2015 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አመራር ኢንስቲትዮት ክልላዊ የሳይንስ የፈጠራ ስራዎች አውደ ርዕይ ውድድር በሦስት ምድቦች ተካሂዷል፡፡ በዚህም ሂደት 94 የፈጠራ ባለቤት ተማሪዎች ለውድድር የቀረቡ ሲሆን ከሦስቱ ምድብ ከ1ኛ-7ኛ ደረጃ ለያዙ 21 ተማሪዎች ዕውቅናና የብር ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ ከሴት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ለአመጣች አንድ ተማሪ የብር ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የዓለም የሳይንስ ቀንን ምክንያት በማድረግ ለ7ኛ ጊዜ በተካሄደው የፈጠራ ስራ ውድድር ክልሉን ወክለው ከቀረቡት 7 የፈጠራ ስራ ተወዳዳሪ ተማሪዎች መካከል ሁለቱ የደረጃ ተሸላሚ በመሆን ላፕቶፕ እና ታብሌት ያገኙ ሲሆን እንደ ክልል ቢሮውም በአጠቃላይ ውጤት 3ኛ ደረጃ በመያዙ የደረጃ የምስክር ወረቀት እና የዋንጫ ተሸላሚ ሁኗል፡፡

## የቅድመ አንደኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ

በበጀት አመቱ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በክልላችን 895,404 (ወንድ 455,726፣ ሴት 439,677) ነባርና አዲስ ገቢ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 46.33% (ወንድ 45.73% ወንድ፣ ሴት 45.81%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 783,926 (ወንድ 400,226፣ ሴት 383,700) ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 39.97% (ወንድ 40.05%፣ ሴት 39.89%) ሲሆን ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ 88.3% (ወንድ 88.6%፣ ሴት 88.0%) ሆኗል፡፡ የበጀት አመቱ አፈፃፀም ከአለፈው አመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሻሻል ያሳየ ነው፡፡

## የቅድመ አንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የክልላችን ንጥር ተሳትፎውን 45.50% (ወንድ 45.50% ወንድ፣ ሴት 45.50%) ለማድረስ ታቅዶ እድሜያቸው ከ4 — 6 ዓመት የሆናቸው እና በደረጃው የተመዘገቡ 779,564 (ወንድ 398,053፣ ሴት 381,511) ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 39.75% (ወንድ 39.83%፣ ሴት 39.66%) ሲሆን ከታቀደው ጋር ሲነጻጸር አፈፃፀሙ 91.4% (ወንድ 91.7%፣ ሴት 91.0%) ሆኗል፡፡

## የአንደኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ

በሁሉም እድሜ በአንደኛ ክፍል 745,709 (ወንድ 380,955፣ ሴት 364,754) ለመጀመሪያ ግዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ የጥቅል ቅበላ ምጣኔውን 104.36% (ወንድ 104.70%፣ ሴት 104.00%) ለማድረስ ታቅዶ 627,667 (ወንድ 332,822፣ ሴት 294,845) ተማሪዎችን ምዝገባ በማከናወን የምዝገባ አፈፃፀሙ 88.26% (ወንድ 91.96%፣ ሴት 84.43%) እና የጥቅል ቅበላ አፈፃፀሙ 84.6% (ወንድ 87.8%፣ ሴት 81.2%) ሆኗል፡፡

## የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ

የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ በተመለከተ በበጀት አመቱ በክልላችን 711,148 (ወንድ 361,937፣ ሴት 349,211) የአንደኛ ደረጃ በ7 ዓመት እድሜ ለመጀመሪያ ግዜ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ቅበላ ምጣኔውን 100% (ወንድ 100%፣ ሴት 100%) ለማድረስ ታቅዶ 556,757 (ወንድ 291,399፣ ሴት 265,358) ተማሪዎችን ምዝገባ በማከናወን የምዝገባና ንጥር ቅበላ አፈፃፀሙ 78.29% (ወንድ 80.51%፣ ሴት 75.99%) ሆኗል፡፡ የእቅድ አፈጻጸሙ አነስተኛ ቢሆንም ከአለፈው አመት ጠቅላላ ተመዝጋቢዎች ጋር ሲነፃፀር በበጀት አመቱ የተመዘገቡ 7 አመት የሞላቸው ህጻናት ቁጥር ከፍ ያለ ነው፡፡

## የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ

በበጀት አመቱ በክልላችን 3,270,172 (ወንድ 1,668,581፣ ሴት 1,601,591) ነባርና አዲስ ገቢ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 81.21% (ወንድ 82.11%፣ ሴት 80.30%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,875,832 (ወንድ 1,460,788፣ ሴት 1,415,044) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 63.73% (ወንድ 63.86%፣ ሴት 63.58%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 78.5% (ወንድ 77.8%፣ ሴት 79.2%) ሆኗል፡፡

## የአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ

በበጀት አመቱ በክልላችን እድሜያቸው ከ7-12 አመት የሆናቸውን ነባርና አዲስ ገቢ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 74.71% (ወንድ 75.61%፣ ሴት 73.80%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 2,566,001 (ወንድ 1,297,807፣ ሴት 1,268,194) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 63.73% (ወንድ 63.86%፣ ሴት 63.58%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 85.3% (ወንድ 84.5%፣ ሴት 86.2%) ሆኗል፡፡

## የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ

በ2015 ዓ.ም በክልላችን 846,486 (ወንድ 404,106፣ ሴት 442,380) የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 70.26% (ወንድ 65.47% ፣ ሴት 75.30%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 715,494 (ወንድ 329,029፣ ሴት 386,465) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 59.39% (ወንድ 53.30%፣ ሴት 65.79%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 84.5% (ወንድ 81.4%፣ ሴት 87.4%) ሆኗል፡፡

## የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ

በበጀት አመቱ በክልላችን እድሜያቸው ከ13-14 አመት የሆናቸውን የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 47.79% (ወንድ 43.00%፣ ሴት 52.83%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 533,238 (ወንድ 241,017፣ ሴት 292,221) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 44.26% (ወንድ 39.04%፣ ሴት 49.74%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 92.6% (ወንድ 90.8%፣ ሴት 94.2%) ሆኗል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ

በ2015 ዓ.ም በክልላችን 1,214,323 (ወንድ 558,084፣ ሴት 656,239) የሚሆኑ ነባርና አዲስ ገቢ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 47.57% (ወንድ 43.03%፣ ሴት 52.26%) ለማድረስ ታቅዶ 962,713 (ወንድ 427,569፣ ሴት 535,144) በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎው 37.71% (ወንድ 32.97%፣ ሴት 42.62%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 79.3% (76.6% ወንድ፣ 81.5% ሴት) ሆኗል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ንጥር የትምህርት ተሣትፎ

በ2015 ዓ.ም በክልላችን እድሜያቸው ከ15-18 አመት የሆናቸውን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በመመዝገብ ንጥር ተሳትፎውን 34.57% (ወንድ 30.03%፣ ሴት 39.26%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 757,966 (ወንድ 327,260፣ ሴት 430,706) ሲሆኑ በዚህ መሠረት ንጥር ተሳትፎው 29.69% (ወንድ 26.06%፣ ሴት 34.30%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 85.9% (ወንድ 86.8%፣ ሴት 87.4%) ሆኗል፡፡

## የአንደኛ ደረጃ (1ኛ - 6ኛ ክፍል) "መጠነ ማቋረጥ"

በአንደኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ መረጃ 107,274 (ወንድ5 63,524፣ ሴት 40,899) ወይም ከተመዘገቡት 3.73% (4.35% ወንድ፣ 2.89% ሴት) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 53.6% ሆኗል፡፡ በቀጣይ አመት ይህን ለማሻሻል በዞንና ወረዳ ደረጃ ከተቋማት ተከታታይ መረጃ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

## የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ - 8ኛ ክፍል) "መጠነ ማቋረጥ"

በመካከለኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ ተሰበሰበ መረጃ 35,933 (ወንድ5 19,357፣ ሴት 16,576) ወይም ከተመዘገቡት 1.25% (ወንድ 1.33%፣ ሴት 1.17%) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 160.1% ሆኗል፡፡ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ይህን ለማስቀጠል ተከታታይ መረጃ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ - 12ኛ ክፍል) "መጠነ ማቋረጥ"

በሁለተኛ ደረጃ በአመቱ መጀመሪያ ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በአመቱ መጨረሻ ድረስ በተሰበሰበ መረጃ 77,103 (ወንድ5 41,076፣ ሴት 36,027) ወይም ከተመዘገቡት 8.01% (9.61% ወንድ፣ 6.73% ሴት) ከትምህርት ቤት ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም በአመቱ ለንቅናቄ ከተያዘው 2% እቅድ ጋር ሲነፃፀር የእቅድ አፈፃፀሙ 24.97% ሆኗል፡፡ በቀጣይ አመት ይህን

ለማሻሻል በዞንና ወረዳ ደረጃ ከተቋማት ተከታታይ መረጃ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

## የጥቅል ተሳትፎ ጾታዊ ምጥጥን

የትምህርትን ፍትሀዊነት ለማሳደግ የታየዘው እቅድ የጾታ ምጥጥንን ማሻሻል ነው፡፡ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2014ዓ.ም ከነበረበት 1.00 በበጀት አመቱ በ1.00 ለማስቀጠል ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 39.89% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 40.05% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 0.99 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 99.6% ሆኗል፡፡

በተመሳሳይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 0.97 በበጀት አመቱ 0.98 ለማድረግ ታቅዶ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 70.95% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 71.88% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 0.99 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 100.9% ሆኗል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ (ከ7 - 8ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 1.19 በበጀት አመቱ 1.15 ለማድረግ ታቅዶ በበጀት አመቱ በደረጃው የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 65.79% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 53.30% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.23 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 107.3% ሆኗል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥንን በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 1.22 በበጀት አመቱ ወደ 1.21 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ 42.62% የደረሰ ሲሆን የወንዶች 32.97% በመሆኑ ጾታዊ ምጥጥኑ (GPI) 1.29 በመሆኑ የእቅድ አፈፃፀሙ 106.4% ሆኗል፡፡

## የሴት መምህራን እና ትምህርት አመራሮች ድርሻ

የቅድመ አንደኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 87.9% በበጀት አመቱ 94.5% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 13,229 የቅደመ አንደኛ ደረጃ መምህራን መካከል 12,143 ወይም 91.8% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 97.1% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 46.9% በ2015 ዓ.ም 47.2% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 146,005 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን መካከል 68,875 ወይም 47.2%

ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 100.0% ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሴት መምህራን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 26.1% በ2015ዓ.ም 27.1% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማስተማር ላይ ከሚገኙ 43,462 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን መካከል 11,488 ወይም 26.4% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 97.5% ሆኗል፡፡

የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት ርዕሰመምህራን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 6.3% በበጀት አመቱ 8% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በበጀት አመቱ በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 9,179 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ርዕሰመምህራን መካከል 645 ወይም 7.0% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 87.8% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ርዕሰመምህራን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 1.8% በበጀት አመቱ 3% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 646 የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰመምህራን መካከል 16 ወይም 2.5% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 82.6% ሆኗል፡፡

የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሴት ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 2.4% በበጀት አመቱ 5% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 2,218 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል 80 ወይም 3.6% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 72.1% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 2% በበጀት አመቱ 4% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በበጀት በክልሉ በማገልገል ላይ ከሚገኙ 226 የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል 14 ወይም 6.2% ሴቶች በመሆናቸው የእቅድ አፈፃፀሙ 123.9% ሆኗል፡፡

## የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ተሳትፎ

በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በበጀት አመቱ በክልላችን 2,321 (ወንድ1,179፣ ሴት 1,142) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 0.67% (ወንድ 0.67%፣ ሴት 0.67%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 1,854 (ወንድ 1,012፣ ሴት 842) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 0.537% (ወንድ 0.58%፣ ሴት 0.50%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 80.0% (ወንድ 86.0%፣ ሴት 73.8%) ሆኗል፡፡

## የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ተሳትፎ

በአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ክፍል) ትምህርት በክልላችን 54,430 (ወንድ 29,424፣ ሴት 25,006) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 7.65% (ወንድ 8.19%፣ ሴት 7.09%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 27,343 (ወንድ 15,319፣ ሴት 12,024) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 3.86% (ወንድ 4.28%፣ ሴት 3.43%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 50.9% (ወንድ 52.7%፣ ሴት 48.7%) ሆኗል፡፡

## የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ተሳትፎ

በመካከለኛ ደረጃ (ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት በክልላችን 10,546 (ወንድ5,838፣ ሴት 4,708) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 4.95% (ወንድ 5.35%፣ ሴት 4.53%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 6,307 (ወንድ 3,445፣ ሴት 2,862) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 2.97% (ወንድ 3.17%፣ ሴት 2.77%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 60.4% (59.5% ወንድ፣ 61.5% ሴት) ሆኗል፡፡

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትልዩ ፍላጎት ተሳትፎ

በሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል) ትምህርት በበጀት አመቱ በክልላችን 9,683 (ወንድ 5,302፣ ሴት 4,381) የልዩ ፍላጎት ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን 2.23% (ወንድ 2.39%፣ ሴት 2.06%) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 4,942 (ወንድ 2,549፣ ሴት 2,393) ልዩ ፍላጎት ያላቸው ታዳጊዎች ሲሆኑ በዚህ መሠረት ጥቅል ተሳትፎው 1.10% (ወንድ 1.12%፣ ሴት 1.08%) ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 51.3% (48.4% ወንድ፣ 54.8% ሴት) ሆኗል፡፡

## የጐልማሶች ትምህርትና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት

የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 6,000 ለማድረስ ታቅዶ 5,875 ጣቢያዎች የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 90.4% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ በስታንዳርዱ መሰረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ብዛት 54 ለማድረስ ታቅዶ 42 ማዕከላት

የተቋቋሙ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 77.8% ሆኗል፡፡ቅጥር የተፈጸመላቸው አመቻቾች ብዛት በአመቱ መጨረሻ 5,100 ለማድረስ ታቅዶ 4,841 (ወንድ 2,022፣ ሴት 2,819) አመቻቾች የተቀጠሩ በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 94.9% ሆኗል፡፡ በዚሁ የሴት አመቻቾች ድርሻ 65.0% እንዲሆን ታቅዶ 58.2% በመሆኑ የእቅድ አፈጻጸሙ 89.6% ሆኗል፡፡



ጎልማሶች በትምህርት ገበታ ላይ

## ከስራና ገበያ ፍላጐት ጋር የተሳሰረ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎ

ከዞኖች በተላከው ሪፖርት መሰረት በጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት እንዲማሩ የተመዘገቡ ጎልማሶች 576,364 (ወንድ 366,686፣ ሴት 209,678) ሲሆኑ በመማር ላይ ያሉት 206,389 (ወንድ 130,319፣ ሴት 76,106) ወይም ከተመዘገቡት 35.7% ሆነዋል፡፡

ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ የተደረጉ ጎልማሶች ብዛት በሩብ አመቱ መጨረሻ 250,000 ለማድረስ ታቅዶ 124,783 (ወንድ 77,264፣ ሴት 47,519) የደረሰ ሲሆን የእቅድ

አፈጻጸሙ 49.9% ነው፡፡ የትምህርት ብርሀን ምዘና የወሰዱ ጎልማሶች እና ታዳጊዎች ብዛት 100,000 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ ይሁንና ምዘናው ሰኔ ወር 2015 መጀመሪያ ላይ በሚደረገው ምዘና ለመሳተፍ የተመዘገቡ ጎልማሶች ብዛት 102,274 (ወንድ 66,544፣ ሴት 35,730) ደርሷል፡፡ የምዝገባ ሂደቱ እየተጠናቀቀ ሲሆን በዚህ አመት እየተማማሩ የሚገኙ ጎልማሶች ትምህርታቸውን አጠናቀው መመዘን የሚችሉት የምዘናው አካል ተደርጎ ወደፊት ሪፖርቱ ተደራጅቶ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

## የማጠቃለያ ፈተና እና ምዘና

የ2015 ዓ.ም ክልል አቀፍ የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና ተዘጋጅቶ ፈተናው ከሰኔ 27-30/2015 ዓ.ም ተሰጥቷል፡፡ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የተፈታኝ ተማሪዎች በተመለከተ በ574 ትምህርት ቤቶች፣ 214,970 ተማሪዎች በ556 የመፈተኛ ጣቢያዎች፣ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ በ10 ዩኒቨርሲቲዎች እና በ25 የዩኒቨርስ ካንፓሶች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን ፈተና እንደሚወስዱ ከምዝገባ እስከ መፈተኛ ጣቢያ ድልድል ተሰርቶ ፈተናውን እንዲወስዱ የቅድመ ዝግጅት ስራ ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩል ለክልላችን በተሰጠን የፈተና አስፈጻሚዎች ኮታ መሰረት የተማሪ ቁጥር መነሻ በማድረግ ለዞኖችና ለከተማ አስተዳደሮች ወደታች በማውረድ ተመልምለው የተላኩ 1685 የፈተና አስፈጻሚዎች እስከ ተጠባባቂዎች ወደ ሶፍት ዌር መመዝገቢያ/መተግበሪያ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ስታንዳርዱን ጠብቆ የተዘጋጀና ከስህተት በጸዳ ሁኔታ የተሰጠ/ተደራሽ የሆነ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ/ ብሄራዊ ፈተና 100% ደርሷል በሚለውም፡- በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የተፈታኞች ምዝገባ በክልላችን በሚገኙ በ5752 የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 347,966 ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን ፈተናው ከሰኔ 26-27/2015 ዓ.ም በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት 8ኛ ክፍል ላይ ብቻ ፈተናውን እንዲወስዱ በቂ ቅድመ ዝግጅት ስራ ተሰርቶ እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡

የ8ኛ ክፍል ክላላዊ ፈተና በተሳካና ዉጤትማ በሆነ ሁኔታ ለመስጠት በዞን እና በክልል ደረጃ የንቅናቄ መድረክ ተደርጓል፡፡በመድረኩም በየደረጃው ካለው አመራር፣ ከትምህርት ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ከተማሪ ወላጆች፣ ከመላ ህብረተሰቡና ከፀጥታ አካላት የተሳተፉ ሲሆን ቢሮው 16,060,905.00 ብር በመመደብ በዞን እና በከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ደረጃ የንቅናቄ መድረክ እንዲካሄድ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በንቅናቄ

መድረኩም ከ2353 በላይ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም በ2015 ዓ.ም እና የ2013 ዓ.ም መረጃቸው የወደመባቸውን ተማሪዎች ጨምሮ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና መፈተን ካለባቸው 352,355(ወ 160,576፣ ሴ 191,779) መካከል 327, 692 (ወ 147083፣180,609) 93% ተማሪዎች ፈተና ላይ ተቀምጠዋል፡፡

## የከፍተኛ ትምህርት አስተዳደር ሥርዓት

በስታንዳርዱ መሰረት በኮሌጅ ደረጃ የተደራጁ የስራ አመራር ቦርዶችን እሰከ አራተኛው ሩብ ዓመት 100% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ከኮሌጆች በተገኘው መረጃ መሰረት ሁሉም የቦርድ አባላትና አመራሮች የተሟሉ በመሆኑ አፈፃጸሙ 100% መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአፈፃፀሙ መሳካትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ምክንያቶች የሚጓደሉ የቦርድ አመራሮችና አባላትን ለመሟላት ኮሌጆች እና ቢሮው የፈጠሩት የተሳለጠ ግንኙነት እንደሆነ በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ የዋለ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች አጠቃላይ በጀት አጠቃቀምን አስመልክቶ ኮሌጆች እስከ 4ኛው ሩብ ዓመቱ ድረስ 100% የሚሆነውን ሃብታቸውን ሥራ ላይ ያውላሉ ተብሎ ግብ የተጣለ ሲሆን አፈፃፀሙ 93.59% መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በእቅድ መሰረት ስራ ላይ የዋለ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የውስጥ ገቢን እስከ 4ኛው ሩብ ዓመት ድረስ 100% ሥራ ላይ ይውላል በሚል የታቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ 92.3% መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በቀሪ ቀናት ደመወዝን ጨምሮ ሌሎች ክፍያዎች ሲጠናቀቁ አፈፃፀሙ ወደ 100% እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ሀብትን እሰከ ሩብ ዓመቱ 5 ሚሊዮን ለማድረስ የታቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ 41.8 ሚሊዮን ሲሆን ከተጣለው ግብ እጅግ የላቀ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ለኮሌጆች ከልማት አጋሮች የሚያገኙትን ሃብት ከማሳደግ አንጻር እስከ ሩብ ዓመቱ ከአጠቃላይ ገቢያቸው ላይ 5% የሚሆነውን መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በድጋፍ እንደሚያገኙ የታቀደ ቢሆነም አፈፃፀሙ 0.3% እጅግ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ማስፋፋትና እድሳት የተደረገላቸው ኮሌጆች ብዛት በቁጥር 10 ይሆናሉ ተብሎ ግብ የተጣለ ሲሆን በዚህ ዓመት ሁሉም ኮሌጆች አዲሱን የሰልጠና መርሃግብር ለማጀመር እንዲችሉ የተለያዩ የግንባታ፣ የማስፋፊትና የእድሳት ተግባራትን ያከናወኑ በመሆኑ አፈፃፀሙ 100% እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

### የከፍተኛ ትምህርት እና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ ፍትሀዊነት እና ተደራሽነት

በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ በተቋቋሙ ክበባት ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሠልጣኞች ብዛት እስከ 4ተኛው ሩብ ዓመት ድረስ 69% ለማድረስ ታቅዶ በሁሉም በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በድምሩ 108 ክበባት የተቋቋሙ እና የክበብ አባላት ምዝገባ ተከናውኖ በየኮሌጁ ከተቋቋሙ ክበባት መካከል ወደ ተግባር እንቅስቃሴ በመግባት ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከተቋቋሙት ክበባት መካከል 70(64.81%) ያህሉ ወደ ተግባር እንቅስቃሴ የገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት ቢሮው በበጀት ዓመቱ ይከናወናሉ ተብለው የተለያዩ ተግባሮች በዕቅድ ተይዘው ማከናወን መቻሉ የሚበረታታ ሆኖ ሌሎች በዓመቱ ውስጥ ሊተገበሩ የሚገባቸው ተግባራት ከ100 % በታች የተከናወኑትን ለቅሞ ይዞ የቀጣይ ዓመት እቅድ ውስጥ በማካተት እንዲከናወኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ

የሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ለማስጠበቅ በበጀት ዓመቱ 10,220 የልጅነት ጋብቻ ጥቆማዎች ደርሰው 7,168 የእድሜ ምርመራ በማድረግ 1,921 የሚሆኑት ከ18 ዓመት በታች ሆነዋል፤ ሊካሄዱ የነበሩ 2,139 ጋብቻዎችም በድርድር እንዲቋረጡ ተደርጓል፤ 1,071 የልጅነት ጋብቻዎች በድብቅ ተፈጽመዋል፤ በተሰሩ ስራዎች 789 ቀበሌዎች ከልጅነት ጋብቻ ነፃ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

### የሴቶች፣ ህፃናት አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በበጀት ዓመቱ ለ7,965 ሴቶች እንዲሁም ለ703 አካል ጉዳተኞች የስራ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ለ23,517 ሴቶች እንዲሁም ለ1,194 አካል ጉዳተኞች የስራ ትስስር ተፈጥሯል፡፡ አፈጻጸሙም ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ የስራ ትስስር ከተፈጠረላቸው መካከል 11,353ቱ ወጣቶች ናቸው፡፡

በበጀት አመቱ በልማት ቡድንና ራስ አገዝ 840,000 (420,000 ወጣት) ሴቶች 72,000,000 ብር እንዲቆጥቡ በዕቅድ ተይዞ 736,557 (282,690 ወጣት) ሴቶች እንዲቆጥቡ በማድረግ ብር 181,667,846 መቆጠብ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የቆጣቢው ብዛት 88% እና የብር መጠን ደግሞ 252% ሆኗል፡፡



እንስሳት በማርባት ስራ ከተሰማሩ ሴቶች መካከል አንዷ- ስ/አቸፈር ( ሊበን)

በተመሳሳይ 638,556 (191,567 ወጣት) ሴቶች በገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት 255,422,760 ብር እንዲቆጥቡ ታቅዶ 350,857 (111,254 ወጣት) ሴቶች 277,366,523 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፤ አፈጻጸሙም በቆጣቢ ሴቶች ብዛት 55% እና በቆጠቡት ገንዘብ መጠን 108.6% ነው።

በተጨማሪም 638,556 (191,567 ወጣት) ሴቶች 153,253,656 ብር እንዲበደሩ በእቅድ ተይዞ 245,054 (38%) ሴቶች፣ 322,893,071 (210%) ብር በህብረት ስራ ማህበራት ብድር እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዚህ አኳያ የሴቶች ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ ስለሆነ ሴቶች መቆጠብ ብቻ ሳይሆን በቆጠቡት ገንዘብ የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሴቶችን ግንዛቤ ለማስፋት 273,353 (82,006 ወጣት) ሴቶች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ ተይዞ ለ647,019 (237%) ሴቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።



በስፌት ስራ ላይ ተሰማርታ ኢኮኖሚዋን ያሳደገች ወጣት -ደ/ማርቆስ

በሌላ በኩል ሴቶችን በተለይም በጦርነቱ የተጎዱትን በልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ለማሳተፍ በተደረገ ጥረት 63,388 ለሚሆኑ ሴቶች ግንዛቤ በመፍጠር በተለያዩ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

ከብድር ተጠቃሚነቱ ባሻገር በሰቆጣ የቃል ኪዳን ስምምነት ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ በ17 ወረዳዎች ለ220 ሴቶች ለእያንዳንዳቸው 10,000 ብር በድምሩ 2,200,000 ብር በመስጠት በገቢ ማስገኛ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ 65,562 መሥራት የሚችሉ አረጋዊያንን መረጃ ለይቶ ለመያዝ በተደረገው እቅድ 52,426 (ወንድ 26,558፣ ሴት 25,868) መሥራት የሚችሉ አረጋዊያንን መለየት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 10,982 የሚሆኑትን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ ለማስማራት በእቅድ ተይዞ የአካባቢውን ፀጋ በማስተባበር እና በሌሎች አግባብ 4,395 (ወንድ 1,993፣ ሴት 2,402) አረጋዊያንን በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራ እንዲሠማሩ በማድረግ 40% መፈጸም ተችሏል፡፡

በተጨማሪም 2,394 አካል ጉዳተኞችን በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 3,864 (ወንድ 1,964፣ ሴት 1,900) አካል ጉዳተኞችን በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ማሰማራት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 161.4% ነው፡፡

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ለሴቶች 394፣ ለህጻናት 325፣ ለአካል ጉዳተኞች 129 እና ለአረጋዊያን 63 በድምሩ 911 ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ ለሴቶች 400፣ ለህጻናት 361፣ ለአካል ጉዳተኞች 125 እና ለአረጋዊያን 113 በድምሩ 999 ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት ተችሏል፤ አፈፃፀሙም ከዕቅድ በላይ ነው። በእነዚህ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ለሴቶች 30 ሚሊየን ብር፣ ለህጻናት 30.27 ሚሊየን ብር፣ ለአካል ጉዳተኞች 15.524 ሚሊየን ብር እና ለአረጋውያን 3.768 ሚሊዮን ብር እንዲሁም ለሌሎች ለችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች 3.4ሚሊዩን ብር በድምሩ 82.96 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 40.787 ሚሊየን ብር በሴቶች፣ 41.31 ሚሊዩን ብር በህጻናት፣ 12.76 ሚሊዩን ብር በአካል ጉዳተኞች እና 10.615 ሚሊዩን ብር በአረጋውያን በድምሩ 105.569 ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል። ፕሮጀክት ቀርፆ ተግባራዊ ከማድረግና ሀብት ከመሰብሰብ አኳያ አፈፃፀሙ በጣም ከፍተኛ ነው።

ፕሮጀክት በመቅረፅ እና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም በሚሰበሰበው ገንዘብ በበጀት ዓመቱ 82,134 ሴቶችን፣ 56,872 ህፃናትን (ወንድ 28,438፣ ሴት 28,438) እና 26,871 አካል ጉዳተኞችን (ወንድ 13,438፣ ሴት 13,438) እንዲሁም 17,912 አረጋውያንን ( ወንድ 8,956፣ ሴት 8,956) ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 95,274 ሴቶችን፣103,620 ህጻናትን (ወንድ 51,517፣ ሴት 52,103)፣ 16,082 አካል ጉዳተኞችን (ወንድ 6,382፣ ሴት 9,700) እና 22,328 አረጋዊያንን (ወንድ 97,719፣ ሴት 12,609) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤ አፈጻጸሙም ከዕቅድ በላይ ነው።

በበጀት አመቱ ለ120,012 አካል ጉዳተኞች ጊዜያዊ የማህበራዊ ተሃድሶ ድጋፍ አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማስቻል የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዶ ለ49,040 (ወንድ 22,850፣ ሴት 26,190) አካል ጉዳተኞች ድጋፉን መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 40.9% ነው። በአጠቃላይ ድጋፉን ካገኙት አካል ጉዳተኞች መካከል ደግሞ 7,031 (ወንድ 3,077 እና ሴት 3,954) ወጣቶች ናቸው።

በበጀት ዓመቱ 2,381 አካል ጉዳተኞችን በግልና በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የነጻ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 179 ወንድ፣ 168 ሴት በድምሩ 347 አካል ጉዳተኞችን የነጻ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 14.6% ነው።

የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ እና ደህንነታቸውን ከማስጠበቅ አንጻር ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት 21,852 (ወንድ 10,897፣ ሴት 10,955) ለሚሆኑ የህጻናት ቤተሰቦች የህግ፣ የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በእቅድ ተይዞ 14,553 (ወንድ 5,465፣ ሴት 9,088) የሚሆኑት ድጋፉን እንዲያገኙ ተደርጓል፤ አፈጻጸሙም 66% ነው።

የህፃናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ወላጆች ህፃናትን በጉዲፈቻና በአደራ ቤተሰብ ይዘው ለማሳደግ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻል 2,200 (ወንድ 1,100፣ ሴት 1,100) ፈቃደኛ ቤተሰቦችን መልምሎ በወላጅነት ክህሎት፣ በልጅ አያያዝና አስተዳደግ ዙሪያ በማሰልጠን ለአደራ ቤተሰብና ለሃገር ውስጥ ጉዲፈቻ አገልግሎት ብቁ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት ለ1,551 /70.5%/ (ወንድ 491፣ ሴት 1,060) ለሚሆኑ ቤተሰቦች ስልጠና በመስጠት ዝግጁ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተከናውኗል።

በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶች አማካኝነት በተሰበሰበ ሃብት በበጀት ዓመቱ 401,459 የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 236,295 (ወንድ 92,304፣ ሴት 143,991) ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 59% ነው፡፡

## ባህልና ቱሪዝም

### የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤን

በ2015 ዓ.ም በቢሮው እና በሁሉም ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በ295 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ በማካሄድ በ20 ቋሚ ቅርሶች ላይ የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ በ330 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ በመስራት ለ27 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በ12 ወሩ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል።በተጨማሪም ለ316 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እና ለ316 ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ278 (87.97 በመቶ) ቋሚ ቀርሶች የይዞታ ማረጋገጫ ማስጠት የተቻለ ሲሆን ለ85 (26.9 በመቶ) ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ ስራ መስራት ተችሏል።.

### *የክልሉን የባህልና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ*

በበጀት ዓመቱ 4500 መድረኮችን በማዘጋጀት 900,000 የህብረተሰብ ክፍሎችን በመጤ ባህሎች እና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲሁም አስተሳሰቦች ዙሪያ የግንዛቤ ትምህርት ለመስጠት

ታቅዶ በ960 መድረኮች ለ451,485(50 በመቶ) ለሚሆነው የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ተችሏል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ለ17ኛጊዜ የተከበረው የብሄር ብሄረሰቦች በዓል በዚህ አመት በአዋሳ ከተማ የተከበረ ሲሆን በክልላችን ከሚገኙ 6ቱም ብሄሮች (አማራ፣አገው፣አርጎባ፣ኦሮሞ፣ቅማንት እና የዋግህምራ) ባህላዊ አጨፋፈር ፣አልባሳት እና የወግ ዕቃዎችን በመያዝ ከሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከሙሉዓለም የባህል ማዕከል የተውጣጡ 54 ወንድ እና 41 ሴት በድምሩ 95 የሉዑካን ቡድን ቦታው ድረስ ሂዶ በመሳተፍ የክልሉን ባህሎች የማስተዋወቅ ስራ ሰርቷል፡፡



የብሄር ብሄረሰቦች በአል -ሀዋሳ

*የክልሉን የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ማጎልበት*

በበጀት ዓመቱ በሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች 579 ነባር የባህል ቡድኖችን በድግግሞሽ በሙያ፣በስልጠና እና በቁሳቁስ ለመደገፍ ታቅዶ 550 (94 በመቶ) በመደገፍ የባህል ቡድኖችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡በተጨማሪም የቱሪዝም መሰረተ ልማት አቅርቦት መስፋፋት

በተመለከተ በበጀት አመቱ 57 ነባር የማህበረሰብ እና ኢኮ ቱሪዝም ለማጠናከር ታቅዶ 40(70%) ማከናወን ተችሏል፡፡

በክልሉ የሚገኙ መስህብ ሀብቶችን 34 አይነት በራሪ ወረቀቶችን በ14,790 ቅጂ በማዘጋጀት ለማስተዋወቅ ታቅዶ 78 አይነት በራሪ ወረቀቶችን በ14,790፣ቅጂ በማዘጋጀት እና በማሰራጨት ማስተዋወቅ በመቻሉ አፈጻጸሙን ከበራሪ ወረቀቶች አይነትም ሆነ ከቅጅ ብዛት አንጻር ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡የማህበራዊ ሚዲያዎች (ፌስቡክ፣ሊንክዲን፣ኢንስታግራም፣ ትዊተር እና ቴሌግራም) በመጠቀም የመስህብ ሀብቶችን የሚያስተዋውቁ 2531 መረጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 3970 መረጃዎችን ማሰራጨት እና ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ከዚህ ውስጥ በቢሮ ደረጃ 400 ጊዜ መስህቦችን እንዲሁም ሁነቶችን የሚያስተዋውቁ 525 የጹሑፍና በፎቶ የተዋሃዱ መረጃዎችን በፌስቡክ የመልቀቅ ስራ ተሰርቷል፡፡



## የቱሪስት ፍሰት

በበጀት አመቱ የሀገር ዉስጥ ቱሪዝም ልማት 661 መድረኮችን በማዘጋጀት ለ165,250 የህብረተሰብ ክፍሎች በቱሪዝም ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሚታዎች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ በ2 መድረኮች በማዘጋጀት ለ20,689 ወንዶች እና ለ20,048 ሴቶች በድምሩ 40,737 የህብረተሰብ ክፍሎች በማዘጋጀት ከሀገር ውስጥ የሚገኘውን ቱሪስት ፍሰትን 9,799,937 ለማድረስ ታቅዶ 13,484,435 በማድረስ ከዕቅድ በላይ በማከናወን ከሀገር ውስጥ የሚገኘውን ገቢ ብር 2,729,757,353 ለማግኘት ታቅዶ ብር 5,253,588,211 በማግነት ከእቅድ በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ደግሞ ብር 486,442,076 ለማድረስ ታቅዶ ብር 98,616903 (20.27 በመቶ) ማከናወን ሲቻል ከቱሪዝም ፍሰቱ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ጎብኚዎች 3,216,199,429 ብር ገቢ ለማግኘት በዕቅድ ተይዞ 5,352,205,114 ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ ከዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡በመሆኑም የቱሪስት ፍሰት የሀገር ውስጥ ከፍተኛ ሲሆን የውጭ ሀገር ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ የውጭ ሀገር ቱሪስት እንዲጨምር መሰራት አለበት፡፡

በበጀት ዓመቱ 2166 የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ600 (27.7 በመቶ) ለሚሆኑ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ መስጠት ተችሏል፡፡ለአፈጻጸሙ ማነስ ከንግድ ሚኒስቴር በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ከንግድ ስራ ፈቃድ በፊት የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጥባቸው የተደረጉ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በለኮከብ ሆቴሎች ላይ ብቻ እንዲከናወን በመደረጉ ነው፡፡

### *የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ*

በባህል፣በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ፣በቤተ-መጽሀፍትና ሙዜዬም ግንባታ 255,343 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ 36.31 ሚሊዬን ብር የሚገመት ተሳትፎ እንዲደረግ በዕቅድ ተይዞ ለ255,343 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የ45 ሚሊዬን ብር በጉልበት፣በገንዘብ፣በቁሳቁስ እና በሙያ ተሳትፎ አስተዋፆ ተደርጓል፡፡ከዚህ ውስጥ 76,280 (61.6 በመቶ) በቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ፣30,976 (25 በመቶ) በቤተ-መጽሃፍት እና በባህል ማዕከል ግንባታ ቀሪው 16,647(13.4 በመቶ) በመዳረሻ ልማት ተሳትፎ ያደረጉ ናቸው፡፡ከዘርፉ ጋር በተያያዘም 39,370 ለሚሆኑ ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ16,668 የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

# ጤና ጥበቃ

በበጀት አመቱ ተቋሙ በጤናው ዘርፍ መከላከልን ማዕከል ባደረገው የጤና ፖሊሲ ውስጥ በመሆን መሰረታዊ የሆነውን የጤና አገልግሎት ለሁሉም የክልሉ ህዝብ ማዳረስ የሚያስችል የጤና ተቋማትን በስፋት በመገንባት ዘላቂ የልማት ግቦችን ለመተግበር ወይም ለማሳካት የእናቶችን፤የህጻናትን ሞት መቀነስ እንዲሁም በምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ምክንያት የሚከሰቱ የህጻናት በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ላይ በማተኮር ጤናው የተጠበቀ ህብረተሰብ መመስረት ነው፡፡ይህንን መሰረት በማድረግ በ2015 ዓ.ም የተከናወኑ ተግባራት በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

## የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መጠን ከ66% ወደ 80% ለማድረስ ታቅዶ 78% በማከናወን 97 በመቶ ለሚሆኑት ለተጠቃሚዎች አገልግሎቱን በማድረስ በዓመቱ ውስጥ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከተያዘው እቅድ አንፃር ሲታይ አፈጻጸሙ የተሻለ ነው፡፡በተጨማሪም የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን 30% ለማድረስ ታቅዶ 18.4% የተፈፀመ ሲሆን ከወሊድ በኃላ ወዲያውኑ በ48 ስዓት ውስጥ የሚሰጥ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ሽፋን 2.4% ሆኗል፡፡ይሁን እንጅ የተቋሙ 12 ወራት ሪፖርት አፈጻጸም ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም በመስክ ምልከታ በ9 ወረዳዎች በተረጋገጠው መሰረት እና ከተቋማት ጋር በተደረገ ውይይት ጥቅል አፈጻጸሙ 54 በመቶ ሲሆን የብዙ ወረዳዎች አፈጻጸም ከ50 በመቶ በታች መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በ2015 ዓ.ም የቅድመ ወሊድ ክትትል1 (ANC1) አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከሚጠበቁ 782,663 እናቶች መካከል 759,476 (97%) አንድ ጊዜ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ይደረሳል ተብሎ ከታቀደው (95%) በላይ ተከናውኗል፡፡ከነዚህ መካከል 183,746 (23%) ያህሉ ከ12 የእርግዝና ሳምንት በፊት የቅድመ ወሊድ ክትትል የጀመሩ ሲሆን ይህ በበጀት ዓመቱ ለማከናዎን ከታቀደው (30%) አንፃር መሻሻል ይኖርበታል፡፡በመሆኑም ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች ከ 12 ሳምንት በፊት ክትትል እንዲጀምሩ ስለሚጠበቅ የነፍሰጡር ልየታ እና ምዝገባ እንዲሁም የቅድመ ወሊድ ክትትል ቀድሞ የማስጀመር ስራ የተጠናከረ መሆን እንዳለበት ያመላክታል፡፡

በ2015 ዓ.ም ቅድመ ወሊድ አገልግሎት-4 (ANC4) ለመስጠት በተሰራው ስራ 583,075 (74.5%) የተከናወነ ሲሆን ከታቀደው (82%) እናቶች አንፃር ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ በጀት

አመት የተሸለ መስራትን ያስፈልጋል።በተጨማሪም ቅድመ ወሊድ አገልግሎት-8 (ANC-8) 71,751 (9.2%) የተከናወነ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከታቀደው (43%) አንፃር ከፍተኛ ክፍተት ያለበት በመሆኑ በቀጣይ በጀት አመት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል ።

## በሰለጠነ ጤና ባለሙያ የሚሰጥ የወሊድና የድህረ-ወሊድ አገልግሎት

በ2015 ዓ.ም በጤና ተቋም በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ ከሚጠበቁ 782,379 እናቶች መካከል 501,557 (64%) በጤና ተቋም የወለዱ ሲሆን ይህም ባለፉት ዓመታት ከተሰራው አፈፃፀም አንጻር ከፍተኛ ሲሆን በዚህ ዓመት ከታቀደው (77%) አንፃር ክፍተት እንዳለ ማየት ይቻላል።ከነዚህም መካከል 39,509 እናቶች በቀዶ ጥገና የወሊድ አገልግሎት ያገኙ ሲሆን ሽፋኑም 5% ነው።



በሰለጠነ ባለሙያ የወለደች እናት (ፍኖተሰላም ሆስፒታል)

## የእናቶችና ጨቅላ ህፃናት ሞት

በ2015 ዓ.ም 182 እናቶች በጤና ተቋም 126 እናቶች ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ በድምሩ 308 እናቶች ከእርግዝና እና ወሊድ ጋር በተያያዘ ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን 7,148 ጨቅላ ህፃናት ደግሞ ህይወታቸው አልፎ ተወልደዋል፡፡

## የድህረ ወሊድ አገልግሎት

የድህረ ወሊድ አገልግሎት ለመስጠት በተሰራው ስራ ከወለዱ በመጀመሪያው 7 ቀን ውስጥ አገልግሎት ያገኙ እናቶች 643,544 (82.9%) ሲሆኑ ይህም በበጀት ዓመቱ ከታቀደው (84%) አንፃር ሲታይ የተሻለ ነው፡፡

## ቅድመ ወሊድ ክትትልና ምርመራ

በቅድመ ወሊድ ክትትል ጊዜ የላበራቶሪ ምርመራወችን ጨምሮ የቂጥኝ ምርመራና በርካታ አገልግሎቶችን ያገኛሉ ተብሎ ከሚጠበቁ እናቶች መካከል 478,692 (61 በመቶ) የተመረመሩ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከታቀደው 94 በመቶ አንጻር 65 በመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡በተደረገው ምርመራም 4046 እናቶች በሽታው ተገኝቶባቸዋል፡፡



ቅድመ ወሊድ ምርመራ (ነፋስ መውጫ ሆስፒታል)

## ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ፅንስ እንዳይተላለፍ ማድረግ

ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል በተሰራው ስራ 782,663 (100%) ለመመርመር ታቅዶ 699,856 (90%) ነፈሰጡር እና አጥቢ እናቶች የኤች አይ ቪ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን በክልላችን በነፍሰጡር እናቶች የኤች አይ ቪ ስርጭት ቀመር መሰረት 5,713 ነፍሰጡር እናቶች ኤች አይ ቪ ይገኝባቸዋል ተብሎ በተገመተው መሰረት ከተመረመሩ 891 እናቶች መካከል አዲስ ኤች አይ ቪ በደማቸው የተገኘ ሲሆን በተጨማሪ ከዚህ በፊት ኤች አይ ቪ ምርመራ አድርገው ውጤታቸውን ያወቁ (pre ART and ART) ሆነው ወደ እናቶች ክፍል የተላኩ 3,690 ሲሆኑ በአጠቃላይ በአመቱ ውስጥ 4,581 ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ነፈሰጡር እና አጥቢ እናቶች ያሉ ሲሆን የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት የማስጀመር አፈፃፀም ሲታይ አዲስ መድሀኒት የጀመሩ 1,060 እንዲሁም የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና እየወሰዱ አሁን ነፍሰጡር የሆኑ 3,427 እናቶች ከ ART ወደ PMTCT የተላኩትን አካቶ በድምሩ 4,487 መድሀኒት እየወሰዱ ያሉ ሲሆን፤ኤች አይ ቪ በደማቸው ይገኝባቸዋል ተብሎ ከታቀደው ከ 5,713( ከሚጠበቁ) እናቶች 4,487(71%) የሚሆኑት የፀረ ኤች አይ ቪ መድሀኒት ጀምረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአመቱ ካሉት ኤች አይቪ ፖዘቲቭ እናቶች ሲሰላ 98% እናቶች የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡ኤች አይ ቪ በደማቸው ተገኝቶባቸው ከተለዩት እናቶች የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና እየወሰዱ ያሉ አፈፃፀም የተሻለ በመሆኑ አጠናክሮ ማስቀጠል እንዳለ ሆኖ ከሚጠበቀው ያለውን 71% አፈፃፀም ለማሻሻል የተጠናከረ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## የጨቅላ ህጻናት ህክምና እና እንክብካቤ

በበጀት አመቱ የጨቅላ ህጻናት ህክምና እና ጤና ክብካቤ 55% ለማድረስ ታቅዶ 133341 (45.1%) ጨቅላ ህጻናት ህክምና አግኝተዋል፡፡የጨቅላ ህጻን መታፈን ህክምና ያገኛሉ ተብሎ ከታቀዱት 83% መካከል 9507 (79.2%) ህፃናት ህክምና ያገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 7528 ጨቅላ ህፃናት ከመታፈን ማዳን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 79% ማድረስ ተችሏል፡፡



የጨቅላ ህፃናት ህክምና (ፈለገ ህይወት ሆስፒታል ,ባህርዳር)

## የሳምባ ምችና የተቅማጥ ህክምና

በበጀት አመቱ ከ5 ዓመት በታች 74% ህፃናት የሳምባ ምች ህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 637172 (74.2%) ህጻናትን አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ይህም ከታቀደው 65% መፈፀም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተቅማጥ ህክምና አገልግሎት ያገኛሉ ተብለው ከታቀደው 30% ከአምስት ዓመት በታች የሆናቸው ህጻናት ውስጥ 719438 (22.6%) የሚሆኑ ህፃናት ህክምና አግኝተዋል፡፡

## የክትባት አገልግሎት

በበጀት ዓመቱ ከሚጠበቁት 745,962 ከ1 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት የክትባት አገልገሎት ለመስጠት ታቅዶ ፔንታቫለንት-1 ክትባት 745, 962 (104%)፤ፔንታቫለንት-3 ክትባት 752,672 (101%)፤የኩፍኝ አንድ ክትባት 715,632 (97%) ለሚሆኑት ህጻናት አገልግሎቱን ለመስጠት ተችሏል፡፡የክትባት አፈጻጸም በተሻለ አፈጻጸም ደረጃ ላይ የደረሰበት ምክንያት፤

በጦርነት ተጎጂ የነበሩ ተቋማትን ወደ ስራ በማስገባት የማካካሻ የክትባት ፕሮግራም በማመቻቸት እንዲከተቡ የተደረገ በመሆኑ ሲሆን በሌሎች ዞኖች ደግሞ ከዚህ በፊት ለክትባት ተደራሽ ያልሆኑ ህጻናትን በኩፍኝ ዘመቻ ወቅት በማቀናጀት ቤት ለቤት በማፈላለግ አገልግሎት እንዲያገኙ በመደረጉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለወጣት ልጃገረዶች የማህፀንበር ካንሰር ህክምና በተለያዩ ትምህርት ቤቶች መስጠት ተችሏል፡፡



የማህጸን በር ካንሰር ህክምና- ሰርፀድንግል ት/ቤት (ባህርዳር)

## የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች አገልግሎት የሚሰጥ ጤና ተቋም

በበጀት አመቱ የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች አገልግሎት የሚሰጥ ጤና ተቋም አፈጻጸም 503 ( 55%) ሲሆን፡፡በተጨማሪም ዕድሚያቸው 10_19 ዕድሜ ያሉ የአፍላ ወጣቶች እርግዝናን ከ13% ወደ 7% ለመቀነስ ታቅዶ 9.5 % ለማከናወን ተችሏል፡፡

## የሥርዓተ ምግብ አገልግሎት

በበጀት አመቱ የሥርዓተ ምግብ አገልግሎትን ለማስፋፋት በአመቱ ከሚጠበቀው 66% ከ2 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ክብደት የተለኩ ሲሆን 44,092 (6%) የሚሆኑት በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ከስታንዳርድ ክብድት በታች የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ችግር በመጋለጣቸው አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት በየደረጃው እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም 85% (1,879,952) ያህል ከ5 ዓመት በታች ህፃናት የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ልየታ የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህ መካከል መካከለኛ የምግብ እጥረት የተገኘባቸው 157,311 (8.4%) ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያለባቸው 13,217(0.7%) ናቸው፡፡በአመቱ መጨረሻ የምግብ እጥረት ተገኝቶባቸው ወደ ህክምና ከገቡት መካከል በደርሶ መልስ ምገባ ፕሮግራም 91% እንዲሁም በአስተኝቶ ምገባ 83% የሚሆኑት ታክመው ድነው መውጣት ችለዋል፡፡በ2015 ዓ.ም ከ6-59 ወር እድሜ ያሉ ሁለተኛ ዶዝ 2,704,722 (95%) ሕጻናት የቫይታሚን ኤ እንክብል ያገኙ ሲሆን ከ2-5 ዓመት እድሜ ያሉ ሁለተኛ ዶዝ 2,337,882 (98%) ሕፃናት ደግሞ የጸረ አንጀት ትላትል መድሀኒት እደላ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡የምግብ እጥረትና አለመመጣጠን ልየታ ለ355,727(91%) አጥቢና ነብሰ ጡር እናቶች በመስራት አስፈላጊው የጤና አገልግሎት ተሰጧቸዋል፡፡

## የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት

የ2015 ዓ.ም የኤች አይቪ መከላከልና መቆጣጠር አፈጻጸም ከሚመለከታቸው ጋር በመገምገም ጥንካሬዎችን እና ክፍተቶችን በመለየት ቀጣይ አፈጻጸምን ለማሻሻል የድርጊት መረሃ ግብርና የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ጤና ተቋማት እንዲወርድ የተደረገ ሲሆን የመጀመሪያውን 95 ኢላማ ለማሳካት በዓመቱ 1,594,118 ሰዎች የኤች አይ ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት ለማድረግ ታቅዶ በአመቱ 1,492,419(93.6% ሽፋን) ለሚሆኑ ሰዎች የምክር እና ምርመራ የተደረገ ሲሆን 9,410 ሰዎች ኤች አይቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በዓመቱ ከታቀደው 24309 ውስጥ 38.7% ሽፋን ይሆናል፡፡በተጨማሪም ራሳቸውን ካወቁ 154676 ደምበኞች መካከል 153758ቱ የፀረ ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመጠቀም ላይ የሚገኙ ሲሆን አፈጻጸሙም 99.4% ደርሷል፡፡እንዲሁም ከጸረ-ኤች አይቪ መድሃኒት ተጠቃሚዎች ውስጥ 103710 ያህሉ በደማቸው ያለው የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን ዓመታዊ ልኬታ በማሰራት 99018 በደማቸው ያለው የኤች አይ ቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1000 ኮፒ በታች በመሆኑ አፈጻጸሙ 95.4% ደርሷል፡፡

በዓመቱ የጸረ ኤች አይ ቪ መድሐኒት ህክምና ተጠቃሚ ደንበኞች የቲቢ ልየታ በመስራት የቲቢ በሽታ ላልተገኘባቸው 12859 የጸረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒት ተጠቃሚ ደንበኞች የቲቢ መከላከያ መድሀኒት ተሰጥቷል፤ ከዚህ በተጨማሪም በወቅታዊ ሁኔታዎች ለተፈናቀሉ ደንበኞች የድንገተኛ የፀረ ኤች አይ ቪ ህክምናን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከፍተኛ የፀረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት ተጠቃሚ ከሏቸው ጤና ተቋማት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በዓመቱ 6072 ለሚሆኑ ደንበኞች አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

## የሁሉም ዓይነት ቲቢ ተጠርጣሪ ልየታ

በበጀት አመቱ የሁሉም ዓይነት ቲቢ ተጠርጣሪ ልየታን 90% ለማድረስ ታቅዶ 20,915 (76%) የተከናወነ ሲሆን ይህም ባለፉት ዓመታት ከነበረው አፈፃፀም እጅግ የላቀ ቢሆንም ከእቅድ አንፃር የሚቀር ክፍተት አለ፡፡ እንዲሁም በቲቢ ህክምና ሙሉ በሙሉ የዳኑ ህሙማን መጠን 90% ለማድረስ ታቅዶ 3720 (85%) ሆኗል፡፡ የቲቢ ህክምናቸውን ያጠናቀቁ 15,564 (94%) ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር አፈጻጸሙ አበረታች ነው፡፡

## የስጋ ደዌ ህክምና

በ2015 በጀት ዓመት 743 ሰዎች ለስጋ ደዌ ይጋለጣሉ ተብሎ ለተገመተው ህሙማን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 872 (117%) ተለይተው ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ይህም የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ቢያሳይም ህክምና እንዲጀምሩ ከተደረጉት አዲስ ታማሚ ውስጥ የ2ኛ ደረጃ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች 89 (12%) ሲሆኑ ይህም ሰዎች ከስጋ ደዌ በሽታ ጋር ተያይዞ ፈጥኖ እክምና እንዲያገኙ ባለመደረጉ ምክንያት የአካል ጉዳት አጋጥሟቸዋል ማለት ነው ስለዚህ ከዕቅዱ አንጻር የተሸለ አፈጻጸም ቢኖርም ዕቅዱን ለቀጣይ ከፍ አድርጎ ማቀድ እንዳለብን ያሳያል፡፡

## የወባ በሽታ ህክምና

በበጀት አመቱ የወባ በሽታ ለማከም በተሰራው ስራ 2,710,891 (63.8%) በማይክሮስኮፕ፣1,536,467 (36.2%) በፈጣን የወባ መመርመሪያ (RDT) የወባ ምርመራ የተደረገላቸው ሲሆን በምርመራ የወባ በሽታ የተገኘባቸው 1,151,538 ህሙማን የወባ የህክምና መመሪያው በሚያዝዘው መሠረት የወባ መድሃኒት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም በምልክት ምርመራ 3,737(0.3%) የወባ ህሙማን ተለይተው ህክምናው በሚያዝዘው መሰረት

የወባ መድሃኒት ሲወስዱ በአጠቃላይ በዓመቱ 1,155,275 (ከጠቅላላ ህሙማን ጋር ያለው ድርሻ 4.6%) የወባ ህሙማን ተገቢውን ህክምና አግኝተዋል፡፡

## ትራኮማ በሽታ

ሀሩራማ በሽታዎች ጋራ በተያያዘ የትምህርት ቤት የትራኮማ ፕሮግራም በክልሉ በ8826 የመንግስት 1ኛ ደረጃ ትህምህርትቤቶች ላይ እየተተገበረ ሲሆን በዚህም ከ4.6 ሚሊዮን በላይ ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎችን ከአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር በክፍል ውጥ ስለበሽታው ትምህርት መስጠት ተችሏል፡፡እንዲሁም ካሉት ትምህርትቤቶች 3812 የጸረ ትራኮማ ክበብ በመመስረት ትምህርትቤታቸውን እና ማህበረሰባቸውን እንዲያገለግሉ ማድረግ የተቻለ ሲሆን 130,010 ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው እንዳሉ በጥናት የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህ አመት 65,005 የችግሩ ተጠቂዎችን አገልግሎት ለመስጠት በእቅድ ተይዞ 14,278 (22%) አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በበጀት አመቱ የአይን ሞራ ግርዶሽ ህክምና መስጠት ተችሏል፡፡



የአይን ሞራ ግርዶሽ ህክምና, ጎንደር ሆስፒታል

## የገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች

የገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ሙሉ በሙሉ በመተግበር የተመረቁ እማወራዎች/አባወራዎች ሽፋን 60% ለማድረስ ታቅዶ 50% ለማከናወን ተችሏል፡፡የከተማ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ሙሉ በሙሉ በመተግበር የተመረቁ እማወረ /አባወራዎች ሽፋን 55% ለማስራት ታቅዶ 54% ደርሷል፡፡ይህንን ስራ የበለጠ ለማጠናከር የጎጥ ጤና መሪዎች ስልጠና በሙከራ ደረጃ የአሰልጣኞች ስልጠና (ጤና ኤክስቴንሽን) በ8 ወረዳዎች የጎጥ መሪ ሰልጠና የወሰዱ የህብረተሰብ ክፍሎች 1,507(100%) ማሰልጠን ተችሏል፡፡በተጨማሪም በዚህ አመት የቤተሰብ ጤና ቡድን በጀመሩ 10 ከተሞች 32 ቡድን በማደራጀት የመረጃ ስብሰባውን በማጠናቀቅ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

## የህክምና አገልግሎትን ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም የሆስፒታሎች አገልግሎት ትራንስፎርሜሽን መመሪያ ትግበራን ወደ 80% ለማድረስ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ሪፖርት የላኩ ሆስፒታሎች (72) ሲሆኑ በጣም ዝቅተኛ አፈጻጸም በታየባቸው ማለትም ከክልሉ አማካይ ውጤት በታች አፈጻጸም የታየባቸው የሪፎረም ምዕራፎች በቀጣይ ዓመት የሆስፒታሉ አመራር ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ስፔሻላይዝድና ጠቅላላ ሆስፒታሎች በተሰራ ስራ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት የቆይታ ጊዜ በደቂቃ 45 ለማድረስ ታቅዶ ዓመታዊ አፈፃፀም 48 ደቂቃ ደርሷል፡፡ይህ ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካች በዳሰሳ ጥናት በየሩብ ዓመቱ የሚሰራ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል የማያሳይ ከመሆኑ ባሻገር አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ እያለ የሚሄድ ስለሆነ በቀጣይ ተከታታይ ግብረመልስ በመስጠት የሚሻሻልበትን መንገድ መቀየስ የሚጠበቅብን ይሆናል፡፡የተገልጋይ እርካታ መጠን ክልላዊ አማካይ አፈፃፀምን ወደ 85% ለማሳደግ ታቅዶ ዓመታዊ አፈጻጸም 76% ማድረስ ተችሏል፡፡በተጨማሪም በሆስፒታሎች አልጋ የመያዝ መጠን ክልላዊ አማካይ አፈፃጸምን 80% ለማድረስ ታቅዶ 75% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ10% ቀንሷል፡፡

የተኝቶ ህክምና ሞት ምጣኔን ከ2.2% ወደ 1.8% ለማውረድ ታቅዶ አፈጻጸሙ 1.7% ሆኗል፡፡ የቀዶ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ህሙማንን ቁጥር ከ68,051 ወደ 120,000 ማሳደግ ታቅዶ 82,409 ሲሆን አማካይ የተኝቶ ህክምና ቆይታ ጊዜ በቀን ከ05 ቀን በታች ለማውረድ ታቅዶ አፈጻጸም 4.6 ቀናት በሽፋን 69% ሆኗል፡፡

## የደም ባንክ አገልግሎት ስርዓትን ለማሻሻል

በበጀት አመቱ በ10ሩም ደም ባንኮች ሞባይል ሴሽን በማካሄድ ደም ማሰባሰብ የተያዘ እቅድ 2600 ጊዜ የነበረ ሲሆን ክንውኑም 2246 ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን አፈፃፀም 86.4 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ ከበጎ ፈቃደኞች የሚሰበሰብ ደም ዕቅድ 93,783 ዩኒት ደም ማሰባሰብ ሲሆን ክንውን 83,447, (88.9%) ነው፡፡በተጨማሪም በ2015 በጀት ዓመት ከተንቀሳቃሽ ቡድን 78,765 ዩኒት ደም መጠን 78,765 ተሰብስቧል፡፡



የደሴ የደም ባንክ

## የጤና መሰረተ ልማትን ማሻሻል

አዳዲስ እና ነባር የጤና ተቋማትን ለመገንባትና ለማስፋፋት በተያዘው ዘላቂ የልማት ዕቅድ መነሻ መሰረት በበጀት ዓመቱ 476 ከቀላል እስከ ከፍተኛ ደረጃ የህክምና አገልግሎት

የሚሰጥባቸው የጤና ተቋማት እየተሰሩ የሚገኝ ሲሆን ያጠናቀቁ 34 (8%) ፕሮጀክቶች ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ በተለያየ አፈጻጸም ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡



ማክሰኝት የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል

## የማህበረሰብ የጤና መድህን

በ2015 ዓ.ም በቢሮ ደረጃ የማህበራዊ ጤና መድህን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የማከናወን ስራ በመስራት ለ184 ማህበረሰብ ጤና መድህን ተጠቃሚ ወረዳዎች መክፈል የማይችሉ የተናጥል ድጎማ 147,629,789.00 በካሽ በአብክመ ጤና ቢሮ በኩል ወደ ወረዳ ማህበረሰብ ጤና መድህን አካውንት እዲገባ ለገንዘብ ቢሮ ተልኳል፡፡የማህበረሰብ ጤና መድህን ተጠቃሚ ወረዳዎች የሁለተኛ ወገን ውል እዲይዙ ማድረግና ጠቅላላ የፌደራል ድጎማ መረጃ በማጠናከር የክልሉን ድርሻ 336,226,235.50 ብር እዲመጣ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም የማህበረሰብ ጤና መድህን አባል ማፍራት 96% ጠቅላላ ሽፋን በአዲስ 88% እና በነባር እድሳት 98% መስራት ከከፋይ አባላት 1,776,770,664 በላይ ብር በማሰባሰብ እስካሁን ድረስ 1,774,498,046 ወደ ወረዳዎች

እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በአዲስ አባል ለሆኑ 654,577 አባ/እማወራዎች መታወቂያ ተዘጋጅቶ እንዲደርስ ሆኗል፡፡




የማህበረሰብ ጤና መድህን

## ወጣቶችና ስፖርት

### የወጣቶችን የመደራጀት መብትን ማስጠበቅ

በ2015 ዓ.ም 1,024,398 (ወንድ 512,199 ሴት 512,199) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 576,143 (ወንድ 322,149 ሴት 253,994) ወጣቶችን በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች (በሊግ፣ በማህበራት፣ በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 1,100,630 (ወንድ 657,600 ሴት 443,030) ወጣቶችን በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 700,464 (ወንድ 464,956፣ ሴት 235,528) በተጨማሪም በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 107% እና 121% ነው፡፡እንዲሁም 1,024,398 (ወንድ 512,199 ሴት 512,199) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 576,143 (ወንድ 322,149 ሴት 253,994) ወጣቶችን በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች (በሊግ፣ በማህበራት፣

በክበባት፣ ወዘተ) እንዲደራጁ ለማድረግ ታቅዶ 1,100,630 (ወንድ 657,600 ሴት 443,030) ወጣቶችን በማደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ግንዛቤ በመፍጠር 700,464 (ወንድ 464,956፣ ሴት 235,528) በአዲስና በነባር ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ ተደርጓል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 107% እና 121% ነው፡፡በተጨማሪ በበጀት አመቱ 18,536 (በሙያ፤ በቁሳቁስ በገንዘብ) የወጣት አደረጃጀቶችን ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 16,183 (በሙያ፤ በቁሳቁስ እና በገንዘብ አደረጃጀቶችን መደገፍ ተችሏል፤አፈጻጸሙ 87.3% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ 80,617 (ወንድ 40,309 ሴት 40,308) ወጣቶች በአመራር ጥበብ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ56,383 (ወንድ 34,109 ሴት 22,274) ወጣቶች በአመራር ጥበብ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፤አፈጻጸሙም 70% ነው፡፡

## የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ

በ2015 ዓ.ም በወጣቶች ብሄራዊ ፖሊሲ፤ ፓኬጅና ስትራቴጅ ለ23,835 የተቋም አመራሮች፣ ለቋሚ ኮሚቴዎች እና ለቡድን መሪዎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ16,355 የተቋም አመራሮች፣ ለቋሚ ኮሚቴዎች እና የቡድን መሪዎች እውቅና እንዲያገኙ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈጻጸሙም 67% ሆኗል፡፡እንዲሁም በወጣቶች ብሄራዊ ፖሊሲ፤ ፓኬጅና ስትራቴጅ ለ594,900 (ወንድ 297,450፣ ሴት 297,450) ለህብረተሠብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ529,150 (ወንድ 299,831 ሴት 229,319) የህብረተሠብ ክፍሎች እውቅና እንዲያገኙ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈፃፀሙም 88.95% ደርሷል፡፡ለ793,200/ወንድ 396,600 ሴት 396,600/ ወጣቶች መልካም አስተዳደርን በማስፈን ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ814,987 /ወንድ 467,148 ሴት 347,839/ ወጣቶች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፤አፈፃፀሙ 102.7% ነው፡

በሰላም ግንባታና ግጭትን በመከላከል ለ544,700 /ወንድ 272,350 ሴት 272,350 / ወጣቶች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ585,565 /ወንድ 354,975 ሴት 230,590/ ወጣቶች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፤አፈፃፀሙ 107.5% ነው፡፡ወጣቶች ከመልካም አስተዳደርና ከሰላም ግንባታ ጋር ተያይዞ ግንዛቤአቸው በማደጉ የአካባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታ በማስከበር ላይ ሚናቸው የጎላ እንደሆነ ማየት ተችሏል፡፡ ሌላው ለ87¸318 (ወንድ 43¸663፣ ሴት 43¸655) ወጣቶች አደረጃጀት አመራሮች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ለማድረግ ታቅዶ 109,291 (ወንድ 63¸163፣ ሴት 46¸128) ወጣቶች እንዲሳተፉ ተደረጓል፤አፈፃፀሙ 125% ነው፡፡በንቅናቄ ተሳትፎ ኮንፈረንስ 1¸209¸191 /ወንድ 605¸753፣

ሴት 605¸758/ ወጣቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ ለ1,308,693 (ወንድ 798,144፣ ሴት 510,549) ወጣቶችን በንቅናቄና ተሳትፎ መድረኮች ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 108% ሆኗል፡፡በተመሳሳይ በበጀት አመቱ ወጣቶች የተለያዩ የበጎ ፈቃድ ስራ ማከናወን ችለዋል፡፡



**የ2015 ዓ.ም የክረምት በጎ ፈቃድ ማስጀመሪያ ፕሮግራም- ባህርዳር**

## የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በ2015 ዓ.ም በየደረጃው 4,153 የስራ እድል ፈጠራ ምክርቤቶችን በማጠናከር ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 2,332 የስራ ዕድል ፈጠራ ግብረ-ሃይል በማጠናከር ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፤አፈጻጸሙም 56% ነው፡፡ በክልል ደረጃ ከኢትዮጵያ ኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢንስቲቲዩት ለ35 (ወንድ 34 ሴት 1) እና በስራና ስልጠና ቢሮ ለ34 (ወንድ 29 ሴት 5) ለወጣት ዘርፉ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች በአስተሳሰብ ለውጥ፣ በቢዝነስ ፕላን ዝግጅት እና በስራ ፈጠራ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ 888,905(ወንድ 444,453 ሴት 444,452) የስራ ፈላጊ ወጣቶችን በከተማና በገጠር ለይቶ በመያዝ መረጃቸውን ለማደራጀት ታቅዶ 1,041,983 (ወንድ 632,794 ሴት 409,189) ስራ ፈላጊ ወጣቶችን መረጃ መለየት

ተችሏል፤አፈጻጸሙም 117% ነው፡፡ለ450,000 (ወንድ 225,000 ሴት 225,000) ወጣቶች በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ በስራ ዕድል ፈጠራና የስራ ባህል ግንዛቤ በመፍጠር የወጣቶችን አመለካከት ለመለወጥ ታቅዶ 1,017,423 (ወንድ 619,007 ሴት 398,416) ወጣቶች ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፤አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

በበጀት አመቱ ለ913,533 (ወንድ 456,766 ሴት 456,767) ወጣቶች በስራ ፈጠራ ኢንተርፕርነርሺፕ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ402,806 (ወንድ 240,936 ሴት 161,870) ወጣቶች ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፤አፈጻጸሙም 44% ነው፡፡እንዲሁም ለ849,898 (ወንድ 424,949 ሴት 424,949) ወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላችው ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 907,229 (ወንድ 588,726 ሴት 318,503)ወጣቶች የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል፤አፈጻጸሙም 107% ነው፡፡

በተጨማሪም 123,125 (በመደበኛ 83,260፣ በተዘዋዋሪ 39,865) ኢንተርፕራይዞችን እና 617,647 (ወንድ 308,823 ሴት 308,824) በኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ ወጣቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ታቅዶ 94,900(በመደበኛ 59,608 በተዘዋዋሪ 35,292) ኢንተርፕራይዞችን እና 371,802 (ወንድ 221,732 ሴት 150,070) በኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ወጣቶችን ክትትል በማድረግ ውጤታማ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፤አፈጻጸሙም በኢንተርፕራይዝ ደረጃ 77% ሲሆን በአንቀሳቃሽ ደረጃ ደግሞ 60% ነው፡፡ለ1,048,992 (ወንድ 524,495 ሴት 524,497) ወጣቶች በቁጠባና በብድር አገልግሎት ግንዛቤ በመፍጠር 935,482 (ወንድ 467,741 ሴት 467,741) ወጣቶች 2,337,404,507 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ ለ940,456 (ወንድ 562,061 ሴት 378,395) ወጣቶች በቁጠባና ብድር ግንዛቤያቸውን በማሳደግ 442,442 (ወንድ 255,104 ሴት 187,338) ወጣቶች 1,079,935,566 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 90%፣ 47% እና 46% ማከናወን ተችሏል፡፡በበጀት ዓመቱ በብድርና ቁጠባ ግንዛቤ በመፍጠር 881,799 (ወንድ 441,899 ሴት 439,900) ወጣቶች ብር 2,607,472,971 ብድር እንዲመቻችላቸው ለማድረግ ታቅዶ 301,567 (ወንድ 162,010 ሴት 139,557) ወጣቶች 1,770,068,950 የብደር አገልግሎት ማመቻቸት ተችሏል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 34% እና 68% ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ 5,943 (2,971 ወንድ 2,972 ሴት) ከስደት ተመላሽ የሆኑ ወጣቶችን በመለየት በገቢ ማስገኛ ስራዎች ተደራጅተው እንዲሰሩ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ 8,077 (ወንድ 3,155 ሴት 4,922) ከስደት ተመላሽ ወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፤አፈጻጸሙም 136% ነው፡፡ ከስደት ተመለሽ ወጣቶችን መረጃ ለይቶ

በማደራጀት ያሉባቸውን የስነ-ልቦና ችግሮች በመቅረፍ እና በገቢ ማስገኛ ስራ ተሰማርተው የኢኮኖሚ ችግሮቻቸውን እንዲቀርፉ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ስራ በሁሉም ዞኖች የሚበረታታና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር ነው፡፡ለ3,070 (ወንድ 1,535 ሴት 1,535) ወጣቶች ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን እንዲጠቀሙ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ 3,814 (ወንድ 1,680 ሴት 2,134) ወጣቶች የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 124% ነው፡፡

በበጀት አመቱ በቀበሌ ደረጃ 1¸983 የወጣቶችና የወላጆች ፎረሞች ለማቋቋም ታቅዶ 1¸621 ማቋቋም ተችሏል፤አፈፃፀሙም 81.7% ነው፡፡ 1,983 ፎረሞች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 2,806 መደገፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡በበጀት አመቱ የገጠር ወጣቶች በቤተሰቦቻቸው /ወላጆቻቸው/ መሬት ላይ 1,189,800 (ወንድ 590,900 ሴት 590,900) ወጣቶች በግብርና ስራ እንዲሳተፉ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 1,030,804 (ወንድ 580,938 ሴት 449,866) ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈፃፀሙም 86.6% ነው፡፡

በዚህም 297,450 (ወንድ 148,728 ሴት 148,722) ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 248,089 (ወንድ 129,363 ሴት 118,726) ወጣቶችን ተጠቃሚ ሆነዋል፤ አፈፃፀሙም 83.4% ነው፡፡ ስለሆነም 4,519,.62 ሄክታር መሬት በማልማት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ለ1,586,400 (ወንድ 793,200 ሴት 793,200) ወላጆች ግንዛቤ በመፍጠር ታቅዶ 1,287,345 (ወንድ 720,932 ሴት 566,413) ወላጆች ግንዛቤ ተፈጥሯል፤አፈፃፀሙም 81% ነው፡፡ ስለሆነም በወላጆቻቸው ላይ 6,608.85 ሄክታር መሬት ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በበጀት አመቱ ለ793,200 (ወንድ 396,600 ሴት 396,600) ወጣቶች የግብርና ፓኬጅን፣ የግብዓትና የቴክኖሎጅ ውጤቶች በቅንጅት በመስራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ772,660 (ወንድ 454,468 ሴት 318,192) ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈፃፀሙም 97.4% ነው፡፡በአየር ንብረት ለውጥ ለ427,110 (ወንድ 213,555፣ ሴት 213,555) ወጣቶችን ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ337,968 (ወንድ 200,431 ሴት 137,537) ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈጻጸሙም 79.13% ነው፡፡በበጀት አመቱ ለ793,200 (ወንድ 396,600 ሴት 396,600) ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት ጠቀሜታና ፋይዳ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ633,913 (ወንድ 380,078 ሴት 253,835) መፈጸም ተችሏል፤አፈጻጸሙም 79.9% ነው፡፡

## የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

በአጠቃላይ እንደ ክልል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታዎችን በመገንዘብ ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ ንቅናቄ በመፍጠር በ2014 ዓ.ም የክረምት ወራት የወጣቶች የበጎፈቃድ አገልግሎት መርሐ-ግብር በ12 የስምሪት መስኮች ለ4,850,539 (ወንድ 2,425,270 ሴት 2,425,269) ወጣቶችን ለማሳተፍ ታቅዶ ለ5,072,796 (ወንድ 2,855,254 ሴት 2,217,542) ወጣቶችን ማሳተፍ ተችሏል፤አፈጻጸሙ 104.58% ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑት ዋናዋና የስራ መስኮች መካከል 3,633 አዲስ ቤቶች መገንባት ፣8,735 ነባር ቤቶች መጠገን ፣884. ሚሊዮን ችግኞችን መትከል፣ 100,144 ሄክታር መሬት ሰብል በመስመር መዝራት፣ 59,997 ሄክታር መሬት የአቅመ ደካሞችን እርሻ ማረስና ማረም፣ በ777 ት/ቤት 114,894 ተማሪዎችን ማጠናከሪያ ትምህርት መስጠትና 19,167 ዩኒት ደም መለገስ ተችሏል፡፡በክረምት በጎ ፈቃድ 11,234,330 (ወንድ 5,617,165 ሴት 5,617,165) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 11,168,983 (ወንድ 5,719,251 ሴት 5,449,732)/ 99% የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ በክረምት ብር 5,100,000,000 ታቅዶ ብር 4,819,156,200 የመንግስት ወጪ ማዳን ተችሏል፤አፈጻጸሙም 94.5% ነው፡፡በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለ2,500,428(ወንድ 1,250,214 ሴት 1,250,214) ለማሳተፍ ታቅዶ ለ2,052,967 (ወንድ 1,273,223 ሴት 779,744) ወጣቶችን ማሳተፍ ተችሏል፤አፈጻጸሙ 82 በመቶ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ በዋና ዋና ተግባራት ማለትም 369 የአረጋውያን በአዲስ ቤት መገንባት፣ 625 የአረጋውያ ቤት መጠገን፣ 403,109 ወጣቶችን በተፈጥሮ ሃብት ስራዎች ማሳተፍ፣ 5,335 ሄክታር የአቅመ ደካማና የዘማች ቤተሰብ ሰብል መሰብሰብ፣ 8,386 ዩኒት ደም ልገሳ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በበጀት አመቱ በበጋ በጎ ፈቃድ 2,464,414 (ወንድ 1,232,207 ሴት 1,232,207) የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 4,384,608 (ወንድ 2,616,276 ሴት 1,768,338)/ 100% የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ በማድረግ በበጋ ብር 2 ቢሊዮን ወጭ ለማዳን ታቅዶ ብር 1,969,138,889 የመንግስት ወጪ ማዳን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ 98.5% ነው፡፡ በየደረጃው ለ40,000 ወጣቶች፣ ለ603 ወጣት አደረጃጀቶችና ለ603 ባለድረሻ አካላት እውቅና ለመስጠት ታቅዶ ለ30,208 ወጣቶች፣ ለ1,677 ወጣት አደረጃጀቶችና ለ1,966 ባለድረሻ አካላት እውቅና መስጠት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ እንደ ቅደም ተከተላቸው 75.5%፣ 100%፣100% ነው፡፡
በበጀት አመቱ በማህበራዊ ጠንቅ ለ991,500 /ወንድ 495,750 ሴት 495,750/ ታቅዶ 896,554 /ወንድ 490,258 ሴት 406,296/ ለወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈፃፀሙም 90.4% እንዲሁም ለ594,900 /ወንድ 297,450 ሴት 297,450 ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች

ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ613,839 /ወንድ 342,792 ሴት 271,047/ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሮሯል፤አፈፃፀሙም 103% ነው።

በበጀት አመቱ በህገ-ወጥ የወጣቶች ዝውውር 991,500 /ወንድ 495,750 ሴት 495,750 / ወጣቶች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 967,174 /ወንድ 557,890 ሴት 409284/ ወጣቶች ግንዛቤ ተፈጥሯል፤አፈፃፀሙም 97.5% ነው።በዚህም ምክንያት 34,167 /ወንድ 18,622 ሴት 15,545/ ወጣቶች አመለካከታቸውን በመቀየሩ ከህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዲመለሱ ተደርጓል። ለ594,900 /ወንድ 297,450 ሴት 297,450/ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ560,960 /ወንድ 315,923 ሴት 245,037/ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፤አፈፃፀም 94.2% ነው።በክልል ደረጃ ከ24 በላይ የሚሆኑ የክልል ተቋማት ወጣቶችን ከአሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እጾች ለመከላከል በተቋቋመው ግብረ-ሃይል አባላት አማካይነት የጋራ የ5 ዓመት ስትራቴጅክ እቅድና ዓመታዊ እቅድ ተዘጋጅቶ ለአፈጻጸም በየደረጃው እንዲወርድ ተደርጓል። በበጀት ዓመቱ ግብረ-ሃይሉ 2 ጊዜ ተገናኝቶ በመገምገም የቀጣይ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ችሏል። በተጨማሪም 36 (ወንድ 22 ሴት 14) የክልል ምክርቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እና አባላት በተገኙበት የ2015 በጀት ዓመት ወጣቶችን ከአሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርጊቶችና አደንዥ እጾች የመከላከል ንቅናቄ እቅድ አፈጻጸምና የ2016 በጀት ዓመት መነሻ እቅድ ላይ በመምከር የቀጣይ አፈጻጸም አቅጣጫ ተቀምጧል። በየደረጃው 4,153 የአሉታዊ መጤ ልማዶችና አደንዛዥ እጾች ተከላካይ ግብረ-ኃይሎችን ለማጠናከር እና ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 2,332 ተከላካይ ግብረ ኃይሎችን ለማጠናከር ተችሏል፤አፈጻጸሙም 56% ነው። በበጀት ዓመቱ 870,769 (ወንድ 435,386 ሴት435,383) ወጣቶች በአሉታዊ መጤ ልማዶች /ባህሎች እና አደገኛ መድሃኒቶችና እጾችን ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 681,655 (ወንድ 379,071 ሴት 284,584) ወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈጻጸሙ 78% ነው።ለ6,860 (ወንድ 5,640 ሴት 1,220) በተለያዩ ሱሶች የተጠመዱ ወጣቶችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሰብዕና ልማት ማዕከላት እና በጤና ተቋማት በማስገባትና በዘርፉ የሰለጠኑ አማካሪ ባለሙያዎችን በመመደብ የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አግኝተው ከሱሳቸው አገግመው እንዲወጡ ለማድረግ ታቅዶ 1,164 (ወንድ 786 ሴት 378) ወጣቶች የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አግኝተው ከሱሳቸው አገግመው እንዲወጡ ማድረግ ተችሏል፤አፈጻጸሙም 17% ነው። የዚህ ተግባር አፈጻጸም እጅግ ደካማ ሲሆን ለአፈጻጸሙ ማነስ የማገገሚያ ማዕከላት አለመስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል አለመኖር እንደተጠበቀ ሆኖ የችግሩን አሳሳቢነት ተረድቶ ከሚመለከታቸው ጋር ተቀናጅቶ በመስራት

በኩል የታየው የዞኖች አፈጻጸም በሁሉም ዞኖች ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ሊታሰብበትና ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡በተጨማሪም ሁሉም መዋቅር እንዲነቃነቅ በማድረግ 581,776 (ወንድ 291,790 ሴት 289,986) ወጣቶች በአዕምሮ ውቅር፣ 390,418(ወንድ 195,209 ሴት 195,209) ወጣቶች በህይወት ክህሎት እና 390,414(ወንድ 195,207 ሴት 195,207) ወጣቶች በአቻ ለአቻ ስልጠና በመስጠት የወጣቶችን አመለካከት ለመገንባት ታቅዶ 353,846 (ወንድ 202,631 ሴት 151,215) ወጣቶች በአዕምሮ ውቅር፣ 250,877 (ወንድ 137,444 ሴት 113,433) ወጣቶች በህይወት ክህሎት እና 227,621 (ወንድ 122,919 ሴት 104,702) ወጣቶች ደግሞ በአቻ ለአቻ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 61%፣ 64% እና 58% ነው፡፡ለ192 የጤና ተቋማትና 38 የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላት ምቹና ወጣት ተኮር የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ 141 የጤና ተቋማትና 41 የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላት ለወጣቶች ምቹና ወጣት ተኮር የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 73% እና 108% ነው፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ 1,001,996 (500,998 ወንድ 500,998 ሴት) ወጣቶችና 1,985 (ወንድ 993 ሴት 992) የክበባትና የማህበራት መሪዎች በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና በስነ-ተዋልዶ ጤና ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 822,085 (ወንድ 477,581 ሴት 344,504)ወጣቶች እና 2,295 (ወንድ 1,235 ሴት 1,060) የክበባትና ማህበራት መሪዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 82% እና 116% ነው፡፡

ከመሬት ቢሮ ጋር በቅንጅት በመስራት 160 የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላት መገንብያ ቦታ ለመረከብ እና 187 የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላትን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 106 ማዕከላት መገንብያ ቦታ ርክክብ ተፈፅሟል፡፡ 119 የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ ተደርጓል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 66% እና 64% ነው፡፡ 50 የወጣት ሰብዕና ልማት ማዕከላትን በአዲስ ለመገንባት ታቅዶ 35 ማዕከላትን በአዲስ መገንባት ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 70% ነው፡፡ በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ማቋቋም ጽ/ቤት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ከተለዩ 17 የወጣቶች የሰብዕና ልማት ማዕከላት መካከል ለ10 የስብዕና ማዕከላት ግንባታ አገልግሎት የሚውል 56,100,000 ብር የገንዘብ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 387 የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላት (በሙያ፣ በቁሳቁስ፣ እና በገንዘብ) ሁሉን አቀፍ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ 565፣ (በሙያ፤ በቁሳቁስ እና በገንዘብ) የወጣቶች ሰብዕና ልማት ማዕከላትን መደገፍና ማጠናከር

ተችሏል፤አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ 2,494 (ወንድ 1,236 ሴት 1,258) የማዕከላት የቦርድ አመራሮች /ስራ አስፈጻሚዎች 12,998 (ወንድ 6,499 ሴት 6,499) የወጣት ማዕከላት ስራ አስኪያጆችና ባለሙዎች በወጣቶች ማዕከላት ጠቀሜታና አስተዳደር መመሪያ ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1,523 (ወንድ 1,089 ሴት 434) የቦርድ አመራሮች /ስራ አስፈጻሚዎች እና 3,178 (ወንድ 2,107 ሴት 1071) የማዕከላት ስራ አስኪያጆችና ባለሙዎች ስልጠና ተሰጥቷል፤አፈጻጸሙም እንደ ቅደም ተከተላቸው 61% እና 24% ነው፡፡ 456,550 (ወንድ 228,275 ሴት 228,275) ወጣቶችን በማዕከላት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 572,397 (ወንድ 333,554 ሴት 238,843) ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤አፈጻጸሙም 125% ነው፡፡የግንባታ ውል ስምምነት ከተቋራጮች ጋር በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

## የወጣቶች ጉዳይ ተቋማዊነትን ማጎልበት

በ2015 ዓ.ም ለ4¸882 የተቋም አመራሮች፣ ለ4¸000 ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ለ14¸898 ቡድን መሪዎች እና ለ12,573 አደረጃጀት አመራሮች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ3¸824 የተቋም አመራሮች፣ ለ1¸920 ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ለ7¸436 ቡድን መሪዎች እና ለ6,743¸ አደረጃጀት አመራሮች እውቅና እንዲያገኙ ስልጠና መስጠት ተችሏል፤አፈጻጸሙ እንደ ቅደም ተከተላቸው 78.3%፣ 48%፣ 49.9% እና 53.6% ነው፡፡

## የስፖርት ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር

በበጀት አመቱ ከክልል እስከ ወረዳ 217 መንግስታዊ ስፖርት ተቋማትን ለማደራጀት ታቅዶ 211 መንግስታዊ የስፖርት ተቋማት ተደራጅተዋል፣ አፈጻጸሙም 97.2% ነው፡፡ ከክልል እስከ ቀበሌ 25,000 ስፖርት ህዝባዊ አደረጃጀቶችን ለማጠናከርና ለማደራጀት ታቅዶ 23,657 የስፖርት ህዝባዊ አደራጃጀቶችን ማጠናከርና ማደራጀት ተችሏል፤አፈፃፀሙ 95% ነው፡፡ በዚህም መሰረት 14,741 ፌዴሽኖችና ከሚቴዎችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 8,330 ፌዴሽኖችና ከሚቴዎችን ማጠናከር ተችሏል፤አፈጻጸሙም 56% ነው፡፡ በየደረጃው 374 የአሰልጣኞች ማህበር በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 253 የአሰልጣኞች ማህበር ማደራጀት ተችሏል፤አፈፃፀሙም 67% ነው፡፡374 የዳኞች ማህበር በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 265 የአሰልጣኞች ማህበር ማደራጀት ተችሏል፤አፈፃፀሙም 70% ነው፡፡ 19 የሙያ ማህበር ለማደራጀትና ለማጠናከር ታቅዶ 131 የሙያ ማህበር ማደራጀት ተችሏል፤አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የስፖርት አይነቶች 374 የቴክኒክ ከሚቴዎችን ለማደራጀትና

ለማጠናከር ታቅዶ 230 ቴክኒክ ከሚቴዎችን ማጠናከር የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 61% ነው፡፡ለ4¸500 የስፖርት ምክርቤት ጉባኤዎችን ለማካሄድ ታቅዶ 4,087 የስፖርት ምክርቤት ጉባኤዎች ተካሄደዋል አፈጻጸሙም 91% ነው:: 437 የስፖርት ፌዴሬሽኖች ጠቅላላ ጉባኤዎችን ለማካሄድ ታቅዶ 134 የስፖርት ፌዴሬሽኖች ጉባኤ አካሄደዋል፤አፈፃፀሙም 33.5% ነው፡፡ለአፈጻጸሙ ዝቅ ማለት በቀጣይ ዓመት ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ አልሞ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ለ95 የስፖርት ክለቦችን ለማጠናከር እና 95 ክለቦችን በአዲስ ለመቋቋም ታቅዶ 120 ክለቦችን የማጠናከር እና 257 ክለቦችን በአዲስ ለማቋቋም ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ በማጠናር 100% እና በአዲስ በማቋቋም ከ100% በላይ ነው፡፡ 14,448 የስፖርት ቡድኖችን ለማደራጀት ታቅዶ 6,424 ቡድኞች ተደራጅተዋል፤አፈፃፀሙ 44% ነው፡፡ በየደረጃው ላሉ የስፖርት ክለቦች እንዲሁም የስፖርት ምክርቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ብር 10,000,000 እንዲደረግላቸው በታቀደው መሰረት 14,050,000 ድጋፍ ተደርጓል፤አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡




**24ኛው የአማራ ክልል ስፖርት ምክርቤት ጉባኤ -ባህርዳር**

## የስፖርት ሃብትን ማሳደግ

በበጀት አመቱ በየደረጃው ከህብረተሰቡ ብር 300 ሚሊየን ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 165,771,279 ተሰብስቧል፤አፈፃጸሙ 55.25% ነው፡፡ከህብረተሰቡ የተሰበሰበው ሀብት ለክልሉ10%፤ለዞን 35%፤ ለወረዳ 35% እና ለቀበሌ 20% ለስፖርት ልማት የሚውል

ነው፡፡በየደረጃው የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለልማታዊ ድርጅቶች፤ ለባለሀብቶችና ለግለሰቦች በማቅረብ ብር 40 ሚሊዮን ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 33,350,789 መሰብሰብ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 83.37% ነው፡፡እንዲሁም ህዝባዊ አደረጃጀቶች ፕሮጀክት በመቅረጽ ከስፖንሰርሽፕ 900,000 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 13,965,822 ማሰባሰብ ተችሏል፤አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ ከመንግስት ድጋፍ ለማግኘት 90,000,000 ታቅዶ 115,284,480 ተከናውኗል፤አፈፃፀሙም 100% ሆኖ ታይቷል፡፡ ከተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች ከስቴዲየም መግቢያ ትኬት ገቢ የተሰበሰበ ብር 2,000,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ 1,022645 ብር መሰብስብ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 51.3% ነው፡፡ስፖርትን በባለቤትነት ይዘው ከሚመሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በስራቸው ክለቦችን ለማቋቋምና ለመደገፍ የሚያስችል በጀት ብር 200,000,000 ለማስመደብ ታቅዶ ብር 287,387,000 ማስመደብ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡ከክለቦች ለውድድር መመዝገቢያ ብር 1,205,000 ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 2,971,850 ተሰብስቧል፤አፈፃፀም 100% ነው፡፡

## የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስልጠና ማዕከላት ማስፋፋትና ማሳደግ

በበጀት አመቱ 68 አገር አቀፍ ስታንዳርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመለየትና ለመገንባት ታቅዶ 32 ተለይተዋል፤አፈፃፀሙም 47.1% ነው፡፡እንዲሁም ለ823 የጥርጊያ ሜዳዎችን ለማስፋፋት ታቅዶ 487 ተስፋፍተዋል፤አፈጻጸሙም 57.83% ነው፡፡ለ600 በገጠር የይዞታ ማረጋገጫ የሌላቸው ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ደብተር እንዲያገኙ ታቅዶ 319 አግኝተዋል፤አፈፃፀሙ 53.17% ነው፡፡በተጨማሪም 57 የስፖርት ማዘውተሪያዎች በከተማ የባሌቤትነት ካርታ እና ፕላን እንዲያገኙ ታቅዶ 109 አግኝተዋል፤አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡በት/ቤቶችና በተቋማት 405 የማዘውተሪያ ስፍራዎችን ለማስፋፋት ታቅዶ 1,930 ተከናውኗል፤አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡አስር የ3ኛ ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለመገንባት ታቅዶ 9 ተከናውኗል፤አፈፃፀሙ 90% ነው፡፡እንዲሁም የሚገነቡ የማዘውተሪያ ስፍራዎችን 4 ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 4 ጊዜ ተከናውኗል፤አፈፃፀሙ 100% ደርሷል፡፡በበጀት አመቱ 2 የመ ደረጃ የስፖርት የስልጠና ማዕከላት ለመገንባት ታቅዶ 1 ተገንብቷል፤አፈፃፀሙ 50% ነው፡፡ሁለት የሐ ደረጃ የስፖርት የስልጠና ማዕከላት ለመገንባት ታቅዶ 2 ተገንብተዋል፡፡

የማህበረሰብ ስፖርትን በማስፋፋት የህብረሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ በበጀት አመቱ በአካል ብቃት እንቅስቃሴ 389,308 (ወንድ 191,549 ሴት 191,549 አ/ጉ 6,210) ታቅዶ

658,575 (ወንድ 413,518 ሴት 241,339 አካል ጉዳተኛ 3,718) የህብረተሰብብ ክፍል በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡በጤና ቡድን እንቅስቃሴ 60,200 (ወንድ 39,400 ሴት 20,800) ታቅዶ 357,321 (ወንድ 193,421 ሴት 163,900) ተከናውኗል፤አፈፃፀሙ 100% በላይ ነው፡፡በት/ቤቶች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ 516,876 (ወንድ 258,438 ሴት 258,438) የትምህርት ማህበረሰቡን ለማሳተፍ ታቅዶ 1,191,430 (ወንድ 632,387 ሴት 547,072 አካል ጉዳተኛ 11,971) ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡በህዝባዊ ሩጫ 1,036,907 (ወንድ 517,463 ሴት 517,463 አካል ጉዳተኛ 1,981) የማህበረሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 896,397 (ወንድ 505,167 ሴት 388,109 አካል ጉዳተኛ 3,121) ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 86.45% ነው፡፡በእግር ጉዞ ፕሮግራም 1,036,907 (ወንድ 517,463 ሴት 517,463 አካል ጉዳተኛ 1,981) የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳተፍ ታቅዶ 1,034,123 (ወንድ 570,581 ሴት 461,000 አካል ጉዳተኛ 2,542) ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 99.73% ነው፡፡በክረምት ሥልጠናና ውድድር 350,600 (ወንድ 192,478 ሴት 154,881 እና አካል ጉዳተኛ 3,241) ስፖርተኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 168,637 (ወንድ127,271 ሴት 39,528 እና አካል ጉዳተኛ 1,838) ስፖርተኞችን ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 48.09% ነው፡፡የበጋ ስልጠናና ውድድር 391,253 (ወንድ 256,874 ሴት 134,379) ስፖርተኞችን ለማሳተፍ ታቅዶ 350,291 (ወንድ 246,780 ሴት 102,988 አካል ጉዳተኛ 523) ስፖርተኞችን ማሳተፍ ተችሏል፤አፈፃፀሙም 89.53% ነው፡፡



የሰከላ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል

## በአጭር ጊዜ ስልጠናዎች ስፖርተኞችን ማፍራት

በበጀት አመቱ  ከጀማሪ አስከ 3ኛ ደረጃ የዳኝነት ስልጠና ለ626 ሰልጣኞች ለማስጠት ታቅዶ ለ448 ሰልጣኞች ማሰጠት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 71% ነው፡፡ በኢንስትራክተር የአሰልጣኝነት ስልጠና ለ50 ሰልጣኞች ለማሰጠት ታቅዶ ለ13 ሰልጣኞች ማስጠት ተችሏል፤አፈፃፀሙም 26% ነው፡፡ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ለ322 ሙያተኞች ለማስጠት ታቅዶ ለ300 ሙያተኞች ማስጠት ተችሏል፡፡በደረጃ እድገት የዳኝነት ስልጠና ለ350  ዳኞች ለማስጠት ታቅዶ ለ239 አሰልጣኞች ማስጠት ተችሏል፤አፈፃፀሙም  68% ነው፡፡ በደረጃ እድገት የአሰልጣኝነት ስልጠና ለ672  አሰልጣኞች ለማስጠት ታቅዶ ለ658 አሰልጣኞች ማሰጠት ተችሏል፤አፈፃፀሙም 98% ነው፡፡ በአካል ብቃት የአሰልጣኝነት ስልጠና ለ138 ሰልጣኞች ለማስጠት ታቅዶ ለ281 ሰልጣኞች ማስጠት ተችሏል፤አፈፃፀሙም 100% በላይ  ነው፡፡

## በረጅም ጊዜ ስልጠና ስፖርተኞችን ማፍራት

በዞኖች የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና 9,890 (ወንድ 4,985 ሴት 4,905 ) ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 9,890 (ወንድ 4,985 ሴት 4,905) ማሰልጠን ተችሏል፤አፈፃፀሙ 100% ነው። ባለሙያዎች በተደረገ ውድድር በክልላችን 68 ሰልጣኞች በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ወደ ኢትዮጵያ ወጣቶች አካዳሚ ለመመልመል ከተጠሩት ውስጥ 28 ሰልጣኞች ገብተው እንዲሰለጥኑ ተመርጠዋል። በተለያዩ ዩንቨርስቲዎች በክረምት መርሀ ግብሮች በስፖርት ሳይንስ ስልጠና 32 (ወንድ 25፣ ሴት 7) ሙያተኞች እድሉን አግኝተው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ። ኤሊቶችን በዋና ዋና ክለቦች ላይ ለማሳተፍ 60 (ወንድ 30፣ ሴት 30) ታቅዶ 28 (ወንድ 13፣ ሴት 15) ተሳትፈዋል፤አፈፃፀሙ 46.6% ነው።

## የታዳጊ ወጣቶች የምዘና ውድደር

የ8ኛው የአማራ ክልል ዞን አቀፍ የታዳጊ ወጣቶች የምዘና ውድደር በባህርዳር ከተማ አስተዳደር የተካሄደ ሲሆን በውድድሩም 10 ዞኖች እና 5 ከተማ አስተዳደሮች ተሳታፊ ሆነዋል።



8ኛው የአማራ ክልል የታዳጊ ወጣቶች የምዘና ውድድር

## የዞኖች፣ የክለቦች እና የስልጠና ማዕከላት ውድድሮች

29ኛው የአማራ ክልል የዞኖች፣ የክለቦችና የስልጠና ማዕከላት የአገር አቋራጭ ውድድር በ17 ቡድኖች መካከል 368 (ወንድ 215፣ ሴት 153) አትሌቶች የተሳተፉበት ውድድር በቲሊሊ ከተማ ተካሄዷል። በውድድሩም በዞኖች ሰሜን ጐንደር 4 ዋንጫ፣ ምዕራብ ጎጃም 1 ዋንጫ በክለቦች አማራ ማረሚያ 2 ዋንጫ፤ ተንታ 1 ዋንጫ፣ አማራ ፖሊስ 1 ዋንጫ፣ በማምጣት ተጠናቋል።

### አገር አቀፍ የወጣቶች አትሌትክስ ሻምፒወና ውድድር

በበጀት አመቱ በአገር አቀፍ የወጣቶች አትሌትክስ ሻምፒወና ውድድር ክልሉ 61 ስፖርተኞችን፤ 9 አሰልጣኞችን እና ቡድን መሪዎችን በማካተት 72 ልዑካን በማያዝ ሀዋሳ ላይ በተካሄደው ውድድር ተሳትፎ ተመልሷል።

### አገር አቀፍ የፕሮጀክቶች አትሌትክስ ውድድር

አገር አቀፍ የፕሮጀክቶች አትሌትክስ ውድድር 54 የልኡካን አባላትን በማሳተፍ ድሬዳዋ ላይ በተካሄደው ውድድር ክልላችን ተሳትፎ ተመልሷል። በውድድሩም 15 ወርቅ፤ 10 ብር እና 10 ነሀስ በድምሩ 35 ሜዳሊያዎችን በማግኘት በአጠቀላይ 2ኛ ደረጃ አግኝቷል።እንዲሁም 20ኛው የኢትዮጵያ የባህል ስፖርት ውድድር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በሚዛን አማን ከተማ ተካሂዷል በውድድሩም የአማራ ክልል አጠቃላይ አሸናፊ መሆን ችሏል።




**20ኛው የኢትዮጵያ የባህል ስፖርቶች ውድድር ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሚዛን አማን ከተማ የተካሄደ ውድድር**

## 16ኛው የኢትዩጵያ የግማሽ ማራቶን ውድድር

በ16ኛው የኢትዮጵያ የግማሽ ማራቶን ውድድር 14 አትሌቶችን በማሳተፍ በደብረብርሀን ከተማ በተካሄደው ውድድር ክልሉ ተሳትፏል፡፡ በወድድሩም የአማራ ፖሊስ አትሌትክ ክለብ ቀዳሚ በመሆን በሴቶች የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችሏል፡፡ በተጨማሪም ክልላችን ውድድሩን የተለያዩ ኮሜቴዎችን በማዋቀርና በማዘጋጀት በውጤታማነት ማስተናገድ ችሏል፡፡

## 3ኛው አገር አቋራጭ የፓራኦሊምፒክ አትሌቲክስ ሻምፒወና ውድድር

በ2015 ዓ.ም 3ኛው አገር አቋራጭ የፓራኦሊምፒክ አትሌቲክስ ሻምፒወና ውድድር ክልሉ 45 የልኡካን አባላትን በማሳተፍ አዲስ አበባ በተካሄደው ውድድር ተሳትፎ ተመልሷል፡፡ በውድድሩም በሴቶች 11 ወርቅ፤ 4 ብር እና 7 ነሀስ በድምሩ 22 ሜዳሌያዎችን በማግኘት 2ኛ ደረጃ ተገኝቷል፡፡ በወንዶች 10 ወርቅ፤ 5 ብር እና 2 ነሀስ በድምሩ 17 ሜዳሌያዎች ተግኝቷል፡፡በሴቶችና በወንዶች 39 ሜዳሌዎችን በማግኘት በአጠቃላይ ውጤት 2ኛ ደረጃን ተግኝቷል፡፡

## የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው አትሌትክስ ሻምፒዋና ውድድር

በ2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው አትሌትክስ ሻምፒዋና ውድድር ክልሉ 40 የልኡካን አባላትን በማሳተፍ አዋሳ በተካሄደው ውድድር ተሳትፎ ተመልሷል፡፡ በውድድሩም በአጠቃላይ ውጤት 2ኛ ደረጃን አግኝቷል፡፡

### የስፖርት ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት

የስፖርቱን ዘርፍ ለማሳደግ ለመንግስት ብቻ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡በመሆኑም የስፖርት ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት በዘርፉ የሚሰማራውን የባለ ሃብት ቁጥር ለማሳደግ በተሰራው ስራ በበጀት አመቱ በስፖርት ኢንቨስትመንት 4000 (ወንድ 2700 ሴት 1300) የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ 6313 (ወንድ 4130 ሴት 2183) ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፤አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ባጠቃላይ የወጣትና ስፖርት ቢሮ ለበጀት ዓመቱ ታቅደው ይከናወናሉ የተባሉ ተግባራትን በአብዛኛው ለማከናወን ተሞክሯል፡፡ከእቅድ በታች የተከናወኑ ተግባራትን ለቀጣይ ዓመት በእቅድ በማካተት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## ሲቪልሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳደር

### የሰው ሃይል መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓትን ማጠናከር

በ2015 ዓ.ም በክልሉ በመንግስት ተቋማት የሚገኙ ሰራተኞች የተደራጀ ዓመታዊ የሰው ሃይል መረጃ ለማወቅ በተሰራው ስራ በበጀት አመቱ ያለው ሲቪል ሰርቪስ መንግስት ሰራተኛ ጠቅላላ ብዛት ወ-243,244 (57.5%) ሴ-179,652 (42.5%) ድ- 422,752 ሲሆን በትምህርት ደረጃ ሲታይ ደግሞ ዲፕሎማና በታች ያላቸው ወ-129,885 ሴ-123,200 ድ-235,085 (56%)፣የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ወ-104,815 ሴ-71,025 ድ-175,840 (41.8%)፣ ማስተርስ እና በላይ ያላቸው ወ-6,839 ሴ-2,289 ድ- 9,128 (2.1%) ናቸው፡፡

### የሰው ሃብት አቅም ግንባታ ስራ

በበጀት አመቱ በክልል የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተማከለ እና በዕቅድ እንዲመሩ ለማድረግ የሚያስችል ክልላዊ የስልጠና ዕቅድ ለማዘጋጀት ተቋማት የ2015 የአጭርና የረጅም ጊዜ የስልጠና ዕቅዳቸውን ከዞኖች እና ከክልል በማሰባሰብ ስልጠናዎች በተማከለ እና በዕቅድ እንዲመሩ ለማድረግ የሚያስችል ክልላዊ የስልጠና ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ተቋማት የ2015 የአጭርና የረጅም ጊዜ የስልጠና ዕቅዳቸውን ከዞኖች እንዲሁም ከክልል ተቋማት በማሰባሰብ 5,242 በዲፕሎማ 2,739 በመጀመሪያ ዲግሪ፤5,845 2ኛ ዲግሪ ፤352 በ3ኛ ዲግሪ በድምሩ 14,178 በረጅም ጊዜ ለማስተማር እና በተለያዩ ርዕሶች በአጭር ጊዜ የተያዘውን

ክልላዊ እቅድ መነሻ በማድረግ አጠቃላይ የበጀት ዓመቱን እቅድ 100 ፐርሰንት ለመፈጸም የታሰበ ቢሆንም የእቅዱን 58% ብቻ መፈጸም ተችሏል፡፡በመንግስት የሚያዘው በጀት በመደበኛ መርሃ ግብር ማስተማር እያስከተለ ያለውን የደመወዝ በጀት ጭማሪ ለመቀነስ በክረምት መርሃ ግብር ማስተማር የተሻለ መሆኑን በማመን በክረምት መረሃ ግብር ለማስተማር የተያዘ የስልጠና ዕቅድ በዲግሪ 1000 ክንውን ወ -262 ሴ-112 ድ -374 አፈፃፀም 37.4%፣በ2ኛ ዲግሪ 500 ክንውን ወ- 258 ሴ-135 ድ- 393 አፈፃፀም 78.8% ማስተማር ተችሏል፡፡

ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በ2015 ዓ.ም በመደበኛ መርሃ ግብር በመጀመሪያ እና በ2ኛ ዲግሪ እንዲሁም በሌሎች መርሀግብሮች በመደበኛ መርሃ ግብር ለመማር መስፈርቱን የሚያሟሉ በመጀመሪያ ዲግሪ ወ 119 ሴ 48 ድምር 167 ተመልምለው ቢላኩም ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት መስኮች ሲታጠፉ የሁለተኛ ዲግሪ 87 ተማሪዎች ግን ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

የረጅም ጊዜ ስልጠናን በተመለከተ የተገኙ እድሎችን በወቅቱ ለተጠቃሚዎች ማድረስ መቻሉ በጥንካሬ የሚታይ ቢሆንም አፈጻጸሙ ከእቅድ አንጻር ሲታይ የመጀመሪያ ዲግሪ 48.8%፣2ኛ ድግሪ 78.6% እንደሆነ ያሳያል፡፡ለአፈጻጸሙ መቀነስ ዋናው ችግር ዞኖች በበጀት እጥረት ምክንያት ከኮታ በታች መልምለው መላክ፣በዩኒቨርስቲዎች በኩል ደግሞ ከሚፈለገው ቁጥር በታች ስለሆነ ብዙ የትምህርት መስኮች እንዲታጠፉ መደረጉ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡በመሆኑም በቀጣይ የሰው ሃብት ልማቱን በተማከለ መልኩ ለመምራት እንዲቻል ማንኛውም ስልጠና በኮሚሽን ፀድቆ ማለፍ ያለበት በመሆኑ ከግብርና ቢሮ፣ከጤና ቢሮ እና ከማዕድን ቢሮ የመጡ የረጅም ጊዜ የስልጠና እድሎች መታቀዳቸውን እና በጀት መፈቀዱን በማረጋገጥ ጸድቀው ወደ ዞኖች ለምልመላ የማውረድ ስራ ተሰርቷል፡፡

## የፈፃሚውን አቅም ክፍተት በመለየት የተሰጠ የአጭር ጊዜ ስልጠና

በተቋማት የሚስተዋለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል በየደረጃው ላሉ ፈፃሚዎች ክፍተትን በጥናት ላይ ተመስርቶ በመለየት እና ከዚህ በፊት በተፈጠሩት የንቅናቄ መድረኮች ከሰራተኛው በቀረበው ጥያቄ መሰረት ኮሚሽኑ ሰራተኛውና አመራሩን በአጫጭር የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን ለመስጠት በእቅድ ይዞ ለመስተዳድር ምክርቤቱ የበጀት ጥያቄ አቀርቦ በማስፈቀድ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ኮሚሽኑ የስልጠና ርዕሶችን በጥናት ላይ ተመስርቶ በመምረጥ፣ተግባሩን ለማስፈጸም የሚያስችል አጭር የማስፈፀሚያ እቅድ በማዘጋጀት እና

ለአስፈጻሚ አካላት በቂ ኦረንቴሽን በመስጠት በ5 ማዕከላት ለክልል ዳይሬክቶሬቶችና ለዞን ቡድን መሪዎች በተመረጡ ርዕሶች የስራ ስነ ምግባርና አገልግሎት አሰጣጥ፣የለውጥና ለውጥ አመራር፣ችግር ፈች የውሳኔ አሰጣጥ አመራርነት፣የሃብት አጠቃቀም፣ክትትልና ግምገማ፤የስሜት ብልህነትና ቡድን አመሰራረት በሚሉ ርዕሶች በዩኒቨርሲቲ መምህራን አማካኝነት ስልጠና አእንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የስልጠና አፈጻጸሙም በክልል በ53 የመንግሰት ተቋማት ለሚገኙ 365 ዳይሬክተሮች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ201 (ወ-163፣ ሴ-38) ( 55%) ከአማራ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ስልጠናው እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የክልል ተቋማት ስልጠና አፈፃፀም ዝቅ ያለበት ምክንያት ተቋማት ሰልጣኞችን እንዲያስገቡ ተጠይቀው የተወሰኑ ተቋማት ሰልጣኞችን ባለመላካቸው ምክንያት ነው፡፡

በአንደኛው ዙር ስልጠና ቅድሚያ ተገልጋይ የሚበዛባቸውና ሰፊ የሰው ሃይል ያላቸውን ተቋማት በመለየት በ13 ዞኖች እና በ8 ሪጆፖሊታንት ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ 1,365 የመምሪያ ቡድን መሪዎችን ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,152 (ወ-860፣ሴ-292) (84.4%) ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በአንደኛው ዙር በክልልና በዞን ተቋማት አገልግሎት ለሚሰጡ ለ1,730 ፈፃሚዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,353 /78.2%/ ፈፃሚዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ቀሪዎቹ ፈጻሚዎች ደግሞ በዚህ ዙር ስልጠና ያልተሰጣቸው ፈፃሚዎች በሁለተኛ ዙር በ2016 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ስልጠናው የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በየደረጃው ባለ የሲቪል ሰርቪስና ሰው ሃብት ልማት ተቋማት አማካኝነት በሰው ሀብት አስተዳደር መመሪያዎች፣ከሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና፣ከለውጥ አመራር አደረጃጀትና አሰራር፣ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በሌሎች ጉዳዮች በበጀት አመቱ ለ35,544 የመንግስት ሰራተኞችን ለማሰልጠን በቅድ ተይዞ ለ30,569 (86%) አመራሮችና ሰራተኞች በልዩ ልዩ የአቅም ማጎልበቻ አጫጭር ስልጠና እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በዞንና ወረዳዎች አማካኝነት ለ78,608 አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 77,856 (99%) በሪፎርም ተግባራት ዙሪያ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡በተመሳሳይ የሰውሃብት ስምሪት ስራዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል በተሰራው ስራ ከሁሉም የስምሪት ስራዎች መካከል መደበኛ ቅጥር 4,241፤የደረጃ እድገት 7,752 ፤ዝውውር 1,981 እና ልዩ ልዩ ምደባ 3,741 የተለያዩ ስምሪቶችን መፈፀም ተችሏል፡፡

## የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርምን መገንባት

በ2015 ዓ.ም የተሻሻለውን የስራ የአፈጻጸም ምዘና ስርዓት ለመተግበር የመንግስት ተቋማት ከሃምሌ 01/2014 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30/2015 ዓ.ም ድረስ መረጃ መላክ ከሚገባቸው 48 የክልል ተቋማት በ31 (65%) ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ ካሉት 2,435 ወንድና 1,648 ሴት በድምሩ ከ3,983 ሰራተኞች መካከል 1,778 ወንድና 1,135 ሴት በድምሩ 2,918 (73.3%) ሰራተኞች በቅርቡ በጸደቀው መመሪያ መሰረት በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት የዕቅድ ውል የያዙ ሲሆን፤ቀሪዎቹ (ግብርና ቢሮ፣ ፍትህ ቢሮ፣ የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣ ክልል ም/ቤት፣የከተሞችና መሰረተ-ልማት ቢሮ፣ገንዘብ ቢሮ፣የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ፣የግብርና ጥራትና ደህንነት ባለስልጣን፣የመሬት ይዞታ ምዝገባና ማረጋገጫ ባለስልጣን፣የሴቶች፣ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ገቢዎች ቢሮ፣ሰላምና ደህንነት ቢሮ በአዲሱ መመሪያ መሰረት ውሉን ለመከለስ በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ ቢሆኑም እስከ አሁን ተግባራዊ አላደረጉም፡፡እንዲሁም ከዞን እስከ ወረዳ ባለው ውል መያዝ ከሚገባቸው 158,824 (89,324 ወንድና 69,500 ሴት) ሰራተኞች መካከል ውል የያዙት 145,775 (83,854 ወንድና 61,921 ሴት) ወይም 91.8% ሰራተኞች ናቸው፡፡

## የተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀት ማጎልበት

ከተቋማት ለሚቀርቡ የመዋቅር፣የሥራ መደብ ይፈቀድልን፣ተፈላጊ ችሎታዎች ይካተቱልን፣የደንብ ልብስና ሌሎችም ጥያቄዎች የክልሉን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በጥናት ወይም በዴስክ ኦዲት አግባብ ውሳኔ ለመስጠት ለተፈቀዱ ሥራ መደቦች የተዘጋጀ የተሻሻለ ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ መመሪያ መጠን የበጀት አመቱ እቅድ 100% ክንውን 100% ሲሆን በሶስቱ የተፈላጊ ችሎታ ጥራዞች ላይ ያሉ ጉድለቶችን እና ያልተካተቱ የስራ መደቦችን በማጠቃለል አራተኛ የተፈላጊ ችሎታ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለክልል ተቋማት እና ለሁሉም ዞኖች እና ከተማ አስተዳድር ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት መምሪያዎች በሃርድና በሶፍት ኮፒ የተሰራጨ ሲሆን የተቋማት የደረጃ ይሻሻልልን ጥያቄዎችን በመቀበል አላግባብ የሚመጡትን በመመለስ አግባብነት ያላቸውን የስራ ዝርዝራቸውን በማዘጋጀት እና በመመዘን ወደ ፌደራል ምዘና ማዕከል ተልከው ምላሽ ሲያገኙ የደረጃ እና የስያሜ ለውጥ ደግሞ 610 መደቦች ጸድቀው ተግባራዊ ከመደረጋቸው ባሻገር እስከ ታችኛው ተጠሪ መዋቅራቸው ድረስ በሚያቀርቡት ተጨማሪ የስራ መደቦች ይፈቀድልን ጥያቄዎች የቢሮዎችን የስራ ባህሪ መሰረት በማድረግ የስራ መደቦችን አስፈላጊነት በዴስክ ኦዲት በማረጋገጥ 3717 ቋሚ፣204 ኮንትራት መደቦች መፍቀድ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በአራቱም ዞኖች 1 ዞን፣ 8 ከተማ አስተዳደሮች፣10 ወረዳዎች፣32 የከተማ ቀበሌ እና የገጠር ቀበሌዎች 144 የክልል ተጠሪ ተቋማትን ጨምሮ 903 ሴክተር መስሪያቤቶች ሙሉ መዋቅርና የስራ መደቦች እንዲሁም 456 ትምህርትቤቶች እና 53 ጤና ጣቢያዎች በስታንዳርዱ መሰረት የስራ መደቦች ተፈቅደው ተግባራዊ ተደርገዋል።



የስራ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት ለማጎልበት የተሰጠ ስልጠና

## ወደ አስተዳድራዊ ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮች

በ2015 ዓ.ም በአራቱ ምድብ ችሎቶች 4909 መዝገቦችን ውሳኔ ለመስጠት እቅድ ተይዞ 3958 (80 በመቶ) ይግባኞች ታይተው ውሳኔ ተሰጥተዋል።በተጨማሪም በ32 የክልል ተቋማት በተደረገው የድጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር ስራ እና ምርመራ ተከናውኖ በተፈፀሙ ስምሪቶች ላይ 177 የስምሪት ግድፈት (17.6%) የተገኘ ሲሆን በዚህም በክልልና በዞን ተቋማት የባከነ የመንግስት ገንዘብ ብር 2,096,371 በታዩ 15,385 ፋይሎች ላይ ተገኝቷል።በተሰራው ስራም በዳንግላ ሆስፒታል 44 የጤና ባለሙያዎች ምደባ ስረዛ እና 9 በተለያዩ ተቋማት ላይ

የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን በተለይ ዳንግላ ሆስፒታል ላይ በየወሩ ብር 288,169 የደሞዝ በጀት ያላግባብ እየባከነ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ

### የምዘና ተደራሽነትን ማስፋት

በበጀት አመቱ በአዲስ እውቅና ያገኙ የምዘና ማዕከላትን ለማፍራት በተሰራው ስራ 237 የምዘና ማዕከላትን አዲስ ዕውቅና ለመስጠት ታቅዶ ለ130 የምዘና ማዕከላት አዲስ ዕውቅ የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም 54.85% መሆኑን ያመለክታል፡፡

### የሰልጣኞችን ብቃት ለማረጋገጥ

በ2015 ዓ.ም የሰልጣኞችን ብቃት ለማረጋገጥ ትክክለኛ፣ አስተማማኝና አካታች የሆነ የምዘና ስርዓት መፍጠርና ለማጠናከር በተሰራው ስራ 21,000 በመንግስትና በግል ድርጅቶች በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ የተቀጠሩ ባለሙያዎች ብቃት በምዘና ማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 8,796 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 55.85% ነው፡፡ ተመዝነው ብቁ የሆኑ 4,098 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 46.59% ነው፡፡



## የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ

በበጀት አመቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸውን በምዘና ማረጋገጥን በተሰራው ስራ 24,442 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸው በምዘና እንዲረጋገጥ ለማድረግ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 4,230 ሲሆን አፈፃፀሙም 23.1% ነው፡፡ ተመዝነው ብቁ የሆኑት 2,872 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 67.90% ነው፡፡መደበኛ ስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃታቸው በምዘና ከማረጋገጥ አንጻር በጀት አመቱ 14,113 መደበኛ ስልጠና አጠናቃቂዎች ብቃታቸው በምዘና ማረጋገጥ ታቅዶ ለምዘና የተቀመጡ 20,014 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 100% በላይ ነው፡፡ ተመዝነው ብቁ የሆኑ 7,898 ናቸው፤አፈፃፀሙም 39.5% ነው፡፡



## የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ

የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ የአማራ ህዝብን ታሪክ ለማስረጽ በኪነ-ቅርጽ፤ በመልዕክቶች፤በንባብ ቤቶች፤በኢንተርኔት ቴክኖሎጅ፤ በአንፊ ቲያትር፤ በስዕል ጋላሪ፤ በጋርደኖች፤ በመዝናኛ ቤቶች እያስተማረ ማህበረሰብ መገንባትና የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ ላይ አተኩሮ ይሰራል፡፡በሙዚየምና በስዕል ጋላሪ የሚካተቱ ቅርሶች የአማራ ህዝብ ታሪክና ተጋድሎ የሚያስታውስና ሌሎቹ አሻራዎች ታዋቂ ሰዎችና ሥራዎች እንዲሁም ባለሃብቶች፣ ዮንቨርስቲዎች፣ኮሌጆችና የልማት ድርጅቶች ወዘተ በማሳተፍ የአማራን ክልል ህዝብ ታሪክ ለትውልድ እያስተላለፈ ይገኛል፡፡በመሆኑም በበጀት አመቱ የሀገር ውስጥ የውጭ ሀገር ጎብኝዎች የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያን መገብኘት ችለዋል፡፡



የውጭ ሀገር ዜጎች የአማራ ክልል ህዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሲጎበኙ

### የአገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ

በበጀት አመቱ የጎብኝዎችን ቁጥር በማሳደግ_ለ100,000 የሀገር ውስጥ ጎብኝዎች የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን 46,786 ሲሆን አፈጻጸሙ ደግሞ 47% ነው፡፡ በተመሳሳይ ለ500 የውጭ ሀገር ጎብኝ የጉብኝት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን ወንድ 217 ሴት 78 ድምር 295 አፈጻጸሙ 59% ሆኗል፡፡

በ2015 ዓ.ም ለ80,000 መደበኛ ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ የንባብ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን ወንድ 51,282 ሴት 30,860 ድምር 82,142 (103% )ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ለ30,000 ዲጅታል ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ የንባብ አገልግሎት

ለመስጠት ታቅዶ ክንውን ወንድ 17,651 ሴት 7,836 ድምር 25,487 (85% ) ዲጅታል ቤተ-መጽሃፍት አንባቢ የንባብ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ለ60,000 የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውን ወንድ 55,468 ሴት 2,506 ድምር 57,974 ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 97% ነው፡፡

በተጨማሪም ለ10,000 የኢንተርኔት አንባቢያን የነፃ ንባብ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 599 ሴት 59 ድምር 658 (6.6%) የኢንተርኔት አንባቢያን የነፃ ንባብ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡በተመሳሳይ ለ10,000 አንባቢያን የነፃ ንባብ ለማስነበብ ታቅዶ ወንድ1,199 ሴት 789 ድምር1,988 (19.9 %) አንባቢያን የነፃ ንባብ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል ፡፡ በአጠቃላይ 190,000 በማንዋል፣ በዲጅታልና በኢንተርኔት ንባብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ክንዉን ወንድ 126199 ሴት 42050 ድምር 168249 ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፣አፈጻጸሙ 89% ነው፡፡

## ገቢን ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም ገቢን ለማሳደግ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የጽፈት ቤቱን፣የኢንተርኔት፣የዲጅታል ኮምፒውተሮች፣እስካነርና ፕሪንተሮችን የመጠገን ስራ፣ሲስተምና ኮኔክሽን የማስተካከል ስራ በመስራት ጽፈት ቤቱን ከአላስፈላጊ ወጭ ማዳን ተችሏል፡፡በተመሳሳይ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ከ9ኛ-12ኛ ክፍል በእያንዳዳቸው 13 ዓይነት የመማሪያ መጽሃፍ ድጋፍ ለማግኘት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የትብብር ደብዳቤ ተጽፎ ተጠይቋል ፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በድጋፍ የ12ተኛ መልቀቂያ ፈተና ሽት 25 በሶሻል ሳይንስ 26 በናቹራል ሳይንስ በማምጣት ለንባብ በቅቷል ፡፡እንዲሁም ግማሽ ቢያጆ ለኮምፖስት የሚሆን የእንስሳት ጽዳጅ በትብብር በመጠየቅ ማምጣት የተቻለ ሲሆን ይህም በገንዘብ ሲተመን ብር 2500 የሚገመት ተቋሙን ከወጭ ማዳን ተችሏል፡፡የስእል ጋላሪው ላይ ስዕሎችን ዲስፕለይ ለማድረግ ፕላዝማ ለመትከል ሊወጣ የነበረውን 1,000 ብር በመስሪያ ቤቱ ሙያተኞች እና ከኮብል በመጡ ሙያተኞች ድሪል የማድርግ ድጋፍ በመጠየቅ ተሰርቷል፡፡በተጨማሪም በታሪክና ባህል ሙዚየሙ ውስጥ የአገው ብሔረሰብ መገለጫ የሆነውን ጃንጥላ በጽፈት ቤቱ ሀላፊ ጥረት ከዞኑ በትብብር በማስመጣት ተቋሙ ሊያወጣው የነበረውን ብር 2,800.00/ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ ማዳን ተችሏል፡፡ፎቶዎች ለእይታ የሚቀርቡባቸው 24 ፍሬሞችን ከንብረት ክፍል መርጦ በማውጣትና ያሉትን በመጠቀም ማዕከሉን ሊያወጣው የነበረውን 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ ብር/ አስቀርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለሰርግ ጋርደኖች በካይዘን የተወገደ ማይካን በመጠቀም የህትመት ስራ

በማሰራት ለእያንዳንዱ የሰርግ ጋርደን ቁጥር በማዘጋጀት ቁጥሮችን በየጋርደኖች በማስቀመጥ ጽፈት ቤቱን ከወጭ ማዳን ተችሏል። 31 የፎቶ ፍሬሞችን ከንብረት ክፍል መርጦ በመጠቀም ማዕከሉ ሊያወጣው የነበረውን ብር 50,000 ወጭ ማዳን ተችሏል።ሌላው ቅርስ በትብብር በፅህፈት ቤቱ ባለሙያ ስለቀረበ ተቋሙ ሊያወጣው የነበረውን ብር 1,000 ማስቀረት ተችሏል።

በ2016 በጀት ዓመት ከፕሮጀክት ስራዎች አኳያ ለክልሉ መንግስት የብር 31,136,947.5 ለፏፏቴና የፋዉንቴን ማሰሪያ የሚሆን የፕሮፖዛል ሰነድ የካፒታል በጀት መጠየቂያ ቅጾችን በመሙላትና በማዘጋጀት በሃርደና በሶፍት ኮፒ የማስተሳሰፍ ስራ ተሰርቷል። የቤተመጻህፍት ግብዓቶችን ማሟላትና የኪነ-ቅርስ ፕሮጀክት የሚሉ ሁለት የፕሮጀክት ሃሳቦች ፕሮፖዛል ሰነድ ተዘጋጅቷል። ሰነዱ የተዘጋጀው በዳይሬክቶሬቱ በኩል ታይቶ ለጽፈት ቤቱ የማስተሳሰፍ ስራ በመስራት የተዘጋጁ ሰነዶች ለተመረጡ በቁጥር 03 የግል ባለሃበቶች የማድረስ የተሻለ ቢሆንም ከ1 (ከአንድ ባለሃብት በስተቀር ሁለቱ ባለሃብቶች ማገዝ እንደማይችሉ አሳውቀዋል። አንደኛዉ ባለሃብት ግን ዉጤቱን ያሳሳወቀ በመሆኑ የክትትል ስራ እየተሰራ ይገኛል።በመሆኑም ለባለሀብቶች የተሰራውን ፕሮጀክት በመከለስ በበጀት እንዲደገፍ ለክልሉ መንግስት ቀርቧል።

አጠቃሳይ በበጀት አመቱ የተገኘ የገቢ ዝርዝር ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ቀርቧል

| ተ.ቁ | የገቢ ዝርዝር | ዕቅድ | ክንዉን በብር | አፈጻጸም በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከውጭ ሀገር ጎብኚዎች | 27,500 | 34,500 | 125.45% |
| 2 | ከአዳራሽ ኪራይ | 91666.66 | ------ | ------- |
| 3 | ከሀገር ዉስጥ ጎብኚዎች | 137,500 | 452,010 | 328.73.89% |
| 4 | ፎቶ ካሜራ | 2,750 | 975 | 35.45% |
| 5 | ቪዲዮ ካሜራ | 4,583.33 | 300 | 6.5% |
| 6 | ለሰርግ ቀረፃ | 18,333.33 | 81,325 | 443.59% |
| 7 | ከሰርግ አገልግሎት | 137,500 | 47,000 | 34.18% |
| 8 | ዲኮር | 18,333.33 | ---- | ------- |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 9 | ከላይ በራሪ አገልግሎት | 160,416.66 | 246,907 | 153.91% |
| 10 | ከወንበር ኪራይ | 91666.66 | 19,200 | 20.94% |
| 11 | አንፊ ትያተር | 64,166.66 | ------ | ----------- |
| 12 | ልዩ-ልዩ ገቢ(ልደት) | | 6,725 | -------- |
| | | 754,416.66 | 888,942 | 117.83% |

## የታሪክ መረጃ ስብስብን ማሳደግ

በ2015 ዓ.ም በሙዚየሙ የባህል ኮርነር ውስጥ መሟላት የሚገባቸው ተጨማሪ ባህላዊ አልባሳትና የተለያዩ ቅርሶችን በማሰባሰብ ለጉብኝት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሙዚየሙ ውስጥ ተገዝተው የገቡ የአማራ ህዝብን ባህላዊ መገለጫ አልባሳትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ የአጼ ቴወድሮስ መድፍ (ሲቫስቶፖል) የተሰራበት የብረት ቁርጥራጭ በማምጣት ሙዝየም ላይ ለጉብኝት ማስቀመጥ ተችሏል፡፡ከስዕል ጋላሪ ውጭ በቤተ-መዛግብት ውስጥ ያሉ ስዕሎችን እንደገና በሶፍት ኮፒ ፎቶ የማንሳት፡፡የማደራጀትና በፕላዝማ ለእይታ ዝግጁ እንዲሆኑ ለስዕሎች ካብሽን ማዘጋጀት እና ፕላዝማው ላይ የመጫን ስራ ተሰርቷል፡፡ተጨማሪ የአማራ ህዝብን ታሪክና ባህል የሚያሳዩ 31 የፎቶዎች መረጃ በሶፍት ኮፒ ፎቶ ቤት ተሰጥቶ ማሳጠብ ተችሏል፡፡ቀደምት የአማራ ነገስታት ይጠቀሙባቸው የነበሩትን የአጼ ቴዎድሮስ ጣምራ ጦር በትዕዛዝ ሞዴል ማሰራት ተችሏል፡፡

### የቱሪስት መዝናኛ አገልግሎትን ማስፋፋት

በ2015 ዓ.ም የቱሪስት የመዝናኛ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ከአሁን በፊት ለጥገና አስቸጋሪ ሁኖ የቆየውን የፋዉንቴን ጥገና በጽፈትቤቱ ሰራተኞች ማሻሻያ በመስራት የፋውንቴን አገልግሎት በመስጠት የጎብኝና የቀረጻ ቁጥር እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ጋርደን ልማቱንና ፅዳቱን ለጎብኝዎች ማራኪ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡የውበት አበባዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በየጋርደኖች በማዘጋጀት መትከል ተችሏ፡፡



ጎብኝዎች በፋዉንቴን አገልግሎት ላይ በከፊል

## የስራ ዕድል ፈጠራ

በ2015 ዓ.ም ለ12000 ዜጎች ጊዚያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ4297 ወንድና ለ2407 ሴት በድምሩ ለ6714 ዜጎች የበር ግንባታ ባለሙያና ከካፊቴሪያ ሰራተኞች ጊዚያዊ የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

# IV.መልካም አስተዳደር ዘርፍ

# የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን

### የደንበኛ መረጃ ፍላጎት ጥናት

የደንበኞችን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት በመረጃ ፍላጎት ዙሪያ በክልል ቢሮ ደረጃ አንድ የደንበኛ መረጃ ፍላጎት ጥናት ለመስራት ታቅዶ ክንውን 1 አፈፃፀም 100% እንዲሁም በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃ 194 የደንበኛ መረጃ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 183 ጥናቶችን በማካሄድ አፈፃፀም 95% ደርሷል፡፡

### ኘሮጀክቶች መቅረፅ

ለአካባቢ ሚዲያዎች ማቋቋሚያ፣ ቁሳቁስ ማሟያ እና ለክትትልና ድጋፍ ማስፈጸሚያ የሚሆን 153 የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክት ለመቅረጽ ታቅዶ 203 ፕሮጀክት በመቅረጽ አፈጻጸሙን ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ እቅድ ከነበራቸው ዞን፣ ብሔረስብ እና ከተማ አስተዳደሮች መካከል ከክልል ቢሮ በጀትና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ፕሮጀክት በመቅረጽ ገቢ ያገኙና ለአዲስና ለነባር የአካባቢ ሚዲያዎች ማቋቋሚያና ማጠናከሪያ አገልግሎት ያዋሉ ዞኖችም ምስራቅ ጎጃም ዞን

800,728፣ ሰሜን ሸዋ 987,637፣ ደቡብ ጎንደር ዞን 602,9810፣ ማዕከላዊ ጎንደር ዞን 690,019 ፣ሰሜን ወሎ ዞን 660,858፣ ደቡብ ወሎ ዞን 1609,300፣ ዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር 988,400፣ አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር 138210፣ ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር 51000.00፣ ሰሜን ጎንደር ዞን 30000.00፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን 534340.00፣ምዕራብ ጎንደር ዞን 21000፣ ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር 10250፣ ጎንደር ከተማ አስተዳደር 183800.00 እና ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር 2500.00 በአጠቃላይ ድምር 7,311,023 ብር በማግኘት ስራ ላይ ማዋል ችለዋል፡፡

## የአካባቢሚዲያ ማስፋፋት እና ማጠናከር

በ2015 ዓ.ም በወረዳዎችና በከተሞች የአካባቢ የሚዲያ አውታሮች ማስፋፋትና ማጠናከር በዕቅድ የሚመራ ተግባር ሲሆን እነዚህን ሚዲያዎች በመጠቀም በአካባቢው የተከናወኑ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለአካባቢው ህብረተሰብ በማቅረብ የሚዲያ አሰራሮችን ብቃትና የአካባቢውን ህብረተሰብ ግንዛቤ ማጎልበት ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም 27 ሚኒ ሚዲያ ለማስፋፋት ታቅዶ 15 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 55% ሆኗል፡፡በተጨማሪም ለነባር 2,695 ሚኒሚዲያዎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,729 ድጋፍ በማድረግ የእቅዱን ከ100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡ ከዚህ መካከል 81 የመናኸሪያ፣42 የማረሚያ ቤት እና 1,884 የት/ቤት ሚኒ ሚዲያዎች ሲሆኑ 612 ደግሞ በወረዳና በቀበሌ ለሚገኙ ሚኒሚዲያዎች እንዲሁም 110 ላልተለዩ ሚዲያ ድጋፍ ተደርጓል፡፡እንዲሁም 46 አዲስ ማስታወቂያ ሰሌዳ ለማስፋፋት በዕቅድ ተይዞ 54 በማቋቋም የእቅዱን ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ለ3,306 ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ3,235 ድጋፍ በማድረግ የእቅዱን 98% መፈጸም ተችሏል፡፡በተመሳሳይ 38 አዲስ መረጃ ማዕከል ለማቋቋም እቅድ ተይዞ 27 በማከናወን የእቅዱን 71% መፈፀም ተችሏል፡፡ለ2,371 መረጃ ማዕከላት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ2,355 ድጋፍ በማድረግ የእቅዱን 99% መፈጸም የተቻለ ሲሆን በመረጃ ማዕከል ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በክልል ደረጃ ወንድ 257 ሴት 206 በድምሩ 463፤ በዞንና በከተማ ወንድ 65,902 ሴት 52,613 ድምር 118,515 ሲሆኑ ከነዚህ መካከል 96,125 ያህሉ ወጣቶች ሲሆኑ የደንበኞች የንባብ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡17 አዲስ ቲቪ ፓርክ ለማቋቋም እቅድ ተይዞ ክንውን 19 አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡እንዲሁም 405 ነባር ቲቪ ፓርክ ለማጠናከር ታቅዶ ክንውን 436 አፈፃፀም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

## የማህበረሰብ ሬዲዮ ድጋፍ

በበጀት አመቱ አብዛኛዎቹ የማህበረሰብ ሬዲዮ ያላቸው ዞንና ከተሞችን ለ8ቱ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ በየወሩ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ8 የማህበረሰብ ሬዲዮ ድጋፍ በማድረግ 100% በመፈጸም ለመደገፍ ጥረት የተደረገ ሲሆን ጣቢያዎቹም ወቅታዊ መረጃዎችን ለህዝብ እንዲደርስ አድርገዋል፡፡

## ለአካባቢሚዲያ ድጋፍ በመደረጉ የመጣ ለውጥ

በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡ ሚኒ ሚዲያዎች፣ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣መረጃ ማዕከላት እና ቲቪ ፓርኮች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ በመደረጉ ወቅታዊ መረጃዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡በተደረገው ድጋፍ ራሳቸውን ችለው ያልተደራጁ መረጃ ማዕከላት ራሳቸውን ችለው እንዲደራጁ ማድረግ ተችሏል፡፡በቲቪ ፓረክ ያልተቋረጠ ፈጣን አገልግሎት መስጠት በመቻሉ የተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣ለመረጃ ማዕከላት ግብዓት በመሟላታቸው ደንበኞች የመረጃ ተጠቃሚ መሆናቸው፣የኮሙዩኒኬሽንና የህዝብ ግንኙነት የሚዲያ ተቋማት የጋራ ፎረም ተግባሩ የተፈጸመው በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 4 ለማከናወን ታቅዶ 4 ጊዜ በመወያየት አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡በውይይቱ ወንድ- 40 ሴት- 8 ድምር- 48 የተሳተፉ ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 16% ነው፡፡

## የሕዝብ ግንኙነት፤ የሚዲያ አካላት እና የአማተርና የኪነ-ጥበባት ዘርፍ

በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃ 763 ፎረሞችን ለማካሄድ ታቅዶ 720 በማከናወን አፈፃፀሙም 94% የደረሰ ሲሆን፡፡በክልል ቢሮ ደረጃ 103 የአቋም መግለጫዎችን ታቅዶ 164 ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የኮሚዩኒኬሽን መዋቅሮች በልዩ ልዩ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የመወያያ የፓናል ውይይቶች ማካሄድ የሚጠበቅ ሲሆን አጠቃላይ በክልል ቢሮ፣በዞን እና በወረዳ ደረጃ 743 የፓናል ውይይቶችን ለማካሄድ ታቅዶ 772 ፓናሎችን በማካሄድ እቅዱን ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ በክልል ቢሮ ደረጃ ዕቅድ 4 ክንውን 2 አፈፃፀሙም 50% ሲሆን በውይይቱ ወንድ 1,176 ሴት 613 ድምር 1,789 መሣተፍ ችለዋል፡፡ የሴቶች ተሳትፎም 34% ነው

በበጀት አመቱ በወር አንድ ጊዜ በተመረጡ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ የሚዲያ መግለጫ (የፕሬስ ኮንፈረንስ) መድረኮችን በተመለከተ የክልሉን ርዕሰመስተዳድርና የዞን አስተዳደሮችን ጨምሮ ከክልል እስከ ወረዳ በተለያየ የኃላፊነትና የሙያ ዘርፍ ላይ የሚገኙ የሴክተር

ኃላፊዎች ስለሴክተራቸው እንቅስቃሴ ለኅብረተሰቡ መረጃ እንዲሰጡና በሚዲያ አማካኝነት መልዕክት እንዲያስተላልፉ በዘርፉ 2,244 የሚዲያ መግለጫዎችን ለማስጠት ታቅዶ 2,047 መግለጫዎች እንዲተላለፉ በማድረግ 91% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው በሚገኙ የዘርፉ ተቋማት በክልሉ ልዩ ልዩ አካባቢዎች በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የሚከናወኑ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመር በተሰራው ስራ በክልል ቢሮ ደረጃ 2 ጊዜ ተሞክሮ ቀምሮ ለማስፋት ዕቅድ ተይዞ 2 ጊዜ በማከናወን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡በሌላ በኩል እንደ ክልል 2,240 መልዕክት ለመቅረፅ ዕቅድ ተይዞ 2,654 በመሰራቱ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## ሚዲያ ጥቆማ

በ2015 ዓ.ም በቢሮ ደረጃ በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮችና ክንውኖች በመገኘት ለአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን፣ለብልጽግና ፓርቲ፤ሶሻል ሚዲያ ዘርፍ፣ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ለፋና፣ ቪኦኤ እና ለኢቢሲ ጥቆማ በመስጠት እንዲዘግቡ የተደረገ ሲሆን እንደ ክልል እቅድ 2,242 ክንውን 3,357 ጥቆማ በማድረግ የእቅዱን ከ100% በላይ መፈጸም የተቻለ ሲሆን በክልል ቢሮ ደረጃ እቅድ 24 ተይዞ 70 በማከናወን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡እንዲሁም በዞንና ከተማ አስተዳደሮች 2,218 የሚዲያ ጥቆማዎችን ለመስጠት ታቅዶ 3,287 ጥቆማዎችን ለተለያዩ ሚዲያዎች በመስጠት ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

## ዕለታዊ የስልክ መረጃ ልውውጥ

በበጀት አመቱ የክልሉን ዕለታዊ ሁኔታ ለመከታተል በተሰራው ስራ በስልክ ከ500 በላይ መረጃዎችን በመቀበል ለሚመለከተው ለውሳኔ ሰጭ አካል በወቅቱ በመሰብሰብ መስጠት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ መረጃውን በአግባቡ መያዝ ተችሏል፡፡

## ሳምንታዊ መረጃ ልውውጥ

በክልል ቢሮ ደረጃ በየሣምንቱ ከዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የሚሰበሰበውን ሣምንታዊ መረጃ ልውውጥ ለማጠናቀር በተሰራው ስራ ዕቅድ 52 ክንውን 52 ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡እንዲሁም  የመረጃ ትንተና ሥራ በመሥራት ለተጠቃሚ ከማቅረብ አኳያ መረጃ ለመሰብስብ በዕቅድ የተያዙ መረጃዎች እቅድ 132,748 ክንውን 131,655 አፈፃፀም 99% ተከናውኗል፡፡ ከተሰሩ ሳምንታዊ መረጃ ልውውጥ መካከል  በክልል ቢሮ ደረጃ እቅድ 610

ክንውን 615 አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው፡፡ እንዲሁም በዞንና በከተማ አስተዳደር ዕቅድ 132,138 ክንውን 131,040 አፈፃፀም 99% ሆኗል፡፡

## መረጃ ማደራጀት

በበጀት አመቱ 132,748 የተለያዩ መረጃዎችን ለማደራጀት እቅድ ተይዞ ክንውን 131,655 ሲሆን አፈፃፀሙም 99% ነው፡፡ በተመሳሳይ በክልል ቢሮ 610 የተለያዩ የመረጃዎችን ለማደራጀት ታቅዶ ክንውን 615 አፈፃፀም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡እንዲሁም በዞንና በከተማ አስተዳደር 132,138 የተለያዩ መረጃዎችን ለማደራጀት ታቅዶ ክንውን 131,040 አፈፃፀም 99% ሆኗል፡፡




በክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ የተደራጀ የሶፍት ኮፒ መረጃ

## መረጃ ማሰራጨት

በ2015 ዓ.ም 21,897 መረጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 26,251 መረጃዎችን በማሰራጨት የእቅዱን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡በክልል ቢሮ ደረጃ እቅድ 325 ክንውን 468 አፈፃፀም ከ100% በላይ ሲሆን በዞንና ከተማ አስተዳደር እቅድ 21,572 ክንውን 25,783 አፈፃፀም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

## ወቅታዊ መረጃ መተንተን

በበጀት አመቱ 739 ወቅታዊ መረጃዎችን ለመተንተን እቅድ ተይዞ 785 በማከናወን አፈፃፀሙን 100% በላይ መፈፀም ተችሏል፡፡በዝርዝር ሲታይ በክልል ቢሮ እቅድ 10 ክንውን 9 አፈፃፀም 90% መተንተን ተችሏል፡፡እንዲሁም በዞንና ከተማ አስተዳደር 729 መረጃዎችን ለመተንተን ታቅዶ 776 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀም ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

## ህትመትና ስርጭት

በበጀት አመቱ በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ በተሰራው ስራ በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በዕትም 2,784 በእቅድ ተይዞ 3,040 በማዘጋጀት አፈፃፀሙን ከ100% በላይ ማከናወን የተቻለ ሲሆን 696,000 ቅጅዎችን በማዘጋጀት ለማሰራጨት ታቅዶ 983,411 ቅጅዎችን በማሰራጨት የእቅዱን ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ 4 ፖስተር ለማዘጋጀት ታቅዶ 4 ፖስተሮችን በማዘጋጀት 100% የተፈጸመ ሲሆን ለዌብ ሳይት ዝግጁ ተደርገዋል፡፡ፖስተር የተሰራባቸው ይዘቶችም ወቅታዊና መረጃ ሰጭ በሆኑ በመስኖ ልማት፣ መዘናጋት ይቁም፤ በኤች አይ ቪ ዙሪያ እና በሰብል ልማት ዙሪያ ናቸው፡፡በተመሳሳይ 2 ቡክሌት ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 በማከናወን 50% መፈጸም ተችሏል፡፡የተዘጋጀው የቡክሌት ይዘት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የምርምር ውጤቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡በሌላ በኩል ለዌብ ሳይት የሚመጥን አርቲክል ለማዘጋጀት በተሰራው ስራ 12 አርቲክል ለማዘጋጀት ታቅዶ 12 በማከናወን አፈጻጸሙ 100% ደርሷል፡፡

## ዜና ማዘጋጀት

በበጀት አመቱ በክልል ቢሮ ደረጃ 288 የጽሑፍ ዜናዎችን ለማዘጋጀትና ለማስራጨት ታቅዶ 100 በማሰራጨት የእቅዱን 35% መፈጸም ተችሏል፡፡በዞኖች መሰራት የነበረበት የቴክስት ዜና አቅድ 12,123 ሲሆን ክንውን 16,502 አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አጠቃላይ የተሰራ ዜና እቅድ 12,411 ክንውን 16,602 አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በክልል ቢሮ ደረጃ 144 የምስል ዜናዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 40 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 28% ብቻ

ነው፡፡አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነው በክልል ደረጃ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው ካሜራ በአጋቾች ምክንያት እስከ መረጃው ባለመመለሱ እና ባለመገዛቱ ነው፡፡በዞኖች 10,090 የምስል ዜናዎችን ለመሰራት ታቅዶ ክንውን 9,810 አፈፃፀም 97% ነው፡፡ በአጠቃላይ የምስል ዜና እቅድ 10,234 ክንውን 9,850 አፈፃፀም 96% ነው፡፡

## ፕሮግራምና ዘጋቢ ፊልም መስራት

በዞንና ከተማ አስተዳደር ደረጃ መሰራት የነበረበት የአካባቢ ማስተማሪያ ፕሮግራም ዕቅድ 2,442 ክንውን 2,512 ሲሆን አፈፃፀሙ 100% በላይ ነው፡፡እንዲሁም በቢሮ ደረጃ 12 የቴሌቭዥን ፕሮግራም ለማዘጋጀት ታቅዶ 11 በማከናወን 92% መፈጸም ተችሏል፡፡በቢሮ ደረጃ 2 ዘጋቢ ፊልም በማዘጋጀት የህብረተሰቡን የመረጃ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዶ 1 በማከናወን አፈፃፀሙ 50% ሆኗል፡፡

## መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያ መጫን

በክልል ቢሮ ደረጃ ተሰርተው ለፌስቡክ መጫን የነበረባቸው ዜናዎች ብዛት እቅድ 432 ሲሆን ክንውን ደግሞ 389 አፈፃፀም 90% ነው፡፡በዞኖች ተሰርተው ለፌስቡክ መጫን የነበረባቸው የዜናዎች ብዛት ዕቅድ 22,205 ክንውን 41,405 አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው፡፡አጠቃላይ ለፌስቡክ መጫን የነበረባቸው ዜናዎች እቅድ 22,637 ክንውን 41,794 አፈፃፀም ከ100% በላይ ነው፡፡በዩቲዩብ ክሊፖችን አዘጋጅቶ መጫንን በተመለከተ እንደ ክልል ቢሮ እቅድ 96 ክንውን 30 አፈፃፀም 31% ነው፡፡ በዞኖች መሰራት የነበረበት የዩቲዩብ ክሊፕ ዕቅድ 8,094 ሲሆን ክንውን 7,751 ሲሆን አፈፃፀሙ 96% ነው፡፡ አጠቃላይ በዘርፉ እቅድ 8,190 ክንውን 7,781 አፈፃፀም 95% ነው፡፡

## በሚኒ ሚዲያ መረጃዎችን ማስተላለፍ

የዞኖችን ሚኒ ሚዲያ ተጠቅሞ 16,560 ዜናዎችን ለማስተላለፍ ታቅዶ 21,063 ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ100% በላይ ሆኗል፡፡በሦስቱ ሜትሮ ፖሊታን እና በሶስቱ ሪጅኦ ፖሊቲያን ከተሞች 288 የሬድዮ ፕሮግራም ለማዘጋጀትና ለማስተላለፍ ታቅዶ 233 የሬድዮ ፕሮግራም በማዘጋጀት 81% ማሰራጨት ተችሏል፡፡

## ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

ክልላችንን አስመልክቶ በህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በመንግስት እና በግል ሚዲያዎች ውስጥ የተዘገቡ መረጃዎችን በመዳሰስ እና ከሚመለከተው ዞንና ከተማ አስተዳደሮች በማጣራት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን በአጠቃላይ 1,645 በአዎንታ እና 840 በአሉታ በድምሩ 2,485 ዘገባዎች ተዘግበዋል፡፡እነዚህም በማህበራዊ 473፣ ከኢኮኖሚያዊ 648ና በፖለቲካዊ 1,364 ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

### የህዝብ አስተያየት ጥናት

በ2015 ዓ.ም ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ 1,158 የህዝብ አስተያየት ለማጥናት ታቅዶ 1,186 በማከናወን አፈፃፀሙን ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡እንዲሁም በክልል ደረጃ 2 የህዝብ አስተያየት ለማጥናት ታቅዶ ክንውን 2 አፈፃፀሙ 100% ደርሷል፡፡በተመሳሳይ በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች 1,156 መደበኛ የህዝብ አስተያየት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 1,184 በማከናወን አፈፃፀሙን ከ100% በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡በዚህም ወንድ 3,867፣ሴት 2,825 በድምሩ 6,692 የህብረተሰብ ክፍል የተሳተፈ ሲሆን ከነዚህ መካከል 1,931 ያህሉ ወጣቶች ናቸው፡፡ወቅታዊ የህዝብ አስተያየት ጥናት እቅድ 10 ክንውን 10 አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡በዞን ደረጃ የአካባቢ ሚዲያዎች ላይ ጥናት በማድረግ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅና ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት እንዲሁም ጠንካራ ጎናቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል196 የአካባቢ ሚዲያ ጥናት ለማከናወን ታቅዶ 168 በማከናወን አፈፃፀሙን 86% ማድረስ ተችሏል፡፡

## ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና

### ስልጠናና ግንዛቤ ፈጠራ

በ2015 ዓ.ም ከትምህርት ተደራሽነት አንጻር በገፅ ለገፅ በሁሉም የስልጠናና ግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በማዘጋጀት 519,577 ለሚሆኑ ለተለያዩ የህብተረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ሴት-587,783 ወንድ 606,803 ድምር 1,194,550 ለሚሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስነምግባር እና በሞራል ዕሴቶች ግንባታ እንዲሁም በሙስና መከላከል ዙሪያ ላይ ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡በተጨማሪም የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የመልካም ሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የተከናወኑ የሥነ-ምግባር ሞራል እሴቶችን የሚገነባ መልዕክቶችን በሬዲዮ እና በቴሌቪዥ አንድ ስፖት ለማስተላለፍ ታቅዶ አንድ ማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም የስነ ምግባር አስተምሮ ያላቸውን መልዕክቶች በማህበራዊ ሚዲያ በዓመቱ በቀን 5 መልዕክት ስሌት1,320

መልእክቶችን ለማስተላለፍ ታቅዶ ክንውን 1,257 ወይም 95.22% ማድረስ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ በበኩር ጋዜጣ ማሳተም እና በራሪ ወረቀቶች 24፣ 17 ጊዜ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ለማዘጋጀት ታቅዶ ክንውን 19 እና 30 በቅደም ተከተል በማሳተምና ፕሪንት በማድረግ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል ::



ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፍታውራሪ ሀብተማሪም አጠ/ 2ኛደረጃ ት/ቤት በስነ -ምግባር ዙሪያ ስልጠና ሲሰጥ-ባህርዳር

## ጥናት በማካሄድ በተለዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረግ

በ2015 ዓ.ም ጥናት በማካሄድ በተጠኑ ጥናቶች ላይ ከባለ ድርሻ እና አጋር አከላት ጋር ውይይት ለማድረግ በተሰራው ስራ ከፍተኛ በጀት የሚመደብላቸው እና የአሰራር ክፍተት የሚታይባቸውን ተቋማት በመለየት የአሰራር ሥርዓታቸውን በጥናት በማረጋገጥ 7 የመፍትሄ

ሃሳብ ለማቅረብ ታቅዶ 7 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 100 ደርሷል፡፡ በተመሳሳይ በተቋማት ላይ የተጠኑትን ጥናት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ምክክር ለማድረግ 5 ታቅዶ ክንውን 5 አፈፃፀም 100% ሲሆን ጥናቱ የተካሔደበት ተቋም በባህር ዳር ከተማ በመሠረታዊ ፍጆታዎች በተለይም በሲሚንቶ አቅርቦት እና ሥርጭት፣ በገቢዎች ዙሪያ የተጠናው የአሠራር ሥርዓት የሚመለከታቸውን አካላት በመሰብሰብ አውደ ጥናት ተደርጎበታል፣ በቀበሌ ቤቶች ዙሪያ የተከናውነው የጥናት ሥራ ለሚመለከታቸው የተጠኘ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ቀርቦ ስምምነት ተደርሶበት ወደ ትግበራ ተገብቷል፣በጎንደር ከተማ መሠረተ ልማት እና የስመ ንብረት ዝውውር እንዲሁም በጎንደር ከተማ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ተጠሪ ጽ/ቤት ጥናት ተደርጎ ውጤት ተገኝቶበታል፡፡



በነዳጅ ድጎማ ዙሪያ በተጠና ጥናት ላይ ውይይት ሲደረግ- እንጅባራ ከተማ

### ሀብት ማስመዝገብ

በ2015 ዓ.ም ከሙስና ተግባራት ጋር በተያያዘ ለሚካሄደው የምርመራ ስራ፣የክስና ክርክር ስራ በማስረጃነት በማገልገል እንዲሁም የሙስናን ፍሬ ለመለየትና እንዲመለስ ለማድረግ የማይተካ ሚና እንዳለው የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ አዋጅ ላይ መረዳት ይቻላል፡፡በዚህም መሰረት የመንግስት ተመራጮች፣ተሿሚዎችም ሆኑ ሰራተኞች የዕለት ተዕለት ስራቸውን የሚያከናውኑት ለህዝብ ጥቅም እንደሆነ በማመን ምዝገባ ያካሄዱ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ምዝገባ ዕቅድ 3,000 ክንውን ሴት- 2,702 ወንድ- 5,549 ድምር 8,251 ወይም ከ100% የሚሆኑት ሀብታቸውን ማስመዝገብ ችለዋል፡፡በተጨማሪም በእድሳት ምዝገባ የዓመቱ እቅድ 14,500 ሲሆን ሴት 3,096 ወንድ 6,976 በድምሩ10,072 (69.46%) መፈጸም ተችሏል፡፡

## ርዕሰ-መስተዳድር

የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የተቋቋመበት ተግባርና ዓላማ በክልሉ ለሚካሔድ የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች በተለያዩ አስፈፃሚ አካላት በሁለገብ ልማት ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በመዘርጋት ዘላቂ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት በትኩረት እንዲሰሩና በህግ የተሰጣቸውን ተግባርና ሃላፊነት ለማሳካት በክልል ደረጃ ተቀናጅቶ የሚመራበትና አፈጻፀማቸውንም በየጊዜው የሚገመግምና መንግስታዊ ሀላፊነቱን በብቃት የሚወጣ ተቋም ነው፡፡

### የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም ጽ/ቤቱ የቅሬታና የአሰራር ስርዓቱን በማጠናከርና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ቀልጣፋና ፈጣን የሆነ አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት ወደ ስራ ገብቷል፡፡በዚህም በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎት ፈልገው የመጡ ባለጉዳዬች 13317 ሲሆኑ የፆታ ስብጥር ሲታይ ወንድ 12417፣ ሴት 900 ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በግል የመጡ ባለጉዳዮች 2403 ሲሆኑ የፆታ ስብጥር ሲታይ ወንድ 2208፣ ሴት 195 ሲሆኑ በሌላ በኩል በቡድን የመጡትን ባለጉዳዮች ስናይ ደግሞ 10914 ሲሆኑ ወንድ 10209፣ ሴት 705 ባለጉዳዬችን ተቀብሎ በመመዝገብ ጉዳያቸውን በማጣራት ወደ ሚመለከታቸው አካላት መምራት ተችሏል፡፡አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የቀረቡ አቤቱታዎችን በፆታና በእድሜ ሲታይ ወንድ 68,739፣ ሴት 30,330 ድምር 99,069 ሲሆኑ ወጣቶችን ከማስተናገድ አንፃር ደግሞ እድሜያቸው ከ29 ዓመት በታች የሚሆኑ ወንድ 12,216፣ ሴት 7,021 ፣ ድምር 19,237 ሲሆኑ አፈፃፀሙም 19.43% ነው፡፡በተመሳሳይ ተቋሙ በበጀት አመቱ በእቅድ የያዛቸውን ተግባሮች እየገመገመ

ከመምራት በተጨማሪ ለተቋሙ ሰራተኞች የአቅም ግንባት ስልጠና መስጠት ችሏል፡፡

## ከተገልጋዬች የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች

በ2015 ዓ.ም የጽ/ቤቱን የቅሬታና የአቤቱታ የአሰራር ስርዓቱን በማጠናከር ለተገልጋዮች ቀልጣፋና ፈጣን የሆነ ውሳኔ መስጠት የተቋሙ ተግባር ሲሆን ከክልል እስከ ወረዳ አጠቃላይ የቀረቡ አቤቱታዎች ሲታዩ 63134 ናቸው፡፡ በመሆኑም የተገልጋዬች የፆታ ደረጃ ስብጥር ሲታይ ወንድ 68739፣ ሴት 30330 ፣ ድምር 99069 ሲሆኑ ከ29 ዓመት በታች የሆኑ የወጣቶች ድርሻ ደግሞ ወንድ 12216 ፣ ሴት 7021 ድምር 19237 በመሆኑ አፈፃፀሙን 19.43% ማድረስ ተችሏል፡፡በዚህም ደረጃውን ጠብቆ የቀረበ አቤቱታ ሲታይ ወንድ 6250፣ ሴት 3450 ድምር 9,703 አፈፃፀም 9.79% ሲሆን በሌላ በኩል በጽሁፍ ቀርበው ውሳኔ የተሰጣቸው አቤቱታዎች ወንድ 6,215፣ ሴት 3,436 ድምር 9,654 ናቸው፡፡ሌሎች የቀረቡ አቤቱታዎች ውሳኔ ሳይሰጣቸው በሂደት ላይ የሚገኙባቸው ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች በዝርዝር ሲታዩ ደብረ ማርቆስ ከተማ 47፣ ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር 8፣ ምዕራብ ጎንደር 11፣ ደቡብ ጎንደር 4፣ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህም ደረጃውን ያልጠበቀ አቤቱታን ሲታይ ወንድ 30,724፣ ሴት14,986 ድምር 45,710 ሲሆን አፈፃፀም 46.13% ነው፡፡በደንቡ መሰረት የማይታዩ አቤቱታዎችን በተመለከተ ወንድ፣ 31,765 ሴት 11,894 ድምር 43,659 ሲሆን አፈፃፀሙ 44.06% ሆኗል፡፡

በስታንደርዱ መሰረት ውሳኔ ለመሰጠት በአማካይ የወሰደው ጊዜ በክልል ደረጀ 6 ቀን፣ በዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ 8 ቀን ሲሆን በክልል ደረጃ ከተቀመጠው ስታንደርድ በ14 ቀን ሲቀንስ በዞኖች ደረጃ ከተቀመጠው ስታንደርድ ደግሞ በ7 ቀን በመቀነስ ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን የጽሁፍ ውሳኔ ከተሰጣቸው 7,337 ጉዳዮች ውስጥ በስታንደርዱ መሰረት ውሳኔ የተሰጣቸው 5,715 ሲሆን፣ 117 ደግሞ ከስታንደርዱ በላይ ውሳኔ የተሰጣቸው ናቸው ፡፡ በመሆኑም 1,505 ጉዳዮች በምን ደረጃ ውሳኔ እንደተሰጣቸው ያላሳወቁ ዞኖች ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ ሰሜን ወሎ እና ሰሜን ጎንደር ዞኖች ናቸው፡፡

ከተሰጡት ውሳኔዎች ውስጥ ያልፈፀሙ ወንድ 19 ፣ ሴት 7 ድምር 26 ሲሆኑ በበጀት አመቱ ውሳኔ ተሰጥቶ አለመፈፀም ደግሞ በተቋሙ ላይ አሉታዊ ተፅኖ ስለሚያደረስ በዚህም ዙሪያ ትኩረት ተደርጎ ክትትል ከሚያስፈልጋቸው ዞኖች መካከል ምዕራብ ጎንደር 1፣ ሰሜን ወሎ 2 ፣ ደቡብ ወሎ 1፣ ምዕራብ ጎጃም 3፣ አዊ 1፣ ጎንደር ከተማ 16 በድምሩ 24 የሚሆኑ ጉዳዮች ያልተፈፀሙና በሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡



## በተገልጋይ ቅሬታ ዙሪያ የተካሄደ ውይይት

### የቅሬታ ምንጭ ፍተሻ

በበጀት ዓመቱ በክልል ደረጃ በርካታ ጥናቶችን በማካሄድ በተለያዩ የመንግስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ የቅሬታ ምንጮችን ለይቶ ፍተሻ ለማካሄድ በ15 የዞንና ሪጆፖሊታንት እንዲሁም በ15 ወረዳዎች በሚገኙ 30 ሴክተር መስሪያ ቤቶች ላይ ለማካሄድ ታቅዶ በ8 ዞኖች፣ በ8 ወረዳዎች እና በ16 ተዋረድ ተቋማት ላይ ፍተሻ በማካሄድ ግብረ መልስ አዘጋጅቶ ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ በማድረግ ግብረ መልስ የመስጠት ተግባር ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም በዞን ደረጃ 100 ተቋማት ከተያዘው በ17 ዞን በሚገኙ ለ77 ተቋማት መፈተሽ ችለዋል፡፡ ተግባሩን በዞን ደረጃ ሰሜን ጎንደር ፣ማዕከላዊ ጎንደር፣እና ደብረ ብርሃን ከተማ ውጭ በሌሎች በእቅዱ መሰረት ባይሆንም ለመስራት የቻሉ ናቸው፡፡ በፍተሻው የተገኙ ውጤቶችን ግብረ መልስ አዘጋጅቶ በወቅቱ መስጠትና የመጡ ለውጦች ከመገምገምና ከመለካት አንጻር ገምግሞ በማዘጋጅ በማሳወቅና ችግሮችን በመፍታት ጭምር ለመፈፀም እየተደረገ ቢሆንም በሁሉም አካባቢ ተደራሽ በማድረግና ውጤታማነቱን በመገምገም በኩል በእጥረት የሚታይ ስለሆነ አጠናክሮ መስራት ያስፈልጋል ።

## የግልፅኝነትና የተጠያቂነትን የአሰራር ስርዓትን ማጎልበት

በ2015 ዓ.ም የጽ/ቤቱ የህዝብ ቅሬታ የአሰራር ስርዓት ደንብ ቁጥር 179/2011 እና መመሪያ ቁጥር 2/2012 እንዲሁም በሌሎች የአሰራር ማንዋል ላይ ለተዋረድ የመንግስት ተቋማት ሙያተኞችና አመራሮች ለ1,732,688 ለሚሆኑ የህብተረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመፈጠር ታቅዶ ወንድ፣ 867,518 ሴት 521,131 ድምር 1,405,445 ለሚሆኑት ሙያተኞችና አመራሮች ግንዛቤ የተፈጠረላቸው ሲሆን በዓመቱ ከሚጠበቀው 81.11% መፈፀም ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የተፈጠረው ግንዛቤ ውጤታማነት ሲገመገም ደረጃውን ያልጠበቀ አቤቱታ በብዛት የሚቀርብ በመሆኑ በቀጣይ በጥራትና በተከታታይ ትኩረት ተሰጥቶ የግንዛቤ ፈጠራ ስራውን መፈፀም ያስፈልጋል። በተጨማሪም በክልል ደረጃ የይድረስ ለመንግስት አሰራር እና የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓቱ ላይ እየገጠሙ ያሉ ችግሮችና መፍትሄዎች ከተዋረድ ተቋማት፣ ከአጋርና ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከየጽ/ቤቱ አመራሮችና ሰራተኞች እንዲሁም የህዝብ ክንፍ ጋር በተገኙበት ሦስት መድረክ በማዘጋጀት ወንድ 427 ሴት 280 ድምር 707 አፈፃፀሙ 88.71% ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡

## የአጭር ጊዜ ስልጠና

በበጀት ዓመቱ በ12ቱ ዞኖች ለሚገኙ 88 ለሚሆኑ አመራሮችና ባለሙያዎች በተጨማሪ በተመረጡ 64 ወረዳዎች ለሚገኙ 230 የወረዳ ባለሙያዎችና ሃላፊዎች በ4 ዙር በመረጃ አያያዝ፣ በምርመራና ማጣራት፣ በህዝብ ቅሬታና አቤቱታ የውሳኔ ደብዳቤ አፀጻፍና የውሳኔ አፈፀፀም ዙሪያ 771 ሰልጣኞች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፀፀሙ 876.13% ሆኗል፡፡



የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የ6 ወር የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና አቅም ግንባታ ስልጠና

## አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን

የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የ2015 በጀት ዓመት እቅዶቹን ማከናወን የጀመረው "2015 የመፍትሔ ዓመት" የሚል መርህ በማንገብ ነው፡፡ አሚኮ ለኅብረተሰብ ለውጥ ሲተጋ ችግሮችን ነቅሶ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የችግሮቹን መፍትሔ የሚጠቁሙ ዘገባዎችን በመስራት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በመወጣት ላይ ነው፡፡

### የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማዘመን

በበጀት ዓመቱ የአሚኮ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለማዘመን የተከናወኑ ዋነኛ ተግባሮች የቴሌቪዥን ዜናና ፕሮግራሞች፣ በአሚኮ ኅብር፣ በአማራ ሬዲዮና በአማራ ኤፍ.ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ በበይነ መረብ፣ በአራቱ የበኩርና የብሔረሰብ ጋዜጦች፤በሚዲያ ቴክኖሎጅ ቀረፃ፣ ስርጭትና ቅንብር፣በሥልጠናና ምርምር፣ በአስተዳደር ሠራተኞችና መሪዎች ለኅብረተሰብ ለውጥ በመትጋት ዓላማዎቹን አሳክቷል፡፡

አሚኮ ተደራሽነትን ለማስፋት እንዲሁም ታዳሚያንን ተጠቃሚ ለማድረግ ለአንባቢያን፣ ለአድማጭና ተመልካቾች እንዲሁም ለበይነ መረብ መረጃ ፈላጊዎች ጥራት ያለው ዘገባ በማቅረብ በዘገባዎቹ ቀዳሚና ተዓማኒ የመረጃ ምንጭ ሆኗል፡፡

### የታዳሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ የታዳሚ ጠተቃሚነትን ለማሳካት የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የዘገባ ሽፋንን ማሳደግና ሽፋን ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የታዳሚን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ለአንባብያን፣ለአድማጭና ለተመልካቾች እንዲሁም ለበይነ መረብ መረጃ ፈላጊዎች ጥራት ያለው ዘገባ በማቅረብ ተደራሽነቱን የማስፋት ስራ ሰርቷል፡፡

## የገቢ አቅምን ማሳደግ

አሚኮን ብራንድ ከማድረግ አኳያ የሁነት ዝግጅት ስራዎችን በማዘጋጀት አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም፣አዳዲስ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ፣ዘጋቢ ዘገባዎችን መዘገብ፣ተቋማትና ግለሰቦች ማስታዎቂያዎች እንዲያሰሩ ማነሳሳት፣የአየር ሰዓትና የሕትመት ገፅ እንዲገዙ ዕድል መፍጠር፤አዳዲስ ፕሮግራሞችን መቅረፅ፣የአጭርና በመካከለኛ ግዜ ስልጠና በመስጠት የገቢ አቅምን ማሳደግ፣ ከዩቱብና ከመሳሰሉት የመጠቀም ዓላማ ለማሳካት ከተያዘው እቅድ 276,782,775.98 ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡አፈፃፀሙም 147 በመቶ ነው፡፡ከዚህ ውስጥ ብር 155,680,591.50 ወደ ካዝና ገብቷል፡፡ከውዝፍ ብር 44,021,112.44 ተሰብስቧል፡፡በበጀት አመቱ በሬዲዮ ብር 384,180 እና በቴሌቪዥን ብር 1,506,330 1,506,330 በድምሩ የብር 1,890,510 ነፃ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡የብር 814,400 ደግሞ የዓይነት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡በአገልግሎቶች ገቢን በመሰብሰብ የኮርፖሬሽኑን አቅም ማሳደግ ተችሏል፡፡

## ተደራሽነትን ማስፋት

አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በ2015 በጀት ዓመት በገጠርና በከተማ እንዲሁም በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ በአራት ጋዜጦች፣ በሰባት የራዲዮና የኤፍ.ኤም. ጣቢያዎች፣ በሁለት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ፣በአሚኮ ቴሌቪዥን እና በአሚኮ ህብር ጣቢያዎች፣በበይነ መረብ፣እንዲሁም በአስራ ሁለት ቋንቋዎች የመረጃ አገልግሎት በመስጠት የመረጃ ተደራሽነቱን በማስፋት  እቅዱን  በአግባቡ አሳክቷል፡፡

አሚኮ በበጀት ዓመቱ የሚዲያ መሰረተ ልማትን በተመለከተ የዘገባ ተደራሽነትን በአግባቡ ፍትሐዊ ለማድረግ ፣የዘገባ ሽፋን ባልተደረሰባቸው ቦታዎች ሽፋን መስጠት፣ለሁሉም ታዳሚያን ዘገባዎች የሚደርሱበትን ሽፋን ማረጋገጥ፣የይዘት ሽፋን ተደራሽነትን ለሁሉም አካባቢ ማስፈን፣ፈጣንና ቀልጣፋ የሆነ አሰራርን መዘርጋት፣ጣቢያዎቹን ስትሪም ማድረግ፣አርካይቮችን በየቅርንጫፎች በማደራጀት ተደራሽነቱን ማስፋት ችሏል፡፡

## የታዳሚ ተጠቃሚነትን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የታዳሚ ተጠቃሚነትን ለማሳካት የዘገባ ሽፋንን ማሳደግና ሽፋን ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ በታዳሚያን ዘንድ ተዓማኒነትን አግኝቶ ዕርካታን የፈጠረ ሲሆን፣በአሳታፊ ዘገባዎችም ተጠቃሚነትን አጎልብቷል፡፡በዚህም የታዳሚን ተጠቃሚነት ለማሳካት በሬዲዮና በቴሌቪዥን፣በጋዜጣና በበይነ መረብ የመገናኛ ብዙኃን አውታሮቹ ከጦርነቱም በኋላ የህብረተሰቡ ሰላም ሲሰፍን አሳታፊ የሆኑ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፣ በአገልግሎት አሰጣጦች ዙሪያ፣ በመልካም አስተዳደር ችግሮች እና መፍትሔዎች፣ እንዲሁም መረጃ የሚሰጡ አስተማሪ እና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በመልሶ ግንባታ በንቃት እዲሳተፍ የሚያደርጉ ዘገባዎችን ለታዳሚያን በማቅረብ የሰላም ስምምነቶች እውን እንዲሆኑ ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡

በዚህም ታዳሚያኑያን የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ የቀረቡት ዘገባዎች ፖለቲካዊ ንቃተ ሕሊናቸው እዲዳብርና መረጃ እንዲያገኙ በፖለቲካው ዘርፍ የአማራ ክልል ምክር ቤት መደበኛ ጉባዔ ስለሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የአማራ ህዝብ መፈናቀል በተመለከተ እገታና ግድያ መረጃ የሚሰጡና መፍትሔ የሚጠቁሙ ዘገባዎች ተላልፈዋል፡፡

በሌላም በኩል የሰላም ድርድሩ ሂደት እና ጥንቃቄዎች የአማራ ህዝብ ውስጣዊ አንድነትን ማጠናከር፣ የመደማመጥና የመሰማማት ባህልን ማዳበር፣ የአማራ ፓርቲዎችን የጋራ ጉዳይ ትግሎች፣ የሰርጎ ገብ ቁጥጥርና ሃይል ማዘጋጀት፣ ዲፕሎማሲያዊ ጫናን መቋቋምና የውጭ ጣልቃገብነት በተመለከተ ዘገባዎች እየተተነተኑ ሲሆን ለታዳሚያን ቀርበው ታዳሚያን ግንዛቢያቸውን አሳድገዋል፡፡ በተጨማሪም የአሚኮ የሥራ አፈጻጸም የቋሚ ኮሚቴ ግምገማ፣ የአሚኮ የክልል ምክር ቤት የሥራ ግምገማ በዘገባ ሽፋን ተሰጥቶ ለታዳሚያን ማቅረብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ጦርነትን የሚሸከም ምጣኔ ሐብት በመፍጠር አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት የጠላትን ወረራ መከላከልና መዋጋት ተገቢ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ዘገባዎች ለታዳሚያን ደርሰዋል፡፡ በዚህም የምርት ልማት እንዲያድግ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ልዩ ትኩረት በመስጠት ተዘግቧል፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር የግብርና ስራዎች እንዲሁም የበጋ መስኖ ስንዴ እና መደበኛ የሰብል ልማት ስራዎች፣የአማራ ክልል መሠረተ ልማቶች ተጠቃሚነት፣በክልሉ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሥራ እንቅስቃሴ፣ የቡሬ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክና ሌሎች የመኸር ልማት እንቅስቃሴ፣ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች፣ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር

ውኃ ሙሌት፣የማእድን ሀብትን የኢኮኖሚ አቅም ማድረግ፣ የሜካናይዜሽን አተገባበር፣ በአማራ ክልል የሥራ እድል ፈጠራ የክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና ለረዥም ዓመታት ታጥረው የተቀመጡ የመሬት ጉዳዮች የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ እና ተጠቃሚነት፣የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ውጤታማነት በተመለከተ ዘገባዎች በመተላለፋቸው ታዳሚዎች ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙና ግንዛቤ እንዲጨብጡ አግዟል፡፡

# ክልል ምክር ቤት

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በህገ- መንግስቱ የተሰጠውን ዋነኛ ተግባር የሆነውን ህግ የማውጣትና የማፅደቅ እንዲሁም አስፈጻሚ አካላትን መቆጣጠር እንዲሁም የመረጠውን ህዝብ ውክልና መወጣት የሚያስችል ተግባር ማከናወን ነው፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የተጀመረውን የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የተሟላ ልማትና መልካም አስተዳደር እውን ለማድረግ የህዝብ ሁለንተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የመንግስት አሰራር ግልጽና ፍትሃዊነት ያለው ስርዓትና ዘላቂነት ያለው መስመር በመዘርጋት የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ስለመከበሩ ህዝቡ በየደረጃው የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ስለመፍታታቸው ሊያረጋግጥ የሚያስችል ስራ በመስራት ዜጎች በጋራና በተናጠል የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ እንዲመለስላቸው በማድረግ ህዝባዊ ውክልናቸውን ለመወጣት እየሰራ ይገኛል፡፡

### አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ በተቋሙ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ፈልገው ወደ ተቋሙ የመጡ የውስጥ ደንበኞች ቁጥር ወንድ 194፣ ሴት 164 ድምር 358 ሲሆኑ የውጭ ደንበኞች ሲታዩ ደግሞ ወንድ 234፣ ሴት 870 ድምር 1104 ተገልጋዮች አገልግሎ ማግኘት ችለዋል፡፡ ከነዚህ ተገልጋዩች ውስጥ የሴቶች ድርሻ 72% ነው፡፡ ከነዚህ መካከል አገልግሎት ያገኙ ወጣቶች ደግሞ ወንድ 285፣ ሴት 975 ድምር 1260 ሲሆን አፈፃፀሙ 86% ነው፡፡

### ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን ህጎች ጥራት ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም ምክር ቤቱ በተሰጠው ህግ፣ደንብና ስልጣን መሰረት የህጎችን ጥራት በማስጠበቅ በ76% ለማሻሻል አቅዶ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎች ላይ የህዝብ አስተያየት በማሰባሰብና የበሰለ የውሳኔ ሃሳቦችን በማቅረብ ምክር ቤቱ የአሰራር እና የስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ቀደም ብለው በቂ ዝግጅት በማድረግ በምክር ቤቱ የጉባኤ አጀንዳዎችንና የሚፀድቁ አዋጆችን 2 ጊዜ ለመከታተል በታቀደው መሰረት ስድስት አዋጆችን በማዘጋጀት የእቅዱን 100% ማከናወን ችሏል፡፡

### በምክር ቤቱ የሚወጡ ህጎችን ተደራሽነት ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም ምክር ቤቱ በተሰጠው ህግ የማውጣት ስልጣን መሰረት በምክር ቤቱ የሚወጡ ህጎችን ተደራሽ ለማድረግ በአቀደው ግብ መሰረት በበጀት ዓመቱ የታተሙ አዋጅ ቁጥር 284/2014 ዓ.ም. ለሁሉም ምክር ቤቶች እና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ተደራሽ በማድረግ አፈፃፀሙን 100% ደርሷል፡፡በተጨማሪ በምክር ቤቱ በአጣሪ ጉባኤ የታዩና በህገ-መንግስቱ ተርጓሚ የፀደቁ አዋጆች በተቋሙ ደረ-ገጽ ላይ ለመጫንና ለተጠቃሚ ለማድረስ አቅዶ በድረ-ገጽ ላይ መጫን ካለባቸው 284 አዋጆች መካከል 164 አዋጆች ለተጠቃሚ ተደራሽ ማድረግ ችሏል፣አፈፃፀሙም 57.74% ነው፡፡

### የክትትልና ቁጥጥር አሰራርን ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ በክልል እና በተዋረድ የሚገኙ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና የአስፈጻሚ የዳኝነት አካል የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ የተሳለጠ እንዲሆን የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በቡድንና በተናጠል ዕቅድ በማቀድ ለአስፈፃሚ አካላት በመስጠት የጋራ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ መደበኛ ጉባኤዎችና ቋሚ ኮሚቴዎች ባካሄዱቸው የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ስምሪት ግምገማ የተፈጠሩ የጋራ መድረኮችን ሦስት ጊዜ በመደገፍና በማስተባበር በታቀደው መሰረት 100% ማከናወን ችሏል፡፡

### የህዝብ ውክልናን መወጣትና አሰራርን ማሻሻል

በ2015 ዓ.ም በምክር ቤቱ በቋሚ ኮሚቴዎች የሚቀርቡ የመራጭ ተመራጭ መድረኮችን በማካሄድ ከህብረተሰቡ የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎችን አሰባስቦና አዳራጅቶ ለፈፃሚ ሀይሎች በማቅረብ እንዲፈቱ በማድረግ ህዝብ የሰጣቸውን ውክልና በመወጣት አሰራርን በማሻሻልና የአካባቢ ምርጫ እንዴት መካሔድ እንዳለበት የተለያዩ ህጎችን በማጣቀስ ዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም በምክር ቤቱ የአሰራር ሥነ-ሥርዓትና የስነ-ምግባር ማሻሻያ ደንብ መሰረት

የክልል ምክር ቤቱ አባላትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በ119 የምርጫ ክልሎቻቸው የመረጣቸውን ህዝብ ለማወያየት ታቅዶ በ91 የምርጫ ክልሎች ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 76.47% ሆኗል፡፡

## የምክር ቤቶችን የጉባኤ አፈፃፀም ማሻሻል

በህገ-መንግስቱ እንደተደነገገው የምክር ቤት ጉባኤ በክልል ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት 2 ጊዜ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሦስት ጊዜ የወረዳና ከተማ ምክር ቤቶች አራት ጊዜ ሲሆን የቀበሌ ምክር ቤቶች ደግሞ 12 ጊዜ ጉባኤ መካሄድ እንዳለበት ተቀምጧል፡፡በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች ይህንን ተልዕኳቸውን ለመወጣት በየወቅቱ እየተገናኙ ጉባኤአቸውን በየአካባቢያቸው ባሉ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና ወቅታዊ ጉዳዮችን አጀንዳ በማድረግ ጉባኤ አካሂደዋል፡፡

በዚህም ምክር ቤቶች የወከላቸውን የህዝብ ጥያቄ በማንሳት በእቅድና በሪፖርቱ ውይይት በማድረግ የሚወጡ አዋጆችን፣ህጎችን፣ በጀትና ሹመቶችን ያፀድቃሉ፡፡ በመሆኑም ምክር ቤቱ 6ኛ ዙር ፣1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ መደበኛ ጉባኤዎች የቅድመ ጉባኤ ውይይት በመፍጠር የተሳተፉ የምክር ቤት አባላት ወንድ 82፣ ሴት 65 ድምር 147 ሲሆኑ አፈፃፀም 60% ነው፡፡ የተሳተፉት የሴቶች ድርሻ ሲታይ 70% ነው፡፡

የክልሉ ምክር ቤቱ በየደረጃው ላሉ ምክር ቤቶች የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ጠብቀው የሚካሄዱ መደበኛ ጉባኤዎች ማካሄድ የግድ ነው፡፡ በዚህም ጊዜያቸውን ጠብቀው ሳይቆራረጡና ምዕልዓተ ጉባኤውን አሟልተው እንዲያካሂዱ 4 ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 4 ጊዜ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 100% ነው፡፡ በአጠቃላይ የበጀት ዓመቱ የምክር ቤቶችን የጉባኤ አፈፃፀም ሲታይ 91.90% ማድረስ ተችሏል፡፡



የአማራ ክልል ምክር ቤት ጉባኤ ሲካሄድ-ባህርዳር

### የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ብልሹ አሰራርን መከላከል

በበጀት ዓመቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ተግባራትን አቅዶ በመንቀሳቀስ በርካታ ብልሹ አሰራሮች በህገ-ወጥ መንገድ እንዳይፈፀሙ የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡

## ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጣቸውን ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ውጤታማ፣ ነፃና ተጠያቂነት የሰፈነበት የህግ የበላይነትን ማስፈን ነው፡፡ ይህን መሰረታዊ አላማ ተግባራዊ ለማድረግ በ2015 በጀት ዓመት እቅዱን በውጤታማነት ለመፈፀም በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ተቋሙ የተቋቋመበትን ዓላማና ግብ በማሳካት በተደራጀ መንገድ ተግባራትን ለመፈፀም እና የፍትህ ተደራሽነቱን ለማስፋፋት በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ለዜጎቻቸው ተሚጋችና ታአማኒነት ያለው ፍርድ መስጠት እንዲችሉ ማድረግ የዘወትር ተግባራቸው ነው፡፡

### የሰራተኞችን አቅም ማሳደግ

የዳኝነት ስራ ውጤታማ የሚሆነው የዳኞችንና የአስተዳደር ሰራተኞችን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ በየጊዜው በሚሰጡ ስልጠናዎችና የአቅም መገንቢያ መንገዶችን በማሳደግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በየደረጃው ለሚገኙ የፍርድ ቤት ሰራተኞችን አቅም በመገንባት የተሟላ ቁመና ያለው የሰው ሃብት ለመገንባት የአፈፃፀም ግምገማና የእቅድ ትውውቅ በማድረግ

ክህሎታቸውን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በበጀት ዓመቱ በብሄር ግጭት በሚስተዋልባቸው በሰሜን ሸዋ ዞን እና በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚገኙ አጎራባች ወረዳዎች ላይ በሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችና ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለአስተዳደር ሰራተኞች የአጭር ጊዜ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ወንድ 97 ሴት 85 ድምር 182 ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪ ለዳኞች፣ ተ/ጠበቆች፣ ለሴቶች እና ህፃናት፣ ለፖሊስ እና አቃቢ ህግ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በስልጠናው የተሳተፉ ወንድ 75 ሴት 15 ድምር 90 እንዲሁም የህግ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች፣ ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ጉዳኞች ላይ ለዳኞች እና ለጉባዔ ተሿሚዎች ወንድ 121 ሴት 37 ድምር 158 የ2 ቀን ስልጠና  ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጦርነት ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው ከተሞች በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ወሎ እና በዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ስር በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ላሉ አስተዳደር ሰራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ እና በሰብአዊ መብት እንዲሁም የስራ አፈፃፀም ምዘና መመሪያ ዙሪያ በ4 ዙር ለወንድ 244 ሴት 95 ድምር 239 የአስተዳደር ሰራተኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎችን የአቅም ክፍተት በጥናት በመለየት በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች 25% ለሚሆኑ ዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት እቅድ ተይዞ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በስልጠናው የተሳተፉ ወንድ 1,489 ሴት 445 ድምር1,934 ሲሆኑ እነዚህ ሰልጣኞችም ተገቢውን ስልጠና ማግኘት ችለዋል፡፡

## የፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ማሻሻልና ማጎልበት

የፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ ተደራሽነት ማስፋት ለዜጎች የዳኝነት አገልግሎትን በቅርበት እንዲያገኙ በማስቻል ረጅም ርቀት በመሄድ ሊያወጡት ይችሉት የነበረውን የገንዘብ፣ የጊዜ እና የጉልበት ወጪን በመቀነስ የፍትህ አገልግሎት አሰጣጡን ለማረጋገጥ የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ይህን በመረዳት በበጀት ዓመቱ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽነት ለማሳደግና ፍትህ ፈላጊውን ማህበረሰብ በቅርበት ፍትህ እንዲያገኝ ለማድረግ የወረዳ ፍርድ ቤቶችን ተደራሽነት ማስፋት ተችሏል፡፡




በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ የተደረገ ውይይት

## ተዘዋዋሪ ችሎት

በጠቅላይ ፍርድ ቤት በ9 ተዘዋዋሪ የችሎት ጣቢያዎችና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በ45 የተዘዋራሪ ችሎት ጣቢያዎች እና በወረዳ ፍርድ ቤት በ510 የተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎች ጉዳዮችን ለማየት በእቅድ ተይዞ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በ7 ተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎች 4,685 መዛግብት ቀርበው 3,722 መዛግብት እልባት ሲያገኙ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ደግሞ በ41 ተዛዋዋሪ የችሎት ጣቢያዎች 10,180 መዛግብት ቀርበው ለ6,915 መዛግብት እልባት መስጠት ተችሏል፡፡ በዚህም በወረዳ ፍርድ ቤቶች በ500 ተዛዋዋሪ የችሎት ጣቢያዎች ላይ 24,915 መዛግብት ቀርበው 18,986 መዛግብት እልባት አግኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በ548 የተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት ቀጠናዎች ላይ 39,780 መዛግብት ቀርበው 29,623 መዛግብት ውሳኔ ያገኙ ሲሆን ወንድ 93,923 ሴት 50,952 በድምሩ 144,875 ባለጉዳዮች አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

### የመዛግብት የማጣራት አቅም ማሳደግ

በበጀት ዓመቱ ፍርድ ቤቶች የስራ አፈጻጸም ምዘና ስርአትን በመተግበር ተጨማሪ ዳኞችን በማሾም እና የዳኞችን ውሳኔ የመስጠት አቅም በማጐልበት የመዛግብት የማጣራት አቅም ከፍ ለማድረግ እቅድ ተይዞ በተሰራው ስራ የመዛግብት የማጥራት አቅም አፈፃፀም ሲታይ በሰበር ሰሚ ችሎት 15,413 መዛግብት በአዲስ የተከፈቱና ከመዝገብ ቤት

የተንቀሳቀሱ ሲሆን 13,471 መዛግብት ደግሞ እልባት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙን 87.4% ማድረስ ተችሏል፡፡ በጠቅላይ ፍርድ ቤት 11,766 በአዲስ የተከፈቱና ከመዝገብ ቤት የተንቀሳቀሱትን 11,833 መዛግብት እልባት መስጠት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ100.57% ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀም 98.89% ሲሆን በወረዳ ፍርድ ቤት ደግሞ 100.29% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የፋይሎችን የመጨናነቅ መጠን መቀነስ

በበጀት ዓመቱ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓትን አጠናክሮ በማስቀጠል የፋይሎችን የመጨናነቅ መጠን የተመዘገበው ውጤት ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1ለ1.25 ፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ 1.25፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት 1.05 ፣ በወረዳ ፍርድ ቤቶች 1.01 መዛግብት የመጨናነቅ መጠን ያሳያል፡፡

## የመጽናት ምጣኔን ማሳደግ

በፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅም እና ክህሎት ለማሳደግ በተሰራው ስራ በይግባኝ ቀርበው የሚፀኑ መዛግብት ቁጥር ከአመት አመት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የመፅናት ምጣኔ 95.1% የነበረውን ባለበት ለማስቀጠል ታቅዶ አፈጻጸሙ መረጃውን ማግኘት ስላልቻልን መለካት አልተቻለም፡፡በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመፅናት ምጣኔ 80.14% የነበረውን በበጀት ዓመቱ ወደ 86.5% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 81.73% ላይ በመሆን ግቡን ማሳካት አልተቻለም፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔ 75.67% የነበረውን በበጀት ዓመቱ ወደ 80% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 76.12% ላይ በመሆን ግቡን ማሳካት አልተቻለም፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመፅናት ምጣኔ 64.20% የነበረውን በበጀት ዓመቱ ወደ 77% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 65.77% ላይ በመሆኑ ግቡን ማሳካት አልተቻለም፡፡በመሆኑም በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተመዘገበው ውጤት ባለፈው በጀት ዓመት ከነበረው አፈጻጸም የተሻለ ቢሆንም የዚህን ዓመት ግብ ያልተሳካ በመሆኑ በቀጣዩ በጀት ዓመት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይስፈልጋል፡፡

በተለይም በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በወረዳ ፍርድ ቤቶች ታይተው ቀጥሎ ባለው ፍርድ ቤት ደረጃ በይግባኝ ወይም በሰበር ቀርበው ሲታዩ የመጽናት ምጣኔያቸው ግቡን ካለማሳካቱም ባሻገር ያለው አፈጻጸም ከግቡ ያለው ርቀት ሲታይ ከፍተኛ የሆነ የፍርድ

ጥራት ችግር እንዳለ የሚያሳይ ስለሆነ ለፍርድ ጥራት መጓደል መሰረታዊ መንስኤው ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ አሁንም መመለስ ያስፈልጋል፡፡

## የመሻር ምጣኔን መቀነስ

ፍርድ ቤቶች የዳኞችን አቅምና ክህሎት ለማሳደግ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ክህሎታቸውንና ስነ-ምግባራቸውን ለማሳደግ የፍርድ ምርመራውን አጠናክሮ በማስቀጠል በይግባኝ ቀርበው የሚሻሩ መዝገቦችን ቁጥር ከዓመት ዓመት እንዲቀንሱ ተደርገዋል። በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻር ምጣኔው 1.4% የነበረውን ባለበት ለማስቀጠል ታቅዶ አፈጻጸሙ መረጃ ባለማግኘቱ መለካት አልቻለም በዚህ መሰረት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻር ምጣኔው አፈጻጸሙ11.61%፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሻር ምጣኔው 15.26%፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ታይቶ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሻር ምጣኔው 22.98% ማድረስ ተችሏል፡፡

## የመሻሻል ምጣኔ

